1. በሽፋኑ ላይ ተስለው የሚታዩት የታሪክ ቦታዎች:
   1. አክሱም 2. ላሊበላ 3. ጎንደር

ሌሎችም የክርስትና እምነት ታሪካውያን ማእከላት ከታች ወደ ላይ:

4. ኢየሩሳሌም 5. እስክንድርያ 6. አቴንስ←ቁስጥንጥንያ
7. ሮም

Historical Places Shown on the Cover:

1. Axum 2. Lalibela 3. Gonder

Other Historical Centers of Christianity

4. Jerusalem 5. Alexandria 6. Athens ←Constantinople
7. Rome


ዲበኩሉ ዘውዴ
- ቲ ኤች.ቢ.(TH.B.)
- ቢ.ኤ፡ሥነ መንግሥት(B.A.Pol.Sc.)
- ቢ.ኤ፡ ሥነ ሕ. አስተዳደር(B.A. Pub.Adm.)
- ኤል ኤል.ቢ.(LL.B.)
- ኤል ኤል.ዲ.(LL.D.)


# 81 ቅዱሳት መጻሕፍትና ምንጮች-ቀኖናት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን:

- ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቤተክርስቲያን
- ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት
- ሲኖዶስ - ሥርዐተ ሐዋርያት
- ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን
- ፍትሐ ነገሥት - አንቀጽ 2

በጥንት አብያተ ክርስቲያናትና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መካከል ንጽጽራዊ ጥናት


አዲስ አበባ 1987



www.ethiopianorthodox.org

የደራሲው የባለቤትነት መብት የተጠበቀ ነው
(C) ዶ/ር ዲበኩሉ ዘውዴ

ALL RIGHTS RESERVED

መታሰቢያነቱ የአገር ፍቅር ታሪክንና ሥልጣኔን ለአወረሱን የአገራችን ሊቃውንት

አዲስ አበባ 1987

DIBEKULU ZEWDE
- ቲ ኤች.ቢ.(TH.B.)
- ቢ.ኤ:ሥነ መንግሥት(B.A.Pol.Sc.)
- ቢ.ኤ: ሥነ ሕ. አስተዳደር(B.A. Pub.Adm.)
- ኤል ኤል.ቢ.(LL.B.)
- ኤል ኤል.ዲ.(LL.D.)

# THE 81 HOLY BIBLES AND THE SOURCES - CANONS

## In the Ethiopian Orthodox Church:

- Synodos - Canons of the Church
- Synodos - Canons of the Holy Apostles
- Synodos - Constitutions of the Apostles
- Synodos - Canons of Apostles the Holy
- Fetha Nagast - Article 2

Comparative Study Between Ancient Churches and Ethiopian Orthodox Church

www.ethiopianorthodox.org

Addis Ababa 1995

All Rights (c) Dr. DibeKulu Zewde
All Rights Reserved

Monument for the scholars of our country for their investments of patriotic history and civilization to us.

Addis Ababa 1995

## መቅድም

# ከአባት የመውረስ መብት ለልጅ የማውረስ ግዴታን ያስከትላል

የሰው ልጅ ታሪክ እንደ ሰንሰለት ወይም እንደ ወይን ሐረግ የተሳሰረ ነገር ነው፡፡ ታሪክንም የመውረስና የማውረስ ታሪካዊ ሂደት ይህን ይመስላል፡፡ ትልቁ ችግር ያለውን ማውረስ አይደለም፡፡ ይህን ውርስ-የታሪክ ቅርስ-እንዳለ ጠብቆ ብቻ ሳይሆን በአግባቡ አሻሽሎ፣ አሳድጎና አባዝቶ ማውረስ ታሪካዊ ግዴታ መሆኑ ነው፡፡ በአገራችን ይህ የተወረሰውን ታሪክ፣ ሥልጣኔና ባህል ሌላ ቢቀር እንዳለ እንኳን ጠብቆ ለማስተላለፍ ብዙ ጊዜ እያዳገተን ነው፡፡ በርግጥ ቀደም ያሉ አባቶች ብዙ አስደናቂ የኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ ሥራዎችን እየሠሩና የአዕምሮ ፈጠራ ውጤቶችን እያዳበሩ አልፈዋል፡፡

ስለዚህ ብዙ ባንልም ለማንኛውም ዜጋ ዕውቀትና አቅም በፈቀደ መጠን የሚቻለውን ያህል ጥረት አድርጐ ማለፍ ታሪካዊ ግዴታ ነው፡፡

በዚህም መሠረት ነበር አንዱ የዚህ መጽሐፍ መነሻ ዓላማ፡፡

ስለዚህ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት የጠየቀውን ከፍተኛ ድካምና የማይመለስ ወጪ ለመቋቋም የተከፈለው መስዋዕትነት ቀላል ባይሆንም ከዓላማው አንጻር እጅግም የሚሰማ አልነበረም፡፡

ነገር ግን የበለጠ ከአቅም (ኢኮኖሚ አቅም) በላይ ሆኖ የተገኘው ችግር የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ግብ ታትሞ ሥርጭት ነበር፡፡

ሆኖም ይህን ለመሰለው ቅዱስ ዓላማና ግብ በቆሙ አባት ዜጋ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማትና የክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽነር ቅን አመለካከት በዚሁ ኮሚሽን በኩል ታትሞ እንዲሠራጭ በመደረጉ ከልብ ሳመሰግን መጽሐፉ ተሸጦ የዚህን ኅትመት ወጪ በቀላሉ እንደሚመልስም ጽኑ ተስፋ አለኝ፡፡

ዶ/ር ዲበኩሉ ዘውዴ

www.ethiopianorthodox.org

## ማ ው ጫ


| ር እ ስ | ገ ጽ |
|---|---|
| መቅድም ........................................ | 5 |
| ማውጫ ........................................ | 6 - 12 |
| መግቢያ ........................................ | 13 -22 |
| **ምዕራፍ አንድ** | |
| ቅድስት ቤተክርስቲያን እንድትቀበላቸው ስለታዘዙትና ቁጥራቸው 81 ስለሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት =«አምላካውያት መጻሕፍት»ና ምንጮች-ቀኖናት.. | 23 - 34 |
| 1. ቅዱሳት ሲኖዶሳት ........................................ | 28 - 29 |
| 2. የቤተክርስቲያን አባቶች ........................................ | 29 - 34 |
| **ምዕራፍ ሁለት** | |
| ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት........................................ | 35 - 80 |
| 1. ሲኖዶሳውያት ቀኖናት........................................ | 35 - 48 |
| 1.1 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት........................................ | 35 - 41 |
| 1.2 ቀኖናት ዘላኦዶቅያ /ሎዶቅያ/ ............ | 41 - 45 |
| 1.3 ቀኖናት ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ ........ | 45 - 48 |
| 2. ቀኖናተ አበው........................................ | 48 |
| 2.1 መልእክተ አትናቴዎስ ........................................ | 48 - 54 |
| 2.2 ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት........... | 54 - 57 |
| 2.3 ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን........... | 57 - 61 |
| (1) የተዘረዘሩት - የተተነተኑት ቀኖናትን ማነጻጸርያ ሰንጠረዥ - ሰሌዳ 1.............. | 62 - 67 |
| 3. የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር፣ ቀኖናዊነት ዓይነትና መጠን..................... | 68 - 80 |
| **ምዕራፍ ሦስት** | |
| የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናት ግእዝ ትርጉሞች ........................................ | 81 - 128 |





| ር እ ስ | ገ ጽ |
|---|---|
| (1). ሲኖዶሳውያት ቀኖናት-ሐዋርያት ቀኖናት ........................................ | 81 |
| 1. ፍትሐ ነገሥት ........................................ | 81 - 93 |
| 2. ሲኖዶስ - መድበለ ቀኖናት ........................ | 93 - 111 |
| 2.1 ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን - ትእዛዝ 57/56 ረስጠጅ/........................................ | 96- 99 |
| 2.2 ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 /ረስጠአ/........................................ | 99 - 105 |
| 2.3 ሥርዓተ ሐዋርያት ምስለ ቀለሚንጦስ - ትእዛዝ 80 ........................................ | 105 - 108 |
| 2.4 ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን - አብጥሊስ 80........................................ | 108- 111 |
| 3. ፍትሐ ነገሥት (2)........................................ | 111-116 |
| 4. እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማን የ81 መጻሕፍት ዝርዝር .................. | 116-118 |
| 5. እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ የ81 ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ........................ | 118-123 |
| (2) የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና እና የአራት ግእዝ ትርጉሞች ሲኖዶሳት-ቀኖናት ፍትሐ ነገሥትን ጨምሮ ማነጻጸሪያ ሰንጠረዥ ሰሌዳ 2 .......... | 124-128 |
| **ምዕራፍ አራት** | |
| በጥንት ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሳውያት፣ አበውያት ቀኖናትና በቀኖናቱ ግእዝ ትርጉሞች ቀኖናት መካከል የሚታዩት ግንኙነቶችና ልዩነቶች....... | 129-146 |




www.ethiopianorthodox.org

## ር እ ስ

ገ ጽ


1. በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖናና በቀኖናው ግእዝ ትርጉሞች አራት ቀኖናት የመጨረሻ ቀኖናት መካከል የሚታዩ ግንኙነቶችና ልዩነቶች...129-132
   - 1.1 ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቤተክርስቲያን - ትእዛዝ - ቀኖናት 57/56ና ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ............................ 129-130
   - 1.2 ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳት - አብጠሊሳት ቀኖናት 82 81ኛ ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና .............. 130
   - 1.3 ሥርዐተ ሐዋርያት - ትእዛዝ - ቀኖናት 80 80ኛ ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና .................................. 130 - 131
   - 1.4 ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን - አብጠሊስ - ቀኖናት 81 80ኛ ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖና 85ኛ ቀኖና ................ 131-132
2. በ60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ/ሎዶቅያ/እና በቀኖናው ግእዝ ትርጉም መካከል የሚታይ ግንኙነቶችና ልዩነቶች ................................................ 132-133
3. በ24ኛ/32ኛ ቀኖናት ዘካርታጌኒስ/ቅርጣግና/ እና በቀኖናቱ ግእዝ ትርጉም መካከል የሚታዩ ግንኙነቶችና ልዩነቶች .................................. 133-134.
4. በቀኖናተ አበውና በቀኖናቱ ግእዝ ትርጉሞች መካከል የሚታዩ ግንኙነቶችና ልዩነቶች.... 134 - 137
   - 4.1 መልእክተ አትናቴዎስ ......................... 135
   - 4.2 ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ............... 135-136
   - 4.3 ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን ........... 136-137
5. ፍትሐ ነገሥት ............................................ 137




## ር እ ስ

ገ ጽ


(3) የ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍትና የአራቱ ግእዝ ትርጉሞች ሲኖዶሳት ቀኖናት ማነጻጸርያ ሰንጠረዥ - ሰሌዳ 3........................................ 138-146


## ምዕራፍ አምስት


ቅዱሳት መጻሕፍትና ቀኖናውያን ገላጭ ቅጽሎች.. 147-184

1. የቀኖናውያን ገላጭ ቅጽሎችዓይነቶች...... 147-151
2. የቅዱሳት መጻሕፍት ሥርጭቶች .............. 151-170
   - 2.1 ዕብራይስጥ - ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን.................. 151-153
   - 2.2 ግሪክ ቅዱሳት መጻሕፍት .............................. 153-157
     - 2.2.1 ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት.............153-156
     - 2.2.2 ሐዲስ ኪዳን ........................................... 156-157
   - 2.3 ግእዝ - አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት.............. 157-170
     - 2.3.1 የ1918 የእጅ ጽሑፎች ቅዱሳት መጻሕፍት........................................ 158-161
     - 2.3.2 የ1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ......................... 161-164
     - 2.3.3 የ1947(1953) ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት...... 164-166
     - 2.3.4 የ1980 አዲስ ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት.........166-170

(4) የ1918 የእጅ ጽሑፎች፣ የ1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት፣ የ1947(የ1953) ኅትመትና የ1980 ኅትመት ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማነጻጸርያ ሰንጠረዥ-ሰሌዳ 4...... 171-175

3. በ1918፣ 1929፣ 1947(1953) እና 1980 ሥርጭቶች ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል የሚታዩ ልዩነቶች.....176- 177


www.ethiopianorthodox.org

ር እ ስ ገ ጽ

4. ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ከመሠረታውያን ምንጮቻቸው ጋር ሲነጻጸሩ ........................................ 178-179

(5) የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን፣ ግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናትና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አዲስ ትትመት መጽሐፍ ቅዱስ፡ ብሉይ ኪዳን

2/ የግሪክ ሐዲስ ኪዳንና የግእዝ-አማርኛ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ማነጻጸርያ ሰንጠረዥ-ሰሌዳ 5........................................ 180-184

## ምዕራፍ ስድስት

በግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት-ብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና በጽርእ-ግሪክ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ሰብዓ ሊቃናት መካከል አንድነትና ልዩነት ...................... 185-212

1. መጽሐፈ ሶስና ........................................ 185-186
2. ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ/ጸሎተ አዛርያስ ወሠለስቱ ደቂቅ/........................................ 186-188
3. ተረፈ ዳንኤል /ቤልና ደራጎን/ ...................... 188-189
4. መጽሐፈ አስቴር ........................................ 190-194
5. ተረፈ ኤርምያስ ........................................ 195-196
6. ጸሎተ ምናሴ ........................................ 196-197
7. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ........................................ 197-198
8. መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ........................................ 198-199
9. መጽሐፈ ኩፋሌና መጽሐፈ ሄኖክ ................ 199-201
10. 3 መጻሕፍተ መቃብያን ........................................ 201-212

ር እ ስ ገ ጽ

## ምዕራፍ ሰባት

በሐዲስ ኪዳን የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና፣ ስምንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚ ንጦስና ስምንቱ ግእዝ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ.... 213-224

1. ሰመንቱ ብሔረ ቀለሚንጦስ...................... 213
   1.1 ሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ..214-215
   1.2 ዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ..215-216
   1.3 ቅብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ... 216-217
   1.4 ግእዝ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ.. 217-218
2. ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ /8ቱ ብሔር ዘቀለሚንጦስ/........................................ 218-225
3. ሐዋርያውያት ትእዛዛት ዘበእደ ቀለሚንጦስ /ሰመንቱ ብሔራተ ቀኖናት/...................... 220-224

## ምዕራፍ ስምንት

የቅዱሳት መጻሕፍትና ምንጮች-ቀኖናት ማጠቃለያ ማገናዘቢያና መደምደሚያ ............ 225-290

1. ማጠቃለያና ማገናዘቢያ.................... 225-266
   1.1 የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥርና ቀኖናዊነት........ 225-231
   (6) የአራት ግእዝ ትርጉሞች ሲኖዶሳት - ቀኖናት ከራሳቸውና ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ጋር ሲነጻጸሩ ሰንጠረዥ-ሰሌዳ 6... 232-236
   1.2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶሳት- መጻሕፍተ ቀኖናት /መድበላተ ቀኖናት/ ሥነ ትርጓሜ........................237-255፣ 262-266
      1.2.1 ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቤተክርስቲያን - ትእዛዝ 57/ረስጠጅ/ ............................ 247-248



www.ethiopianorthodox.org

ር እ ስ　　　　　　　　　　　　ገ ጽ


1.2.2 ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት-
አብጠሊሳት 82 /ረስጠአ/............................ 248-250

1.2.3 ሲኖዶስ-ቀኖናት ሥርዓተ ሐዋርያት-
ቀኖናት 80............................................... 250-251

1.2.4 ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን-
አብጠሊስ 81............................................ 251-252

1.3 ፍትሐ ነገሥት .......................................... 252-255

1.4 ሲኖዶሳት ................................................ 255

(7) - በአራቱ ሲኖዶሳት-ግእዝ ትርጉሞች ሐዋር
ያውያት ቀኖናት መሠረት የቅዱሳት መጻሕፍት
ቁጥርን 81 ማሳያ ሰንጠረዥ- ሰሌዳ 7...... 256-261

2. መደምደሚያ ...................................... 267-290

2.1 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ:............ 267-286

2.1.1 81 ቅዱሳት መጻሕፍት በሥርጭት
ላይ እንደሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት... 269-281

2.1.2 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ
ፍትሐ ነገሥት ...................................... 281-282

2.1.3 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገ
ሥት መተርጉማንና እንደ ሊቃውንት ጉባኤ...283-284

2.1.4 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ሲኖ
ዶሳት- ቀኖናት........................................ 284-286

2.2 የሚታሰብባቸው አማራጮች................. 286-290

2.2.1 አማራጭ አንድ ........................... 286-289

2.2.2 አማራጭ ሁለት ........................... 289-290

2.2.3 አማራጭ ሦስት ........................... 290

APPENDIX ...................................................... 291-295




# መ ግ ቢ ያ

## «በቤተ ክርስቲያን ምእመናን የተቀበሏቸው መጻሕፍት» «መጻሕፍት እንተ (እለ) ተወከፍዎን ምእመናን ውስተ ቤተ ክርስቲያን»

ቤተ ክርስቲያን ተቀብላ ትምህርተ መለኮትን እንድታስተምርባቸውና ሥርዐተ አምልከትን ለመፈጸም እንድትገለገልባቸው የታዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍትን ቁጥርና ቀኖናዊነት ለማጥናትና ወደ አንድ ውጤት-መደምደሚያ ለመድረስ ብዙም ሳንሄድ በአጭሩ በመወሰን ለጊዜው በቅርብ በተገኙ ምንጮችና መረጃዎች በመደገፍ የሚቻለውን ያህል ጥረት ተደርጓል:: ለዚህ ጥናት ጽሑፍ መነሻ አንድ አጋጣሚ ምክንያት ነበር::

በውጪ አገር በት/ቤት በነበርኩበት ወቅት በተለይ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መግቢያን እከታተል በነበርኩበት ጊዜ በእየአንድአንዱ መጽሐፍ ታሪክና ቀኖናዊነት በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን የመገንዘብ ዕድል ወይም አጋጣሚ ነበር:: በዚህን ጊዜ ነበር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳሉ የሚነገረውን ነገር ማሰላሰል የጀመርኩት::

ስለዚህ በመጀመሪያ «81» የሚለው ቁጥር ወደ ጥያቄ ውስጥ መግባት የለበትም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም ባይባልም ይህ 81 ቁጥር አንድ በአንድ ተዘርዝሮ የተለላፈበት መንገድ ያው እንደተለመደው በቃል - በትውፊት እንጂ በግልጥ በጽሑፍ ተቀምጦ የተላለፈ ስላልሆነ ባለበት መልኩ ቁመን የምንገኝ ብቻ ከሆነ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ጋር እንዴት ይታያል? ወደ ሚል ጥያቄ መግባቱ ግድ ነበር::

በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ [illegible] የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር /39 የብሉይ

www.ethiopianorthodox.org

ኪዳን መጻሕፍት እና/ 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት =(39 + 27=66)66 መጻሕፍት መሆናቸው ይታወቃል:: የካቶሊክ ቤተክርስቲያንም ብትሆን የ419 ካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ 24/32 ቀኖናን በመከተል የምትቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት በዚያ ቀኖና የተዘረዘሩት መጻሕፍት /43 የብሉይ ኪዳንና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማለት መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል::

ነገር ግን የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳን በተለያዩ ቀኖናት ተደንግገው የመጡት መጻሕፍትን ከ8 ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በስተቀር ተቀብላ ብትገኝም የቅዱሳትን መጻሕፍት ዝርዝርና መጨረሻ ቀኖናዊ ውሳኔን ለመስጠት አንድ ዐቢይ ሲኖዶስ ለመጠራት ከመታሰብ አላለፈም:: እኔም ከዚህ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝርና ቁጥር ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ቤተ ክርስቲያን 81 መጻሕፍት አንድነት ወይም ልዩነት እንዳላቸው ለማማሳከር አግባብነት ያላቸው ምንጮችን ማናበብና ማስታወሻዎችን ማሰባሰብ ጥረት ባደርግም ወደ ዝርዝር ውስጥ ለመግባት አልተሳካልኝም ነበር:: ወደ አገሬ ከተመለስኩ በኋላ በሌሎች የሥራ መስኮች ስለተማራሁ አሁንም ይህን ነገር ቁጭ ብሎ ለመመልከት ዕድል አላጋጠመኝም:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በውጭ አገር እንደገና ታትሞ ወደ አገር ውስጥ በሚገባበት ጊዜ ተፈጥሮ የነበረው ችግር እንዲነሳ ተደርጎ ሊገባ በመቻሉ አንድ ቅጅንም ለማግኘት ጊዜው ፈቀደለኝ::

በዚህ ጊዜ ነበር ያለፈው ምኞቴ እንደገና ሊያንሰራራ የቻለው:: ስለሆነም በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ እ.ኤ.አ. በ1950 የታተመ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዐ ሊቃናት በእጄ ይገኝ ስለነበር ጊዜን ባገኘሁ ቁጥር ከዚህ መጽሐፍ



ቅዱስ ጋር /ሁለቱን ቅዱሳት መጻሕፍት ጋ ለማስተያየት መሞከሬ አልቀረም ነበር:: ሆኖም ግን 1983 ዓ.ም. ለሕክምና ወደ አቴንስ ሄጄና በዚያም ምክንያት ትንሽ በርከት ያለ ጊዜ በዚያች ከተማ ስለተቀመጥኩ ባለፈው ዓመት/1986/ ታትሞ በሥርጭት ላይ የሚገኘ መጽሐፍ «ፍትሐ ነገሥት፡ ብሔረ ሕግ ወቀኖና» ረቂቅን ከምንጮችና መረጃዎች ጋር ለማመሳከርና ለማስተካከል - ለማረም አብዛኛውን ጊዜ ስለተሻማብኝ ብቸገርም ለዚህ ቅዱሳን መጻሕፍት ዝርዝርና ቀኖናዊት የተሻለውን ያህል ጊዜ በመሰዋት ከምንጮችና ከሊቃውንትም ማስታወሻዎችን ከማሰባሰብ አልቦዘንኩም ነበር::

ወደ አገሬ እንደተመለስኩ ይኸው «ፍትሐነገሥት፡ ብሔረ ሕግ ወቀኖና» ከእሱም ጋር ሌሎች ሁለት መጻሕፍት «የሰዎችና የዜጐች በሕግ ፊት እኩልነትና» «የመንግሥት ገጻተ ባሕርያት» ኅትመት ሥራ ክትትል አሁንም ጊዜን ስላጣበበብኝ የጥናቱ መገባደድ ትንሽ መዋልና ማደር ግድ ሆነ:: አሁን ግን በአምላክ ፈቃድ ይኸ ረቂቅ ይህን ቅርጽ ይዞ ሊጠናቀቅ ችሎአል::

እንግዲህ ቅዱሳት መጻሕፍት ወይም እንደ ፍትሐ ነገሥት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙ «አምላካውያት መጻሕፍት»[1] ወይም ምእመናን በቤተ ክርስቲያን የተቀበሏቸው መጻሕፍት[2] የትኞቹ መጻሕፍት መሆናቸውና ይህን ሊያሰኛቸው የቻለው ታሪካዊ ቀኖናዊነት እንዴት እንደሆነ ግልጥ መሆን ስለነበረበት ይህን ለመመልከት አጋጣሚ ሆኖአል::

የጥንት ቤተክርስቲያን ለትምህርተ መለኮትና ለሥርዐተ አምልኮት በምንጭነት እንድትቀበል የታዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ አንድም ዘርዝሮና ቆጥሮ ለማሳየት - ለማመልከት ወይም በተለያዩ ሲኖዶሳውያት ቀኖናት እና

---

1. ፍትሐነገሥት አንቀጽ 2/ርእስ/
2. ፍትሐነገሥት አንቀጽ 2 ቁ.15

www.ethiopianorthodox.org

ቀኖናት አበው እየተነገረላቸው የተላለፉ ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ የሚያሳዩና በምንጭነት የሚያገለግሉ እነዚህ ቀኖናት ይመረመራሉ::

ስለዚህም ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝርና ቀኖናዊነት የሚናገሩ ቀኖናት - ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት 6 ናቸው:: ከእነዚህም 3ቱ ሲኖዶሳውያት ቀኖናት /85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና፣ ቀኖናት ዘሎዶቅያ /ላኦደቅያ/ 60ኛ ቀኖና እና ቀኖናት ዘቅርጣግና ( ካርታጊኒስ) 24/32 ቀኖና /እና 3ቱ ቀኖናተ አበው /39ኛ መልእክተ አትናቴዎስ፣ ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት እና ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን/ ሲሆኑ መጻሕፍቱን ከሰጧቸው ገላጪ ቀኖናዊነት - ቅጽልነት ጋር ለማመሳከር ተሞክሯል ወይም እየአንድ አንዱ ቅዱስ መጽሐፍ በየቀኖናቱ ከተሰጠው ቀኖናዊነት አንጻር ተመርምሯል::

ስለዚህ ቀኖናዊነቱ የሚገለጥበት - የሚረጋገጥበት ወይም የሚገለጽበት ቅጽል እንደተጠበቀ ሆኖ የመጻሕፍቱ ቁጥሮችም ከቀኖና ወደ ቀኖና እንደሚለያዩ ለማመልከት በሰንጠረዦችም - ስሌዳዎችም እንዲነጻጸሩ ተደርጓል:: ከዚያም እየአንድአንዱ ቅዱስ መጽሐፍ ከ6ቱ በስንቱ ቀኖናት: በ6ቱ፣ በ5ቱ፣ በ4ቱ ወይም በ3ቱ፣ በ2ቱ ወይም በአንዱ ብቻ እየተመለከተ እንደሚገኝ ለማሳየት ተጥሯል:: ከዚህም ጋር ተያይዞ እነዚህ ቀኖናት ወደ ግእዝ ተተርጎመው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ይታወቁ እንደሆነ አሰሳ ቢደረግም ይህን ለማግኘት የተቻለው ለጊዜውም ሊሆን ይችል ይሆናል ከ6ቱ ቀኖናት አንዱ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ብቻ ነው /ናቸው/:: እሱም /እነዚህም/ ቀኖናት ቢሆን/ቢሆኑ/ በመጀመርያ ቅርጻቸው ሳይሆን በ4 ስያሜዎች፣ ቅርጾችና ቁጥሮች ግን የጋራ «ሲኖዶስ» የሚል ርእስን /ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን 57/56/ - የፍትሐ ነገሥት ረስጠጅ፣ ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት - አብጥሊሳት 82 - የፍትሐ ነገሥት ረስጠአ 81፣ ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን 80



እና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን - አብጠሊስ 81 ይዞ እንደሚገኝ ይዘው /እንደሚገኙ/ ተዘርዝሯል:: በዚህም የሚመረመሩትን መጽሐፍት የተለዩ(ልዮች) የሚያደርጋቸው በ85ቱ ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ያልተያዙ ግን በሌሎች 5 ቀኖናት በአንዱ ወይም በሌላው ቀኖና ተይዘው የሚገኙት ተጨምሮባቸው ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ቀኖና መጻሕፍት ያልታዩ መጻሕፍት - ኩፋሌ ከአራቱ በሦስቱ ቀኖናት ሰፍሮ መገኘቱ ሲሆን ይህም እንዴት እንደሆነ የማይታለፍ ጥያቄ መሆኑ ተቀምጧል:: በሌላም በኩል ፍትሐ ነገሥትም ከእነዚህም ቀኖናት ጋር በመጣመር ከ85 ሐዋርያውት ቀኖናት ወይም በጠቅላላ ከ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት ጋር ያለው አንድነት ወይም ልዩነት በንጽጽር ሰሌዳ እንዲታይ ተደርጓል::

ቀጥሎም እነዚህ ግእዝ ትርጉም ቀኖናትና ፍትሐ ነገሥት በመካከላቸው በሰንጠረዥ - ስሌዳ ተቀርጸውና ተነጻጽረው እንዲታዩ ተደርጓል:: ከዚህ በኋላ ዘርዘር ብሎ በተቀረጸ ማጠቃለያ፣ ማገናዘቢያና መደምደሚያም ሁሉንም ምንጮች በማመሳከር ወደ 81 ቁጥር ለመድረስ በአንድአንድ አሐዝ የማለፍ ወይም የማነስ - የመቀነስ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲታይ እነዚህም ከሁለት ችግሮች የተፈጠሩ መሆናቸውን ለመጠራጠር አስችሏል:: ከእነዚህም አንዱ ለምሳሌ መቃብያን 3 መጻሕፍት መሆናቸው እንኳን ቢቀር በአንድ ቀኖና አንድ መቃብያን በሌላው ቀኖና ሁለት መቃብያን እየሆኑ መገኘታቸው ወይም ያልተያዙበት ቀኖና መኖሩ በሌላም በኩል በማንኛውም ቀኖና ያልተያዘ መጽሐፍ - ኩፋሌ ከ4ቱ ቀኖናት - ሲኖዶሳት በሦስቱ ተይዞ እና በአንዱ ሳይያዝ መገኘቱ ነው:: በመሠረቱ ከዚህ ላይ መስተካከል ተደርጎ በቀኖናቱ መሠረት 81 መጻሕፍት ይመጣሉ:: ሌላው ችግር የግሪኩ መቃብያንና የግእዙ - የአማርኛው መቃብያን ይዘትና ምዕራፍ ልዩነት ነው:: ቀጥሎ ሌላው ችግር 8ቱ መጻሕፍተ ቀለማንጦስን /8 ብሔር ዘቀለማ.ንጦስን/ ለይቶ 12

www.ethiopianorthodox.org

ማረጋገጥና ከዚያም ከግሪክ 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ዘቀለሚንጦስ ጋር ማመሳከሩ ነው:: ፈጽሞ ግንኙነት የላቸውም ነው ለማለት ባይቻልም በሌላም በኩል ከቀኖናቱ በመለስና ብዙም ሳንርቅ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገኙበት መልካቸው መመልከትና ማነጻጸር ይሆናል::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 81ም ሆኑ ወይም አልሆኑ /በዙ ወይም አነሱ - ተቀነሱ/ ቅዱሳት መጻሕፍት ለሕዝብ በቀላሉ ሊገባ እንዲችል በማሰብ በግእዝና ነጠላ አማርኛ ትርጉም ተተርጉመው በ1918 የእጅ ጽሑፎች፣ በ1929 ፎቶ ኦፍሴት፣ በ1947/1953/ እና በመጨረሻም ሌሎች መጻሕፍትም ተጨምረውባቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በ1980 ታትመው ተሰራጪተዋል:: እነዚህን የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ርስ በራሳቸውን በማነጻጸር በተለይ በተጨማሪ ከያዟቸው ሌሎች መጻሕፍት በመነሳት በመጨረሻ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በ1980 የታተመ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን፡ በመጀመርያ ብሉይ ኪዳንን በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ፆታተመ ብሉይ ኪዳንን እንደ ሰብዓ ሊቃናትና ማሶራዊ ብሉይ ኪዳንን መሠረት አድርጐ ከታተመ ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ጋር ለማነጻጸር ሲሞከር የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና የሚባሉት መጻሕፍትን ብቻ ይዞ በመገኘቱ ሊለይ ሲችል በግእዝ-አማርኛው ብሉይ ኪዳንና በግሪኩ ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት መካከልም ቢሆን በቂ ልዩነት ይታያል::

1. ግእዙ - አማርኛው ብሉይ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት የሌሉ በቀኖናተ መጻሕፍትም ያልተመለከቱ መጻሕፍትን ይዞ ይገኛል:: መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤልን፣ ጸሎተ ምናሴን፣ ተረፈ ኤርምያስን፣ ኩፋሌንና ሄኖክን ይዞ በመገኘቱ ትልቅ ልዩነት ይታያል:: በሌላ በኩል ደግሞ ከ...



መጻሕፍት መካከል የሚገኙትን መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና=ሶስናን፣ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅን፣ ተረፈ ዳንኤልንና ከመጻሐፈ አስቴር ተመሳሳይ ክፍሎችን ለይቶ ይዞ በመገኘቱ በዚህ ይለያል:: ልዩነቱ የይዘት ባለመሆኑ መሠረታዊ አለመሆኑ ሲደገፍና ሆኖም ከዚህ የተነሳ ግሪኩ ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት 49 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ይዞ ሲገኝ ግእዝ-አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በመቅድሙ እንደተመለከተው 52 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ሆኖም ግን 54 መጻሕፍትን ይዞ ይገኛል:: 52 ሊሉ የታቻሉበት ምክንያት ሦስት መቃብያን አንድ መቃብያን ተብለው ስለመዘገቡ ነው:: ይህም ሲባል ጸሎተ ምናሴ፣ ጥበበ ሲራክ፡ ጸሎተ - መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ከትንቢተ ዳንኤል (ም.3ቁ. 23 እና 24 መካከል ቁ. 1-67) እና ተግሣጽ ከምሳሌ ሰሎሞን (ም.25 - 31) ተለይተው ወጥተው ሳይጨመሩበት ነው:: ሲጨመሩ ግን የአማርኛው ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 58 ይሆናል:: ከዚህም ጋር የቃላት አመራረጡ እንደተጠበቀ ሆኖ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሁለት መልኮች መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና እና መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተብለው ተከፍለው መታየታቸው አይታለፍም::

ሐዲስ ኪዳንን በመሚመለከት በሁለቱ ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ግእዝ-አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ 8 መጻሕፍተ ቀላሚንጦስን እንደ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቆጥሮ ባለመያዙ ልዩነት አይታይም:: ምክንያቱ ሁለቱም ቢሆኑ 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ብቻ ይዘው መገኘታቸው ነው:: በዚህ ጽሑፍ የሚታየው ጉዳይ የአዲስ ቃላትን አጠቃቀም አማራጭ የማግኘቱ ጉዳይ ነው:: ከላይ የተጠቀሱት ቀኖናተ መጻሕፍት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት በአንድነት ወይም እንደ አትናቴዎስ በተናጠል ቀኖናዊ ኃይልን ለመስጠት በተቀረጹበት ቋንቋ - ግሪክ /ልሳነ ጽርእ/ የተለያዩ ቃላትን ተጠቅመዋል:: እነዚህ ቃላት

www.ethiopianorthodox.org

በአማርኛ ምትክ ቃላትን ማግኘት ስለሚያስቸግር እንደተለመደው ወደ ግእዝ ቋንቋ ቃላት የተሻለ አማራጭ ፍለጋ መመለስ ነበር አስፈላጊው ሁኖ የተገኘው::

ስለዚህም ከዚህ ግእዝ ቋንቋ ቃላት: ስም፣ ግስ፣ ወይም ቅጽል ላይ በአዲስ ቅርጽም ቢሆን አዳዲስ ቃላትን መፍጠር ወይም ለተለመዱት ቃላት አዲስ ትርጉምን መስጠት ነበር አማራጩ:: ለምሳሌ ቀኖናዊ ኃይል ሊሰጣቸው ለሚያስፈልጉ ወይም የሚሰጣቸው ሁነው ለሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍትም የተሰጠው አንዱ ቅጽል ምትክ ወይም ትርጉም ቃል: ቅጽል «ምቅናን» - «ምቅናናውያት» የሚል ሆኖ ተመርጧል:: ከዚህም ጋር በተመሳሳይነት ንባባውያትና «ምንባባውያት» የሚሉ ቅጽሎችንም ተጠቅመን እንገኛለን:: መነበብ ያለባቸው ወይም መነበብ እንዳለባቸው ለተደነገጉ ቅዱሳት መጻሕፍት ለተሰጠው ቅጽል ምንም እንኳን ከሰዋሰው አንጻር ምትክ ትርጉም ሆኖ ሊገኝ የሚያስችለው ቅጽል «ንቡባት» የሚለው ቢሆንም ለንባብ ቀናነት «ንባባውያት» የንቡባትን ትርጉም ይዞ እንዲቀረጽ ተደርጓል::

ቀጥሎ መነበብ የሚኖርባቸው ተብለው ለተገለጹት መጻሕፍት ለተሰጠው ቅጽል አሁንም ይህንኑ ትርጉም እንዲይዝ ሆኖ በመታሰብ «ምንባባዊ» - «ምንባባውያን(ት)» የሚል ቅጽል ተወልዷል:: ሌሎች ግን በቦታው እንደሚያመለከተው ምትክ ቃላት ተገኝቶላቸዋል:: አምላካውያት፣ ቀኖናውያት፣ በሐረግም ቢሆን ጽሑፋት በመንፈስ እግዜአብሔር::

ለመሆኑ ጽሑፉ ተሠራጭቶ በሙሉ ከተነበበ በኋላ አማራጭ ቃላት ከተገኙ መቀበሉ አያጠያይቅም:: በመጨረሻ አቅም ከፈቀደና በኢትዮጵያ በተለይ ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በኩል የሚደረግ ትብብር ከተገኘ



1. የግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት 3 መቀብያንን ወደ አማርኛ በመተርጎምና በመጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሚገኙት 3 መቃብያን ጋር አስተያይቶ

2. ስምንቱ(8) ግሪክ ሐዋርያውያት ትእዛዛትን ዘቀለሚንጦስ ወደ አማርኛ በመመለስ ከዚያም የፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 መተርጉማንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ምን ያህል በቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክና ትርጓሜ መደገፋቸውን ለመረዳት ባልችልም የራሳቸው አመለካከት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በሐዋርያውያት ቀኖናት-ሲኖዶሳት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ 81 ቁጥር አስደርሰዋል ተብለው በታሪክ የሚታመኑትንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን ወደ አማርኛ መልሶ ከእነሱም ጋር አነጻጽሮ ምክንያቱም የይዘት ልዩነታቸው በጣም ሰፊ ነውና::

3. ግሪክ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናትን ወደ አማርኛ በመተርጎምና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መድበለ ቀኖናት «ሲኖዶስ» ተይዘው የሚገኙትን አራት ግእዝ ሐዋርያውያት ቀኖናት ምስለ ቀለሚንጦስንም ወደ አማርኛ በመመለስ ሁለቱን አቅራርቦ ማሳተምና ለማሳየት ምኞት አለኝ::

www.ethiopianorthodox.org

በመጨረሻ ይህ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቅድሚያ ከአገለጉሉትና በየቦታው ከሚገኙት መሠረታውያን ምንጮች: ሲኖዶሳውያትና አበውያት ቀኖናት በሌሎችም ብዙ ድጋፍ ሰጭ መረጃዎች ሊገናዘቡም ቢችሉ ቅሉ ከኅትመት ወጭ ቁጠባ አንጻር ሲባል መጽሐፉ የበለጠ እንዳይገዝፍ በመፍራት መጀመሪያ ወይም በመጨረሻ አልተመለከቱም:: ከዚህም ጋር ዋና መሠረታውያን ምንጮችም ቢሆኑ ከግርጌ ማስታወሻ አልፈው በመዝገበ መጻሕፍት (Bibliography) ሰፍረው አይታዩም::



# ምዕራፍ አንድ

# ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው ስለታዘዙ 81 አምላካውያት መጻሕፍት

«በእንተ መጻሕፍት አምላካውያት ዘእዙዝ ተወክፎቶን ኀበ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ዘትልቆሙ 81» = «ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው ስለታዘዙና ቁጥራቸው 81 ስለሆነ አምላካውያት መጻሕፍት»[1]

## 1. «አምላካውያት መጻሕፍት»ና ምንጮች-ቀኖናት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንድዋ እንደመሆኗ መጠን የምታስተምረው ትምህርተ መለኮትና የምትፈጽመው ሥርዐተ አመልኮት በቅዱሳት መጻሕፍትና በቅዱስ ትውፊት ላይ ተመሥርቶና እየዳበረም የመጣ ነው::

ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ስንመለከት በመጀመሪያ የሚነሳው ጥያቄ በበጐ መልክም ሆነ በደካማ ስልቱ የቁጥራቸው መጠን ነው:: አንድ ነገር ኖሮ ከአንድ በላይ ከሆነ ብዙ ነው የሚባለው ግን ስንት መሆኑ አንድም በአሐዝ: ሁለት፣ ሦስት፣ አራት ተብሎ ተወስኖ ይታወቃል ወይም በግምት ይህን ያህል /10 ወይም 15 ያህል /ተብሎ ይነገራል::

1. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2(ርእሰ) - ምንጮች ረስጠአ 81 እና ረስጠብ 56:: ነገር ግን ረስጠብ 56 ስለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር አይናገርም:: ስለዚህ በስሕተት ረስጠጅ 56 ረስጠብ 56 የተባለ ይመስላል ምክንያቱም እንደረስጠአ 81 ረስጠጅ 56 ነው ስለ ቅዱሰት መጹሕፍት ዝርዝር የሚናገረው:: ወደፊት እንደም ንመለከተው ስለቅዱሳት መጸሕፍት ዝርዝር የሚናገረው የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ረስጠአ 81 እና ረስጠጅ 56 እንጂ ረስጠብ 56 አይደ ለም:: ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና፤ አዲስ አበባ 1986 ረስጠአ ገጽ 137 - 166 ረስጠብ ገጽ 167 - 196 እና ረስጠጅ ገጽ 197 - 205::

www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን ይህን ያህል ይሆናል ተብሎ ቁጥራቸው በድፍኑ ሊታለፍባቸው የማይችሉ ነገሮች አሉ ለምሳሌ የተነሳንባቸው ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው ያዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን ያህል ናቸው ወይም ይሆናሉ ተብሎ የሚታለፉ አይደሉም:: የግድ በግልጥ ማንነታቸው ተዘርዝሮ ትክክለኛ አሐዛዊ ቁጥራቸው መረጋገጥ ይኖርበታል:: ይህ ካልሆነ እውነተኞች ቤተክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጻሕፍትን ከአልባሌ መጻሕፍት ለይቶ ለመገልገል እንዴት ይቻላል? ለዚህ ምሳሌ «እመቦ ብእሲ ዘነሥአ እመጻሕፍተ ሐሰት እንተ እንበርዋ ከሐዲያን ወአብአ ውስተ ቤተ ክርስቲያነ እግዚአብሔር ቅዱስ ከመ ይእቲ መጽሐፈ እግዚአብሔር ንጽሕት በእንተ ሙስና ሕዝብ ይሰደድ» « ከሐዲያን ከአስቀመጧቸው የሐሰት መጻሕፍት የወሰደና ሕዝብን ለማሳሳት ንጽሕት የእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደሆነች አድርጐ ወደ ቅዱስ እግዜአብሔር ቤተ ክርስቲያን ያስገባ ሰው ይለይ»[2]

ከዚህም በመነጨ አብያተ ክርስቲያናት ለትምህርተ መለኮት፣ ሥርዐተ አምልኮት፣ ሕግና ሥርዐት የምትገለገልባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአሐዝ ተለይተው ይታወቃሉ:: ከዚህም አንጻር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በተ ክርስቲያን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 81 መሆኑ ይነገራል:: ይህም በመነሻው እንደተመለከተው በፍትሐ ነገሥት 2ኛው አንቀጽ ርእስ መመልከቱ ሲታይ መጻሕፍቱ ሲዘረዘሩ ግን 81 አይደሉም /ወደ 81 አይደርሱም እንደ ምንጭም የተጠቀመባቸውም ሐዋርያውያት ቀኖናት (ረስጠአ 81 እና ረስጠጅ 56)[3] ይህን አሐዝ አይመልሱም:: ነገር ግን መጻሕፍቱ ሲዘረዘሩ 73 መጻሕፍት ሁነው ነው የሚገኙት:: የተመለሱባቸው 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ይዞአቸው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት ቁጥር 78 ወይም 78+1=79 ነው::

እንግዲህ አንድም ይህን 81 ቁጥር ወይም በዝርዝር የተመለከቱትን 73 መጻሕፍት ለመቀበል በመጀመሪያ እነዚህ 81 ተብለው የታዘዙት መጻሕፍት በስምና በዝርዝር ተለይተው መታወቅ ይኖርባቸዋል::

ስለዚህ በስምና በዝርዝር እንኳን ሊታወቁ ቢችሉም እንኳን የእያንዳንዱ መጽሐፍ ርግጠኛነት ታምኖበት ሆኖ እንዴትስ በ81 ቁጥር ተወሰኑ?

ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጽሕፍት 81 መጻሕፍትም ሆኑ ወይም አነሱ ወይም በዙ ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ አሁን ቤተክርስቲያን ተቀብላቸው ስታ ስተምርባቸውና ስትገለገልባቸው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ጊዜ ተገኝተው 81ንም ሆነ ወይም ሌላ ቁጥርን አልያዙም:: በብዙ ዘመናት መካከል የተጻፉ ሆነው ግን በሐዋርያት፣ ቅዱሳት ሲኖዶሳትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቀኖናት እየተሰባሰቡና እየተለዩ መጥተው በመጨረሻ አሁን በአብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንመለከታለን::

ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጻሕፍት ብቻ አልነበሩም «ቅዱሳት፣ አምላካውያት፣» ወዘተ የሚባሉትም፣ እነዚህን ቅጽሎች ይዘው የተሰራጩ ግን ቅዱሳት መጻሕፍት

---

2. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ቁጥር 19: ምንጮች ረስጠአ 55 እና ረስጠብ 41:: ዲበኩሉ ዘውዴ ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ረስጠአ ገጽ 137 - 166 ረስጠብ ገጽ 167 - 196::

3. ወደፊትም ስለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር በሚነገርበት ቦታ ረስጠብ ተብሎ ቢገኝም በዚህ ጽሑፍ ወደ ቦታው ተመልሶ ረስጠጅ ነው እየተባለ የሚገኘው::


www.ethiopianorthodox.org

ያልነበሩ /ያይደሉ/ ብዙ መጻሕፍተ ሐሰት /Peudepigraha - Ψευδεπιγραφα/ መገኘታቸው የታወቀ ነበር:: የአንድ ቅዱስ መጽሐፍ እውነተኛ አምላካዊነት - (ΘΕΤΟΝ) አምላካዊ ሆኖ መገኘት የሚረጋገጥበት ቅድመ መመዘኛ «ቅዱስ» የሚለውን ቅጽል መግጠነው አይደለም ግን ይዘቱና መንፈሱ አምላካዊ - የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት /የተቃኘበት መጽሐፍ ሆኖ መገኘቱ ነው[4]::

ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ይህን» ቅዱስ/ቅዱሳት፣ ቅዱሳን/ የሚለውን ቅጽል በመሻማት ብዙ አምላካዊነት የሌላቸው መጻሕፍት እየተጻፉ መሠራጨታቸው ድብቅ አልነበረም:: ከዚህ በመነጨ ክርስቲያኖች አንዱን «ቅዱስ መጽሐፍ» ከሌላው «ቅዱስ መጽሐፍ» ለይቶ የመቀበሉና የመጠቀሙ ጉዳይ በጣም አስቸጋሪ ነበር:: አሁንም ሊሆን ይችላል::

ለነዚህ ቅዱሳት ሲኖዶሳትም ሆኑ አባቶች እንደእየአጋጣሚው የተረዱትን ያህል-ያረጋገጡትን ያህል አምላካውያት መጻሕፍትን[5] በመለየት የቅዱሳት መጻሕፍትን ቀኖናት/ቀኖናተ መጻሕፍት አምላካውያትን/ እየቀረጹ ለማስተላለፍ ጥረት አድርገዋል::

በየጊዜው በቅዱሳት ሲኖዶሳትም የተደነገጉ፣ በቅዱሳን አባቶች የታወጁ የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ቀኖናት ቀስ በቀስ እየተሟሉ በመምጣት ለጊዜዉም ቢሆን የተወሰኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ድምርን የያዙ ቀኖናት ሊሰፍኑ ችለዋል:: በአንድ ወጥነት ተቀባይነትን ወደ ማግኘት ደርሰዋል::

---

4. ሁለተኛ ጢሞቴዎስ 3.16 - 17 «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፤ ልብንም ለማቅናት፤ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል»
5. አምላካዊነት ሲባል ከሥነ መለኮት ጋር ማዛመድ ሳይሆን ስለ አምላክነት - መለኮትነት ቤተ ክርስቲያን የምታስምርባቸውን መጻሕፍት ይዞታ ይመለከታል::



በአጠቃላይ መልካቸው ሲታዩ በአንድ ወይም በሌላው የቅዱሳት ሲኖዶሳት ወይም የአባቶች ቀኖናት ቁጥሮቻቸው የተዘረዘሩት ቅዱሳት መጻሕፍት በአብዛኛው አንድም ሲበዙ ወይም ሲቀነሱ ቢገኙም ቅሉ ተመሳሳይነታቸው ያይላል:: ከዚህም በመነሳት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፍትሐ ነገሥትን በመመርኮዝ ይመሳሰላል 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ አሉ ይነገራል[6]:: ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስያን የምትቀበላቸው፣ የምትጠቀመባቸውና ምሥጢረ መለኮትን የምታስተምርባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት እነማን /የትኞቹ/ ናቸው? እነዚህም ከታወቁ በትክክል 81 ናቸው? ይበዛሉ? ወይስ ያንሳሉ? ሌሎች የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ከሚገላገሉባቸውና ከሚያስተምሩባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ጋርስ በስም፣ በዓይነትና በመጠን ይመሳሰላሉ? ወይም ልዩነት ይታይባቸው ይሆን? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች የሚጠብቁት መልስ አንድም እንደ ፍትሐ ነገሥቱ ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍት 81 ናቸው ብሎ መቀበል ወይም ራሱ ፍትሐ ነገሥት 81 ቅዱሳት መጻሕፍት ብሎ ተነስቶ ሲዘረዝራቸው 73 ስለሚሆኑ 81 ቁጥርን አስተባብሎ 73 ቁጥርን መቀበሉ ወይም በሆነ መንገድ የሚቻል ከሆነ ሁለቱን ቁጥሮች ለማስታረቅ መሞከር ወይም ከታሪክ ጋር በማዛመድ ቅዱሳት ሲኖዶሳትና ቅዱሳን አባቶች ቀኖናትን እየሰሩላቸው የመጡትን መጻሕፍት ዝርዝር በመመርመር ወደ አንድ መደምደሚያ አሐዝ መድረስ ይሆናል::

ከዚህ በመነሳት እነዚህ ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙትን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ለማመልከት /ለመቀነንና ለማስተላለፍ/ የተደረጉትን ጥረቶች አስመልክቶ በአጭሩ እስከ 451 ዓ.ም. (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር እስከ ነበራት አንድነት ዘመን ድረስ) በቅዱሳት

www.ethiopianorthodox.org

ሲኖዶሳትና በቅዱሳን አባቶች በምዕራብም ሆነ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የተደረጉትን ተከታታይ ጥረቶች መመልከት አንዱ መሠረታዊ ቁም ነገር ነው::

ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሥነ መለኮት ለትምህርተ መለኮትና ሥርዐተ አምልኮት በአጠቃላይ ለትምህርተ ክርስትና እንድትቀበላቸው፣ እንድትጠቀምባቸውና እንድ ትገለገልባቸው ሁነው ተገኝተው የተደረሰባቸው አምላካውያት መጻሕፍትን ዝርዝር ወይም ለእነዚህ ትምህርቶች: ነገረ መለኮትና ሥርዐተ አምልኮት ማስተማርያና ማሳመኛ ምንጭነት የተጠቀመችባቸውንም አሁንም ቅዱሳት መጻሕፍትን ከአመለከቱት ሲኖዶሳውያት ቀኖናት፣ ቀኖናተ አበው፣ ከቤተክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት የተወሰኑትን ለማስረጃ ያህል ቀጥለን እናመለክታለን::

## 1. ቅዱሳት ሲኖዶሳት

1.1 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት /85ኛ ቀኖና/[7]፤

1.2 በጳጳስ /ፓፕ/ ደምሲስ ቀዳማዊ/ 366 - 384 /በሮሜ በ302 ተጠርቶና የግላሲያኖስን ድንጋጌ - Decretum Gelasianum ያወጀው ጉባኤ - ሲኖዶስ[8]፤

1.3 በኢጳን (ሰሜን አፍሪካ) በ393 የተጠራ ጉባኤ- ሲኖደስ 6ኛ ቀኖና[9]፤

7. Ραλλη-ποτλη: Συνταγμα των θείων και Ιερων Κανονων; Αθηνα, 1852 - 1859 T.B; ገጽ 109 -110 J.P Migne, Patrologiae Cursus Completus Series Gracca, Parisiis 1857. T. 137. ዐምድ 212 B -D, Mansi: Sacrorum conciliorum Nova et amplissima Colletio, Austria 1960 - 1961. T.1. ዐምድ48 A-C.
8. Decretum de libris recipiendis et non recipiendis, T.1. J.P. Migne: Patrologiae Cursus completus series latina, parisiis 1878... T. 19 ዐምድ 157-159: 166-168::
9. Concilii Hipponcnsis, statuta canon XXXVI. : Mansi : Sacrorum Conciliorum.. T.3 ዐምድ 924 A - C.



1.4 በካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ በ397 የተሰበሰበ 3ኛ ጉባኤ - ሲኖዶስ /የ393 ሲኖዶስ 6ኛ ቀኖና የጸደቀበት 47ኛ ቀኖና/[10]፤

1.5 በካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ በ419 የተጠራ ጉባኤ-ሲኖዶስ /የ393 ኤጳን ሲኖዶስ 6ኛ ቀኖና እና የካርታጌኒስ/ ቅርንጣግና /47ኛ ቀኖና የጸደቀበት /Codex canonum ecclesiae africanae, ቀኖና 29[11]፤

1.6 በሎዶቅያ /ላኦዶቅያ/ በ360 የተጠራ ጉባኤ - ሲኖዶስ /60ኛ ቀኖና/[12]፤

## 2. የቤተ ክርስቲያን አባቶች

### 2.1 በመሥራቅ ክልል

2.1.1 ሚሊጦን ሰርድዮን (180 ገደማ) ለጓደኛው ኦኒሲሞን የጻፈው ደብዳቤ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ዝርዝር - መዝገበ መጻሕፍት ብሉይ ኪዳን አስፍሮ ይገኛል[13]::

10. Councilium Carthaginense canon XLVII (47); Mansi: sacrorum conciliorum nova et amplissima collectio .. t. 3 ዐምድ 891 A - B.
11. Ραλλη-ποτλη: Συνταγμα των θειων και Ιερων Κανονων T.Γ. ገጽ 368 - 369; J. Mansi: sacrorum conciliorum... T.3 ዐምድ 273 - 724 A - C: T. 4 ዐምድ 430 A - B.
12 Ραλλη-ποτλη: Σύνταγμα των θείων και Ιερων Κανονων T.Γ. P. Migne: ገጽ 225 - 226 Patrologiae Cursus completus series Graeca ... T. 137 ዐምድ 1420 B - C ; Mansi; sacrorum concilium ... T. 2 ዐምድ 574. D-C/.
13. አውሳብዮስ ዘቂሳርያ: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 4ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 26 ቁ. 13 -14.



www.ethiopianorthodox.org

2.1.2 /ኦርጌኒስ/ኦርጌኒስ/ 2252 - 254/ በመዝሙረ ዳዊት ትርጓሜው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ዝርዝር ያመለክታል[14]:: ከዚህም በስተቀር በማቴዎስ ወንጌል[15]፣ በዮሐንስ ወንጌል[16]፣ በዕብራውያን መልእክት[17] ስለ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ያወሳል::

2.1.3 አውሳብዮስ ዘቂሳርያ /+340/ተቀባይነትን ያገኙትን፣ በክርክር ላይ /በጥያቄ ውስጥ/ ያሉትንና ስህተት ያለባቸውን መጻሕፍት ልዩነቶች ያሳያል[18]::

2.1.4 ትልቁ አትናቴዎስ /+393/ ወደፊት የምንመለከተው በ39ኛ የፋሲካ መልእክቱ[19]፤

2.1.5 ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም /+385 - 386/ በ4ኛ ትምህርተ ንዑስ ክርስቲያን[20]፤

2.1.6 ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት — ታኦጎሎስ /ቴሎጉስ /+390/ /ወደፊት በምንመለከተው /በ34 ስንኝ ግጥሞች/[21]፤

2.1.7 ኤጲፋንዮስ ዘሳላሚኖስ ዘቆጵሮስ /+403/ በ80 ክህደቶች /ምልዓተ አርዮስ/ ላይ በጻፈው ድርሰቱ[22]፤

2.1.8 ዮሐንስ አፈወርቅ /+407/ በብሉይና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አጭር መግለጫው (synopsis)[23]፤

2.1.9 አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን /+395/ ለሴውኩስ «አንድ ዝነኛ ወጣት» በሚል መነሻ በአወራረዳቸው ግጥሞት[24]፤

2.2 በምዕራብ በኩል የቤተ ክርስቲያን አባቶች

2.2.1 በ2ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ በአንድ ባልታወቀ ጸሐፊ ተዘጋጅቶ የሚገኘው የሐዲስ

---

14. P.Migne: Partrologiae... Graeca T. 12 ዐምድ 1984 B - C.
15. P.Migne: Patrologiae ... Graeca T. 13 ዐምድ 829 A.
16. P. Migne: Patrologiae... Graeca T. 14 ዐምድ 188 C - 189 A.
17. P. Migne: Patrologiae ... Graeca T. 14 ዐምድ 1308 D - 1309 B.
18. አውሳብዮስ ዘቂሳርያ: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 3ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 25 ቁ. 1 - 14.18.
19. Ράλλη-ποτλη: Σύνταγμα των θειών καὶ Ἱερων Κανόνων Τ.Δ. ገጽ 78 ...፣ ΣΤ. Σάκκου: Η Λθ ἑορταστική ἐπιστολή τοῦ Μ. Ἀθανασίου 1973-74 ገጽ 41፣ P. Migne: Partrolgiae... Graeca... T. 26 ዐምድ 1176 B - 1180 A., 1436 B - 1440 T. 28 ዐምድ 283-438::
20. Κυρίλλου Ἱεροσολύμων: Κατηχήσεις Περιτων Θείων Γραφῶν (ትምህርታተ ንዑሳነ ክርስቲያን) : P. Migne: Patrologiae ... Graeca T.33. ዐምድ 493 C - 501A

21. Γρηγορίου θεολόγου ἔπη ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ግጥሞች: መጽሐፍ 1.1.12 Ράλλη-ποτλη: Σύνταγμα των θείων καὶ Ἱερων Κανόνων Τ.Δ. ገጽ 363 - 364፣ P. Migne: Patrologiae.. Graeca.. T.37 ዐምድ 472A. 474 A; T.138. ዐምድ 924 A-C. T.38. ዐምድ 841 - 846.
22. ኤጲፋንዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘሳላሚና Κατὰ αἱρέσεων ὀγδοήκοντα [πανάριος] «በ80 ክህደቶች ላይ» 1ኛ መጽሐፍ T.1 8.6 P. Migne: Patrologiae ... Graeca.. T.41. ዐምድ 213 A -B; 2ኛ መጽሐፍ T.1.76.5; P. Migne Patrologiae ... Graeca... T. 42 ዐምድ 560 D - 561 A.T.
23. ዮሐንስ አፈወርቅ Σύνοψις τῆς παλαιᾶς καὶ καινῆς Διαθήκης P. Migne: Patrologiae... Graeca.. T. 56 ዐምድ 313 - 317.
24. Ράλλη-ποτλη: Συνταγμα των θείων κυὶ Ἱερων Κανόνων Τ.Δ. ገጽ 365 - 367; P. Migne: Patrologiae... Graeca.. T 37 ዐምድ 1593 A - 1598 A. T. 138. ዐምድ 925 C - 928 D.


www.ethiopianorthodox.org

ኪዳን መጻሕፍት ቀኖና-ቀኖና ሙራቶሪ -Muratori ነው:: ነገር ግን ይህ ቀኖና Muratori እንድም ለአቡሊዲስ ዘሮሜ /+235/ ወይም ለጳጳስ ቢክቶር /+189 - 199/ ወይም ለዘፈሪኖስ /199 - 217/ እየተሰጠም ይገኛል::

ይህ ቀኖና Muratori ዘሐዲስ ኪዳን በሚላኖ የአምብሮሲዮስ ቤተ መጻሕፍት በአንድ Muratori በሚባል ጣሊያናዊ ታሪክ ፀሐፊ ተገኝቶ በ1740 በራሱ በአገኘው ሰው በመታተሙ ይህን ስም ሊይዝ ችሏል[25]::

2.2.2 በሰሜን አፍሪካ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ዝርዝር ይዞ የሚገኘው /359 - 360/ መዝገብ ሌላው ሲሆን ይህ መዝገበ መጻሕፍት ቅዱሳት በ1886 በCheltenham በ T. Mommsen በላቲን ቋንቋ ተጽፎ የተገኘው ነው[26]::

2.2.3 በላቲን ግሪክ ቋንቋዎች በ4ኛው ምዕተ ዓመት ተጽፎ የሚገኘው የክላሮሞንታኑስ (Claromontanus) መዝገበ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ ነው[27]::

---

25. ΣΤ. Σακκου: ὁ κατάλογος τοῦ Muratori Συμβολή εἰς τήν εἰσαγωγήν εἰς τὴν Καινήν Διαθήκην, Θεσσαλονίκη 1970 , T. Zahn: Geschichte des neutestamentalischen Kanons 1970 T.2. 1-11 1890-1892 ገጽ 5 - 8. 139 - 143.
26. T. Zahn: Geschichte des neutestamentalischen Kanons T. 2.1 ገጽ 143 - 145.
27. T. Zahn: Geschichte des Neutestamentalischen Kanons T. 2.1 158 - 159, A souter - C. Williams: The Text and Canon of the New Testament London, 1960 ገጽ 194 - 195.

2.2.4 ፊላስትርዮስ ዘብረስኪያ /+397/[28]

2.2.5 ሩፊኑስ /ሩፊኖስ/ የአኩዊሊያስ ዘጣሊያን ሊቀ ካህናት /+410 - 411/[29]

2.2.6 ታላቁ ጸሐፊ ኢሮኒሞስ /+420/[30]

2.2.7 ታላቁ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ አውግስጢኖስ የኤጶን ኤጲስቆጶስ /+430/[31]

እስከ አሁን የተዘረዘሩት ሲኖዶሳትም ሆኑ አባቶች ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አንድም በሥነ ጽሑፎቻቸውና በንግግሮቻቸው በምንጭነት ወይም ሆነ ብለው የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝር የሚመለከቱ ቀኖናትን ለመቅረጽ እንደ ተነሱ ተመልክተናል:: ስለዚህ በተለይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝሮች የሚደነግጉ የቅዱሳት ሲኖዶሳትንና የቅዱሳን አባቶችን ቀኖናት በዝርዝር እንመለከታለን::

---

28. S. Philastrii : Liber de haeresibus 88. P. Migne: patrologiae... Latina T. 12 ዐምድ 1999 A - 1200 A, A. Souter - C Williams : The Text and Conon of the New Testament ገጽ 201 - 203.
29. Rufini, Aquileiensis presbyterii, commentarius in symbolum Apostolorum 37 : P. Migne: patrologiae... Latina T. 21 ዐምድ 373 - 374 A -B; A. Souter - C. Williams : The Text and Canon of The new Testament ገጽ 201 -203.
30. Eusebii Hieronymi: epistolae 53, Ad paulinum 8. P. Migne: patrologiae ... Latina T. 22 ዐምድ 545 - 549 : Praefactio in libros Solomonis. P. Migne : Patrologiae .. Latina T. 28 ዐምድ 1306 - 1308, syonopsis Divinae bibliothecae ex epistola Hieronymi ad paulinum desympta. P. Migne : patrologiae ... Latina T. 28 ዐምድ 173 - 178.
31. S. Aurelii Augustini : De doctrina christiana Lib 2.8.13 P. Migne : patrologiae ... Latina T. 34 ዐምድ 41 A. souter - C williams : The Text and canon of the New Testament ... 204 - 205.

www.ethiopianorthodox.org

እስከ አሁን የተዘረዘሩት ሲኖዶሳትም ሆኑ አባቶች ስ[illegible] ቅዱሳት መጻሕፍት አንድም በሥነ ጽሑፎቻቸውና በንግ[illegible] ሮቻቸው በምንጭነት ወይም ሆነ ብለው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚመለከቱ ቀኖናትን ለመቅረጽ እንደ ተነ[illegible] ተመልክተናል:: ስለዚህ በተለይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝር የሚደነግጉ የቅዱሳት ሲኖዶሳትንና የቅዱሳን አባቶችን ቀኖና[illegible] በዝርዝር እንመለከታለን::



# ምዕራፍ ሁለት

# ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት

## 1. ሲኖዶሳውያት ቀኖናት

### 1.1 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሐዋርያት በሲኖዶስ የወሰኗቸው /የደነገጓቸው/ 85 ቀኖናት እንደ አሉ ይተረካል:: በርግጥ «ሐዋርያውያት ቀኖናት» እንደተባለው በሐዋርያት ሲኖዶስ ተደንግገዋል ወይ? ነው ጥያቄው:: የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ምንጮችም ራሳቸው ሐዋርያት ስለመሆናቸው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፍትና የቀኖናተ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ምርምርና ጥናት ርእስ ሆኖ ሲያመራምር ቆይተል::

በመጀመሪያ በተለይ ከምሥራቅ ቤተ ክርስቱያን ልምድ ስንነሳ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት የሐዋርያትን ትምህርትና ሥርዐት ይዘው ቢገኙም ቅሉ በቀጥታ በሐዋርያት ሳይሆን ከእነሱ በኋላ የዳበሩ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ይዘው ግን ቆይተው እንደተቀረጹ ነው የምንረዳው[1]::

ስለዚህ እነዚህን 85 ሐዋርያውት ቀኖናት በሐዋርያት ትምህርት ላይ ተመሥርተው ግን በሐዋርያት ስም እየተጠሩ የመጡ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናት መሆናቸውን በማረጋገጥ በ691 በትሩሎ የተጠራው 5ኛ - 6ኛ ሲኖዶስ አጽድቋቸዋል:: በዚህም ወቅት ነበር ይህ ዐቢይ ሲኖዶስ በእነዚህ ቀኖናት 85ኛው ቀኖና የቅዱሳት መጻሕፍት ዘር ሆነው የሚገኙትን ባለ 8 መጻሕፍት «ሐዋርያውያት ትእዛዝትን» /በእኛ 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ የሚባሉት ይሆን?/ ባዕድና ስህተት ትምህርት አለባቸው በማለት ውድቅ ያደረጋቸው[2]:: በተመሳሳይ ሁኔታም

1. [illegible] ብሉይ ሕግ ወቀኖና:: ገጽ 137::
2. [illegible] 2::

www.ethiopianorthodox.org

በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ከሐዋርያት ስለመምጣታቸው ያከራክርም ነበር ለምሳሌ የሮማ ሊቀ ጳጳሳ ጌላስዮስ ቀዳማዊ /492 - 496/ ሐዋርያውያት ቀኖናት በሐዋርያት ስም የመጡ እንጂ በሐዋርያት ያልተጻፉ መሆናቸውን አውጆ እንደ ነበር ይታወሳል[3]:: እነዚህ አባቶችና ሊቃውንት በተከታታይ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር በየአጋጣሚው ለማመልከት ጥረት አድርገዋል::

በምዕራብ በላቲን ቋንቋ ተመልሰው በመጀመሪያ ሊታወቁ የቻሉት የመጀመሪያዎቹ 50 ቀኖናት ነበሩ:: ነገር ግን የቀሩት 35 ቀኖናት ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ጋር የሚቃረኑ በመሆናቸውም ምክንያት ለምሳሌ ቀዳሚ ቀንን መጾምን የሚከለክለው 66ኛው ቀኖና አልተተረጐሙም ነበር[4]:: ሆኖም ቆይተው እነዚህም ተተርጉመው በአንድነት 50+35 =85 ወይም 84 ቀኖናት ሁነው ሊያዙ ችለዋል::

በአጭሩ ሐዋርያውያት ቀኖናት በራሳቸው በሐዋርያት ተጻፉ የሚባል ከሆነ የ1ኛው ምዕተ ዓመት ሥራዎች = ቀኖናት ናቸው ማለት ይሆናል:: ነገር ግን በሌላ አጋጣሚም እንደምንገልጠው[5] ሐዋርያውያት ቀኖናት መቼ ተጻፉ? የሚለውን ጊዜ ለመወሰን የተለያዩ አስተሳሰቦችን በማቅረብ ይሆናል::

ስለዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት በሐዋርያት ዘመን መጻፋቸውን ለመደገፍ የሚያስችሉ ብዙ ምክንያቶችም ቢኖሩም ቅሉ በመጀመርያ ደረጃ ወይም ቅርጻቸው ሐዋርያውያት ቀኖናት

3. Codex canonum Ecclesiasticorum Dionycii exiquii dicuntar apostolorum.
4. «እሑድ ቀን ወይም ከአንድ ቀን በስተቀር ቅዳሜን ሲጾም የተገኘ ካህን ይሻር፣ ምእመን ከሆነ ይወገዝ»:: ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 38 የግርጌ ማስታወሻ 539.
5. ከዚሁ ገጽ 89 - 90



የጴጥሮስና ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ቆይቶም የሮሜ ኤጲስ ቆጶስ ቀለሚንጦስ የሐዋርያት ትምህርትና ትእዛዛት ግልባጮች እንደነበሩ ይደገፋል:: ለዚህም ድጋፍ እንደምንጭነት የሚያገለግለው በ85ኛው ቀኖና «ሐዋርያውያት ትእዛዛት ለእናንተ ኤጲስቆጶሳትና ካህናት በእኔ በቀለሚንጦስ እጅ ተላኩ የሚል የመጨረሻው ሐረግ ነው:: ነገር ግን በሐዋርያት ትምህርትና ትእዛዛት ላይ ተመሥርተውና ቆይተው ተቀርጸው ግን ለሐዋርያት ተሰጥተው መምጣታቸው ነው በአሁኑ ጊዜ አግባብ ዕውቀት በአላቸው ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶና ተሠራጭቶ የሚገኘው አመለካከት::

ስለዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በአሁኑ ቅርጻቸው ተቀነባብረው ሊገኙ የቻሉበት የጊዜ መነሻና ማቆሚያ ገደብ /Terminus a quo እና Terminus ad quem,/ ይታያሉ::

## ሀ. የሐዋርያውያት ቀኖናት ቅንብር መነሻ ጊዜ

ሐዋርያውያት ቀኖናት የተቀነባበሩበት መነሻ ጊዜ /Terminus a quo/ 2ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው ክፍል ዘመን /አጋማሽ ክፍል ዘመን/ ሲሆን

## ለ. የሐዋርያውያት ቀኖናት ቅንብር ማቆሚያ ጊዜ

ሐዋርያውያት ቀኖናት የተቀነባበሩት ጊዜ ገደብ - ማቆሚያ /Terminus ad quem,/ 3ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ መሆኑ ነው ከፍተኛ በቂ ድጋፍን ያገኘው ጊዜ

እንግዲህ ከይዘት አንጻር ሐዋርያውያት ቀኖናት 85 ቀኖናትን ይዘው ሲገኙ የመጨረሻው 85ኛ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙትን ማለትም ለሁሉም ለካህናትና

www.ethiopianorthodox.org

ምእመናን የተላኩትን ክቡራትና ቅዱሳት - አምላካውያት መጻሕፍት ዝርዝር የያዘው ቀኖና ነው[6]::

ከዚህም በመነሳት ይህን 85ኛ ቀኖና እንመለስበታለን:: "ለሁላችሁም ከህናትና ምዕመናን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት=ቅዱሳትና ክቡራት ይሁኑ::

5 መጻሕፍተ ሙሴ: ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቁ፣ ዘዳግም፣ ኢያሱ ወልደ ነዌ 1: መሳፍንት 1፣ ሩት 1፣ ነገሥት4፣ ዜና መዋዕል /ትሩፋት/ 2፣ ዕዝራ 2፣ አስቴር 1፣ መቃብያን 3፣ ኢዮብ 1፣ መዝሙረ ዳዊት 1: ሰሎሞን 3 ምሳሌያት፣ መክብብ፣ ማሕልየ መሓልይ፣ መጻሕፍተ ነቢያት /ደቂቀ ነቢያት/ 12፣ ኢሳይያስ 1፣ ኤርምያስ 1፣ ሕዝቅኤል 1፣ ዳንኤል 1፣ ከእነዚህ ውጭ ልጆቻችሁ ጥበበ ሲራክ ምሁርን ያጠኑ ዘንድ ተቀበሉ:: በተለይ የእኛም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቅዱሳትና ክቡራት መጻሕፍት ይሁኑ:: አርባዕቱ ወንጌላት: ወንጌል ዘማቴዎስ፣ ወንጌል ዘማርቆስ፣ ወንጌል ዘሉቃስ፣ ወንጌል ዘዮሐንስ፣ መልእክታተ ጳውሎስ 14፣ መልእክታተ ጴጥሮስ 2፣ መልእክታተ ዮሐንስ 3፣ መልእክተ ያዕቆብ 1፣ መልእክተ ይሁዳ 1፣ መልእክታተ ቀለሚንጦስ 2 እና «በእኔ በቀለሚንጦስ አማካይነት /እጅ/ ለእናንተ ኤጲስቆጳሳት የተላኩ ትእዛዛት በ8 መጻሕፍት: እነዚህም በውስጣቸው ስለሚገኙ ምሥጢራት ለሁሉም አይገለጡም እና የእኛ የሐዋርያት ሥራዎች/ ግብረ ሐዋርያት»[7] ከዚህ በመነሳት የቅዱሳት - አምላካውያት መጻሕፍት ዝርዝር

6. ስለ 85 ሐዋርያውት ቀኖናት ዝርዝር መረጃዎች፣ ዲበኩሉ ዘውዱ፣ ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 137 - 166::

7. Ράλλη-ποτλῆ: Σύνταγμα των θειων κυί Ἱερων Κανόνων T.B. ገጽ 109 - 110::



ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. መጻሕፍተ ሙሴ አምስት - አምስቱ ብሔረ ኦሪት

1.1 ኦሪት ዘፍጥረት
1.2 ኦሪት ዘጸአት
1.3 ኦሪት ዘሌዋውያን
1.4 ኦሪት ዘኍልቁ
1.5 ኦሪት ዘዳግም
1.6 መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ
1.7 መጽሐፈ መሳፍንት
1.8 መጽሐፈ ሩት
9. መጻሕፍተ ነገሥት 4
9.1 መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ
9.2 መጽሐፈ ነገሥት 2ኛ
9.3 መጽሐፈ ነገሥት 3ኛ
9.4 መጽሐፈ ነገሥት 4ኛ
10. ትሩፋት - ዜና መዋዕል 2
10.1 ትሩፋት - ዜና መዋዕል 1ኛ
10.2 ትሩፋት-ዜና መዋዕል 2ኛ
11. መጻሕፍተ ዕዝራ 2
11.1 መጽሐፈ ዕዝራ 1ኛ
11.2 መጽሐፈ ዕዝራ 2ኛ/+ነህምያ/
12. መጽሐፈ አስቴር
13. መጻሕፍተ መቃብያን 3
13.1 መጽሐፈ መቃብያን 1ኛ
13.2 መጽሐፈ መቃብያን 2ኛ
13.3 መጽሐፈ 3ኛ መቃብያን
14. መጽሐፈ ኢዮብ
15. መዝሙረ ዳዊት
16. መጻሕተ ሰለሞን 3
16.1 ምሳሌያት
16.2 መክብብ
16.3 ማሕልየ መሓልይ
17. መጻሕፍተ/ትንቢታተ/ / ነቢያት/ደቂቀ ነቢያት/12
17.1 ትንቢተ ሆሴዕ
17.2 ትንቢተ አሞጽ
17.3 ትንቢተ ሚክያስ
17.4 ትንቢተ ኢዮኤል
17.5 ትንቢተ አብድዩ/ኦብድዩ/
17.6 ትንቢተ ዮናስ
17.7 ትንቢተ ናሆም
17.8 ትንቢተ አባኩም/ዕንባቆም/
17.9 ትንቢተ ሶፎንያስ
17.10 ትንቢተ አንጌዮስ/ሐጌ/
17.11 ትንቢተ ዘካርያስ
17.12 ትንቢተ ሚልክያስ
18.ትንቢታተ ዐበይት ነቢያት 4
18.1 ትንቢተ ኢሳይያስ
18.2 ትንቢተ ኤርምያስ
18.3 ትንቢተ ሕዝቅኤል
18.4 ትንቢተ ዳንኤል

www.ethiopianorthodox.org

19. ጥበበ ሲራክ[8]

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ድምር 41/41+1=42/

## ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. ወንጌላት 4
1.1 የማቴዎስ ወንጌል
1.2 የማርቆስ ወንጌል
1.3 የሉቃስ ወንጌል
1.4 የዮሐንስ ወንጌል
2. መልእክታተ ጳውሎስ 14
2.1 ወደ ሮሜ ሰዎች
2.2 ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 1ኛ
2.3 ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 2ኛ
2.4 ወደ ገላትያ ሰዎች
2.5 ወደ ኤፌሶን ሰዎች
2.6 ወደፊልጵስዩስ ሰዎች
2.7 ወደ ቆላስይስ ሰዎች
2.8 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
2.9 ወደ ተስሎንቄ ሰዎች 2ኛ
2.10 ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
2.11 ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
2.12 ወደ ቲቶ
2.13 ወደ ፊልሞና
2.14 ወደ ዕብራውያን
3. መልእክታተ ሐዋርያት 7
3.1 መልእክታተ ጴጥሮስ 2
3.2 መልእክተ ጴጥሮስ 1ኛ
3.3 መልእክተ ጴጥሮስ 2ኛ
3.4 መልእክታተ ዮሐንስ 3
3.2.1 መልእክተ ዮሐንስ 1ኛ
3.2.2 መልእክተ ዮሐንስ 2ኛ
3.2.3 መልእክተ ዮሐንስ 3ኛ
3.3 መልእክተ ያዕቆብ
3.4 መልእክተ ይሁዳ
4. መልእክታተ ቀለሚንጦስ 2
4.1መልእክተ ቀለሚንጦስ 1ኛ
4.2 መልእክተ ቀለሚንጦስ 2ኛ[9]
5. ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀሚንጦስ 8
5.1 ትእዛዝ ምስለ ቀለሚንጦስ 1ኛ
5.2 ትእዛዝ ምስለ ቀለሚንጦስ 2ኛ
5.3 ትእዛዝ ምስለ ቀለሚንጦስ 3ኛ
5.4 ትእዛዝ ምስለ ቀለሚንጦስ 4ኛ
5.5 ትእዛዝ ምስለ ቀለሚንጦስ 5ኛ
5.6 ትእዛዝ ምስለ ቀለሚንጦስ 6ኛ
5.7 ትእዛዝ ምስለ ቀለሚንጦስ 7ኛ
5.8 ትእዛዝ ምስለ ቅለሚንጦሱ 8ኛ
6. ግብረ ሐዋርያት

8. ጥበበ ሲራክ «ለሁላችሁም ካህናትና ምእመናን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ክቡራትና ቅዱሳት ይሁኑ» ተብለው ከተዘረዘሩት መጻሕፍት ውጪ ግን ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ይሆን ዘንድ እንዲቀበሉት የታዘዘ መጽሐፍ ነው:: ፍትሐ ነገሥታት አንቀጽ 2 ቁጥር 17 ከዚህ ጋር ይስማማል::

9. K.Μπόνη: Κλήμεντος Ρώμης ἐπιστολὴ Α΄ πρὸςΚορινθίους 1973 καὶ Ἡ καλουμένη Β' ἐπιστολὴ Κλήμεντος Ρώμης προςΚορινθίους 1976 (ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላኩ 1ኛ እና 2ኛ የቀለሚንጦስ መልእክቶች)

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር = 36

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 36 ሲሆን በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና «ክቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት» ተብለውና ተመዝግበው የሚገኙት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 41 ሆኖ ቢታይም ከእነዚህ መጻሕፍት ጋርም ነገር ግን ከእነዚህ ውጪ ለልጆቻችሁ ጥናት ጥበበ ሲራክ ሊቅን ተቀበሉ በሚል ሐረግ ጥበበ ሲራክ ተጨመሮ ይገኛል:: ይህንም እንቀበል ከተባለ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት ወደ 42 ይደርሳል ማለት ነው::

በአጠቃላይ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ተመዝግበው የሚገኙት «ክቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት» የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 41 /+1=42 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 36 ድምር 41+36 = 77 (41+1+36 = 78) ይሆናል::

## 1.2 ቀኖናት ዘሎዶቅያ (ላኦዶቅያ)

ስለ ቀኖናውያት ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ከጥንት አብያተ ክርስቲያናት ሲኖዶሳውያት ቀኖናት የተወሰኑት ይናገራሉ:: ከእነዚህ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ሲኖዶሳውያት ቀኖናት መካከል አንዱ የሎዶቅያ /ላአዶቅያ/[10] ሲኖዶስ 60ኛ ቀኖና ነው:: በርግጥ ይህ ቀኖና የሎዶቅያ ሲኖዶስ ቀኖና

10. G. Bardy: Concile et Canons de Laodice'e: Dictionaire de droit Canonique T.VI (1957) ገጽ 338.

www.ethiopianorthodox.org

ለመሆኑ አጠራጥሮ ነበር:: ምክንያቱም ይህ ቀኖና በመጀመሪያ በሉዶቅያ ሲኖዶስ ቀኖናት እንደ አልነበረና ቆይቶ የቀኖና 59 ማሟያ ሆኖ እንደተጨመረ ይደገፋል::

እንደ መረጃም የተወሰደው ቀኖና 59 ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር እንደማይናገር ማለትም ይህ 60ኛ ቀኖና በጥንት ትርጉሞች እንደ አልነበረ ነው[11]::

ስለዚህም በጥንት አንድ አንድ የእጅ ጹሑፎች አንድ አንድ ጊዜ ከ59 ቀኖና ጋር ተደምሮ-ተጣምሮ አንድ አንድ ጊዜ ራሱን ችሎ ይገኛል:: ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ያለው ዝንባሌ ቀኖናውን መቀበል እንደሚገባ ነው:: በቀኖና ዘላኦዶቅያ /ሉዶቅያ/ ለቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጠው ስያሜ - ገጸ ባህርይ - መነበብ የሚኖርባቸው የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት: 1 ዘፍጥረተ ዓለም፣ 2 ዘጸአት እም ግብጽ፣ 3 ዘሌዋውያን፣ 4 ዘኁልቁ፣ 5 ዘዳግም፣ 6 ኢያሱ ወልደነዌ፣ 7 መሳፍንት እና ሩት፣ 8 አስቴር፣ 9 መጻሕፍተ ነገሥት 1ኛ እና 2ኛ፣ 10 መጻሕፍተ ነገሥት 3ኛና 4ኛ፣ 11 ትሩፋተ ነገሥት 1ኛ እና 2ኛ፣ 12 ዕዝራ 1ኛና 2ኛ፣ 13 መጽሐፈ መዝሙራት 150፣ 14 ምሳሌያተ ሰሎሞን፣ 15 መክበብ፣ 16 ማሐልየ መሓልይ፣ 17 ኢዮብ፣ 18 12 ነቢያት /ደቂቀ ነቢያት/፣ 19 ኢሳይያስ፣ 20 ኤርምያስ እና ባሮክ፣ ሰቆቃውና መልእክታት[12]፣ 21 ሕዝቅኤል፣ 22 ዳንኤል::

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው::

11. J.B. Pitra: Juris Ecclesiastici Graecorum, Historia et Monumenta T.A' Romae. 1886, ገጽ 502; Th. Zahn: Geschichte des Neutestamentalischen Kanons T. 2.1 ገጽ 197፣ ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 1፣ ሲኖዶስ ገጽ 136 - 154::
12. የኤርምያስ መልእክት አንድ ጊዜ አንድ መልእክት ሌላ ጊዜ ብዙ መልእክታት ሆነው ይታያሉ ሆኖም የሚታመነው አንድ መልእክት እንደሆነ ነው::



አርባዕቱ ወንጌላት: የማቴዎስ ወንጌል፣ የማርቆስ ወንጌል፣ የሉቃስ ወንጌል፣ የዮሐንስ ወንጌል፣ ግብረ ሐዋርያት፣ 7 ካቶሊካውያት-ሐዋርያውያት መልእክታት፣ መልእክተ ያዕቆብ 1፣ መልእክታተ ጴጥሮስ 2፣ መልእክታተ ዮሐንስ 3፣ መልእክተ ይሁዳ 1፣ መልእክታተ ጳውሎስ 12 ወደ ሮሜ ሰዎች፣ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2፣ ወደ ገላትያ ሰዎች፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1፣ ወደ ፊሊጲስዩስ ሰዎች 1፣ ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1፣ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2፣ ወደ ዕብራውያን 1፣ ወደ ጢሞቴዎስ2፣ ወደ ቲቶ 1 እና ወደ ፊልሞና 1፤

ከእነዚህ በላኦዶቅያ /ሉዶቅያ/ 60ኛ ቀኖና በጥቅል መልካቸው የተመለከቱት ምንባባውያትና ቅዱሳት መጻሕፍት በዝርዝር ሲታዩ[13]

## ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘኁልቁ
4. ዘሌዋውያን
5. ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. መጽሐፈ አስቴር
10. መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ
11. መጽሐፈ ነገሥት 2ኛ
12. መጽሐፈ ነገሥት 3ኛ
13. መጽሐፈ ነገሥት 4ኛ
14. ትሩፋተ ነገሥት 1ኛ
15. ትሩፋተ ነገሥት 2ኛ
16. መጽሐፈ ዕዝራ 1ኛ
17. መጽሐፈ ዕዝራ 2ኛ
18. መዝሙረ ዳዊት

13. Ράλλη-ποτλη: Σύνταγμα των θείων κυί Ιερων Κανόνων Τ.Γ. ገጽ 115 - 226::



www.ethiopianorthodox.org

19. ምሳሌያተ ሰሎሞን
20. መክብብ
21. ማሕልየ መሐልይ
22. ኢዮብ

12 ነቢያት/ደቂቀ ነቢያት/

23. ትንቢተ ሆሴዕ
24. ትንቢተ አሞጽ
25. ትንቢተ ሚክያስ
26. ትንቢተ ኢዩኤል
27. ትንቢተ አብድዩ/አብድዩ/
28. ትንቢተ ዮናስ
29. ትንቢተ ናሆም
30. ትንቢተ ዕንባቆም
31. ትንቢተ ሶፎንያስ
32. ትንቢተ ሐጌ
33. ትንቢተ ዘካርያስ
34. ትንቢተ ሚክያስ
35. ትንቢተ ኢሳይያስ
36. ትንቢተ ኤርምያስ
37. ኤርምያስ
38. ሰቆቃው
39. መልእክታተ ኤርምያስ
40. ትንቢተ ሕዝቅኤል
41. ትንቢተ ዳንኤል

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 41

## ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

### አርባዕቱ ወንጌላት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት

ሰባት ካቶሊካውያት-ሐዋርያውያት መልእክታት[14]

6. የያዕቆብ መልእክት
7. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ
8. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
9. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
10. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
11. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
12. የይሁዳ መልእክት

የጳውሎስ መልእክታት

13. ወደ ሮሜ ሰዎች
14. ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 1ኛ
15. ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 2ኛ
16. ወደ ገላትያ ሰዎች
17. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
18. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
19. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
20. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
21. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
22. ወደ ዕብራውያን
23. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
24. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
25. ወደ ቲቶ
26. ወደ ፊልሞና

- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 26

በ60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ /ሎዶቅያ/ የቅዱሳት መጻሕፍት ድምር የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 41 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት =(41+26=67)67 ነው::

## 1.3 24 እና 32 ቀኖናት ዘቅርጣግና/ ካርታጌኒስ/

በአፍሪካ ቅርንጣግና-ካርታጌኒስ በ393 በኤጳን እና በ397 በካርኬዶና በተደረጉ ሲኖዶሳት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናት - ዝርዝር የሚደነግጉት ቀኖናት /ቀኖናት 6 እና 47/ እንደ ጸደቁበት የሚታሰበው ቀኖና በ419 የተደረገው የቅርንጣግና ሲኖዶስ ቀኖና ሌላው ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚናገረው ቀኖና ነ0 ወይም በአፍሪካ የቤተ ክርስቲያን «መጽሐፈ ቀኖናት» - መድበ ቀኖናት (Codex canonum ecclesiae africanae)[15] «ከቀኖናውያ መጻሕፍት ውጪ በአምላካውያት መጻሕፍት ስም በቤ ክርስቲያን ምንም ዓይነት መጽሐፍ መነበብ እንደማይገባ ተወሰ

14. ሰባቱ መልእክታተ ሐዋርያት «ካቶሊካውያት ሐዋርያውያት ሁለ አቀፍ መልእክታት» በመባል ይታወቃሉ:: «ካቶሊክ» (ካቶሊኮስ፣ ካቶሊኮን እና ካቶሊኪ የሚለው ቃል-ቅጽል ግሪክ - ቃል ነው:: ትርጉሙም ሁለ አቀፍ ፡ ሁለአድማስ /Universal/ ማለት ነው:: ከዚህም ትርጉም አንጻር ነው የሮማ ቤተ ክርስቲያን ይህን ቅጽል ለመጠቀም የመረጠችው::
ስለዚህ እነዚህ ሰባት መልእክታት እንደ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ለተወሰኑ- ለታወቁ አገሮችና ሰዎች ሳይሆን የተሰራጩት ለአልተወሰነ አገር - ከተማ ወይም ግለሰብ በመሆኑ ይህን ቅጽል ሊይዙ ችለዋል:: ልዩነቱ ግን የይዘት አይደለም::

15. Παύλου Σουηδίας: Η ἐν Καρθαγένη Σύνοδος τοῦ 419 "Aksum-Thyateira" A Festschrift for Archb. Methodios, London, 1985 ገጽ 257::



www.ethiopianorthodox.org

«ቀኖናውያት መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው[16]:: ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቁ፣ ዘዳግም፣ ኢያሱ ወልደ ነዌ፣ መሳፍንት፣ ሩት፣ መጻሕፍተ ነገሥት 4፣ ሕጹጻን መጽሕፍት 2፣ ኢዮብ፣ መዝሙር፣ መጻሕፍተ ሰሎሞን 5፣ መጻሕፍተ ነቢያት 7 /ደቂቀ ነቢያት/ 12፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቄኤል፣ ዳንኤል፣ ጦቢያስ፣ ዮዲት፣ አስቴር፣ መጻሕፍተ ዕዝራ 2፣

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡ አርባዕቱ ወንጌላት፣ ግብረ ሐዋርያት 1 መጽሐፍ፣ መልእክታተ ጳውሎስ 14፣ መልእክታተ ጴጥሮስ ሐዋርያ 2፣ መልእክታተ ዮሐንስ 3፣ መልእክተ ያዕቆብ ሐዋርያ 1፣ መልእክተ ይሁዳ ሐዋርያ 1፣ አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ 1 መጽሐፍ::

የዚህ ቀኖና መጽደቅና መረጋገጥ ለወንድማችንና ለሥራ ባልደረባችን ቮኒፋትዮስና ለወቅቱ ኤጲስቆጰሳት መታወቅ እንደሚኖርበት ያስፈልጋል:: ምክንያቱም እነዚህ መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን መነበብ እንደ አለባቸው ከአባቶች ወርሰናልና»::

በዚህ ቀኖና በመሰብሰብ የተቀመጡት:

ቀኖናውያት - አምላካውያት - ምንባባውያት መጻሕፍት ዝርዝር

## ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም
6. ኢያሱ ወልደነዌ
7. መሳፍንት
8. ሩት
9. ነገሥት 1ኛ
10. ነገሥት 2ኛ
11. ነገሥት 3ኛ
12. ነገሥት 4ኛ
13. ሕጹጻን 1ኛ
14. ሕጹጻን 2ኛ
15. ኢዮብ
16. መዝሙር

16. Ράλλη-ποτλῆ: Σύνταγμα των θείων κσὶ Ἱερων Κανόνων Τ.Γ. ገጽ 368 - 369::27. T. Zahn: Geschichte des Neutestamentalischen Kanons T. 2.1 158 - 159, A souter - C. Williams: The Text and Canon of the New Testament, London, 1960 ገጽ 194 - 195.



መጻሕፍተ ሰሎሞን 5

17. ምሳሌያተ ሰሎሞን
18. መክብብ
19. ማሕልየ መሓልይ
20. ጥበበ ሰሎሞን

\- -

21. መጻሕፍተ - ትንቢታተ ነቢያት(ደቂቅ ነቢያት)12

(22. ትንቢተ ሆሴዕ
23. ትንቢተ አሞጽ
24. ትንቢተ ሚክያስ
25. ትንቢተ ኢዩኤል
26. ትንቢተ አብድዩ/ኦብድዩ/
27. ትንቢተ ዮናስ
28. ትንቢተ ናሆም
29. ትንቢተ ዕንባቆም
30. ትንቢተ ሶፎንያስ
31. ትንቢተ ሐጌ
32. ትንቢተ ዘካርያስ
33. ትንቢተ ሚልክያስ)
34. ትንቢተ ኢሳይያስ
35. ትንቢተ ኤርምያስ
36. ትንቢተ ሕዝቅኤል
37. ትንቢተ ዳንኤል
38. መጽሐፈ ጦቢያስ /ጦቢት
39. ዮዲት
40. አስቴር
41. ዕዝራ 1ኛ
42. ዕዝራ 2ኛ/+ነህምያ/

43-44 በላቲን ትርጉም ሁለት መቃብያን፣

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 43

## ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት

የጳውሎስ መልእክታት 14

6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 1ኛ
8. ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ስዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17. ወደ ቲቶ
18. ወደ ፊልሞና
19. ወደ ዕብራውያን

ሰባቱ መልእክታት:

20. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ



www.ethiopianorthodox.org

21. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
22. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
24. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
25. የያዕቆብ መልእክት
26. የይሁዳ መልእክት
27. አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ
=የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 27

ስለዚህ በ24ኛ/32ኛ ቀኖና ካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ መሠረት የቅዱሳት፣ ቀኖናውያት፣ አምላካውያትና ምንባባውያት መጻሕፍት /የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 43 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 27 እንደ መሆናቸው መጠን/ በድምሩ 43 እና 27 (43+27=70)70 መጻሕፍት ይሆናሉ::

## 2. ቀኖናተ አበው

ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናት ዝርዝር ድንጋጌ የሚገኝባቸው አባቶችም ይገኛሉ::

### 2.1 ትልቁ አትናቴዎስ

በ325 ኒቅያ ዐቢይ ጉባኤ-ሲኖዶስ የትንሣኤን በዓል በሚመለከት የሚከበርበትን ጊዜ ማለትም ከፍሥሐ አሪት - ፋሲካ አይሁድ ቀጥሎ በሚውለው እሑድ ቆጥረውና ቀኑን ወስነው የእስክንድርያ /ሊቃነጳጳሳት/ ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲያስተላልፉ ተወስኖ እንደነበር ይታወሳል[17]::

ምክንያቱም በዚያን ወቅት እስክንድርያ በሥነ ባሕረ ሐሳብ - ሥነ ከዋክብት /Astronomy/ ማእከል ስለነበረች በዚህ አጋጣሚ የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት የትንሣኤ በዓል ወድቆ የሚከበርበትን ቀን አስበውና ወስነው ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንዲያስተላልፉ የመደረጉ አስፈላጊነት ሲሆን[18] ሊቃነ ጳጳሳቱም የትንሣኤ በዓል የሚውልበትን ቀን አስልተው በሚያስተላልፉአቸው መልእክቶች እንደ አየአጋጣሚው ሌሎችንም ጉዳዮች: ምሥጢረ መለኮትን፣ ሥርዐተ ቅዳሴን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ቀኖናትን እና የመሳሰሉትን ጭምር ያስተላልፉ ስለነበር በዚህ መሠረት ትልቁ አትናቴዎስ /367/ በዚህ በፋሲካ 39ኛ መልእክቱም የፋሲካ በዓል የሚውልበትን ቀን ከማብሰሩ ጋር የሚቀነኑ - አምላካውያት - መንፈስ እግዚአብሔር ያለባቸውን መጻሕፍት ዝርዝር በቀኖና መልክ አመልክቷል[19]::

«ነገር ግን ስለዚህ ስከሐዲዎች እንደሙታን እንደሆኑና ለእኛ ግን ለመድኃኒትነታችን ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ አሉን ተናግረናል::

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆርንቶስ ሰዎች እንደ አዘዘው ከቅንንትና ከደግነታቸው የተነሳ ፍጹም ከሆኑት ጥቂቶች በሰዎች መጥፎ ተግባር ምን አልባት ሊሳሳቱ ወደ ስህተት ላይ ሊወደቁ እንደሚችሉ ወደ ፊትም ከእውነተኞች ቅዱሳት መጻሕፍት ስያሜዎች ጋር በማመሳሰል ለመታለል የታቃዱ ሌሎች ስውር-ድብቅ መጻሕፍትን ማጥናት እንደጀመሩ ስለ ፊራሁ በደንብ ስለመታወቋቸው ስለእነዚያ እኔም በጽሑፍ ስለተናገርኳቸው እና ከፍላጐት የተነሳና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ትእግስትን እንድታሳዩ እለምናለሁ::

እነዚህንም ለማለት ጽናቴን ለማሳየት የወንጌላዊ ሉቃስን ስልት እኔም እጠቀማለሁ፣ እደግመዋለሁ:: በትክክል የተወሰኑ /ጥቂቶች/ ሰዎች ለራሳቸው ኅቡአት መጻሕፍትን አዘጋጅተው

17. ΣΤ. Σάκκου: Ἡ ΛΘ εορταστικὴ ἐπιστολὴ τοῦ Μ. Ἀθανασίου 1973 - 1974 ገጽ 9::

18. ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 7ኛውን ቀኖና እና ከሲኖዶስ /ሎዶቅያ/ ቀኖናት 1ኛውን ቀኖና ተመልከት::

19. Ράλλη-ποτλὴ: Σύνταγμα των θείων κυι Ἱερῶν Κανόνων Τ.Δ. ገጽ 78 - 80::



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን በመጀመርያ የዓይን ምስክሮችና የቃሉ አገልጋዮች ለአባቶች እንደሰጧቸው ከተረዳናቸው አምላካውያት መጻሕፍት ጋር ለማመሳሰል-ለማቀላቀል ጥረት አድርገዋል:: ለእኔም ወንድሞች ስለ አበረታቱኝና የላይኛውን ከእነሱ ስለሰማሁ ቀጥሎ የሚቀነኑትንና ሲያያዙ የመጡትን አምላካውያት መጻሕፍት ለመተንተን ለእኔ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖልኛል::

ስለዚህም ተሳስቶ ከሆነ እነዚያን ያሳሳቱትን በትክክል እንዲያውቅ ያልተሳሳተው ደግሞ ይህን ማስታወስ እንዲችል ያበቃዋልና::

እንግዲህ ቁጥራቸው 24 የሆነ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይኖራሉ::

እነዚህም እንደሰማሁት በልማድና በዝርዝር በዕብራውያን ያሉት መጻሕፍት ናቸው:: በተራ /ቅደም ተከተል/ እና ስም /ርእስ/ የሚከተሉት ናቸው::

መጀመሪያው ዘፍጥረት፣ ቀጥሎ ዘጸአት፣ ከዚያም ዘሌዋውያን፣ ተከትሎም ከእሱም በኋላ ዘኁልቁ፣ ተከትሎም ዘዳግም:: ከእነዚህም በኋላ ኢያሱ ወልደነዌ እና መሳፍንት ናቸው:: ከዚህ በኋላ ሩትና ቀጥሎም 4 መጻሕፍተ ነገሥት - ከእነዚህም 1ኛ ነሥትና 2ኛ ነገሥት አንድ መጽሐፍ፣ 3ኛ ነገሥት እና 4ኛ ነገሥት ሌላ አንድ መጽሐፍ ሁነው ይቆጠራሉ:: ከዚያም ትሩፋተ ነገሥት 1ኛ እና 2ኛ አንድ መጽሐፍ ቀጥሎም 1ኛ ዕዝራ እና 2ኛ ዕዝራ በአንድ መጽሐፍ ተጠርዘው ይገኛሉ:: ከነዚህም ቀጥሎም መጽሐፈ መዝሙራት፣ ከዚያም ምሳሌያተ ሰሎሞን፣ ቀጥሎም መክብብና ማሕልየ መሓልይ፣ ከነዚህም በስተቀር ኢዮብም፣ ቀጥሎም ነቢያት እነሱም 12 ነቢያት/ደቂቀ ነቢያት/ አንድ መጽሐፍ ሁነው ሲቆጠሩ ቀጥሎም ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ ከእሱም ጋር ባሮክ፣ ሰቆቃውና መልእክት፣ ከእነዚህም በኋላ ሕዝቅኤል እና ዳንኤል፣ እስከዚህ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ይደርሳሉ::



የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ለመጥራት መጠራጠር አይኖርብኝም:: እነሱም የሚከተሉት ናቸው:: 4 ወንጌላት: የማቴዎስ ወንጌል፣ የማርቆስ ወንጌል፣ የሉቃስ ወንጌል፣ የዮሐንስ ወንጌል፣ ከእነሱም ቀጥሎ ግብረ ሐዋርያት እና የሚከተሉት «ካቶሊካውያት» የሚባሉት ሰባት መልእክታተ ሐዋርያት: ዘያዕቆብ 1፣ ዘጴጥሮስ 2፣ ቀጥሎ ዘዮሐንስ 3፣ ከእነዚህም በኋላ ዘይሁዳ 1፣ ከእነዚህም በስተቀር በሚከተለው ቅደም ተከተል 14 የጳውሎስ መልእክታት በመጀመርያ ወደ ሮሜ ሰዎች፣ ቀጥሎም ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2፣ ከዚያም ወደገላትያ ሰዎች፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች ተከትሎም ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎችና ወደ ቆላስይስ ሰዎች፣ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2፣ ወደ ዕብራውያን ቀጥሎም ወደ ጢሞቴዎስ 2፣ ወደ ቲቶ 1 እና የመጨረሻ ወደ ፊልሞና 1 የተላኩ መልእክታት እንደገናም አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ::

እነዚህ የተጠማ በውስጣቸው በሚገኙ ቃላት ይረካ ዘንድ የእውነተኛ ደኅንነት ምንጮች ናቸው:: በእነዚህ ብቻ የቅድስና ትምህርት ይሰበካል:: ከእነዚህም ማንም ምንም መጨመር ወይም መቀነስ አይችልም:: ስለ እነዚህም /ቅዱሳት መጻሕፍት/ ጌታ ሰዱቃውያን ቅዱሳት መጻሕፍትን ወይም በእነሱም ውስጥ ያለውን ኃይል ባለማወቅ እንዳትሳሳቱ በማለት ይወቅሳቸዋል:: አይሁድን ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን ተመራመሩ በማለት ያበረታታቸዋል:: ምክንያቱም ስለ እኔ የሚመሰክሩት እነሱ ናቸውና:: ነገር ግን በርግጥ ስለ በለጠ እርግጠኛነታቸው ከእነዚህ በስተቀር ከሚቀነኑት መጻሕፍት ጋር ያልሆኑ ነገር ግን አዲስ ለሚመጡትና ትምህርተ ቅድስናን - ክርስትናን ለመማር ለሚፈልጉ ይነበቡ ዘንድ በአባቶች የታዘዙ ሌሎች መጻሕፍት እንደ አሉ መጻፍ አስፈላጊ መሆኑን እጨምራለሁ:: እነዚህም ጥበበ ሰሎሞን፣ ጥበበ ሲራክ፣ አስቴር እና ዮዲት ጦቢያስ/ጦቢት/፣ ትምህርተ ሐዋርያት የሚባል መጽሐፍና



www.ethiopianorthodox.org

ሆኖም ወዳጆች እነዚያ የመጀመሪያዎች የተቀነኑ - ቀኖናውያት ተብለው ሲታወቁ ሁለተኛዎች ተነባቢዎች ምንባባውያት በመባል ይለያሉ::

ሆኖም ኀቡአት መጻሕፍት ምን ጊዜም አይጠቀሱም:: ነገር ግን በፈለጉበት ጊዜ የሚጽፉአቸው ከሐድያን /ሐራጥቃዎች/ ዘዴ/ ተንኮል ነው:: ነገር ግን በእነሱ አማካይነት ደግ ሰዎችን ለማሳሳት መነሻ ይሆናቸው ዘንድ እንደ ጥንታውያት መጻሕፍት አድርገ ለማሳየት ጊዜያችን ያመለክቱባቸዋል»::

በዚህ 39ኛ መልእክተ አትናቴዎስ በዝርዝር የተቀመጡ የሚቀነኑ - አምላካውያት - መንፈስ እግዚአብሔር ያለባቸው መጻሕፍት ዝርዝር:

## ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም
6. ኢያሱ ወልደ ነዌ
7. መሳፍንት
8. ሩት
9. ነገሥት 1ኛ
10. ነገሥት 2ኛ
11. ነገሥት 3ኛ
12. ነገሥት 4ኛ
13. ትሩፋት 1ኛ
14. ትሩፋት 2ኛ
15. ዕዝራ 1ኛ
16. ዕዝራ 2ኛ(+ ነህምያ)
17. መዝሙራት
18. ምሳሌያተ ሰሎሞን
19. መክብብ
20. ማሕልየ መሓልይ
21. ኢዮብ

ነቢያት/ደቂቀ ነቢያት/12

(22. ሆሴዕ
23. አሞጽ
24. ሚክያስ
25. ኢዩኤል
26. አብድዩ/አብድዩ/
27. ዮናስ
28. ናሆም
29. ዕንባቆም
30. ሶፎንያስ
31. ሐጌ
32. ዘካርያስ
33. ሚልክያስ)
34. ኢሳይያስ
35. ኤርምያስ
36. ባሮክ
37. ሰቆቃወ ኤርሞያስ
38. መልእክተ ኤርምያስ
39. ሕዝቅኤል
40. ዳንኤል

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 40/40+5=45/

## ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት

ካቶሊካውያት -- ሐዋርያውያት መልእክታት 7[20]

6. ዘያዕቆብ
7. ዘጴጥሮስ 1ኛ
8. ዘጴጥሮስ 2ኛ
9. ዘዮሐንስ 1ኛ
10. ዘዮሐንስ 2ኛ
11. ዘዮሐንስ 3ኛ
12. ዘይሁዳ

የጳውሎስ መልእክታት 14

13. ወደ ሮሜ ሰዎች
14. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
15. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
16. ወደ ገላትያ ሰዎች
17. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
18. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎ፡
19. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
20. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
21. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
22. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
23. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
24. ወደ ዕብራውያን
25. ወደ ቲቶ
26. ወደ ፊልሞና
27. አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 27

## ሐ. የንባብ-ምንባባውያት መጻሕፍት

1. ጥበበ ሰሎሞን
2. ጥበበ ሲራክ

---

20 ከዚሁ ገጽ 14 የግርጌ ማስታወሻ 14



www.ethiopianorthodox.org

3. አስቴር
4. ዮዲት
5. ጦቢያስ/ጦቢት/
6. ትምህርተ ሐዋርያት
7. ኖላዊ (ሄርማ)

በ39ኛው የትልቁ አትናቴዎስ መልእክት በሁለት ተከፍለው የተመዘገቡት ቅዱሳት መጻሕፍትና የንባብ - ምንባባውያት መጻሕፍት ብዛት: የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 40 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 27 = አምላካውያት መጻሕፍት 40+27=67 እና ምንባባውያት መጻሕፍት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 5 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 2=5+2=7 ስለዚህ በጠቅላላ 67+7 = 74 መጻሕፍተ ይሆናሉ::

## 2.2 ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት /ዘእንዚናዙ/

እንደሚታወቀው ስለቅዱሳት መጻሕፍት የሚናገረው የጎርጎርዮስ ነበቤ መለኮት - ታኦጎሎስ ቀኖና በብዙዎች ጽሑፎች (Manuscripts) እና መድበላተ ቀኖናት አይገኝም[21] ቢሆንም በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን እንደ አገኘ አላጠራጠረም:: ጎርጎርዮስ ነባቤ መለከት በዚህ አንድ ብቻ ቀኖናው[22] በግጥም ቅርጽ የሚከተሉትን ቅዱስት መጻሕፍት ይዘረዝራል:: «በባዕዳን መጻሕፍት ላለመሳሳት ምክንያቱም በተንኮል የተጻፉ መስሕታት መጻሕፍት /መጻሕፍተ ሐሰት/ አሉ:: ወንድም ይህን የኔን የቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛ ቁጥር ተቀበል:: በታሪክ 12 መጻሕፍት ሁሉም የጥንት የዕብራውያን ጥበብ መጻሕፍት አሉ:: የመጀመሪያው ዘፍጥረት

21. M-Αποστολοπούλου: Εκκλησιαστιχον δίκαιον της Ορθοδόξου Ανατολιχης Εκκλησίας: Αθηναι 1905 ገጽ - 146 A. Αλιβιζάτου:Οι Ιεροὶ κανόνες χαὶ Εκκλησιαστικοὶ νόμοι, Αθηναι 1942 ገጽ408::
22. T. Zahn: Geschichte des Neutestamentlischen Kanons T.2.1 ገጽ 212 - 213::



ቀጥሎ ዘጸአትና ዘሌዋውያን፣ ከዚያም ዘኁልቁ፣ ቀጥሎም ዘዳግም ከዚያም ኢያሱ ወልደነዌ እና መሳፍንት: ስምንተኛ ሩት፣ 9ኛ እና 10ኛ መጻሕፍት /ግብራተ/ ነገሥትና ትሩፋተ ነገሥት፣ የመጨረሻም ዕዝራ ይኖርሃል:: አምስት የግጥም መጻሕፍት: ከእነሱም የመጀመሪያው ኢዮብ፣ ቀጥሎም መዝሙረ ዳዊት፣ ከዚያም ሦስት መጻሕፍተ ሰሎሞን: መክብብ፣ ማሕልየ መሓልይና ምሳሌያተ ሰሎሞን:: እንደዚሁም አምስት መጻሕፍተ ትንቢታዊ መንፈስ፣ ከእነዚህም 12 ነቢያት/ደቂቀ ነቢያት/ አንድ መጽሐፍን ይዘው ይገኛሉ:: ሆሴዕና አሞጽ፣ 3ኛ ሚክያስ፣ ከዚያም ኢዩኤል፣ ቀጥሎም ዮናስ፣ አብድዩ /አብድያስ/፣ ናሆናምና ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ከዚያም ዘካርያስና ሚልክያስ:: ይህ አንድ መጽሐፍ ሲሆን ሁለተኛው /መጽሐፍ/ ኢሳይያስ ቀጥሎም በጎፃንነቱ ነቢይ ሆኖ የተጠራ ኤርምያስ፣ ከዚያም ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል /በጸጋ የተጻፈ ትንቢት/፣

ጥንታውያት ግን መጻሕፍት /ዘብሉይ ኪዳን/ በዕብራውን ፊደሎች /ሆሀያት/ ቁጥሮች መጠን 22 መጻሕፍትን ይይዛሉ::

አሁን ደግሞ የሐዲሱ ምሥጢር መጻሕፍት - የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይቆጠራሉ:: ማቴዎስ ለዕብራውያን ተአምራተ ኢየሱስን ጻፈ፣ ማርቆስ በጣልያን፣ ሉቃስ በአካይያ - ግሪክ፣ ከሁሉም ታላቁ ሰባኪ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ /ረድአ ሰማይ/ ወንጌላቱን ጻፉ::

ከዚያም ግብረ ሐዋርያት ጠበብት፣ ቀጥሎም 14 የጳውሎስ መልእክታት፣ በሌላም በኩል ሰባት ካቶሊካውያት መልእክታት[23] ከእነሱም መልእክተ ያዕቆብ፣ 2 መልእክታተ ጴጥሮስ፣ 3 መልእክታተ ዮሐንስ፣ 7ኛ መልእክተ ይሁዳ፣ ሁሉም መጻሕፍት እነዚህ ናቸው::

23. ከዚሁ ገጽ 44 የግርጌ ማስታወሻ 14

www.ethiopianorthodox.org

ከእነዚህ እውነተኞች /ቅዱሳት» መጻሕፍት ወይም መልእክታት/ በስተቀር ሌሎች መጻሕፍት አይኖሩም::

ስለዚህ በቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት «የተረጋገጡ» ተብለው ተመዝግበው የሚገኙት መጻሕፍት ዝርዝር[24]

## ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም/ካልዕ ሕግ/
6. ኢያሱ ወልደነዌ
7. መሳፍንት
8. ሩት
9. መጻሕፍተ - ግብራተ ነገሥትና ትሩፋት
9.1 ነገሥት 1ኛ
9.2 ነገሥት 2ኛ
9.3 ነገሥት 3ኛ
9.4 ነገሥት 4ኛ
9.5 ሕጹጻን 1ኛ
9.6 ሕጹጻን 2ኛ
10. ዕዝራ 1ኛ
11. (ዕዝራ 2ኛ/+ነህምያ/)
12. መዝሙራት አምስት
12.1 ኢዮብ
12.2 ዳዊት/መዝሙር/
12.3 ሰሎሞናውያት ሦስት
12.3.1 መክብብ
12.3.2 ማሕልየ መሓልይ
12.3.3 ምሳሌያት
13. 12 ነቢያት
13.1 ሆሴዕ
13.2 አሞጽ
13.3 ሚክያስ
13.4 ኢዩኤል
13.5 ዮናስ
13.6 አብድዩ/አብድያስ/
13.7 ናሆም
13.8 ዕንባቆም
13.9 ሶፎንያስ
13.10 ሐጌ/አንጌዎስ/
13.11 ዘካርያስ
13.12 ሚልክያስ
14. ኢሳይያስ
15. ኤርምያስ
16. ሕዝቅኤል
17. ዳንኤል

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 37

24. Ράλλη-ποτλῆ: Σύνταγμα των θειών κυὶ Ἴερων Κανόνων Τ.Δ ገጽ 363 - 364::



## ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት
6. የጳውሎስ መልእክታት 14
6.1. ወደ ሮሜ ሰዎች
6.2 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
6.3 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
6.4 ወደ ገላትያ ሰዎች
6.5 ወደ ኤፌሶን ሰዎች
6.6 ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
6.7 ወደ ቆላስይስ ሰዎች
6.8 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
6.9 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
6.10 ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
6.11 ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
6.12 ወደ ቲቶ
6.13 ወደ ፊልሞና
6.14 ወደ ዕብራውያን

ካቶሊካውያት-ሐዋርያውያት መልእክታት 7

7. ዘያዕቆብ
8. ዘጴጥሮስ 1ኛ
9. ዘጴጥሮስ 2ኛ
10. ዘዮሐንስ 1ኛ
11. ዘዮሐንስ 2ኛ
12. ዘዮሐንስ 3ኛ
13. ዘይሁዳ

በጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ቀኖና ሰፍረው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ድምር የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 37 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 26/37 + 26 = 63/= 63 መጻሕፍት ይሆናል::

## 2.3 ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን

ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና የሚናገረው ቀኖና ዘአምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን የጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት (ታኦጎሎስ) ቀኖና ሆኖ ይቆጠር የነበረበት ጊዜ ነበር:: ይህም በጥንት የእጅ ጽሑፎችና ኅትመቶች ከጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ግጥም ሥራዎች ጋር ተያይዞ ይገኝ ስለነበር ነው ተብሎ ይተረካል:: ነገር ግን ቆይቶ የ691 የ5ኛ-6ኛ-ትሩሎ ሲኖዶስ 2ኛ ቀኖና እንደ

www.ethiopianorthodox.org

ቀኖና አምፊሎኪዮስ ቆጥሮ ያጸደቀው ስለሆነ የግድ ይህ ቀኖና የአምፊሎኪዮስ ቀኖና መሆኑ ተቀባይነትን አግኝቷል[25]::

በቀኖና አምፍሎኪዮስ ዘኢቆንዮን ባለ 69 ስንኞች ግጥሞች ወይም መዝሙሮች የተቃኙት ወይም የተያዙት እሙራትና ጽሓፉት በመንፈሰ እግዚአብሔር መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው[26]::

«ከሁሉ በፊት/በላይ/ ይህን ማጥናት ይገባሃል::ምክንያቱም አንድ አንድ ጊዜ መስማተ ቅዱሳት መጻሕፍት (በውሸት ስም የታወቁ መጻሕፍት) ያጋጥማሉ:: ስለዚህ የተቀደሰ ወይም የተከበረ ስምን የያዘ መጽሐፍ ሁሉ ርግጠኛ ቅዱስ መጽሐፍ አይሆንም::

በተለየ አንድ ሰው ሊል ይችላል ከነዚያ ጥቂቶች እውነተኛ ቃላት ጋር ተመሳሳይና ተቃራቢ ነገር ግን በመጨረሻ መስሕታትና በጣም አደገኞች የሆኑ መጻሕፍት ለምሳሌ የንጉሥ ሥዕልን - መልክን የያዙ የሐሰት ገንዘቦችና መዳልያ በአሠራራቸው - በዓይነታቸው በሸፍጥነት እየተቀረጹ እንደሚገኙ ሁሉ ስለዚህ በእግዚአብሔር መንፈስ ከተጻፉ መጻሕፍት እየአንድአንዱን እዘረዝራአለሁ:: በግልጥ ለማወቅ ትችል ዘንድ በመጀመርያ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እዘረዝራለሁ:: አምስቱ ብሔረ ኦሪት: ዘፍጥረትን፣ ቀጥሎም ዘጸአትንና መካከለኛውን መጽሐፍ የያዘውን ዘሌዋውያን፣ ከእሱ ቀጥሎ ዘኁልቁን ከዚያም ዘዳግምን ይይዛል:: ከእነሱም ኢያሱ ወልደነዌን፣ እና መሳፍንትን ጨምሮ:: ቀጥሎም ሩትን እና አራት መጻሕፍተ ነገሥትን፣ ሁለት ሕጹጻንን፣ ከዚያም 1ኛ ዕዝራና ቀጥሎም 2ኛ

25. Κοσμᾶ Ἰνδικοπλεύστου: Χριστιανικὴ τοπογραφία Λόγος Ζ (VII) Migne: Patrologiae . . . T. 88 ዐምድ 372 D - 373 A::
26. Ράλλη-Ποτλῆ: Σύνταγμα των θείων και Ιερων Κανόνων Τ.Δ. ገጽ 365 - 367::



ዕዝራ ይከተላሉ:: በማከታተል አምስት የግጥም መጻሕፍትን: የተለያዩ ሥቃዮችን በመቋቋም አክሊለ ክብርን የተቀዳጀ ኢዮብንና የመንፈስ ዕረፍትን የሚሰጥ ቅኝት-መጽሐፈ መዝሙራትን እንደዚሁም ሦስት/መጻሕፍት/ ዘጠቢብ ሰሎሞንን፣ ምሳሌያትን፣ መክብብንና ማሐልየ መሓልይን አሳይአለሁ:: ከእነዚህም ላይ 12 ነቢያትን / ደቂቀ ነቢያትን/ ጨምር:: መጀመርያ ሆሴዕን፣ አሞጽን፣ ሚክያስን፣ ኢዩኤልን፣ /አብድያን/ እና ዮናስን የሦስት ቀኖናተ ሥቃይ ምሳሌ፣ ከእነዚህም በኋላ ናሆምን ከዚያም 7ኛን ዕንባቆምን፣ ሶፎንያስን እና ሐጌን፣ ዘካርያስንም፣ መልአከ ተብሎ የሚታወቀው ሚልክያስን:: ከእነሱም በኋላ አራቱን ነቢያት /ዐበይት ነቢያትን/ ትልቅ ዝና ያለው ኢሳይያስን፣ ተወዳጅ ኤርምያስን፣ ምሥጢራዊ ሕዝቅኤልን፣ በሥራውና በቃላት ጥበብን የተሞላ ዳንኤልን አጥና ከእነዚህም ላይ አንድአንዶች አስቴርን ይጨምራሉ::

አሁን ደግሞ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የሚመለከትበት ጊዜ ነው:: አባርዕቱ ወንጌላውያንን ብቻ ተቀበል:: ማቴዎስን ከዚያም ማርቆስን፣ ከእሱም ላይ ሶስተኛ ሉቃስን ጨመርህ በጊዜ ቅደም ተከተል 4ኛን ከትምህርተ መለኮት አንጻር ግን 1ኛን ዮሐንስን ቁጠር ምክንያቱም እኔም ወልደ ነጐድጓድ ብዬ በግልጥ እጠራለሁ:: ከሁሉም በላይ ስለ ቃለ እግዜአብሔር በከፍተኛ ምስጢር ድምፁን አሰምቷልና/እንደ መብረቅ ነጎድጓድ ድምፁን አሰምቷልና/፣ ቀጥሎም ሁለተኛው የሉቃስን መጽሐፍ/ግብረ ሐዋርያት/ እና ካቶሊካውያት-ግብራተ ሐዋርያትን ተቀበል:: አንድን ወደሮሜ ሰዎችና ከእሱም ጋር ለማያያዝ አስፈላጊ የሆኑትን ሁለትን ወደ ቆርንቶስ ሰዎች፣ አንድን ወደ ገላትያ ሰዎችና አንድን ወደ ኤፌሶን ሰዎች ከእሷም በኋላ አንድን ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች፣ ቀጥሎም አንድን ወደ ቆላስይስ ሰዎች፣ ሁለትን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች፣ ሁለትን ወደጢሞቴዎስ፣ አንድን ወደ ቲቶና አንድን ወደ ፊልሞና፣ አንድን ወደ ዕብራውያን የተላኩ 14 መልእክታትን የጻፈ የምርጫ እቃ ሰባኬ አሕዛብ ʼ



www.ethiopianorthodox.org

ጳውሎስ ሐዋርያንን ጨምር:: አንድአንዶች ግን እውነት ሳይኖራቸው ወደ ዕብራውያን የተላከችው መልእክት የጳውሎስ አለመሆንዋን ይናገራሉ:: ግን በውስጥ የሰፈረው ቃል (ጸጋ) እውነተኛ ነውና የጳውሎስ እውነተኛ መልእክት ትሁን:: ምን ቀረ? ካቶሊካውያት መልእክታትን እንመለከታለን:: አንድአንዶች ሰባት ሌሎች ሦስት ብቻ ናቸው ይላሉ:: ሦስት ሲሉ አንድ የያዕቆብን፣ አንድ የጴጥሮስን፣ አንድ የዮሐንስን መልእክታት መቀበል ይኖርብናል ማለታቸው ሲሆን ሌሎች ግን ጥቂቶች ከእነዚህ በስተቀር ሦስት የዮሐንስ መልእክታትን፣ ሁለት የጴጥሮስን፣ አንድ የይሁዳን መልእክት እንደ ሰባተኛ ይቀበላሉ:: አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስን አሁንም እንደገና አንድአንዶች በእውነተኛነት ቆጥረው ሲቀበሉ የበለጡት ግን እውነተኛ አይደለም ይላሉ:: ነገር ግን ይህ የአምላካውያት መጻሕፍት ቀኖና የማይተባበል መሆን ነበረበት፣»:: በአምፊሎኪዮስ ዘኢቆዮን ቀኖና ተቀንነው የሚገኙት አምላካውያት መጻሕፍት ዝርዝር

**ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት**

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም
6. ኢያሱ ወልደ ነዌ
7. መሳፍንት
8. ሩት
9. ነገሥት 1ኛ
10. ነገሥት 2ኛ
11. ነገሥት 3ኛ
12. ነገሥት 4ኛ
13. ትሩፋት 1ኛ

15. ዕዝራ 1ኛ
16. ዕዝራ 2ኛ/+ነህምያ/
17. ኢዮብ
18. መዝሙራት
19. ምሳሌያተ ሰሎሞን
20. መክብብ ዘሰሎሞን
21. ማሕልየ መሓልይ
22. ሆሴዕ
23. አሞጽ
24. ሚኪያስ
25. ኢዩኤል
26. አብድዩ/አብድያስ/
27.



29. ዕንባቆም
30. ሶፎንያስ
31. ሐጌ
32. ዘካርያስ
33. ሚልክያስ
34. ኢሳይያስ
35. ኤርምያስ
36. ሕዝቅኤል
37. ዳንኤል
38. አስቴር/አልፎ አልፎ/

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 37/+1 = 38/

## ለ.የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት

የጳውሎስ መልእክታት ሁለት ጊዜ ሰባት

6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 1ኛ
8. ወደ ቆርንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች 2ኛ
17. ወደ ቲቶ
18. ወደ ፊልሞና
19. ወደ ዕብራውያን

ካቶሊካውያት-ሐዋርያውያት መልእክታት ሰባት

20. የያዕቆብ መልእክት
21. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ
22. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
24. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
25. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
26. የይሁዳ መልእክት
27. አቡቀለምሲስ

እንደ አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን ቀኖና መሠረት የአምላካውያት መጻሕፍት ብዛት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 37 እና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት 27 = (37+27 = 64) 64 ወይም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 37+1 = 38 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 27 = (38+27 = 65) 65 ይሆናል::

www.ethiopianorthodox.org

## 3. አጠቃላይ የቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ማሰባሰቢያና ማስተያያ

### ሰንጠረዥ - ሰሌዳ 1

### የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር

| ብሉይ ኪዳን | ቀ ኖ ና ት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስ ም | 85 ሐዋርያው ያት ቀኖናት | ቀኖናት ዘላአዶቅያ | ቀኖናት ዘቅርጣግና | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎ-ክዮስ |
| ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት |
| ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት |
| ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን |
| ዘኁልቁ | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ |
| ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም |
| ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ |
| መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት |
| ሩት | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት |
| 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት |
| 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት |
| 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት |
| 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት |
| 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት |
| 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት |
| 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ |
| 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ |
| (ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ) |
| አስቴር | አስቴር | አስቴር | አስቴር | አስቴር | - | አስቴር |



| ብሉይ ኪዳን | ቀ ኖ ና ት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስ ም | 85 ሐዋርያው ያት ቀኖናት | ቀኖናት ዘላአዶቅያ | ቀኖናት ዘቅርጣግና | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎ-ክዮስ |
| ዮዲት | - - | - - | ዮዲት | ዮዲት | - - | - - |
| ጦቢያ | - - | - - | ጦቢያ | ጦቢያ | - - | - - |
| 1ኛ መቃብያን | 1ኛ መቃብያን | - - | 1ኛ መቃብያን | - - | - - | - - |
| 2ኛ መቃብያን | 2ኛ መቃብያን | - - | 2ኛ መቃብያን | - - | - - | - - |
| 3ኛ መቃብያን | 3ኛ መቃብያን | - - | - - | - - | - - | - - |
| መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር |
| ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ |
| ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ |
| መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ |
| መሐልይ | መሐልይ | መሐልይ | መሐልይ | መሐልይ | መሐልይ | መሐልይ |
| ጥ/ሰሎሞን | - - | - - | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን | - - | - - |
| ጥበበ ሲራክ | ጥበበ ሲራክ | - - | - - | ጥበበ ሲራክ | - - | - - |
| ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ |
| ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ |
| ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ |
| ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ |

www.ethiopianorthodox.org

| ብሉይ ኪዳን | ቀ ኖ ና ት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስ ም | 85 ሐዋርያው ያት ቀኖናት | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ | ቀኖናት ዘቅርጣግና | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎክዮስ |
| ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም |
| ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም |
| ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ |
| ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ |
| ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ |
| ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ |
| ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ |
| ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ |
| ባሮክ | - - | ባሮክ | - - | ባሮክ | - - | - - |
| ሰ/ኤርምያስ | - - | ሰ/ኤርምያስ | - - | ሰ/ኤርምያስ | - - | - - |
| መ/ኤርም | - - | መ/ኤርም | - - | መ/ኤርም | - - | - - |
| ያስ | | ያስ | | ያስ | | |
| ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል |
| ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል |
| 48 | 42 | 41 | 43 | 45 | 37 | 38 |

| ሐዲስ ኪዳን | ቀ ኖ ና ት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስ ም | 85 ሐዋርያው ያት ቀኖናት | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ | ቀኖናት ዘቅርጣግና | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎክዮስ |
| ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ |
| ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ |
| ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ |
| ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ |

| ሐዲስ ኪዳን | ቀ ኖ ና ት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስ ም | 85 ሐዋርያው ያት ቀኖናት | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ | ቀኖናት ዘቅርጣግና | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎክዮስ |
| ግብረሐዋ | ግብረሐዋ | ግብረሐዋ | ግብረሐዋ | ግብረሐዋ | ግብረሐዋ | ግብረሐዋ |
| ርያት | ርያት | ርያት | ርያት | ርያት | ርያት | ርያት |
| የጳውሎስ | የጳውሎስ | የጳውሎስ | የጳውሎስ | የጳውሎስ | የጳውሎስ | የጳውሎስ |
| ወደ | ወደ | ወደ | ወደ | ወደ | ወደ | ወደ |
| ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ |
| ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ |
| 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ |
| ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ | ቆሮንቶስ |
| 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ |
| ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ |
| ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን |
| ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ |
| ቆላይስ | ቆላይስ | ቆላይስ | ቆላይስ | ቆላይስ | ቆላይስ | ቆላይስ |
| ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ |
| 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ |
| ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ | ተሰሎንቄ |
| 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ |
| ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ |
| 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ | 1ኛ |
| ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ | ጢሞቴዎስ |
| 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ | 2ኛ |


www.ethiopianorthodox.org

| ሐዲስ ኪዳን | ቀ ኖ ና ት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስም | 85 ሐዋርያው ያት ቀኖናት | ቀኖናት ዘሳአዶቅያ | ቀኖናት ዘቅርጣግና | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሉኪዮስ |
| ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ |
| ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና |
| ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን |
| ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ |
| ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ |
| ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ |
| ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ |
| ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ |
| ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ |
| ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ |
| አቡቀለምሲስ | - - | - - | አቡቀለምሲስ | አቡቀለምሲስ | - - | አቡቀለምሲስ |
| መ/ቀለሚንጦስ 1ኛ | መ/ቀለሚንጦስ 1ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| መ/ቀለሚንጦስ 2ኛ | መ/ቀለሚንጦስ 2ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 1ኛ | ቀለሚንጦስ 1ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 2ኛ | ቀለሚንጦስ 2ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 3ኛ | ቀለሚንጦስ 3ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 4ኛ | ቀለሚንጦስ 4ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 5ኛ | ቀለሚንጦስ 5ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 6ኛ | ቀለሚንጦስ 6ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 7ኛ | ቀለሚንጦስ 7ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ቀለሚንጦስ 8ኛ | ቀለሚንጦስ 8ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| ት/ሐዋርያት | - - | - - | - - | ት/ሐዋርያት | - - | - - |
| ኖላዊ ሄርማ | - - | - - | - - | ኖላዊ ሄርማ | - - | - - |
| 87 (87+1=88) | 78 | 67 | 70 | 74 | 63 | 65 |


www.ethiopianorthodox.org

## 4. የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝርና ቀኖናዊነት ዓይነትና መጠን

ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝርና ቀኖናዊነት በቅዱሳት ሲኖዶሳትና አበው ሊቃውንት የተደነገጉባቸው ቀኖናት ስድስት(6) ቀኖናት መሆናቸውን ተመልክተናል:: በእነዚህ ሲኖዶሳውያትና አበውያት ቀኖናት ተዘርዝረው የተደነገጉት ቅዳሳት መጽሐፍት ቁጥር 88 ሲሆን ከእነዚህም መጻሕፍት መካከል አብዛኞቹ መጻሕፍት በ6ቱም ቀኖናት የሚገኙ ሆነው፣ ከቀሩት አንድ አንዶች በ5 ቀኖናት፣ ሌሎች በ4 ወይም በ3 ቀኖናት እንደሚገኙ ሲታዩ በጣም ያነሱት ደግሞ በ2 ቀኖናት ወይም በ1 ቀኖና ብቻ ተወስነው ይገኛሉ::

### 1. በሁሉም 6 ቀኖናት[27] ተይዘው የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍት

### ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቊ
5. ዘዳግም
6. ኢያሱ ወልደነዌ
7. መሳፍንት
8. ሩት
9. 1ኛ ነገሥት
10. 2ኛ ነገሥት
11. 3ኛ ነገሥት
12. 4ኛ ነገሥት
13. 1ኛ ዜና መዋዕል-ትሩፋት
14. 2ኛ ዜና መዋዕል-ትሩፋት
15. 1ኛ ዕዝራ
16. 2ኛ ዕዝራ
17. መዝሙር
18. ኢዮብ
19. ምሳሌያተ ሰሎሞን /ምሳሌ ሰሎሞን/
20. መክብብ
21. ማሕልየ መሓልይ
22. ሆሴዕ
23. አሞጽ
24. ሚክያስ/ሚኪያስ/
25. ኢዮኤል/ኢዩኤል/
26. አብድዩ/አብድዩ/
27. ዮናስ
28. ናሆም/ናኡም/
29. ዕንባቆም/አባኩም/አባኩክ/
30. ሶፎንያስ
31. ሐጌ/አንጌዮስ/
32. ዘካርያስ
33. ሚልኪያስ/ማላኪያስ/
34. ኢሳይያስ
35. ኤርምያስ
36. ሕዝቅኤል
37. ዳንኤል

### ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት

- የጳውሎስ መልእክታት 14

6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
8. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቆ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17. ወደ ቲቶ
18. ወደ ፊልሞና
19. ወደ ዕብራውያን

ሰባት-ሐዋርያውያት መልእክታት

20. የያዕቆብ መልእክት
21. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
22 የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
24. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
25. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
26. የይሁዳ መልእክት

---

27. - ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና
- ቀኖናት ዘላኦዶቅያ 60ኛ ቀኖና
- ቀኖናት ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/24/32ኛ ቀኖና
- መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ መልእክት
- ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት (ታኦጎሎስ-ታአሉጎስ)
- ቀኖና አምፊሉኪዮስ ዘኢቆንዮን

በዚህ መልክ በሁሉም 6ቱ ቀኖናት ሰፍረው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 37 መጻሕፍትና ከሐዲስ ኪዳን 26 መጻሕፍት በድምሩ ከ88 መጻሕፍት 63ቱ መጻሕፍት ናቸው::

## 2. ከ6ቱ ቀኖናት ከ5ቱ ቀኖናት[26] ታቅፈው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት

### ሀ. ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. አስቴር

መጽሐፈ አስቴር ከላይ እንደተጠቀሱት ቅዱሳት መጻሕፍት በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና «ቅዱስና ክቡር» እና በቀኖናት ዘላአዶቅያ /ሎዶቅያ/ 60ኛ ቀኖና እና በካርታጌኒስ (ቅርጣግና) 24/32 ቀኖና ቀኖናውያትና ንባባውያት መጻሕፍት መካከል እና በመልእክተ አትናቴዮስ/የሚነበቡ/ ምንባባውያት መጻሕፍት በመባል የሌሎችን ቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናዊነት ባልተከተለ መልክ ተመዝግበው ከሚገኙት መጻሕፍት /ጥበበ ሰሎሞን፣ ጥበበ ሲራክ፣ ዮዲት፣ ጦቢያስ፣ ትምህርተ ሐዋርያት እና ኖላዌ ዘሄርማ/ መካከል ሆኖ ይገኛል:: በቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን ደግሞ በአንድ አንዶች ብቻ ተቀባይነት እንደ አለው ሆኖ ሰፍሮ ይገኛል::

### ለ. ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. — — —

---

28. - 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና
- ቀኖናት ዘላአዶቅያ/ሎዶቅያ/ 60ኛ ቀኖና
- ቀኖናት ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/24ኛ/32ኛ ቀኖና
- መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ
- ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን —



## 3. ከ6ቱ ቀኖናት በ4ቱ ቀኖናት[29] ተይዘው የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍት

ሀ - ለ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ሆነ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል ከ6ቱ ቀኖናት በ4ቱ ቀኖናት ተመዝግበው የሚገኙ መጻሕፍት የሉም:: በትርጉም ግን ባሮክ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ እና መልእክተ ኤርምያስ በስም ተለይተው ባይጠቀሱም ከ6ቱ ቀኖናት በ4ቱ ቀኖናት/በኤርምያስ ስም እንደ ታቀፉ ሁነው ይታሰባሉ:: ሆኖም ተቀባይነቱ አጠራጣሪ ከመሆን አያመልጥም:: በተለይ በተጠቀሱት 4 ቀኖናት በሁለቱ 60ኛ ቀኖና ዘላአዶቅያ /ሎዶቅያ/ ንባባውያትና በመልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ ቀኖናውያት መጻሕፍት ተብለው ተመዝግበው ሲገኙ በ24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ /ቅርንጣግና/ እና በቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት/ታኦጎሎስ/ ኤርምያስ ሲባል ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር እነዚህም ሦስት መጻሕፍት እንደሚታቀፉ ሆኖ ስለሚተረጎም ነው::

## 4. ከ6ቱ ቀኖናት በ3 ቀኖናት[30] ሰፍረው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት

### ሀ. ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. — — —

### ለ. ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. አቡቀለምሲስ - ራእየ ዮሐንስ

---

29. - ቀኖናት ዘካርታጌኒስ (ቅርግጣና) - 24ኛ/32ኛ ቀኖና
- ቀኖናት ዘላአዶቅያ (ሎደቅያ) - 60ኛ ቀኖና
- መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ
- ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት

30. - ቀኖናት ዘካርታጌኒስ(ቅርጣግና) 24ኛ/32ኛ ቀኖና
- መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ
- ቀኖና አምፊሎኪዮስ

www.ethiopianorthodox.org

አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ በ24/32ኛ ቀኖና ዘካርተጌኒስ/ቅርጣግና/ እና በመልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ ቀኖናዊ - ቅኑን ተብሎ ተመዝግቦ ሲገኝ በቀኖና አምፌሎኪዮስ ተቀባይነቱ በአንድ አንዶች ብቻ መሆኑ ተመልክቱ ይታያል::

## 5. ከ6ቱ ቀኖናት በ2ቱ ቀኖናት[31] ተይዘው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት

### ሀ. ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዮዲት
2. ጦቢት
3. መቃብያን 1ኛ
4. መቃብያን 2ኛ
5. ጥበበ ሰሎሞን
6. ጥበበ ሲራክ

ከእነዚህ 6 መጻሕፍት መካከል ዮዲትና ጦቢት፣ ጥበበ ሰሎሞን በ24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ (ቅርጣግና) «ቀኖናውያት መጻሕፍት» ተብለው ተመዝግበው ሲገኙ በመልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ ግን እንደ መጽሐፈ አስቴር የሚነበቡ ምንባባውያት መጽሕፍት ተብለው ተለይተው ተመዝግበው የሚገኙ ናቸው:: 1ኛ መቃብያን፣ 2ኛ መቃብያ እና 3ኛ መቃብያን በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና «ቅዱሳትና ክቡራት» በመባል ተጽፈው ከመገኘታቸው ጋር የመጀመርያዎች ሁለት መቃብያን በ24ኛ/32ኛ ቀኖና ካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ ሳቲን ሰነድ ቀኖናውያት መጻሐፍት ተብለው ተመዝግበው ይታያሉ::

ከ6ቱ ቀኖናት በ2ቱ ቀኖናት ብቻ ተቀንነው የሚገኙ መጻሕፍት 6 መጻሕፍት ሲሆኑ ሁሉም በአሁኑ ጊዜ የ2ኛ ቀኖና-መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ሁነው የሚገኙት ናቸው::

31. - ቀኖናት ዘካርታጌኒስ(ቅርጣግና) 24ኛ/32ኛ ቀኖና
- 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ወይም
- መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ



### ለ. ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. - - - -

## 6. ከ6ቱ ቀኖናት በአንድ-አንድ ቀኖና ብቻ[32] ተይዘው የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍት

### ሀ. ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. - - -

### ለ. ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስ
2. ስምንት ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ
3. ትምህርተ ሐዋርያት
4. ኖላዊ /ሄርማ/

ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስና ስምንት ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና «ቅዱሳትና ክቡራት መጻሕፍት» ተብለው ከተጠቀሱት መጻሕፍት መካከል ሆነው ሲገኙ ነገር ግን 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት በውስጣቸው በሚገኙት ምስጢራት ምክንያት ለሁሉም መዳረስ - ሞሠራጨት እንደሌለባቸው ታትቷል:: ሌሎች ሁለት መጻሕፍት: ትምህርተ ሐዋርያትና ኖላዊ በመልእክተ አትናታዎስ 39ኛ ከግዴታዎች ቀኖናውያት መጻሕፍት መካከል ሳይሆን የሚነበቡ-ምንባባውያት መጻሕፍት ተብለው በመጨረሻ ከተያዙት መጻሕፍት መካከል ሁነው ነው የሚገኙት:: በሌላ በኩል በመልእክተ አትናቴዎስ ትምህርተ ሐዋርያት ተብሎ የተመለከተው መጽሐፍ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ መሆኑ ይታመናልም-ይደገፋልም::

ሀ. በሌላ በኩል ግን ትልቁ አትናቴዎስ ትምህርተ ሐዋርያት

32. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ወይም መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ::



www.ethiopianorthodox.org

ሲል 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስን ሳይሆን ራሱን ትምህርተ ሐዋርያትን -(Διδαχη) ወይም ይህ መጽሐፍ በብዛት ቁጥር ይታወቃል:: ትምህርታተ ሐዋርያት (διδαχαι) መሆኑ ይበልጥ ይደገፋል[33]::

ስለዚህ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ እና ትምህርተ ሐዋርያት ወይም ትምህርታተ ሐዋርያት አንድ መጽሐፍ አለመኖናቸው ይታያል:: ትምህርተ ሐዋርያት ከ4ኛው ምዕተ ዓመት በኋላ ጠፍቶ ይገኝ ነበር:: ስለዚህም በ39ኛ መልእክተ አትናቴዎስ «ትምህርተ ሐዋርያት» ሲባል ሰዎች ሊገነዘቡ ይችሉ የነበረው ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ማለት መሆኑን ነበር:: ነገር ግን ይህ ትምህርተ ሐዋርያት በ1883 ዓ.ም. እንደገና በመገኘቱ ሁለቱ መጻሕፍት: ትምህርተ ሐዋርያትና ሐዋርያውያት ትእዛዛት አንድ አለመሆናቸው ሊታይ ችሏል::

ነገር ግን 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ከቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት ተብለው ተመዝግበው ቢገኙም በ692 በትሩሎ በተጠራው 5ኛ - 6ኛ ሲኖዶስ በአለባቸው ቤተ ክርስቲያን በማትቀበላቸው ትምህርቶች ምክንያት ሳይጸድቁ ቀርተው ውድቅ ሁነዋል:: እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይህን ሲኖዶስ አታውቀውም::

«ኖላዊ» የሚባለውን መጽሐፍ በሚመለከት ብዙ የሚታተት ባይኖርም ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈው መጽሐፍ ግን ቁጥር ያልገባና «ወሪድየ ብሔረ ሮሜ» ብሎ የሚጀምር መጽሐፍ

33. ዲብኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 147 የግርጌ ማስታወሻ 580 - 581::

34. Th. Klauser: Doctrina duodicim Apostolorum, Bonn 1940. P.Nautin: La Composition de la "Didche" et son tire-revue de l' histoire des Religions T.55. (1959) ገጽ 191 - 241::



መሆኑ በአንድ በኩል ሲነገር በሌላ በኩል ደግሞ ሄርሜን የሚባል ሰው እንደጻፈውና ስለዚህም በዚህ ሰው ስም እንደተጠራ ይተረካል[35]:: ነገር ግን ይህ መጽሐፍ በትክክል በመልእክተ አትናቴዎስ ኖላዊ እንጂ ኖላዊ ዘሄርማ ተብሎ አይገኝም::

እንግዲህ ከላይ በተመለከቱት 6 ቀኖናት በ6ቱም በሙሉ ወይም በአንድ አንዶች ወይም በሌሎች የተወሰኑት ቀኖናት በድምር ተይዘው የሚገኙት መጻሕፍት 49 የብሉይ ኪዳን እና 39 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍ: 88 መጻሕፍት ሁነው ሲገኙ በመጨረሻ ቅዱሳት መጻሕፍት መሆናቸው ተቀባይነትን አግኝተው በአሁኑ ጊዜ የሚገኙት መጻሕፍት በሁለት መልክ ይታያሉ::

በግሪክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በ1950 /እ.እ/ የታተመ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ስንመለከት የሚከተሉትን መጻሕፍት ይዞ ይገኛል::

## ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

| | |
|---|---|
| 1. ዘፍጥረት | 12. 4ኛ ነገሥት |
| 2. ዘጸአት | 13. 1ኛ ዜና መዋዕል - ትሩፋት |
| 3. ዘሌዋውያን | 14. 2ኛ ዜና መዋዕል - ትሩፋት |
| 4. ዘኁልቁ | 15. 1ኛ ዕዝራ |
| 5. ዘዳግም | 16. 2ኛ ዕዝራ |
| 6. ኢያሱ ወልደነዌ | 36. ዮናስ |
| 7. መሳፍንት | 37. ናሆም/ናኡም/ |
| 8. ሩት | 38. ዕንባቆም /አባኩም/ |
| 10. 2ኛ ነገሥት | 17. ነህምያ |
| 11. 3ኛ ነገሥት | 18. ጦቢት |

35. አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ: መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አዲስ አበባ 1948፤ ገጽ 373:: A Abbadie: Catalogus ... Le Pasteur Herma. No. 174::

www.ethiopianorthodox.org

19. ዮዲት
20. አስቴር
21. 1ኛ መቃብያን
22. 2ኛ መቃብያን
23. 3ኛ መቃብያን
24. መዝሙር
25. ኢዮብ
26. ምሳሌያተ ሰሎሞን
27. መክብብ
28. ማሕልየ መሓልይ
29. ጥበበ ሰሎሞን
30. ጥበበ ሲራክ
31. ሆሴዕ
32. አሞጽ
33. ሚክያስ
34. ኢዩኤል
35. አብድዩ/አብድዩ/
36. ዮናስ
37. ናሆም
38. ዕንባቆም
39. ሶፎንያስ
40. ሐጌ
41. ዘካርያስ
42. ሚልክያስ
43. ኢሳይያስ
44. ኤርምያስ
45. ባሮክ
46. ሰቆቃወ ኤርምያስ
47. መልእክተ ኤርምያስ
48. ሕዝቅኤል
49. ዳንኤል

ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት

- የጳውሎስ መልእክታት

6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
8. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17. ወደ ቲቶ
18. ፊልሞና
19. ወደ ዕብራውያን
20. የያዕቆብ መልእክት
21. የይሁዳ መልእክት



22. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
24. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
25. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ
26. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
27. አቡቀለምሲስ-ራእየ ዮሐንስ

የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 49+27=76 መጻሕፍት ሲሆኑ በአለፉት በ6ቱ ቀኖናት ከተመዘገቡት 88 መጻሕፍት 76ቱ ሲቀነሱ /88-76/ = 12 መጻሕፍት እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ተቆጥረው አልተወሰዱም ማለት ነው::

እነዚህም 12 መጻሕፍት ሁለት የቀለሚንጦስ መልእክታት፣ 8 ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ፣ ትምህርተ ሐዋርያትና ኖላዊ ናቸው[36]::

በሌላም በኩል በሲቃውንት ሐተታም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 3 መቃብያን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግበው የማይገኙበት ሁኔታ ያጋጥማል::

ስለዚህም ከ49 መጻሕፍት 3 መቃብያን ሲቀነሱ/49-3=46/ =46 በመቅረት 46+27=73 መጻሕፍት እየተመዘገቡ ይገኛሉ::

ነገር ግን በተመለከቱት ቀኖናት የተዘረዘሩት መጻሕፍት ቁጥር 49 ሳይሆን 48 ነው:: ሆኖም 49ኛው ቁጥር ሊከሰት የቻለው ከ6ቱ ቀኖናት በአንድም እንኳን ቀኖና ያልተመለከተ-ያልተያዘ አንድ መጽሐፍ - መጽሐፈ ነህምያ በቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ቆይቶ ገብቶ በመገኘቱ ነው::

ይህ መጽሐፈ ነህምያ በመጻሕፍተ ዕዝራ ተይዞ - ተሸፍኖ ይገኝ ስለነበረ ነው::

---

36. Παν. Μπούμη: οἱ Κανόνες τῆς Ἐκκλησιάς περὶ τοῦ Κανόνος της Ἁγιάς Γραφῆς, Ἀθῆναι 1991 ገጽ 205 - 210::

www.ethiopianorthodox.org

ከ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት ዝርዝር በ5ቱ ቀኖናት[37] ሁለቸ መጻሕፍተ ዕዝራ ተመዝግበው ይታያሉ[38]::

እንግዲህ የሚነሳው ጥያቄ ነህምያ /መጽሐፈ ነህምያ/ ከወዴት መጣ? ነው::

የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ታሪክ ሲጠና ነህምያን /መጽሐፈ ነህምያን/ በሚመለከት ለተነሳው ጥያቄ መልስ የተገኘ ይመስላል:: በመጀመርያ ነህምያ /መጽሐፈ ነህምያ/ በስም ተለይቶ ባይጠቀስም ዕዝራዎች /መጻሕፍተ ዕዝራ ጋር ተዋሕዶ ይሰማ እንደነበር ሲደገፍ ከዚህ የተነሳ በአንድ ወቅት አንደኛው መጽሐፈ ዕዝራ ማለትም 2ኛው መጽሐፈ ዕዝራ ከሁለት ተከፍሎ አንድ ዕዝራ እና ሌላው ነህምያ /አንዱ መጽሐፍ ዕዝራ ካልዕ/ እና ሁለተኛው መጽሐፈ ነህምያ የሚሉ ስሞችን ሊይዝ እንደቻለ ይተረካል::

ስለዚህም አንድ መጽሐፍ የነበረው መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ከሁለት ሲከፈል በምዕራፎች 1-10 ያለው ክፍል የመጀመሪያው መጽሐፍ ራሱ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ሆኖ ሁለተኛ ከምዕራፍ 11 ቀጥሎ ያለው ክፍለ መጽሐፈ ዕዝራ መጽሐፈ ነህምያ ሆኖና ተብሎ ይገኛል::

እንግዲህ በቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት የታወቁት ሁለት መጻሕፍተ ዕዝራ ሁለተኛው መጽሐፍ በሁለት ተከፍሎ ከመገኘቱ የተነሳ ሶስት መጻሕፍት ሁነው ሊገኙ ችለዋል::

37. - 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና
- ቀኖናት ዘሳኦዶቅያ /ሉደቅያ/ 60ኛ ቀኖና
" - ቀኖናት ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ 24ኛ/ 32ኛ ቀኖና
- መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ
- ቀኖና ዘአምፊሎኪዮስ ዘኢንቆንዮን

38. በጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ቀኖና አንድ ዕዝራ ብቻ ነው ተመዝግቦ የሚገኘው::



በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ዕዝራ እና ነህምያ /መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ እንጂ 1ኛ መጽሐፈ ዕዝራ፣ 2ኛ መጽሐፈ ዕዝራ እና መጽሐፈ ነህምያ ተብለው አይገኙም:: በዚህም ጊዜ መጽሐፈ ዕዝራ ተብሎ የሚገኘው መጽሐፍ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ነው:: በዕብራይስጥ -ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሰብዐ ሊቃናት የተመዘገበ 1ኛ እዝራ አይገኝም::

ስለዚህ 2ኛ ዕዝራ ብቻ ተመዝግቦ እንደመገኘቱ መጠን ይህ ዕዝራ ነው 1ኛ. ዕዝራ ወይም አንድ ዕዝራ ብቻ ሆኖ የቀረበው:: ከዚህም በስተቀር ከሌሎች አብያተ ክርስቲያትያናትና - ቋንቋዎች ቅዱሳት - አምላካውያት መጻሕፍት ትርጉሞች ይህ ዕዝራ ብቻ ነው አንድ ዕዝራ ሆኖ የሚገኘው:: 2ኛ ዕዝራ የሚባል መጽሐፍ የለም:: ነህምያ - መጽሐፈ ነህምያ ግን አለ:: 2ኛ መጽሐፈ ዕዝራ እንደተባለው ከ1 - 10 ያሉ ምዕራፎችን ይዞ የሚገኘውና መጽሐፈ ነህምያ የተካፈለበት መሆኑ ነው:: ይህንም ወደፊት ከግእዝ ትርጉም ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እንመለከታለን::

www.ethiopianorthodox.org

በሌላም በኩል እንደተባለው ወደፊት የምንመለከተው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዕብራይስጥ ቋንቋ የሚገኙት መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፈ ነህምያ በሰብዓ ሊቃናት-ጽርእና ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት - የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት «መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና» ተብለው ሲታወቁ በዚህም ጊዜ መጽሐፈ ዕዝራ ሆኖ የሚገኘው መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ሲሆን መጽሐፈ ዕዝራ ቀዳማዊ ግን መጽሐፈ ዕዝራ ዘዳግም ቀኖና ሆኖ ይታያል።

በአጭሩ በሰብዓ ሊቃናት - ጽርእና ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ሁለት መጻሕፍተ ዕዝራ፡ መጽሐፈ ዕዝራ ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕና ከዚህም ከምዕራፍ 11 - 24 (1-13) ተከፍሎ የወጣ መጽሐፈ ነህምያ ሲገኙ በግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ሌላ መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ይገኛል[39]።

39. ከዚሁ ገጽ 158 - 170።



# ምዕራፍ ሦስት
# የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናት ግእዝ ትርጉሞች

በአለፈው ምዕራፍ በተመለከቱት የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ቀኖናት /ሲኖዶሳውያትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቀኖናት/ የተዘረዘሩት ቅዱሳት መጻሕፍት-አምላካውያት መጻሕፍት ቀኖናቱ ወደ ግእዝ በተመለሱባቸው መልኮቻቸው ይመረመራሉ። በመጨረሻም እነዚህ የግእዝ ትርጉም ቀኖናት ቅዱሳት መጻሕፍት ፍትሐ ነገሥትን ጨምሮ ከምንጮቻቸው ግሪክ ቀኖናተ መጻሕፍት /በተለይ ከብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት/ ጋር ይመሰከራሉ።

## (1) ሲኖዶሳውያት ቀኖናት 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት

ከአብያተ ክርስቲያናት ቀኖናት በመጀመርያ የሚታዩት ሲኖዶሳውያት ቀኖናት ሲሆኑ ከእነዚህ ቀድመው የሚታዩት ሐዋርያውያት ቀኖናት ወይም ቀኖናተ ሐዋርያት ናቸው። እነዚህንም ለመመልከት ሁለት ምንጮች ያጋጥሙናል። ከእነዚህም አንዱ ፍትሐ ነገሥት ሲሆን ሌላው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን «ሲኖዶስ» ተብሎ የሚታወቀው መድበለ ቀኖናት ነው።

## 1. ፍትሐ ነገሥት

ፍትሐ ነገሥት ሲቀነባበር ለጸሐፊው እብነ አል አሳል በምንጩነት ያገለገሉት አራት/4/ ሐዋርያውያት ቀኖናት ወይም ቀኖናተ ሐዋርያት ወይም መጻሕፍተ ቀኖናት ተብለው በመቅድሙ ላይ ተመዝግበው ይገኛሉ።



www.ethiopianorthodox.org

## 1.1 ለመጻሕፍተ ቀኖናትስ ቀዳሚ/ቀዳሚሆሙ/ ቀኖና ዘሠርዕዋ ሐዋርያውት-ሐዋርያት የሠሯት ቀኖና = ዓይን/ሥርዐተ ጽዮን/

የሰዋሰውን ሕግ ከተከተለ «መጻሕፍተ ቀኖናትስ ቀዳሚሆሙ ቀኖና ዘሠርዕዋ ሐዋርያት[1]» ስህተት ነው:: ማለት የነበረበት አንድም ለመጻሕፍተ ቀኖናትስ ቀዳሚሆሙ መጽሐፈ ቀኖናት ዘሠርዕዎን ሐዋርያት=ሐዋርያት የሠሯቸው የመጻሕፍተ ቀኖናት የመጀመሪያው መጽሐፈ ቀኖናት ወይም ለመጻሕፍተ ቀኖናትስ ቀዳሚያቲሆሙ /ቀዳሚያቲሆን/ ቀኖናት ዘሠርዕዎን ሐዋርያት=ሐዋርያት ለሠሯቸው መጻሕፍተ ቀኖናት የመጀመሪያዎች ቀኖናት ማለት ነበረበት:: ምክንያቱም ስለ አንድ ቀኖና ሳይሆን ስለብዙ ቀኖናት /30 ቀኖናት/ ነው የሚናገረው:: እነዚህ ቀኖናተ ሐዋርያት ከክርስቶስ ዕርገትና ረድተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ለሰብከተ ወንጌል ወደ ዓለም ከመበተናቸው አስቀድሞ በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው የሠራቸው - የደነገጓቸው ቀኖናት ናቸው::

ስለዚህም «ሥርዐተ ጽዮን» ተብለው ይጠራሉ፤ መሪ ምልክታቸው-ትእምርተ ጥቅሳቸው «ዓይን» ነው:: ዓይን ምኅጻረ ቃል ነው:: ይህም የመጀመሪያው ፊደል «ዓ» ከጽርሐ እና ይን ከጽዮን ሁለት ቃላት ተወስዶ ከጽርሐ ጽዮን ሥርዐተ ጽዮን «ዓይን» እንደ ተወለደ ይነገራል[2]::

በሌላም በኩል «ዓይን» ሐዋርያት ከተሰበሰቡበት ጽርሐ ጽዮን ሰገነት የመጀመሪያው ፊደል ነውም ይባላል:: ሥርዐተጽዮን ወይም ቀኖናተ ሐዋርያት ቁጥራቸው 30 ወይም

1. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2፤ ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና: ሥርዐተ ጽዮን /ዓይን/ ገጽ 113-136::
2. ፍትሐ ነገሥት ንባባና ትርጓሜው offset ኀትመት 1958 ገጽ 26 ::



27 ሆኖ ሲገኝ በሌላ በኩል ከሐዋርያ ታዴዎስ ትምህርት /ከትምህርተ ታዴዎስ ሐዋርያ/ እንደ ተወሰደም ይታመናል::

የትምህርተ ታዴዎስ መግቢያ - መንደርደርያ በአጭሩ የሥርዐተ ጽዮን በፍትሐ ነገሥት መቅድም ከተቀመጠው መቅድም ጋር የተቃረበ ነው::

ክርስቶስ ወደ ሰማይ አርጎ በአባቱ ቀኝ እንደተቀመጠና መንፈስ ቅዱስ ወደ ሐዋርያት ወርዶ መንፈስ ኃይልን እንደመላባቸው ከዚህም የተነሳ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች እንደ አናገራቸው፣ ይህንም ጸጋ በመላበሳቸው በዓለም ዙርያ ተሠራጭተው በተለይ የቋንቋ ችግር ሳይገጥማቸው ወንጌልን ለመስበክ እንደተሰማሩ የሚናገረው የትምህርተ ታዴዎስ መቅደም-መግቢያ ነው[3]:: ወደ ትምህርተ ታዴዎስ ሐዋርያት ዝርዝር ሁኔታ ሳንገባ በአጭሩ ሥርዐተ ጽዮን «ዓይን» በአለበት መልኩ እንወስናለን[4]::

እንግዲህ «ዓይን» በሚል ምንጻረ ቃል የተመለከተው ሥርዐተ ጽዮን /30 ቀኖናተ ሐዋርያት/ የተጻፋበት ዘመን በግሪኮች ዘመነ መንግሥት ቀመር ሐምሌ 14 ቀን 342 ነው ማለትም ክርስቶስ የተወለደው በዚህ ቀመረ ዘመን 309 ስለሆነ 342 - 309 = 33 በጰንጠቆስጤ ዕለት ሐዋርያት በጽርሓ ጽዮን ሰገነት በአደረጉት የመደመሪያ ስብሰባ /ቀዳሚ ሐዋርያዊ ጉባኤ - ሲኖዶስ/ የተጻፈ ግብረ ሐዋርያት ሆኖ ስለሚቆጠር የተጻፈበት ጊዜ ይህ የሐዋርያት የመጀመሪያ ስብሰባ ዕለት ነው የሚለው ታሪክ ይታወሳል:: ነገር ግን ሥርዐተ ጽዮን ማለትም

3. P.De Lagarde: Reliquiae Juris Ecclesiastici antiquissimae Graec ገጽ 82 - 90::
4. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 114 - 128::

www.ethiopianorthodox.org

የሚመረመሩት 30 ቀኖናተ ሐዋርያት ግብራተ ሐዋርያት ናቸው? ወይስ አይደሉም? የሚሉት ጥያቄዎች በእነዚህ ቀኖናት ላይ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት በምንመለከታቸው ሌሎች ልዩ ልዩ ቀኖናት ላይም የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው:: ሆኖም የሚታመነው ከክርስቶስ ዕርገትና ርድተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌል ከመበተናቸው አስቀድሞ በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው የሠሯቸውን ቀኖናት የያዘ ሥርዐተ ጽዮን ከመጻፍተ ቀኖናት የመጀመርያ መጽሐፈ ቀኖናት መሆኑ ነው::

ነገር ግን «ሥርዐተ ጽዮን» በመባል የሚታወቁት እነዚህ 30 ቀኖናት በሐዋርያት እንደ ተሰጡ ማለትም በሐዋርያት ዘመን /በጽርሐ ጽዮን ጉባኤ - ሲኖዶስ/ እንኳን ባይሆን /በሐዋርያት ዘመን እንደተጻፉ ማመኑ አስቸጋሪ ሆኖ ይገኛል:: ስለዚህም ሁልጊዜ የሚቀርበው ምክንያት ቢያንስ በዘመነ ሐዋርያት ያልታወቁ - ገና ያልዳበሩ የተወሰኑት ቀኖናት ድንጋጌዎች - ትእዛዛት ተደንግገው ለምሳሌ: የሦስቱ /ማዕርጋተ ክህነት ቅርጽና መልክ፣ በዓለ ጥምቀት፣ በዓለ ልደት፣ ቅድመ ፋሲካ ጾም-ጾመ አርብዓ፣ ወዘተ[5] ስለሚገኙበት በዚያን ወቅት - ዘመነ ሐዋርያት በተግባር ላይ ሊውሉ አይችሉ ስለነበር በሐዋርያት ዘመን ተደንግገዋል ብሎ ለመቀበል የሚያስቸግረው ስለዚህ ነው:: ሆኖም ጸሐፊው ሐዋርያት እነዚህን ቀኖናት ሲደነግጉ በዘመናቸው ይተረጎማሉ ማለት ሳይሆን ነገር ግን ወደፊት ለሚመጣው ጊዜ ያገለግላሉ ብለው እንደሆነ ነበር ሲል ዓረፍተ ነገሮችን አሰፍሮ ስለሚገኝ ለዚህ ጥያቄ መልስ አዘጋጅቷል:: «ይህን ሐዋርያት በዘመናቸው ሳይሆን ከእነሱ በኋላ ለሚመጣው ዘመን ደነገጉት» ይላል[6]:: ቢሆንም ሥርዐተ ጽዮን /30 ቀኖናተ ሐዋርያት/ በአጭሩ ከዘመነ ሐዋርያት በኋላ ቆይተው የተጻፉ

5. ቀኖና 6፣7፣10 ::
6. መጽሐፈ ትምህርት ዘታዴዎስ መግቢያ::



www.ethiopianorthodox.org

ቀኖናት መሆናቸውና ግን በሐዋርያት ስም እንዲጠሩ ተደርጓ የሚለው አስተሳሰብ የጸና ነው[7]::

በሌላ በኩል ግን እነዚህ ቀኖናት ፍትሐ ነገሥት ሲቀነባበር እንደምንጮች ሁነው ቢመለከቱም ቅሉ «በዓይን ምኅጸረ ቃልነታቸው በሰነዱ ውስጥ እንደሌሎች ምንጮች በአንድም ቦታ ላይ ተጠቅሰው አይገኙም::

ሥርዐተ ጽዮን የተጻፈበት /30 ቀኖናተ ሐዋርያት የተጻፉበት/ ቋንቋ ጽርእ/ግሪክ/ መሆኑን አሁንም በፍትሐ ነገሥቱ መቅድም ላይ መረዳት ሲቻል ከዚያም ቀጥሎ የፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ እብነ አል አሳል መለካውያንና ንስጥሮሳውያን ይህን ሥርዐተ ጽዮን ከልሳነ ጽርእ/ግሪክ/ ወደ ዐረብኛ /ዐረቢ/ ለመተርጎም እንደደከሙ ይህም ሥርዐተ ጽዮን በያዕቆባውያን - ሶርያውያን ዘንድ እንደሚገኝ ይናገራል[8]::

ሥርዐተ ጽዮን /30 ወይም 27 ቀኖናተ ሐዋርያት/በምሥራቅ ቋንቋዎች: ሱርስጥ፣ ግብጥ፣ ዐረብኛና ግእዝ ተተርጉመው ይገኛሉ::

### 1.1.1 የሥርዐተ ጽዮን ሱርስጥ ትርጉም

የሥርዐተ ጽዮን 27 ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም ምንአልባት ከሌሎች ቋንቋዎች /ዐረብኛና ግእዝ/ ትርጉሞች ቅድሚያ እንደ አለው ይታመናል:: ጊዜውም በ5ኛው ምዕተ ዓመት እንደነበረ ይገመታል[9]:: የእነዚህ ቀኖናት ቁጥር በሱርስጥ ትርጉማቸው 27 ወይም 30[10] እየሆነ ይገኛል::

7. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 125::
8. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
9. Cureton: anciennes syriac documents London 1984. ገጽ 149::
10. A. Land: Anecdota syriaca 1862. ገጽ 65 -66፣94::

## 1.1.2 የሥርዐተ ጽዮን ዐረብኛ ትርጉም - ቅብጥ ትርጉምን ጨምሮ

ከላይ እንደተባለውም እንደፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብን አል አሳል እነዚህ 30 ቀኖናት በሦስቱ ኅብያተ ክርስቲያናት /መለካውያት፤ ንስጥሮሳውያት[11] እና ያዕቆባውያት[12] አብያተ ክርስቲያናት /ዘንድ ወደ ዐረብኛ/ዐረቢ/ ተተርጉመው መገኘታቸው ሲታወቅ በቅብጥ ቋንቋ አንድ አንድ ጊዜ «ቲትላሳት» (ተጥላሳት) የሚል ርእስን ይዞ ይገኛል[13]::

## 1.1.3 የሥርዐተ ጽዮን ግእዝ ትርጉም

ሌላው የሥርዐተ ጽዮን /30 ቀኖናት/ ግእዝ ትርጉም ነው:: ከዐረብኛ ትርጉም ስንድ ምን አልባት የተመለሱት እነዚህ ግእዝ ትርጉም ቀኖናት «ሥርዐተ ጽዮን» ወይም «ቀኖናት ዘጽዮን» በሚል ቅርጽ ይገኛሉ[14]::

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አንድ ቀኖናዊ መደበል «ሲኖዶስ» በሚል ርእስ መገኘቱ ሲታወቅ የዚህ ሲኖዶስ የመጀመሪያው ክፍል ሐዋርያውያት ቀኖናትን በተለያዩ ርእሶች ይዞ ሲገኝ ከእነዚህ ቀኖናት መድበል ሥርዓተ ጽዮን «መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት» አንዱ ነው::

---

11. Gregorius Bar Hebraeus: Nomocanon Ecclesiae Antiochenae (Syrorum) Latin Interprete Alyosio Assemano ገጽ 1 -268፤ A.Maio: Scriptorum. T.X. ገጽ 3 - 5፤ 169 - 173::
12. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
13. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
14. ሲኖዶስ ገጽ 52 - 58::



## 1.2 ዳግማዊ ቀኖና ዘአስተናበርዎ ኀዐበ ሐዋርያት = ሐዋርያት ዳግመኛ ያዘጋጁት ሁለተኛ ቀኖና - ሬኒበስ

አሁንም በአለፈው ክፍል እንደተመለከትነው ይህ ርእስ የሰዋሰው ስህተት አለበት:: ዐረፍተ ነገሩ በሙሉ የሚያመለክተው «ወዳግማዊ ቀኖና ዘአስተናበርዎ ኀዐበ ሐዋርያት ወፈነውዎ በእደ ቀለሚንጦስ ረድኦ ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት . . ./ ሐዋርያት አዘጋጅተው በሐዋርያው ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ቀለሚንጦስ እጅ ወደ ምእመናን ዳግመኛ የላኩት ሁለተኛ ቀኖና»:: ነገር ግን ይህ አንድ ቀኖና አይደለም:: ብዙዎች ቀኖናት ናቸው:: ስለዚህም በነጠላ መነገሩ ስህተት ነው:: ምንአልባት ዳግማዊ መጽሐፈ ቀኖናት ለማለት ፈልጎ ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል ምክንያቱም ሲነሳ ለመጽሐፍተ ቀኖናትስ ቀዳሚሆሙ ... ይላልና::

ወደ መሠረተ ሐሳቡ ስንመለስ - ስንመለከት እንደ ፍትሐ ነገሥቱ ጸሐፊ አብን አል አሳል አገላለጥ እነዚህ ሁለተኛዎች - ዳግማይያት ቀኖናተ ሐዋርያት ወይም ሐዋርያውያት ቀኖናት በሐዋርያት ተዘጋጅተው በሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ቀለሚንጦስ እጅ ወደ ሁሉም አርድእትና ምእመናን የተላኩ መሆናቸውና ከዚያም ቀኖናቱን በአንድ መጽሐፍ በማሰባሰብ ይህንም መጽሐፈ ቀኖናት ወደ ዐረብኛ /ዐረቢ/ እንደተረጎሙ /እንደተረጎሟቸው/ ሁነው እንደተገኙና የቀኖናቱንም ቁጥር በመለካውያን ዘንድ 83 ሲሆን በያዕቆባውያን - ሶርያውያን ዘንድም ይኸው ቁጥር /83/ ነው ያለው:: በንስጥሮሳውያን ዘንድ ግን ንስጥሮዊ ወልደ ጠይብ ያሰባሰበው መጽሐፈ ክርስቲያን /መጽሐፈ ኩሎሙ ክርስቲያን/ እንደሚናገረው የእነዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት ቁጥር 82 ነው::



www.ethiopianorthodox.org

የእነዚህ ቀኖናት መሪ ምልክት - ትእምርተ ጥቅስ አራት /4/ፊደላት/ ረስጠአ/ ናቸው[15]::

ከእነዚህ አራት ፊደላት /ረስጠአ/ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፊደላት «ረስ» ዐረብኛ ቃል «Rusul» /ሩሱል/ ትርጉሙ ሐዋርያ /ሐዋርያት/ የሚለው ቃል ምኅጻረ ቃል - የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፊደላት ናቸው:: 3ኛው ፊደል «ጠ» ቀኖናቱ በእጅ የተላከበት ቀለሚንጦስ ምንጻረ ቃል ነው:: 4ኛው ፊደል «አ» በዐረብኛ ቋንቋ /በግሪክ ቋንቋም ቢሆን/ አሐዝ ቁጥር አንድ ቁጥርን የሚተካ ፊደል ነው::

ስለዚህ «ረስጠአ» ማለት ረስጠአ ዘውእቱ ቀለሚንጦስ ቀዳማዊ = 1ኛ መጽሐፈ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ /1ኛ ቀለሚንጦስ ማለት/ ነው::

ረስጠአ - ቀለሚንጦስ ቀዳማዊ በማንኛውም መድበለ ቀኖናት መጀመርያ ምዕራፍን እያያዙ የሚገኙት 85 ሐዋርያት ቀኖናተ ትርጉም ነው:: እነዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት 85 ቀኖናት ሁነው የሚገኙት በተጻፉበት ጽርእ ቋንቋ /ግሪክ/ ሲሆን ወደ ላቲን ቋንቋ /ልሳነ ሮማይስጥ/ ሲመለሱ 84 ቀኖናት ሁነዋል:: ይህም 49ኛው እና 50ኛው ቀኖናት አንድ ቀኖና 49ኛ ቀኖና ሁነው ስለተቀረጹ ከ85 ወደ 84 መውረድ ግድ ሆነ::

ሆኖም ከላይ እንደተባለው አሁንም እነዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በሐዋርያት በራሳቸው እንደአልተጻፉ ነገር ግን የሐዋርያትን ትምህርትና ሥርዐት ይዘው ወይም ከሐዋርያት ትምህርትና ሥርዐት ጋር ተጣጥመው በተጨማሪም ሌሎችን ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ይዘው የተቀረጹ ቀኖናት መሆናቸው ተቀባይነተን አግኝቶ መገኘቱ የወል ግንዛቤ ሆኗል:: ስለዚህም ብዙ መረጃዎች ቀርበዋል[16]::

---

15. ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ... ገጽ 27::
16. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 137 - 154::



ሆኖም ግን በ2ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በ3ኛው ምዕተ ዓመት መጀመርያ አካባቢ ድረስ ነበር የተጻፉት አስተማማኝ መረጃዎች አሉ:: ከእነዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ለምሳሌ የአሌክሳንድርያ ሊቀ ጳጳሳት እለእስክንድሮስ /አለክሳንድሮስ/ /325/12.13. 14 ቀኖናትን[17]፤ ትልቁ አትናቴዎስ 13 ቀኖናትን[18]፤ ትልቁ ባስልዮስ 17፤ 25 ቀኖና ትን[19] ተጠቅመው ይገኛሉ::

ስለዚህ በአጭሩ በዚህ በተጠቀሰው ክፍለ ዘመን መጻፋቸውን መቀበሉ አስተማማኝ ነው የሚያሰኙ ብዙዎች መረጃዎች ይሰነዘራሉ:: ለዚህ የተሻለው «ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና» በዝርዝር ያቀነባበራቸው ስለሆነ ያንኑ መጽሐፍ መመለከቱ ይሆናል[20]:: 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ከላይ እንደተመለከተው በግሪክ ቋንቋ ተጽፈው ወደ ላቲን ቋንቋ መተርጎማቸው ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ የምሥራቅ ቋንቋዎች: ሱርስጥ፤ ዐረብኛ፤ ግብጽ እና ግእዝ ተተርጉመው ይገኛሉ::

### 1.2.1 የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም

ይህ ሱርስጥ ትርጉም የሚገኘው ሁለት አብያተ ክርስቲያናት /ንስጥሮሳውያትና ያዕቆባውያት አብያተ ክርስቲያናት/ ሲሆኑ በያዕቆባዊት ቤተክርስቲያን ሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም 85 ቀኖናት በመሆን ፈንታ 83 ቀኖናት ሁነው ይገኛሉ[21]:: ይህም ሊሆን የቻለበት ሁለት ወይም የበለጡ ግሪክ ቀኖናት ወደ አንድ ወይም ወደ አንዱ ቀኖናት በመሰባሰብ

---

17. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 140::
18. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 141::
19. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 139 -154::
20. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 137-166
21. Mansi: sacrorum conciliorum ... T.1 ገጽ 29 - 48::



www.ethiopianorthodox.org

በ83 ቀኖናት ሊወሰኑ ችለዋል ለምሳሌ 12 እና 13 ግሪክ ቀኖናት በሱርስጥ ትርጉም አንድ ቀኖናን /12ኛውን ቀኖና/፣ 49 እና 50 በሱርስጥ ትርጉም አንድ ቀኖናን /49ኛውን ቀኖና/ እያያዙ ሲገኙ የቅደም ተከተል ልዩነትም ይታያል[22]:: 48ኛ ቀኖናም የለም::

በንስጥሮሳዊት ቤተክርስቲያን ሐዋርያውያት ቀኖናት ሱርስጥ ትርጉም ከአንድ አንድ የተሰወኑት ለውጦች በስተቀር ከተጠቀሱት ያዕቆባዊት ቤተክርስቲያን ቀኖናት ጋር ልዩነት የላቸውም[23]:: ሆኖም በንስጥሮሳዊት ቤተክርስቲያን 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቁጥር 82 ነው[24]:: 48ኛ ቀኖናም ጎድሎ አይታይም::

## 1.2.2 የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቅብጥ ትርጉም

85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በቅብጥ ቤተሰብ ሁለት ቋንቋዎች ተባይቅና ሳዲቅ እንደሚገኙ ይታወቃል[25]::

## 1.2.3 የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ዐረብኛ ትርጉም

የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ወደ ዐረብኛ መመለሳቸው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አርእስት 83.82.81 ቁጥሮችን ይዘው ይገኛሉ[26]:: ከላይ እንደተመለከተው 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቁጥሮች እንደ ዐረብኛ ትርጉማቸው ቁጥር በመለካውያንና በያዕቆባውያን ዘንድ ሲሆን በንስጥሮስውያን ዘንድ 82 ናቸው::

## 1.2.4 የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ግእዝ ትርጉም

85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በሐዋርያት ተዘጋጅተው በቀለሚንጦስ ... እጅ የተላኩ በሚል ርእስ ግን ልዩ ልዩ

---

22. Lightfoot: St. Clement of Rome T.1 ገጽ 373 - 374፤ De lagarde: Reliquiae ...Graec. ገጽ 62 XXIX - XXX፤ ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 156 - 157::
23. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 55 -158::
24. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
25. Lightfoot: St. Clement of Rome T.1 ገጽ 342::
26. ዲበኩሉ ዘውዴ፤ ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 158 - 159::


www.ethiopianorthodox.org

የአርእስትን፣ ቅርጾችንና ቁጥሮችን ይዘው ወደ ግእዝ ቋንቋ ተመልሰው ይገኛሉ[27]::

## 1.3. ሣልሳይ ቀኖና - ሁለት መጻሕፍተ ቀኖናት

ከላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ /ረስጠአ/ ግብጻውያን በሁለት ክፍሎች/ ሁለት መጻሕፍት/ ከፍለው እንዲአሠራጩት ከእነዚህም የአንዱ ክፍል ቀኖናት ቁጥር 72 ሲሆን ትእምርተ ጥቅሱም «ረስጠብ» ዘውእቱ ቀለሚንጦስ ዳግም ማለት እንደሆነ ታይቷል[28]::

ይህም መጽሐፈ ቀኖናት «ረስጠብ» በመሠረቱ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ወይም እንደ መለካውያንና ያዕቆባውያን ዐረብኛ ትርጉም 83 ቀኖናት ወይም እንደ ንስጥሮሳውያን አሁንም ዐረብኛ ትርጉም 82 ቀኖናት /ረስጠአ/ ከሁለት ተከፍሎ የመጀመሪያው አንድ ክፍል አይደለም:: ነገር ግን ከሌሎች ልዩ ልዩ ቀኖናት 1/ ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት[29] 2/ግብጻዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ[30] እና 3/ ቀኖናት 48 - 71/63 -78/[31] ተቀነባብሮ የተቀረጸ መጽሐፈ ቀኖናት ነው::

ስለዚህም ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ከሚናገሩት 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ጋር አንድ አይደለም:: የሁለተኛው ቀኖናት ቁጥር 56 ሲሆን ትእምርተ ጥቅሱም /ረስጠጅ ዘውእቱ ቀለሚንጦስ ሣልስ - ሶስተኛ ቀለምንጦስ ማለት ነው[32]::

---

27. ዲበኩሉ ዘውዴ፤ ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 160::
28. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
29. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 168 - 181::
30. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 181 - 192::
31. ዲበኩሉ ዘወዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 192 - 196::
32. ፍትሐ ነገሥት መቅድመ ክፍል 2::

ይህ ሦስተኛ መጽሐፈ ቀኖናት ወደ አነስተኛ ቁጥሮች /ከ85 ወደ 56 ከመሰባሰቡ በስተቀር/ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉም ነው[33]::

እንግዲህ በፍትሐ ነገሥት ቅንብር ወቅት ጸሐፊው አራት /4/ ዓይነት ሐዋርያውያት ቀኖናትን 1/ 30 ቀኖናት-ሥርዓተ ጽዮንን «ዓይን» 2/82 ወይም 83 ቀኖናትን (ረስጠአ) 3/-74 ቀኖናትን /ረስጠብ/ እና 4/ 56 ቀኖናትን /ረስጠጅ/ በምንጭነት እንደተገለገለባቸው ሲታይ[34] ከእነዚህ አራት ቀኖናተ ሐዋርያት ሁለቱ ረስጠአ እና ረስጠጅ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉሞች እንደመሆናቸው መጠን የ56 ቀኖናት 56ኛው ቀኖና እና የ82 ቀኖናት የመጨረሻው 81ኛው ቀኖና በትክክል ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚደነግጉት ቀኖናት ናቸው[35]::

በአንድ በኩል እነዚህ 74 እና 56 /74+56/ 130 ቀኖናት መሆናቸው በዐረብኛ ትርጉማቸው ሲታይ[36] በሌላ በኩል በግብጻውያን ዘንድ የመጀመሪያው 71/ወይም 79/[37] ቀኖናት /በ74 ቀኖናት ፋንታ/ የሁለተኛውን 56 ቀኖናትን በመጠበቅ ሁለቱ ሲደመሩ /71+56 = 127/ 127 ቀኖናት ይሆናሉ[38]:: እነዚህም 127 ቀኖናት በዐረብኛ ቋንቋም መገኘታቸው የታወቀ ነው[39]::

33. ዲበኩሉ ዘውዴ፤ ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 102-197::
34. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
35. ከዚሁ ገጽ 91 - 100::
36. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
37. Tattam H. The apostolical constitutions or the canons of the Apostles London 1884, p. De Lagarde: Aegyptiaca .. ገጽ 209 - 281::
38. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 199::
39. J. Perierr et Augustin: Les 127 canons des ap6tres P.O.T. 8 ገጽ 551 - 710::



127 ቀኖናት ወደግእዝ ቋንቋም ተተርጉመው እንደሚገኙ ታውቋል:: የእነዚህም ቀኖናት በመጀመሪያ አርእስቶች ብቻ፣ ከዚያም ሰነዱ ከላቲን ትርጉም ጋር ታትመዋል[40]::

ቀጥሎም ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉመው ይገኛሉ[41] ሆኖም በዚህ መልክ በፍትሐ ነገሥት በምንጭነት አልተመለከቱም:: ነገር ግን ከዚህ ላይ መመልከቱ ተገቢ ሆኖ የታየው 56 ሐዋርያውያት ቀኖናትን በሚመለከት ነው::

## 2. ሲኖዶስ - መድበለ ቀኖናት

«ሲኖዶስ» የሚለው ቃል በመጀመሪያ ግሪክ /ጽርእ/ ቃል (Συνοδος) ነው[42]:: ትርጉሙ አንድ ዐቢይ ጉባኤ ወይም ስብሰባ ማለት ሲሆን በተለይ ለአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤያት ወይም ስብሰባዎች የሚሰጥ ስም ነው:: ስለዚህም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶች /ሊጳጳሳትና ሊቃነ ኤጲስቆጶሳት/ ጉባኤ ሲኖዶስ ቅዱስ ሲኖዶስ በመባል ይታወል፣ ጽሕፈት ቤቱም በዚሁ ስም ይጠራል - «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ»::

ይህም እንደተጠበቀ ሆኖ አሁንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአብያተ ክርስቲያናት ቀኖናትና መሰል ሥራዎች ተሰባስበው የሚገኙበት መዝገብ ወይም ጉባኤ ቀኖናት ወሥርዐታት «ሲኖዶስ» በመባል ይታወቃል:: መድበለ ቀኖናት ወሥርዐታት ማለት ነው:: በዚህም ብቻ ሳይሆን እየአንድአንዱ ክፍለ ቀኖናት ወይም ሥርዐታት «ሲኖዶስ»ም ይባላል ለምሳሌ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ግእዝ ትርጉሞች አራት ሲሆኑ እየአንድአንዳቸው ሲኖዶስም ይባላሉ ለምሳሌ ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን - - ረስጠጅ::

40. J. Ludolphus: Commentarius ad suam historiam Aethiopicam, Frankfurt. 1691 ገጽ 303 -314::
41. Platt T. Pell: Canones Appostolorum Aethiopici, Lipsiae 1871.
42. ዲበኩሉ ዘውዴ:: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 12 የግርጌ ማስታወሻ 175 - 176::



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ሲኖዶስ በዚህ መልኩ በተለያዩ የእጅ ጽሑፎች ሲገኝ እስከ አሁን ግን ለኅትመት አልበቃም።

ስለዚህም እኔ በዚህ ጽሑፍ ለመጠቀም የቻልኩት በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር የሚገኝ አንድ የእጅ ጽሑፍን ነው።

ከዚህም የተነሳ ወደ ኋላም ሆነ ወደፊት በዚህ ጽሑፍ በየቦታው ለሚጠቀሱትና ለተጠቀሱት ቀኖናት በምንጭነት «ሲኖዶስ» ተብሎ' ስሞች፣ ምዕራፎች፣ ቁጥሮች፣ ገጾች፣ ወዘተ. ተመልክተው የሚገኙበት ይህ ሲኖዶስ - የእጅ ጽሑፍ ነው።

ስለዚህም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ከያዛቸው የአብያተ ክርስቲያናት ቀኖናት መካከል ከላይ እንደተመለከትነው ለፍትሐ ነገሥት ቅንብር በምንጭነት ያገለገሉት አራት «ሐዋርያውያት ቀኖናት» ወይም ቀኖናተ ሐዋርያት» በቅድሚያ የሚገኙባቸው ሲሆኑ ግን በተለያዩ ርእሶች ተቀርጸውና በአንጻራቸውም በተለያዩ ቁጥሮች ተከፋፍለው ነው የሚገኙት።

በተለይ በፍትሐ ነገሥት «ረስጠብ» በሚልም ምንጻረ ቃል የሚታወቁት 71 /72 ወይም 74 ወይም 78 ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት /Canones ecclesiastici/ ወይም ቀኖናት ዘአበው ሐዋርያት ተቀርጸው ሲገኙ ሌሎች ሁለቱ ቀኖናት - ረስጠአና ረስጠጅ እንደገና ሁለቱ ወደ አራት ተባዝተው ተቀድተውና የተለያዩ ርእሶችንና ቁጥሮችን ይዘው ይገኛሉ።

ስለዚህ በአራት ቅርጾች በአንጻሩ የሚከተሉትን ቁጥሮች 56፣ 82፣ 81 እና 80 ይዘው ይገኛሉ። ከዐረብኛ ወደ ግእዝ እንደተተረጎሙ ሲታመን ከቁጥር 56 በስተቀር ሌሎቹ 3ቱ ቀኖናት፡ ቁጥሮች 82፣ 81 እና 80 አንድ ወይም ሁለት ናቸው። ከአራቱ ቀኖናት ቁጥሮች ሁለቱ ቁጥሮች፡ ቀኖና 56 እና ቀኖና 82 ቀኖናት ለፍትሐ ነገሥት በምንጭነት እንደአገለገሉ የተጠቀሱ ሲሆን[43] ሁለቱ ቀኖናት ቁጥሮች - 81 እና 80 አልተመለከቷም በሌላ በኩል ግን ተደጋግሞ በተጠቀሰው የቤተክርስቲያን መድበለ ቀኖናት በ«ሲኖዶስ» አራቱ አሁንም በተለያየ መልክ ተቀርጸው ይገኛሉ ማለት ነው። የቁጥር ልዩነቶችም ይታያሉ ግን ከእጅ ጽሑፍ ግልባጭ ስህተት ሊኖር ይችላል የሚል ግምት አለ።

85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በመሠረቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በፍትሐ ነገሥት መሠረት ይበልጥ ረስጠአ፣ ረስጠጅ[44] ወይም በሲኖዶስ አብጠሊሳት ወይም አብጠሊስ በመባል በተለያዩ ስሞች ሲጠሩ መቻላቸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን በነዶቹ በተያዙበት ሰነድ «ሲኖዶስ» ብሎ በመነሳትና ከዚያም ልዩ ልዩ ቅጽሎችንና ዘርፎችን በማስከተል ይገኛሉ። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

1 «ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ዘወሀብዎ ሐዋርያት በእደ ቀለሚንጦስ ዘለአክዎ ቀዲሙ ትእዛዝ 57 = ሐዋርያት አስቀድመው በላኩት ቀለሚንጦስ እጅ የሰጧት የቤተክ ርስቲያን ሲኖዶስ እሷም 57 ትእዛዝ»[45]

2 ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን ዘዜነወ ቀለሚንጦስ በእንተ ጴጥሮስ /ወ/ መምህሩ... ወትልቆሙ 82 አብጠሊሳት = የቅዱሳን ሐዋርያትሲኖዶስ እሷም ቀለሚንጦስ ስለ መምህሩ ጴጥሮስ ሆኖ ያበሰራት - የጻፋት አብጠሊሳት ተብላ ትጠራለች። ቁጥርዋም 82 «አብጠሊሳት»[46]

3 ሥርዐተ ሐዋርያት ምስለ ቀለሚንጦስ ዘተፈነወ ለሕዝብ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ 80 = ሕገ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ በቀለሚንጦስ እጅ ለአሕዛብ የተላከ ሥርዐተ ሐዋርያት-ትእዛዝ 80 [47]

---

43. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል2፣ ዲበኩሉ ዘውዴ፡ ፍትሐ ነገሥት፡ ብሔረ ሕግ ወቀኖና፡ ረስጠአ ገጽ 137 - 166፣ ረስጠጅ ገጽ 197 -200።

44. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2።
45. ሲኖዶስ ገጽ 41 - 48።
46. ሲኖዶስ ገጽ 58 - 70።
47. ሲኖዶስ ገጽ 81 - 86።



www.ethiopianorthodox.org

4 ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን ዘሀገረ ቀለሚንጦስ ወይእቲ ትሰመይ አብጠሊስ = የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስ እሷም አብጠሊስ ተብላ የምትጠራ 81 ቀኖናት[48]

ሐዋርያውያት ቀኖናት ወደ ግእዝ ቋንቋ መተርጎማቸው ሲታወቅ ግን በተለያዩ ቅርጾችና ቁጥሮች፣ ስሞችም መመልከታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በፍትሐ ነገሥት ረስጠአ እና ረስጠጅ /ብዙ ጊዜ በስሕተት ረስጠብ/ በሚል ምኅጻረ ቃላት ይገኛሉ[49]:: ሁሉንም በፍትሐ ነገሥት ብሔረ፡ ሕግ ወቀኖና «በዝርዝር የተጻፉ ስለሆነ ያኑን የመድገሙ አስፈላጊነት አይታይም[50]:: ወደፊት ግን አንድም ከእናቱ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ጋርም ሆነ በመካከላቸው ያለውን ልዩነትና ተመሳሳይነት ለማመልከት ይሞክራል[51]::

## 2.1 ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን -ትእዛዛት 56/57/

ብዚህ ስም-ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን - ትእዛዝት 57 ተብለው የሚጠሩት ሐዋርያውያት ቀኖናት ቁጥር 57 ሲሆን የ56ኛው /የ85 ግሪክ ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛው ቀኖና ግልባጭ/ ይዘት የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ነው::

### ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. መጻሕፍተ ሙሴ/5ቱ መጻሕፍተ ሙሴ -አምስቱ ብሔረ ኦሪት/
1.1 ዘፍጥረት
1.2 ዘጸአት
1.3 ዘሌዋውያን
1.4 ዘኁልቁ
1.5 ዘዳግም
2. ሕግ ዘኢያሱ ወልደ ነዌ
3. ዘመሳፍንት
4. ዘሩት
5. መጻሕፍት ዘነገሥት 4
5.1 መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ
5.2 መጽሐፈ ነገሥት 2ኛ
5.3 መጽሐፈ ነገሥት 3ኛ
5.4 መጽሐፈ ነገሥት 4ኛ
6. ትሩፋተ ነገሥት 2
6.1 ትሩፋተ ነገሥት /ተረፈ ነገሥት/ 1ኛ
6.2 ትሩፋተ ነገሥት/ተረፈ ነገሥት/2ኛ
7. መጻሕፍተ ዕዝራ 2
7.1 መጽሐፈ ዕዝራ 1ኛ
7.2 መሐፈ ዕዝራ 2ኛ
8. መጽሐፈ ኢዮብ
9. መጽሐፈ አስቴር
10. መጽሐፈ ጦቢት
11. መክብብ/ያለቦታው/
12. ተግሣጽ/ያለቦታው/[52]
13. መዝሙረ ዳዊት 150
14. ምሳሌያተ ሰሎሞን
15. ማሕልየ መሓልይ
16. 12 ንዑሳን ነቢያት /ደቂቀ ነቢያት/
(16.1 ትንቢተ ሆሴዕ
16.2 ትንቢተ አሞጽ
16.3 ትንቢተ ሚክያስ
16.4 ትንቢተ ኢዩኤል
16.5 ትንቢተ አብድዩ
16.6 ትንቢተ ዮናስ
16.7 ትንቢተ ናሆም
16.8 ትንቢተ ዕንባቆም
16.9 ትንቢተ ሶፎንያስ
16.10 ትንቢተ ዘካርያስ
16.11 ትንቢተ ሐጌ
16.12 ትንቢተ ሚልክያስ)
17. 4 ዐበይት ነቢያት
17.1 ትንቢተ ኢሳይያስ
17.2 ትንቢተ ኤርምያስ
17.3 ትንቢተ ዳንኤል

---

48. ሲኖዶስ ገጽ 87 -86::
49. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ቁ. 15::
50. ዲበኩሉ ዘውዴ፡ ፍትሐ ነገሥት፡ ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 137 - 166 197 - 200::
51. ከዚሁ ገጽ 129-132::

52. ተግሣጽ የምሳሌ ሰሎሞን ምዕራፍ 25 - 31 ሲሆን በግእዝ ይህን ስም ይዞ ተቀርጽዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገ ጽ 905 - 921::



www.ethiopianorthodox.org

17.4 ትንቢተ ሕዝቅኤል[53]
18. ጥበበ ሰሎሞን መጽሐፍ
በእንተ ሕፃናት
19. መጻሕፍተ መቃብያን 2[54]
19.1 መጽሐፈ መቃብያን 1ኛ
19.2 መጽሐፈ መቃብያን 2ኛ
20. ጥበበ ኢያሱ ወልደ
ሲራክ - ዐቢይ ትምህርት
21. መጽሐፈ ዮዲት
22. መጽሐፈ ኩፋሌ[55]
የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት
ድምር 46
ለ. የሐዲስ ኪዳን
መጻሕፍት
1. አርበዕቱ ወንጌላት
1.1 የማቴዎስ ወንጌል
1.2 የማርቆስ ወንጌል
1.3 የሉቃስ ወንጌል
1.4 የዮሐንስ ወንጌል
2. መልእክታተ ሐዋርያት 7
2.1 መልእክተ ጴጥሮስ 1ኛ
2.2 መልእክተ ጴጥሮስ 2ኛ
2.3 መልእክተ ዮሐንስ 1ኛ
2.4 መልእክተ ዮሐንስ 2ኛ
2.5 መልእክተ ዮሐንስ 3ኛ
2.6 መልእክተ ያዕቆብ
2.7 መልእክተ ይሁዳ
3. ግብረ ሐዋርያት
4. መልእክታተ ጳውሎስ 14
4.1 ወደ ሮሜ ሰዎች
4.2 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
4.3 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
4.4 ወደ ገላትያ ሰዎች
4.5 ወደ ኤፌሶን ሰዎች
4.6 ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
4.7 ወደ ቆላስይስ ሰዎች
4.8 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
4.9 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
4.10. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
4.11 ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
4.12 ወደ ቲቶ


53. ሕዝቅኤልና ዳንኤል በተራ ተዘዋውረዋል::
54. መጻሕፍተ መቃብያን በግሪክ ቋንቋ በአባሪነት የተያዘውን ጨምሮ አራት ሲሆኑ በዚህ ትርጉማቸው ግን ሁለት ሁነው ተቀምጠዋል:: ተራቸውም ከአስቴር ቀጥሎ ነው::
55. መጽሐፈ ኩፋሌ ወደፊት እንደ ምንመለከተው በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አይገኝም:: ከዚህ ገጽ 197-199 ::




4.13 ወደ ፊልሞና
4.14 ወደ ዕብራውያን
5. አቡቀለምሲስ ዘውእቱ ራእየ
ዮሐንስ 55
6. መልእክታተ ቀለሚንጦስና
ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት
-ትእዛዛት[56]
6.1 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 1ኛ
6.2 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 2ኛ
6.3 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 3ኛ
6.4 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 4ኛ
6.5 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 5ኛ
6.6 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 6ኛ
6.7 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 7ኛ
6.8 ትእዛዘ ቀለሚንጦስ 8ኛ


የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 37 ነው:: ስለዚህም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 46+35=81::

2.1 «ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን ዘጸሐፈ - ዘዜነወ ቀለሚንጦስ በእንተ ጴጥሮስ (ወ) መምህሩ ወይእቲ ትሰመይ አብጠሊሳት ወትልቆሙ 82 አብጠሊሳት» «የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስ እሷም ቀለሚንጦስ ስለ መምህሩ (እና) ጴጥሮስ የጻፋትና አብጠሊሳት ተብላ የምትጠራውና ቁጥራቸውም 82 የሆን»

አብጠሊስ 82 «ሀሎ በፍትሐ ነገሥት» ብሎ የሚጀምረው ሌላው የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ግእዝ ትርጉም ነው:: እነዚህ ቀኖናት ከ85 በ82 ወይም 81

55. አቡቀለሚሲስ (ʼAnokaλυψιs) በግሪክ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና አልተመለከተም:: ግን በቀኖናት ዘካርታጌኒስ (ቅርጣግና) 24ኛ/32ኛ ቀኖና እና በ39ኛ መልእክተ አትናቴዎስ በአንድ አንዶች ደግሞ በቀኖና አምፊሎኪዮስ ተይዞ እንደሚገኝ ሲታወቅ በዚህ ሲኖዶስ ሊያዝ ችሏል::
56. በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና መልእክታተ ቀለሚንጦስ የሚባሉት ሁለት መልእክታት ሲሆኑ ስምንቱ መጻሕፍት ግን ትእዛዛት ነው የተባሉት:: በዚህ ቀኖና ሁለቱ መልእክታተ ቀለሚንጦስ አልተወሰኑም::



www.ethiopianorthodox.org

ቀኖናት ሲወሰኑ አብጠሊሳት ተብለውም ተሰይመዋል[57]:: አብጠሊስ በፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና እንደ ተመለከተው[58] አብጠሊሳት - አፖስቶሎስ /Ἀπόστολος/ ሐዋርያ ወይም የተሻለ አፖስቶሊ/Ἀπόστολοι / ሐዋርያት የሚለው ግሪክኛ ቃል እንደ አለም ባይሆን ተወስዶ ነው:: ትርጉሙ በሲኖዶስ ቀኖና ነው ተብሏል:: አብጠሊስ ከተጥላሳት ጋር አንድ መሆኑም ተመልክቷል:: በመሠረቱ «ጠስ» ተጥላሳት ዐረብኛ እተጣለሳት ከላቲን ቃል ቲትሉን ወይም ወደ ግሪክ ቋንቋ በተወሰደ መልኩ ቲትሎስ/ቴትሊ ሲበዛ/ መሆኑ ሲደገፍ ተጥላሳት ከቲትሉ ወይም ቲትሎስ(TITλOS) - ቲትሊ (TITλOI) መውሰዱ ሊያከራክር ባይችልም አብጠሊሳት ግን ከአፖስትሎስ - አፖስቶሊ መወሰዱ ከቅርጹ ብቻ ሳይሆን ከይዘቱም አንጻር ነው ሊደገፍ የሚችለው::

ስለዚህ ትርጉሙ ሐዋርያውያት ቀኖናት ማለት ሆኖ ይገኛል:: በሲኖዶስ 3ኛው መጽሐፍ ሆኖ መገኘቱ ሲመለከት ግጽው ወሥርዐት ወአብጠሊስ ወይም /ረስጠጅ/ ዘውእቱ ቀለሚንጦስ ሣልስ[59]፣ ነገር ግን በፍትሐ ነገሥት ረስጠጅ ቀኖናተ ሐዋርያት ሣልስ ሆኖ የሚታወቀው ከላይ የተጠቀሱትን 57/56/ ቀኖናት የያዘው መጽሐፈ ቀኖናት ነው[60]::

በሌላ በኩል «ሰመዝ መሐሩነ ሐዋርያት በአብጠሊሶሙ»[61] ሲል አሁንም መጽሐፈ ቅዳሴን ስመንለከት ሐዋርያውያት ቀኖናት - ሲኖዶሳት ተብለው ተተርጉመው ነው

57. ሲኖዶስ ገጽ 58 - 70::
58. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 137 - 166::
59. ሲኖዶስ ገጽ 41 - 48::
60. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
61. መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝና አማርኛ 1942 ምዕራፍ 3 ሚመጠን ግርምት ቁጥር 3 ገጽ 12::



የምናገኘው:: [illegible] መሆኑን ፍካሬ አብጠሊስ አው ተጥላሳት ቀኖና ውእቱ በልሳነ ጽርእ ብሎ የሚገኘው ሲኖዶሳዊ ጥቅስ ያመለክታል[62]::

በአጭሩ ሁለቱም ቃላት /አብጠሊሳትና ተጥላሳት/ አንድ ናቸው ብሎ መተው ሊደገፍ የሚችል አይደለም:: ይህም ማለት በፍትሐ ነገሥቱ የቀኖናተ ነገሥት የመጀመሪያው መጽሐፍ አብጠሊስ ወይም ተጥላሳት «ጠስ» በሚል ምኅጻረ ቃል 40 አንቀጾችን ይዞ የሚገኘው በቢዛንቲን ንጉሠ ነገሥት ባስልዮስ ቀዳማዊ ዘመቄዶንያ /870 - 879/ የታወጀ መጽሐፈ ሕግ /Proheiros Nomos - πρόχειρος Nómos / ነው[63]::

ከዚህ በላይ ተጥላሳት የቴትሎስ ወይም ቴትሊ ግልባጭ ነው ሲባል ይደገፋል ምክንያቱም የዚህ መጽሐፍ-(Procheiros Nomos) ክፍፍል በቲትሎስ ወይም ቲትሊ ነው ማለትም ምዕራፍ አንድ ወይም አንቀጽ አንድ በማለት ፋንታ ቲትሎስ አንድ፣ ቲትሎስ ሁለት እያለ ነው የሚገኘው:: በሌላ በኩል አብጠሊስ ከቲትሎስ ሊወለድ አይችልም ለማለት የሚያስችለው ነጥብ አብ - /አብ/ጠሊስ/ ከየት መጣ? የሚል ጥያቄን ስለሚያስከትል ነው:: ነገር ግን ከላይ የተመለከተው አብጠሊስ- አብጠሊሳት ከአፖስቶሎስ - አፖስቶሊ ነው የመጣው የሚለው አስተሳሰብም ቢሆን የግድ ሊቆም አይችልም ምክንያቱም ብዙ የግሪክ ቃላት ወደ ግእዝ ሲመለሱ/ወደ ዐረብኛም ሊሆን ይችል ይሆናል/ « አ» እየተጨመረባቸው ይገኛሉ ለምሳሌ ግብረ ሐዋርያት በግሪክ ቋንቋ - በተጻፈበት ቋንቋ «ፕራክሲስ ቶን አፖስቶሎን» የሚባል ሲሆን በግእዝ «አብረክሲስ» ሲል ነው የሚገኘው[64]:: በዚህ መልክ አብጠሊስንም ከቲትሎስ ጋር ማያያዝ ይቻላል:: የእነዚህ

62. ሲኖዶስ ገጽ 58 - 70::
63. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 290::
64. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::



www.ethiopianorthodox.org

ቀኖናት ስያሜ በአብጠሊሳት ብቻ ሳይቆም ትእዛዛትም ቀኖናትም እንደሚባሉ ሲነገር ቁጥራቸው 82 ወይም 81 መሆኑንም ይገለጣል[65]::

«ምእመናን እነዚህን መጻሕፍት ይጠብቁ:: በክርስቶስ /ስም/ ለምእመናን ያዘዝናቸው የቤተ ክርስቲያን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስሞች የሚከተሉት ናቸው::

እነዚህም መጻሕፍት ከእግዜአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የወረዱ መጻሐፍተ ዜና ሲሆኑ እነሱም ትእዛዝ /ትእዛዛት/ ይባላሉ:: ቁጥራቸውም 81 መጻሕፍት ናቸው። የመጀመሪያዋ ኦሪት ስትሆን እሷም 8 ብሔር ናት::

1. አንደኛ ብሔረ ኦሪት ዘፍጥረት
2. ጸአተ ደቂቀ እስራኤል እምግብጽ - ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኁልቈ
5. ዘዳግም
7. ዘመሳፍንት
8. ዘሩት
9. ኩፋሌ[66]
10. ነገሥት /4 ብሔር/
11.1 ነገሥት 1ኛ
11.2 ነገሥት 2ኛ
12. መጻሕፍተ ዕዝራ-2 ብሔር
12.1 መጽሐፈ ዕዝራ 1ኛ
12.2 መጽሐፈ ዕዝራ 2ኛ
13. መጽሐፈ ኢዮብ
14. መዝሙረ ዳዊት
15. መጻሕፍተ ሰሎሞን 5 /ስማቸው አልተጠቀሰም/ ቢሆንም)
15.1 ምሳሌያተ ሰሎሞን
15.2 መክብብ
15.3 ማሕልየ ማሓልይ
15.4 ጥበበ ሰሎሞን
15.5 ተግሣጽ[68]
16. 4 ዐበይት ነቢያት
16.1 ትንቢተ ኢሳይያስ
16.2 ትንቢተ ኤርምያስ
16.3 ትንቢተ ሕዝቅኤል
16.4 ትንቢተ ዳንኤል
17. 12 ንኡሳን ነቢያት /ደቂቀ ነቢያት/
17.1 ትንቢተ ሆሴዕ
17.2 ትንቢተ አሞጽ
17.3 ትንቢተ ሚክያስ
17.4 ትንቢተ ኢዩኤል
17.5 ትንቢተ አብድዩ
17.6 ትንቢተ ዮናስ
17.7 ትንቢተ ናሆም
17.9 ትንቢተ ሶፎንያስ
17.10 ትንቢተ ሐጌ
7.11 ትንቢተ ዘካርያስ
17.12 ትንቢተ ሚልክያስ
18. መጽሐፈ ዮዲት[69]
19. መጽሐፈ ጦቢት[70]
20. መጽሐፈ አስቴር
21.መጽሐፈ መቃብያን(አንድ መቃብያን)[71]
22. መጽሐፈ ሲራክ[72]

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ድምር 45

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር

1. አርባዕቱ የወንጌላት
1.1 የማቴዎስ ወንጌል
1.2 የማርቆስ ወንጌል
1.3 የሉቃስ ወንጌል

---

65. ሲኖዶስ ገጽ 58፣ ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2 አንቀጽ 2 ቁጥር 15::

66. መጽሐፈ ኩፋሌ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖና 85ኛ ቀኖና አልተመዘገበም:: ታዲያ ለምን ከዚህ ተቀዳ? ወደፊት እንመለከተዋለን:: ከዚሁ ገጽ 169-170::

67. ጥበበ ሰሎሞን በ85 ሐዋርያውያት ቀኖና 85ኛ ቀኖና የለም:: ታዲያ እንዴት ከዚህ ሊሰፍር ቻለ? ወደፊት እንመለከተዋለን::

68. ስለ ተግሣጽ በአለፈው ተገልጽዋል:: ቁጥር አምስትን ለማሟላት ይመስላል::

69. መጽሐፈ ዮዲት በ85 ሐዋርያውያት ቀኖና 85ኛ ቀኖና ስለአልተመለከተም እንዴትስ ተገኝቶ ከዚሁ ተያዘ? ወደፊት ይታያል::

70. መጽሐፈ ጦቢት በ85 ሐዋርያውያት 85ኛ ቀኖና አልሰፈረም:: ታዲያ እንዴት ከዚህ ተገለጠ? ይህም ወደፊት ይታያል::

71. በ85 ሐዋርያውያት 85ኛ ቀኖና የተመለከቱት «ሐቡራትና ቅዱሳት» 3 መጻሕፍተ መቃብያን ሳይሆኑ አንድ መቃብያን ብቻ ተመልክቷል::

72 መጽሐፈ ሲራክ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖና 85ኛ ቀኖና «ሐቡራትና ቅዱሳት መጽሐፍት» ውጪ ሆኖ ነው ተመልክቶ የሚገኘው::



www.ethiopianorthodox.org

1.4 የዮሐንስ ወንጌል

2 ግብረ ሐዋርያት

3. መልእክታተ ሐዋርያት 7

3.3 መልእክተ ጴጥሮስ 2

3.2.1 መልእክተ ጴጥሮስ 1ኛ

3.2.2 መልእክተ ጴጥሮስ 2ኛ

3.3 መልእክተ ዮሐንስ 3

3.3.1 መልእክተ ዮሐንስ 1ኛ

3.3.2 መልእክተ ዮሐንስ 3ኛ

3.3.3 መልእክተ ዮሐንስ 3ኛ

3.4 መልእክተ ያዕቆብ

3.5 መልእክተ ይሁዳ

3.6 14 መልእክታተ ጳውሎስ

3.6.1 ወደ ሮሜ ሰዎች

3.6.2 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ

3.6.3 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ

3.6.4 ወደ ገላትያ ሰዎች

3.6.5 ወደ ኤፌሶን ሰዎች

3.6.6 ወደ ፊሊጵስዩስ ሰዎች

3.6.7 ወደ ቆላስይስ ሰዎች

3.6.8 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ

3.6.9 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ

3.6.10 ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች 1ኛ

3.6.11 ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች 2ኛ

3.6.12 ወደ ቲቶ

3.6.13 ወደ ፊልሞና

3.6.14 ወደ ዕብራውያን

4. አቡቀለምሲስ

5. ሰመንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ

(ሰመንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ)

5.1 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 1ኛ

5.2 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 2ኛ

5.3 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 3ኛ

5.4 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 4ኛ

5.5 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 5ኛ

5.6 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 6ኛ

5.7 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 7ኛ

5.8 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 8ኛ

5.9 መልእክተ ቀለሚንጦስ 9ኛ[73]

---

73. በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስ ሲመለከቱ በዚህ ቀኖና ግን አንድ መልእክተ ቀለሚንጦስ ብቻ የተመለከተ ይመስላል ግልጥ ባለመሆኑ:: ወደፊት እንደምንመለከተው 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ - ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን(ረስጠጅ) መልእክታት ተብለው እንደተጠሩ ሁሉ ምንአልባት ከዚህም ላይ ትእዛዛትን በነጠላም እንኳን ቢሆን መልእክት ለማለት ፈልጎ ሲሆንም ስለሚችል መጽሐፈ(መጻሕፍተ) ቃለሚንጠስንና መልእክተ (መልእክታተ) ቃለሚንጠስን መለየቱ ግድ ይሆናል::



የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር 35(ወይም [illegible]

የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት ድምር 45+36=81 ወይም 46+35 = 81 ሲሆን ከአለፈው ጋር ሲተያይ የአሐዝ ልዩነት የለውም[74]:: በሌላም በኩል ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛው ቀኖና ዝርዝር የበለጠ 2 ወይም 3 ቁጥርን ይዞ ይገኛል::

## 2..3.: «ሥርዐተ - ቀኖናተ ሐዋርያት ምስለ ቀለሚንጦስ ዘተፈነወ ለአሕዛብ ሕገ ቤተክርስቲያን =ትእዛዝ 80» «በቀለሚንጦስ እጅ ለአሕዛብ ሕገ ቤተክርስቲያን ሆኖ የተላከው ሥርዐተ ሐዋርያት- ትእዛዝ 80»

የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ሦስተኛው ግእዝ ሰነድ ሥርዐተ ሐዋርያት ምስለ ቀለሚንጦስ ዘተፈነወ ለአሕዛብ ሕገ ቤተ ክርስቲያን[75] = በቀለሚንጦስ /ከቀለሚንጦስ ጋር/ ለአሕዛብ የተላከው ሥርዐተ ሐዋርያት - ሕገቤተክርስቲያን ትእዛዘ 80 ተብሎ የሚገኘው ነው[76]::

ሲጀምርም - ሲደረድርም ያለ ሕጋውያት መጻሕፍት - በሕግ ከተወሰኑት መጻሕፍት በስተቀር በቤተ ክርስቲያን ሌላ መዝሙርን መዘመር ወይም ሌላ መጽሐፍን ማንበብ እንደማይገባ ነገር ግን በሕግ ሐዲስና ትካት - ብሉይ ሥርዐት መሠረት መነበብና የዓለም ሥራዎችም መገለጥ የሚኖርባቸው መጻሕፍት:

---

74. በሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን (ረስጠጅ) ሁለት መቃብያን ተይዘው ሲገኙ በሲኖዶስ ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት (ረስጠአ) አንድ መቃብያን ብቻ ተይዞ ግን አንድ መልእክተ ቀለሚንጦስም በግልጥም ባይሆን ተመዝግቦ በመገኘቱ የቁጥር (81) ተመሳሳይነት ይታያል::

75. ሲኖዶስ የሚለው ቃል በሥርዐት ተተክቷል::

76. ሲኖዶስ ገጽ 81 - 86::



www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው ትእዛዝ እሱም /አሷም /አሪት ብሔር/ / ሰምንቱ ብሔረ ኦሪት/

1. ዘፍጥረት
2.. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኁልቁ
5. ዘዳግም
6. ዘኢያሱ
7. መሳፍንት
8. ሩት
9. መጻሕፍተ ነገሥት 4
9.1 መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ
9.2 መጽሐፈ ነገሥት 2ኛ
9.3 መጽሐፈ ነገሥት 3ኛ
9.4 መጽሐፈ ነገሥት 4ኛ
10. ሕጹጻን መጻሕፍት(ትሩፋት)-2
10.1 መጽሐፈ ሕጹጻን 1ኛ/ ትሩፋት/
10.2 መጽሐፈ ሕጹጻን 2ኛ/ትሩፋት/
11. መጻሕፍተ ዕዝራ 2
11.1 መጽሐፈ ዕዝራ 1ኛ
11.2 መጽሐፈ ዕዝራ 2ኛ
12. መዝሙረ ዳዊት 150
13. መጻሕፍተ ሰሎሞን - 3
13.1 ምሳሌ ሰሎሞን
13.2 መክብብ
13.3 ማሕልየ መሓልይ
14. መጽሐፈ ኢዮብ[77]
15. 12 ንዑሳን ነቢያት - ደቂቀ ነቢያት
(15.1 ትንቢተ ሆሴዕ
15.2 ትንቢተ አሞጽ
15.3 ትንቢተ ሚክያስ
15.4 ትንቢተ ኢዩኤል
15.5 ትንቢተ ዮናስ
15.6 ትንቢተ አብድዩ
15.7 ትንቢተ ናሆም
15.8 ትንቢተ ዕንባቆም
15.9 ትንቢተ ሶፎንያስ
15.10 ትንቢተ ሐጌ
15.11 ትንቢተ ዘካርያስ

77. መጽሐፈ ኢዮብ ተራውን ለቋል።



15.12 ትንቢተ ሚልክያስ)
16. 4 ዐበይት ነቢያት
16.1 ትንቢተ ኢሳይያስ
16.2 ትንቢተ ኤርምያስ
16.3 ትንቢተ ሕዝቅኤል
16.4 ትንቢተ ዳንኤል
የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ድምር 37[78]
ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት
1. አርባዕቱ ወንጌላት
(1.1 የማቴዎስ ወንጌል
1.2 የማርቆስ ወንጌል
1.3 የሉቃስ ወንጌል
1.4 የዮሐንስ ወንጌል)
2. ግብረ ሐዋርያት
3. መልእክታተ ሐዋርያት
3.1 መልእክታተ ጴጥሮስ 2
3.1.1 መልእክተ ጴጥሮስ 1ኛ
3.1.2 መልእክተ ጴጥሮስ 2ኛ
3.2 መልእክታተ ዮሐንስ 3
3.2.1 መልእክተ ዮሐንስ 1ኛ
3.2.2 መልእክተ ዮሐንስ 2ኛ
3.2.3 መልእክተ ዮሐንስ 3ኛ
3.3 መልእክተ ያዕቆብ
3.4 መልእክተ ይሁዳ
4. መልእክታተ ጳውሎስ 14
4.1 ወደ ሮሜ ሰዎች
4.2 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
4.3 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
4.4 ወደ ገላትያ ሰዎች
4..5 ወደ ኤፌሶን ሰዎች
4.6 ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
4.7 ወደ ቆላስይስ ሰዎች
4.8 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
4.9 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
4.10 ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
4.11 ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
4.12 ወደ ቲቶ
4.13 ወደ ፊልሞና
4.14 ወደ ዕብራውያን
የሐዲስ መጻሕፍት ድምር 26

78. መጽሐፈ ከፋሌ በዚህ ቀኖና ተዘሏል። በ85 ሐዋርያውያት ቀኖና 85ኛ ቀኖና አለመኖሩንም እናስታውሳለን።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ቀኖና - ሥርዐተ ሐዋርያት አቡቀለምሲስ - ራእየ ዮሐንስ አልተመዘገበም:: ምክንያቱም በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ባለመኖሩ ሊሆን ይችላል:: ግን ደግሞ በእነዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስና ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ - ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ተመዝግበው እንደሚገኙ እየታወቀ አልተወሰዱም:: ስለዚህ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር: የብሉይ ኪዳን 37 እና የሐዲስ ኪዳን 26 መጻሕፍት (37+26=63) 63 መጽሐፍት ናቸው::

## 2.4. «ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያውያት ቅዱሳን ዘሀገረ ቀለሚንጦስ ወይእቲ ትሰመይ አብጠሊስ=የቅዱሳን ሐዋርያት . . . ሲኖዶስ እሷም «አብጠሊስ» ተብላ የምትጠራ[79] ቁጥሯም 81 ቀኖናት[80]»

ከ81 ቀኖናት 80ኛው ቀኖና ስለ ብሉይና ሐዲስ መጻሕፍትና ስለ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ስሞችና ቁጥራቸውም 81 ስለመሆኑ ቀጥሎ ይታያል::

1. 8 ብሔረ ኦሪት
1.1 ዘፍጥረት
1.2 ዘጸአት
1.3 ዘሌዋውያን
1.4 ዘኁልቁ
1.5 ዘዳግም
2. ዘኢያሱ ወልደ ነዌ 6ኛ
3. ዘ መሳፍንት 7ኛ
4. ዘሩት 8ኛ
5. መጽሐፈ ኩፋሌ[81]
6. መጻሕፍተ ነገሥት 4 ብሔራት
6.1 መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ
6.2 መጽሐፈ ነገሥት 2ኛ
6.3 መጽሐፈ ነገሥት 3ኛ

---

79. ስለ «አብጠሊስ» በሁለተኛው ቀኖና የታተተ ስለሆነ ያንኑ መመልከት በቂ ሊሆን ይችላል:: ከዚሁ ገጽ 94 - 97::
80. ሲኖዶስ ገጽ 87 - 98
81. መጽሐፈ ኩፋሌ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ሳይመዘገብ በዚህ ቀኖና ግን ተመዝግቦ ይገኛል: ጥያቄው_ያው ጥያቄ ነው::



6.4 መጽሐፈ ነገሥት 4ኛ
7. ትሩፋተ ነገሥት 2
7.1 ትሩፋተ ነገሥት 1ኛ
7.2 ትሩፋተ ነገሥት 2ኛ
8. መጻሕፍተ ዕዝራ-2 ብሔር
8.1 መጽሐፈ ዕዝራ 1ኛ
8.2 መጽሐፈ ዕዝራ 2ኛ/
9. መጽሐፈ ኢዮብ
10. መዝሙረ ዳዊት
11. መጻሕፍተ ሰሎሞን 5
11. 1 ምሳሌያተ ሰሎሞን
11.2 መክብብ ዘሰሎሞን
11.3 ማሕልየ መሓልይ ዘሰሎሞን
11.4 ጥበበ ሰሎሞን[82]
11.5 ተግሣጽ[83]
12. 4 ዐበይት ነቢያት
12.1 ትንቢተ ኢሳይያስ
12.2 ትንቢተ ኤርምያስ
12.3 ትንቢተ ሕዝቅኤል
12.4 ትንቢተ ዳንኤል
13. 12 ንዑሳን ነቢያት /ደቂቀ ነቢያት/
13.1 ትንቢተ ሆሴዕ
13.2 ትንቢተ አሞጽ
13.3 ትንቢተ ሚክያስ
13.4 ትንቢተ ኢዩኤል
13.5 ትንቢተ አብድዩ
13.6 ትንቢተ ዮናስ
13.7 ትንቢተ ናሆም
13.8 ትንቢተ ዕንባቆም
13.9 ትንቢተ ሶፎንያስ
13.10 ትንቢተ ዘካርያስ
13.11 ትንቢተ ሐጌ
13.12 ትንቢተ ሚልክያስ
14. መጽሐፈ ዮዲት[84]
15. መጽሐፈ ጦቢት[85]

---

82 ጥበበ ሰሎሞን በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ሳይመዘገብ አሁንም በዚህ ቀኖና ተመዝግቧል::
83. ስለ ተግሣጽም ቢሆን እንደተገለጸው ወደፊት ይታያል፤ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና አይታይም::
84. መጽሐፈ ዮዲት::
85. መጽሐፈ ጦቢት /ጦቢያ/ እንደተመለከተው በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ባይመለከትም ቅሉ በዚህ ቀኖና ተመዝግቧል::

www.ethiopianorthodox.org

16. መጽሐፈ አስቴር
17. መጻሕፍተ መቃብያን 2[86]
17.1 መጽሐፈ መቃብያን 1ኛ
17.2 መጽሐፈ መቃብያን 2ኛ
18. ጥበበ ሲራክ[87]

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ድምር 46

ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. አርባዕቱ ወንጌላት
1.1 የማቴዎስ ወንጌል
1.2 የማርቆስ ወንጌል
1.3 የሉቃስ ወንጌል
1.4 የዮሐንስ ወንጌል
2. ግብረ ሐዋርያት ወመልእክታት 7
2.1 ግብረ ሐዋርያት
2.2 መልእክታተ ጴጥሮስ 2
2.2.1 መልእክተ ጴጥሮስ 1ኛ
2.2.2 መልእክተ ጴጥሮስ 2ኛ
2.2.3 መልእክታተ ዮሐንስ 3
2.3.1 መልእክተ ዮሐንስ 1ኛ
2.3.2.መልእክተ ዮሐንስ 2ኛ
2.3.3 መልእክተ ዮሐንስ 3ኛ
2.3.4 መልእክተ ያዕቆብ
2.3.5 መልእክተ ይሁዳ
3. 14 መልእክታተ ጳውሎስ
3.1 ወደ ሮሜ ሰዎች
3.2 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
3.3 ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
3.4 ወደ ገላትያ ሰዎች
3.5 ወደ ኤፌሶን ሰዎች
3.6 ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
3.7 ወደ ቆላስይስ ሰዎች
3.8 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
3.9 ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
3.10 ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
3.11 ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
3.12 ወደ ቲቶ
3.13 ወደ ፊሊሞና
3.14 ወደ ዕብራውያን

---

86. በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና የተመዘገቡት 3 መጻሕፍተ መቃብያን ሲሆኑ በአለፉት አራት(4) ሲኖዶሳት-ቀኖናት በሁለቱ፡ 1ኛውና 4ኛው ሁለት - ሁለት በአንዱ 2ኛው አንድ መቃብያን ተይዘው ሲገኙ በሌላው አንዱ 3ኛው ግን አንድም መቃብያን አልተመዘገበም::

87. ጥበበ ሲራክ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና እንደ ክቡርና ቅዱስ ባይታይም ቅሉ በዚህ ቀኖናም ስፍሮ ይገኛል::



4. አቡቀለምሲስ[88]
5. 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ
5.1 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 1ኛ
5.2 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 2ኛ
5.3 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 3ኛ
5.5 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 5ኛ
5.4 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 4ኛ
5.6 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 6ኛ
5.7 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 7ኛ
5.8 መጽሐፈ ቀለሚንጦስ 8ኛ[89]

ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ወደ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት /ቁጥር ውስጥ ገብተው የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 81፡ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 46 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሐፍት 35 = 81 ይሆናሉ:: እነዚህም 7/8/ ትእዛዛት በውስጣቸው በያዟቸው ምስጢራት ምክንያት ለሕዝብ አይሰራጩም::[90]

## 3. ፍትሐ ነገሥት

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን መቀበላቸው የታዘዙ ቁጥራቸው 81 የሆነ አምላካውያት መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት ረስጠአ 81 እና ረስጠጅ 56[91]::

---

88. አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ባይያዝም ቅሉ በዚህ ቀኖና ተይዟል::

89. በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ተመዝግበው የሚታዩ ሁለት የቀላሚንጦስ መልእክታት በተጠቀሰው ቀኖና ትርጉም አብጠሊስ አልተያዙም::

90. ሲኖዶስ ገጽ 90፡ ከአራቱ ሲኖዶሳት - ቀኖናት በሁለቱ ሲኖዶሳት - ቀኖናት፡ ሲኖደስ - ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት - አብጠሊሳት 82(ረስጠአ 81) እና ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን - አብጠሊስ ስምንት (8) መጻሕፍት ቀለሚንጦስ - ትእዛዛት ምስለ ቀላሚንጦስ ክህናት በስተቀር ለምእመናን በያዟቸው ሕግና ሥርዐት መሠረት እንዳይሰራጩ ታዘው ይገኛሉ::

91. ስለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚናገረው ቀኖና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖና ግልባጭ ትርጉም ረስጠጅ እንጂ በፍትሐ ነገሥቱ እንደተመለከተው ረስጠብ አለመሆኑን ቀደም ብለን ገልጠናል:: በዚህም ገጽ በዚሁ መሠረት ረስጠብ ረስጠጅ ተብሎ መነበብ ይኖርበታል:: ዲበኩሉ ዘውዴ፡ ፍትሐ ነገሥት፡ ብሔረ ሕግ ወቀኖና=ረስጠብ 167 - 196፡ ረስጠጅ ገጽ 197 -200::



www.ethiopianorthodox.org

በቤተ ክርስቲያን ምእመናን የተቀበሏቸው መጻሕፍት አምስቱ ብሔረ ኦሪት፣ መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ 1፣ መጽሐፈ መሳፍንት 1፣ መጽሐፈ ሩት 1፣ መጽሐፈ ዮዲት 1፣ መጽሐፈ ነገሥት/መጻሕፍተ ነገሥት/ አራት: መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ አንድ መጽሐፍ፣ መጽሐፈ ነገሥት ሣልስና መጽሐፈ ነገሥት ራብዕ አንድ መጽሐፍ፣ ሕጹጻን 2 መጻሕፍት፣ 2 መጻሕፍተ ዕዝራ ጸሐፊ፣ መጽሐፈ አስቴር1፣ መጽሐፈ ጦቢያ1: 2 መጻሕፍተ /ነገረ/ መቃብያን 2፣ መጽሐፈ ኢዮብ 1፣ መዝሙረ ዳዊት 1፣ መጻሕፍተ-ጥበበ ሰሎሞን = 5 መጻሕፍት: ቆሀልት /መክብብ/፣ ምሳሌ፣ ማሕልየ መሓልይ፣ ጥበብ፣ ጥበበ ባጎር ወልደ ብኩ

የነቢያት መጻሕፍት 16: ዐበይት ነቢያት 4: እነዚህም ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ንኡሳን ነቢያትም (ደቂቀ ነቢያት) 12: እነዚህም ሆሴዕ፣ አሞጽ፣ ሚክያስ፣ ኢዩኤል፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ሚልክያስ ናቸው:: ከእነዚህ ውጪ ወይም ከእነዚህ የወጡ ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክ ለትምህርተ ሕፃናት እና ሌላውም መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን እሱም መጽሐፈ መቃብያን፣

መጻሕፍተ ሐዲስ ኪዳን: አራቱ ወንጌላውያን ሰባኪያን: ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ፣ መጽሐፈ አብረክሲስ፣ (መጽሐፈ ሐዋርያት)፣ ሰባቱ መልእክታት ከእነሱም የጴጥሮስ 2 መልእክታት፣ የወንጌላዊ ዮሐንስ 3 መልእክታት፣ የያዕቆብ መልእክት 1፣ የይሁዳ መልእክት 1፣ መጽሐፈ ጳውሎስ: 14 መልእክታት፣ መጽሐፈ አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ ወንጌላዊ 1፣ እንድትጸኑባቸው ያዘዝናችሁ ሕገጋተ እነዚህ ናቸው::[92]

የእነዚህም አምላካውያት መጻሕፍት ዝርዝር

92. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ምንጮች = ረስጠአ 53 እና ረስጠብ 41::



ሀ. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. መጽሐፈ ዮዲት
10. መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ
11. መጽሐፈ ነገሥት 2ኛ
12. መጽሐፈ ነገሥት 3ኛ
13. መጽሐፈ ነገሥት 4ኛ
14. ሕጹጻን 1ኛ
15. ሕጹጻን 2ኛ
16. መጽሐፈ ዕዝራ ጸሐፊ 1ኛ
17. መጽሐፈ ዕዝራ ጸሐፊ 2ኛ
18. መጽሐፈ አስቴር
19. መጽሐፈ ጦቢያ[93]
20. መጽሐፈ መቃብያን 1ኛ
21. መጽሐፈ መቃብያን 2ኛ
22. መጽሐፈ ኢዮብ
23. መዝሙረ ዳዊት

93. መጽሐፈ ጦቢት በ24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጊኒስ(ቅርጣግና) እና በመልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ እንደ ፍትሐ ነገሥቱ መጽሐፈ ጦቢያስ ነው የሚባለው::

www.ethiopianorthodox.org

24. ምሳሌ ሰሎሞን
25. መክብብ /ቆሀልት/
26. ማሕልየ መሓልይ
27. ጥበብ ሰሎሞን[94]
28. ጥበበ ባጎር ወልደብኩ[95]
29. ኢሳይያስ
30. ኤርምያስ
31. ሕዝቅኤል
32. ዳንኤል
33. ሆሴዕ

---

94. ጥበበ ሰሎሞን 4ኛው መጽሐፈ ሰሎሞን መሆኑ እየታወቀ 1. Guidi ይህ መጽሐፍ ምሳሌ ሰሎሞንን ምዕራፍ 25 - 31 እንደሚሸፍን ይናገራል:: 1. Guidi: Le Fetha Nagast O "Legislazione dei Re" Codice Ecclesiastico e Civile di Abyssinia 1899. ገጽ 21.1:: በሌላም በኩል ይህ ክፍለ-ምሳሌ ሰሎሞን ምዕራፍ 25-31 ተግሣጽ (መጽሐፈ ተግሣጽ) በሚል ርእስ እንደሚገኝም ይታወቃል:: መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሕፍት ገጽ 513::
95. ጥበበ ባጎር ወልደ ብኩ የሚል መጽሐፍም በየትኛው ቀኖና መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚገኝ አይደለም::
ታዲያ የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ ይህን መጽሐፍ ከወዴት አምጥቶ መዘገበው? የሚለው ጥያቄ የሚታለፍ አይደለም (እንደ ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ም.30.1 ነው:: እንደ ሰብዓሊቃናት ብሉይ ኪዳን ም. 24.22 ሲሆን ልጅ የሚለው ቃል እንጃ አጉር ወልደያኬ የሚል ቃል አይታይም):: በሌላ በኩል ጥበበ በጎር የምሳሌ ሰሎሞንን 30ኛውን ምዕራፍ ይዞ የሚገኘው ክፍል መሆኑና ባጉር የሚለው ቃልም በምሳሌ ሰሎሞን ምዕራፍ 30:1 አጉር የተሰኘው ስም የመጀመሪያው ፊደል «አ» ወደ «ባ» ተለውጦ =አጉር ባጎር ሆና ሊገኝ እንደቻለ ይነገራል:: 1. Guidi: Le Fetha Nagast O "Legislazione di Re" Codice Ecclesiastico e Civile di Abyssinia ገጽ 2.2::
በግእዝ ደግሞ ባጎር ማለት ጉበዝ፣ ጀግና ማለት ነው:: አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ... ገጽ 253::
በሌላም በኩል እንደፍትሐ ነገሥት መተርጉማን ባጎር የሰሎሞን የፍልስፍና ስም እንደ ነበርና ወልደ ብኩ ማለት የፍቁር ዳዊት /ብኩ ፍቁር/ ልጅ ማለት መሆኑን ይተረጎማል:: ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ገጽ 43:: በምን ላይ ተመርኩዞ እንደሆነ ግን ግልጽ አይደለም::



34. አሞጽ
35. ሚክያስ
36. ኢዩኤል
37. አብድዩ
38. ዮናስ
39. ናሆም
40. ዕንባቆም
41. ሶፎንያስ
42. ሐጌ
43. ዘካርያስ
44. ሚልክያስ

ሌሎች

45. ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክ[96]
46. መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን[97]

የብሉይ ኪዳን ብዛት 44 (44+2=46) ሲሆን ወደ 81 ለመድረስ 46 ድምርን መቀበል ያሻል::

## ለ. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት
6. መልእክተ ጴጥሮስ 1ኛ
7. መልእክተ ጴጥሮስ 2ኛ
8. መልእክተ ዮሐንስ 1ኛ
9. መልእክተ ዮሐንስ 2ኛ
10. መልእክተ ዮሐንስ 3ኛ
11. መልእክተ ያዕቆብ

---

96. የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ ጥበበ ኢያሱ ወልደሲራክ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና እንደተመለከተው ከ«ቅዱሳትና ክቡራት መጻሕፍት» ውጪም ወይም በሌላ አተረጓጐም ከእነዚህ መጻሕፍት የተውጣጣ መሆኑን ይደግፋል:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2: ቁጥር 17::
97. መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የሚባል መጽሐፍ በተመለከትናቸው የትኛውም ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ተመልክቶ አይገኝም:: ቢሆንም ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጪ መሆኑ ቢመለከትም እሱ መቃብያን ዜና አይሁድ ነው ግን ተብሏል:: «እሱም መጽሐፈ መቃብያን ነው»:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ቁጥር 17[1] ስለ 2 መጻሕፍተ መቃብያን ከፍ ብለን ተናግረናል:: ምን አልባት 3ኛ መቃያን ማለት ይሆን? ይህም ካልሆነ የትኛው መቃብያን ነው?



www.ethiopianorthodox.org

12. መልእክተ ይሁዳ
መልእክታተ ጳውሎስ 14
13. ወደ ሮሜ ሰዎች
14. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
15. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
16. ወደ ገላትያ ሰዎች
17. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
18. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
19. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
20. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
21. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
22. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
23. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
24. ወደ ቲቶ
25. ወደ ፊልሞና
26. ወደ ዕብራውያን
27. አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ
= የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 27

ስለዚህ በፍትሐ ነገሥት የተመዘገቡት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 44 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 27 = 71/44+27 = 71/ ወይም 44 + 2 = 46 + 27 =73 መጻሕፍት ሲሆኑ በመነሻው የተመለከተው አሐዝ 81 ነበረ ግን ሲዘረዘሩ 71 ወይም 73 መጻሕፍት ሁነው ይቆማሉ:: በምንጭነት የተጠቀሱት ቀኖናት ረስጠአ 81 እና ረስጠጅ 56 ቢሆኑም 81 መጻሕፍትን አይዘረዝሩም:: በእናት ምንጩ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ቢሆንም ተመዝግበው የሚገኙት መጻሕፍት 81 ሳይሆኑ 78 (79) ናቸው::

ስለዚህ ከ81 - 71(81 -71) ሲቀነስ 10 ወይም ከ81-73 (81 - 73) ሲቀነስ 8 መጻሕፍት ከወዴት መጡ? ይህን ጥያቄ ቀጥለን እንመለከተዋለን::

## 4. እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማን የ81 መጻሕፍት ዝርዝር

አሁን እንደተመለከትነው ፍትሐ ነገሥት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 81 (ሰማንያ አንድ) ብሎ ተነስቶ[98] መጻሕፍቱ ሲዘረዝሩ ከ73 ቁጥር ላይ ይቆማሉ:: ከእነዚህም 73 መጻሕፍት በጥያቄ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት ይገኛሉ:: ምክንያቱም ከ1 - 71 መጻሕፍት ድረስ በተራ እየዘረዘረ ከመጣ በኋላ የመጨረሻ ሁለት መጻሕፍት፡ ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክና መጽሐፈ ከርዮን ወልደ ብኩ ከእነዚህ የወጡ (ወፁእ - ወፁአን እምኔሆሙ) በሚል ሐረግ ተቀምጠው ስለሚገኙ[99] አንድም ከእነዚህ ውጭ የሆኑ ወይም ከእነዚህ የተውጣጡ የሚል አሻሚ ትርጉም ይዘው ይገኛሉና ነው::

ከዚህም የተነሳ የፍትሐ ነገሥት መተርጉማን እነዚህን ከእነዚህ ውጪ ወይም ከእነዚህ የተውጣጡ ተብለው የተቀመጡትን ሁለት መጻሕፍት፡ ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክንና መጽሐፈ ከርዮን ወልደ ብኩን ከ71 ጋር ደምረው 73 መጻሕፍትን በመቀበል ከእነዚህም 73 መጽሐፍት ማለት በ27 ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ስምንት (8) መጻሕፍትን:

1. ሁለት መጻሕፍተ ኪዳንን
2. አራት መጻሕፍተ ሲኖዶስን
3. አንድ መጽሐፈ ቀለሚንጦስን
4. አንድ ዲድስቅልያን

በመጨመር (73 + 8 = 81) 81 ቁጥርን (81 መጻሕፍትን አሟልተው ይተረጎማሉ[100]:: ሆኖም በቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ላይ የተመረኮዘ ትርጓሜ አይደለም:: በ8ቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ መካከል ይህ መጽሐፈ ቀለሚንጦስ የትኛው ነው? ሁሉም መልስን ይፈልጋል::

እንግዲህ በፍትሐ ነገሥት መተርጉማን ዘንድ 81 መጻሕፍት በራሱ በፍትሐ ነገሥቱ ስነድ የተዘረዘሩት 73 መጻሕፍትና በእነሱ ላይ የተጨመሩት ስምንት (8) መጻሕፍት

---

98. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2(ርእስ)::

99. ስለ ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖናን ተመልከት:: 100. ፍትሐ ነገሥት 30ብና ትርጓሜው አፍሲት ጎትመት ገጽ 19::



www.ethiopianorthodox.org

- ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን
- አራት መጻሕፍተ ሲኖዶስ
- አንድ መጽሐፈ ቀለሚንጦስ
- አንድ ዲድስቅልያ

ሲሆኑ 73ቱ መጻሕፍት ግን የተዘረዘሩ ስለሆነ መድገሙ አያስፈልግም::

## 5. እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ የ81 ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር

ከላይ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም በአለፉት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ጥረትም ሆነ ቆይቶም በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከእጅ ጽሑፎች አልፈው በኅትመት መሣሪያ እየተባዙ በየወቅቱ 1918፣ 1929፣ 1947(1953) እና 1980 እየተሠራጩ የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ሲታይ በመካከላቸው አንድ አንድ ልዩነቶች ቢታዩም 81 ቅዱሳት መጻሕፍት የተኞቹ እንደሆኑ በሁሉም (አራቱ ኅትመቶች) አልተመለከቱም::

ከዚህም ጋር በተያያዘ በአንድ በኩል ከ81 ቅዱሳት መጻሕፍት እየበለጡ (81 ቁጥርን እያለፉ) ሲገኙ ለዚህም ምንም ምክንያት አልተሰጠም:: በሌላ በኩል አንድም በመሠረቱ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ሲደነገግ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክፍሎች ሆነው ተቆጥረው ሲያያዙ የመጡ ስምንት(8) ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀላሚንጦስ (8 ብሔር ዘቀለሚንጦስ) አልተመለከቱም::

እንግዲህ ይህ እንደአለ ሆኖ ስለ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት ከታወቁት የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተጨማሪ እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማንም የሊቃውንት ጉባኤ 81 መጻሕፍት የሚላቸውን አመልክቷል:: በአንድ በኩል ከፍትሐ



ነገሥቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ድምሩ 46 ከመሆን ጋር ቢስማማም በመጻሕፍቱ መካከል ግን ልዩነት ይታያል:: ለምሳሌ በፍትሐ ነገሥት ዕዝራ ሱቱኤል የለም በሊቃውንት ጉባኤ ዝርዝር ግን እንደፍትሐ ነገሥት ሁለት ዕዝራ ሲኖር 3ኛ ዕዝራ ሱቱኤልም ተመዝግቦ ይገኛል:: በፍትሐ ነገሥት ጥበበ [illegible] ሲኖር በሊቃውንት ጉባኤ ዝርዝር አይታይም፣ ወዘተ:: በሌላም በኩል የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን - ሐዲሳት መጻሕፍትን በሚመለከት በሊቃውንት ጉባኤ እና በፍትሐ ነገሥት መተርጉማን መካከል ልዩነት አይታይም:: የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በሁሉቱም ወደ 35 መጻሕፍት ለማድረስ የሚጨመሩት ስምንት (8) መጻሕፍት ናቸው:: በመተርጉማኑ የአራት መጻሕፍተ ሲኖዶስ አለመዘርዘር እንደተጠበቀ ሆኖ የሊቃውንት ጉባኤ እንደመተርጉማኑ 46 የብሉይ ኪዳንና 27 የሐዲስ ኪዳን (46+27 = 73) 73 መጻሕፍትን ተቀብሎ ግን ወደ 81 ቁጥር ለማድረስ የሚያስችሉት ስምንት መጻሕፍትን ዘርዝሮ ጨምሮ ይገኛል:: እነዚህም «ስምንት መጻሕፍተ ኪዳን» በሚል ተነስተው ተዘርዝረዋል[101]::

ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን

1. 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን
2. 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን

አራት መጻሕፍተ ሲኖዶስ

3. ሥርዐተ ጽዮን
4. ትእዛዝ
5. ግጽው
6. አብጥሊስ
7. ዲድስቅልያ

101. ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ በ07-06-1986 ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ተቀርጾ ከመንበረ ፓትርያርክ የተሰጠ የ81 ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር::

www.ethiopianorthodox.org

8. መጽሐፈ ቀስሚንጦስ

በርግጥ ግን በግልጥ ትልቁ ጥያቄ እስከ ማውቀው ድረስ ከምን ታሪካዊ ምንጭ ላይ ጉባኤው ተደግፎ እንደሆነም ሊገባኝ አለመቻሉ ነው::

-በትክክል ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን

1ኛ መጽሐፈ ኪዳንና

2ኛ መጽሐፈ ኪዳን እንደአሉ ይታወቃል:: ከእነዚህ ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን የመጀመርያው መጽሐፍ ኪዳን 55 አንቀጾችን ይዞ ሲገኝ ሁለተኛው መጽሐፈ ኪዳን በስድ ንባብ ተቀርጾ ይገኛል:: የሁለቱ መጻሕፍት ይዘቶች ሥርዐተ ጸሎትና ሥርዐተ ቅዳሴ ነው:: እነዚህንም ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን ከጸሎተ ኪዳን ዘሠለስቱ ጊዚያት ጋር ማስተያየት ያሻል[102]::

-መጻሕፍተ ሲኖዶስ ከሚላቸው

3ኛ ሥርዐተ ጽዮን[103]

4ኛ አብጠሊስ [104]

5ኛ ዲድስቅልያ[105]

የሚታወቁ ቀኖናውያትና ሥርዐተ ቅዳሴያውያት መጻሕፍት መኖራቸው ሲታወቅ

6ኛ ትእዛዝ እና

7ኛ ግጽው

---

102. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 240 -146:: ሲኖዶስ ገጽ 341 - 384፤ መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝና በአማርኛ 1942 ገጽ 195-199 ስለ ሁለት ኪዳናት አሁንም Abbadie A.d. : Catalogues 1-75 / ቁ.199 ገጽ 201-208::

103. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 113 - 136::

104. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 177-166::

105. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 219-239::



ታሪካዊ ምንጫቸው ከወዴት ይሆን?

8ኛ መጽሐፈ ቀላሚንጦስ

ይህ መጽሐፈ ቀላሚንጦስ የትኛው መጽሐፈ ቀላሚንጦስ ነው? በሕግ (ቀኖናት) ቤተክርስቲያን ታሪክ የሚታወቁት ስምንት (8) መጻሕፍተ ቀላሚንጦስ (8 ትእዛዛት ሐዋርያውያት ምስለ ቀለሚንጦስ) ናቸው:: ወደፊት አንድ በአንድ በመጠኑም ቢሆን ይታያሉ[106]::

ነገር ግን እነዚህ መጻሕፍት ከ27 ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ተደምረው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ወደ 35 ከዚያም 35ንና 46ን ወደ 81 መጻሕፍት የሚያስደርሱት ሐዋርያውያት ቀኖናት ምላሾች ሲኖዶሳት ቀኖናት:

- ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን (ረስጠጅ)[107]
- ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት- አብጠሊሳት (ረስጠአ)[108]
- ሥርዐተ (ሲኖዶስ)-ቀኖናተ ሐዋርያት[109]
- ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን-አብጠሊስ[110]

የሚመለከቷቸው መጻሕፍት አለመሆናቸውን እናውቃለን::

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲቃውንት ጉባኤ የ81 መጻሕፍት ዝርዝር

ሀ. <u>መጻሕፍተ ብሉይ ኪዳን</u>

<u>ስምንቱ ብሔረ ኦሪት</u>

1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት
3. ኦሪት ዘሌዋውያን
4. » ዘኁልቁ

---

106. ከዚሁ ገጽ 213 - 224
107. ከዚሁ ገጽ 96 - 99 ::
108. ከዚሁ ገጽ 99 - 105
109. ከዚሁ ገጽ 105 - 108
110. ከዚሁ ገጽ 108 - 111



www.ethiopianorthodox.org

5. » ዘዳግም ሕግ
6. » ዘኢያሱ ወልደ ነዌ
7. » ዘመሳፍንት
8. » ዘሩት

**አራቱ ብሔረ ነገሥት**

9. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ
10. » ሳሙኤል ካልዕ
11. » ነገሥት ቀዳማዊ
12. » ነገሥት ካልዕ

**ሁለቱ መጻሕፍተ ሕጹጻን**

13. ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
14. ዜና መዋዕል ካልዕ

**ሁለቱ መጻሕፍተ ዕዝራ**

15. ዕዝራ ቀዳማዊና ካልዕ
16. » ሱቱኤል
17. መጽሐፈ ነህምያ
18. » ጦቢት
19. » ዮዲት
20. » አስቴር
21. » መቃብያን ቀዳማዊ
22. » » ካልዕ
23. » ኢዮብ
24. መዝሙረ ዳዊት

**አምስቱ መጻሕፍተ ሰሎሞን**

25. መጽሐፈ ምሳሌ ዘሰሎሞን
26. » ተግሣጽ
27. » ጥበብ
29. መኃልይ ዘሰሎሞን
30. መጽሐፈ ሲራክ

**አራቱ ዐበይት ነቢያት**

31. ትንቢተ ኢሳይያስ
32. ትንቢተ ኤርምያስ
33. ትንቢተ ሕዝቅኤል
34. ትንቢተ ዳንኤል

**አሥራ ሁለት ደቂቀ ነቢያት**

35. ትንቢተ ሆሴዕ
36. » አሞጽ
37. » ሚክያስ
38. » ኢዩኤል
39. » አብድዩ
40. » ዮናስ
41. » ናሆም
42. » ዕንባቆም
43. » ሶፎንያስ
44. » ሐጌ
45. » ዘካርያስ
46. » ሚልክያስ

ለ. መጻሕፍተ ሐዲስ ኪዳን

**አርባዕቱ ወንጌላት**

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል



5. ግብረ ሐዋርያት
- የጳውሎስ መልእክታት 14
6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
8. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17. ወደ ቲቶ
18. ወደ ፊልሞና
19. ወደ ዕብራውያን
20. የያዕቆብ መልእክት
21. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ
22. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
24. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
25. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
26. የይሁዳ መልእክት
27. አቡቃለምሲስ - ራእየ ዮሐንስ

ሐ. ስምንቱ መጻሕፍተ ኪዳን

**ሁለቱ መጻሕፍተ ኪዳን**

1. መጽሐፈ ኪዳን 1ኛ
2. መጽሐፈ ኪዳን 2ኛ

**አራቱ መጻሕፍተ ሲኖዶስ**

3. ሥርዐተ ጽዮን
4. ትእዛዝ
5. ግጽው
6. አብጠሊስ
7. ዲድስቅልያ
8. መጽሐፈ ቀለሚንጦስ

በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና በመመሥረት ወደ ግእዝ የተመለሱት ቀኖናትን ሲኖዶስ-(ቀኖናት) ዘቤተ ክርስቲያን ዘወሀብዋ ሐዋርያት በእደ ቀለሚንጦስ-ትእዛዛት 57 ቀኖና 56ን፣ ሲኖዶስ - (ቀኖናት) ዘሐዋርያት ቅዱሳን ዘጽሐፈ ቀለሚንጦስ-አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81ን፣ ሥርዐተ (ቀኖናት) ሐዋርያት ዘተፈነወ ለአሕዛብ ትእዛዝ 80፣ 80ን እና ሲኖዶስ(ቀኖናት) ዘሐዋርያት ቅዱሳን ዘሀገረ ቀለሚንጦስ-አብጠሊስ 81 ቀኖና 80ን እና የፍትሐ ነገሥትን 81 መጻሕፍት ዝርዝር (አንቀጽ) በሚቀጥለው ማነጻጸርያ ሰሌዳ መመልከት ይቻላል።



www.ethiopianorthodox.org

## 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት እና የአራት ግእዝ-ትርጉሞች ሐዋርያውያት ቀኖናት ፍትሐ ነገሥትን ጨምሮን ማነጻጸርያ ሰንጠረዥ-ሰሌዳ 2

| የ ብ ሉ ይ ኪ ዳ ን መጻሕፍት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 85 ቀኖናት 85ኛ ቀኖና | ትእዛዛት 57 ቀኖና 56 | አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጠሊስ 81 ቀኖና 80 | ፍ/ነገሥት አንቀጽ 2 |
| ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት |
| ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት |
| ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን |
| ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ |
| ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም |
| ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ |
| መሳፍንት | መሳፍንት | /መሳፍንት | /መሳፍንት | /መሳፍንት | /መሳፍንት |
| ሩት | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት |
| 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት |
| 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት |
| 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት |
| 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት |
| 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት |
| 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት |
| 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ |
| 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ |
| አስቴር | አስቴር | አስቴር | አስቴር | አስቴር | አስቴር |
| 1ኛ መቃብያን | 1ኛ መቃብያን | 1ኛ መቃብያን | - - | 1ኛ መቃብያን | 1ኛ መቃብያን |
| 2ኛ መቃብያን | 2ኛ መቃብያን | - - | - - | 2ኛ መቃብያን | 2ኛ መቃብያን |



| የ ብ ሉ ይ ኪ ዳ ን መጻሕፍት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 85 ቀኖናት 85ኛ ቀኖና | ትእዛዛት 57 ቀኖና 56 | አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጠሊስ 81 ቀኖና 80 | ፍ/ነገሥት አንቀጽ 2 |
| 3ኛ መቃብያን | - - | - - | - - | - - | 3ኛ መቃብያን |
| ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ |
| መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር |
| ምሳሌያት | ምሳሌያት | ምሳሌያት | ምሳሌያት | ምሳሌያት | ምሳሌያት |
| መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ |
| ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ |
| ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ |
| ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ |
| ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ |
| ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ |
| ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም |
| ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም |
| ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ |
| ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ |
| ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ |
| ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ |
| ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ |





www.ethiopianorthodox.org

| የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 85 ቀኖናት 85ኛ ቀኖና | ትእዛዛት 57 ቀኖና 56 | አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጠሊስ 81 ቀኖና 80 | ፍ/ነገሥት አንቀጽ 2 |
| ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ |
| ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል |
| ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል |
| - - | - - | ጥ/ሰሎሞን | - - | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን |
| - - | - - | - - | - - | - - | ጥበበ ባጎር |
| - - | - - | ተግሣጽ | - - | ተግሣጽ | - - |
| - - | - - | ጦቢት | - - | ጦቢት | ጦቢያ |
| - - | - - | ዮዲት | - - | ዮዲት | ዮዲት |
| ጥ/ሲራክ | ጥ/ሲራክ | ጥ/ሲራክ | - - | ጥ/ሲራክ | ጥ/ሲራክ |
| - - | - - | - - | - - | - - | ዮሴፍ ዘኮርዮን |
| - - | ኩፋሌ | ኩፋሌ | - - | ኩፋሌ | - - |

| የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 85 ቀኖናት 85ኛ ቀኖና | ትእዛዛት 57 ቀኖና 56 | አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጠሊስ 81 ቀኖና 80 | ፍ/ነገሥት አንቀጽ 2 |
| ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ |
| ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ |
| ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ |
| ጳውሎስ ወደ ሮሜ | ጳውሎስ ወደ ሮሜ | ጳውሎስ ወደ ሮሜ | ጳውሎስ ወደ ሮሜ | ጳውሎስ ወደ ሮሜ | ጳውሎስ ወደ ሮሜ |
| 1ኛ ቆሮንቶስ | 1ኛ ቆሮንቶስ | 1ኛ ቆሮንቶስ | 1ኛ ቆሮንቶስ | 1ኛ ቆሮንቶስ | 1ኛ ቆሮንቶስ |
| 2ኛ ቆሮንቶስ | 2ኛ ቆሮንቶስ | 2ኛ ቆሮንቶስ | 2ኛ ቆሮንቶስ | 2ኛ ቆሮንቶስ | 2ኛ ቆሮንቶስ |



| የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 85 ቀኖናት 85ኛ ቀኖና | ትእዛዛት 57 ቀኖና 56 | አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጠሊስ 81 ቀኖና 80 | ፍ/ነገሥት አንቀጽ 2 |
| ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ |
| ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን |
| ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ |
| ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ |
| 1ኛ ተሰሎንቄ | 1ኛ ተሰሎንቄ | 1ኛ ተሰሎንቄ | 1ኛ ተሰሎንቄ | 1ኛ ተሰሎንቄ | 1ኛ ተሰሎንቄ |
| 2ኛ ተሰሎንቄ | 2ኛ ተሰሎንቄ | 2ኛ ተሰሎንቄ | 2ኛ ተሰሎንቄ | 2ኛ ተሰሎንቄ | 2ኛ ተሰሎንቄ |
| 1ኛ ጢሞቴዎስ | 1ኛ ጢሞቴዎስ | 1ኛ ጢሞቴዎስ | 1ኛ ጢሞቴዎስ | 1ኛ ጢሞቴዎስ | 1ኛ ጢሞቴዎስ |
| 2ኛ ጢሞቴዎስ | 2ኛ ጢሞቴዎስ | 2ኛ ጢሞቴዎስ | 2ኛ ጢሞቴዎስ | 2ኛ ጢሞቴዎስ | 2ኛ ጢሞቴዎስ |
| ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ |
| ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና |
| ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን |
| 1ኛ ጴጥሮስ | 1ኛ ጴጥሮስ | 1ኛ ጴጥሮስ | 1ኛ ጴጥሮስ | 1ኛ ጴጥሮስ | 1ኛ ጴጥሮስ |
| ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ |
| 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ |
| 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ |
| 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ |
| ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ |
| ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ |
| - - - | አቡቀለምሲስ | አቡቀለምሲስ | - - | አቡቀለምሲስ | አቡቀለምሲስ |

www.ethiopianorthodox.org

| የ ሐ ዲ ስ  ኪ ዳ ን  መ ጻ ሕ ፍ ት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 85 ቀኖናት 85ኛ ቀኖና | ትእዛዛት 57 ቀኖና 56 | አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጠሊስ 81 ቀኖና 80 | ፍ/ነገሥት አንቀጽ 2 |
| 1ኛ ቀለሚን ጦስ | 1ኛ ቀለሚን ጦስ | 1ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 1ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| 2ኛ ቀለሚን ጦስ | 2ኛ ቀለሚን ጦስ | 2ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 2ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| 3ኛ ቀለሚን ጦስ | 3ኛ ቀለሚን ጦስ | 3ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 3ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| 4ኛ ቀለሚን ጦስ | 4ኛ ቀለሚን ጦስ | 4ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 4ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| 5ኛ ቀለሚን ጦስ | 5ኛ ቀለሚን ጦስ | 5ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 5ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| 6ኛ ቀለሚን ጦስ | 6ኛ ቀለሚን ጦስ | 6ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 6ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| 7ኛ ቀለሚን ጦስ | 7ኛ ቀለሚን ጦስ | 7ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 7ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| 8ኛ ቀለሚን ጦስ | 8ኛ ቀለሚን ጦስ | 8ኛ ቀለሚን ጦስ | - - | 8ኛ ቀለሚን ጦስ | - - |
| መ/ ቀለሚ ንጦስ 1ኛ | - - | መ/ ቀለሚ ንጦስ 1ኛ | - - | - - | - - |
| መ/ቀለሚ ንጦስ 2ኛ | - - | - - | - - | - - | - - |
| | 81 | 81 | 66 | 81 | 71(73) |



# ምዕራፍ አራት
# በጥንት ቤተክርስቲያን ሲኖዶሳውያት፣ አበውያት ቀኖናትና በቀኖናቱ ግእዝ ትርጉሞች - አራት ቀኖናት መካከል የሚታዩት ግንኙነቶችና ልዩነቶች

## 1 በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና እና በግእዝ ትርጉም አራት ቀኖናት መካከል የሚታዩ ግንኙነቶችና ልዩነቶች፣

ከላይ እንደተመለከተው ጽርእ - ግሪክ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ወደ ግእዝ ተተርጉመው ግን አራት ሰነዶችን ይዘው ይገኛሉ::

ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት የተዘረዘሩበት የእነዚህን 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛው ቀኖና በግእዝ ትርጉሙ በአራቱም ሰነዶች ግን የተለያዩ ቁጥሮችን ይዞ ይገኛል::

እንግዲህ ይህ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ተተርጉሞ ከሚገኝባቸው አራት ቀኖናውያን ሰነዶች መጨረሻዎች ቀኖናት ጋር ሲነጻጸር ልዩነቶች ይታያሉ::

ስለዚህም በመጀመሪያ በ85ኛው ሐዋርያዊ ቀኖና የተመዘገቡት መጻሕፍት 78 ወይም 78 + 1 = 79 ሲሆኑ በእነዚህ ግእዝ ትርጉም ቀኖናት በእየአንድአንዳቸው ስንት ስንት እንደሆኑ ማመልከት ይቻላል::

## 1.1 ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን ትእዛዝት 57 56ኛ ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና

ከእነዚህ ቀኖናት 56ኛ ቀኖና ይዟቸው የሚገኙት መጻሐፍት ቁጥር 81 ሲሆን ከዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና 78 መጻሕፍት ጋር ወይም 79 መጻሕፍት ጋር ሲነጻጸር = በግእዙ ሰነድ የ2 ወይም የ3 መጻሕፍት ብልጫ ይታያል::



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህም 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና የማይገኙ አራት መጻሕፍት: መጽሐፈ ዮዲት፣ ጥበበ ሰሎሞን፣ መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ኩፋሌ ሲሆኑ በሌላ በኩል 3ኛ መቃብያን በግእዙ ትርጉም ቀኖና አይገኝም:: ከዚህም ጋር «ተግሣጽ» በሚል ርእስ በግእዝ ትርጉም 56ኛ ቀኖና የሚገኘው መጽሐፍ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ከምሳሌ ሰሎሞን 25 - 31 ምዕራፎችን ይዞ የሚገኘው መጽሐፍ ነው:: በግእዝም ቢሆን ተግሣጽ የሚለው ርእስ ሁልጊዜ አያጋጥምም::

ከዚህም በስተቀር አቡቀለምሲስ - ራእየ ዮሐንስ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና አይገኝም::

## 1.2 ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጠሊሳት 82 81ኛ ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት 85ኛ ቀኖና

ከላይ እንደታየው በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር 78 ሲሆን በዚህ ግእዝ ትርጉም ቀኖናት - አብጠሊሳት 81ኛ ቀኖና ሰፍረው የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር 81 ነው::

ስለዚህ የግእዝ ትርጉም ቀኖና 2 ወይም 3 መጻሕፍትን ጭማሪ ይዞ ይገኛል:: በሌላ በኩል ከመጻሕፍተ መቃብያን አንድ መጽሐፈ መቃብያን ከመገኘቱ ጋር ከሁለቱ መልእክታተ ቀለሚንጦስ አንድዋ በአብጠሊሳት ተመዝግባ የምትገኝ ይመስላል:: ተግሣጽም ከምሳሌ ሰሎሞን ተለይቶ ይገኛል:: እንግዲህ ይህ ሲቻቻል ነው የሁለት ወይም የሦስት መጻሕፍት ልዩነት ሊታይ የቻለው::

## 1.3 ሲኖዶስ- ሥርዐተ - ቀኖናተ ሐዋርያት - ትእዛዝ 80 80ኛ ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና

አሁንም በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ተዘርዝረው የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር 78 ወይም 79 ሲሆን በዚህ ግእዙ ትርጉሙ ሥርዐተ ሐዋርያት 80ኛ ቀኖና ተዘርዝረው የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር 63 ነው:: ሁለቱ ቁጥሮች ሲነጻጸሩ አንድም እኩል ሆነው ወይም አንዱ በልጦ ሊገኙ ቢችሉም ቅሉ ልዩነትም አለባቸው:: በሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ጥበበ ሰሎሞን ሳይኖር ጥበበ ሲራክ በሁለቱም አለ:: ተግሣጽ አሁንም በዚህ ሥርዐት-ቀኖና አልተመለከተም:: መጽሐፈ ኩፋሌ በዚህ ቀኖና አልተመዘገበም:: ከመጻሕፍተ መቃብያንም አንዱም መጽሐፍ አልተመለከተም:: መጽሐፈ ጦቢት በዚህም ቀኖና ተዘሏል:: ሁለቱ መልእክታተ ቀለሚንጦስና 8 ትእዛዛት ሐዋርያውያት ምስለ ቀለሚንጦስ አልተመለከቱም:: በዚህ ሥርዓተ ሐዋርያት 80ኛ ቀኖና እና በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት መካከል የተቃረበ ልዩነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሁለቱ ቀኖናት ቁጥሮች በ15 ወይም 16 ቁጥሮች ላይጋጠሙ ችለዋል::

## 1.4 ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን- አብጠሊስ 81 80ኛ ቀኖና እና የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና

ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና የተመዘገቡት መጻሕፍት ቁጥር 78 ወይም 79 ሲሆን አሁንም ይህ ቀኖና በግእዝ ትርጉም አብጠሊስ 80ኛ ቀኖና መጻሕፍት ዝርዝር ጋር ሲተያይ በአብጠሊስ 80ኛ ቀኖና የተዘረዘሩት መጻሕፍት ቁጥር 81 ነው::

አሁንም የ2 ወይም የ3 መጻሕፍት ልዩነት ይታያል:: በዚህም ጊዜ ከላይ እንደተባለው በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ያልተመዘገቡ መጻሕፍት: መጽሐፈ ኩፋሌ፣ ጥበበ ሰሎሞን፣ መጽሐፈ ጦቢያ(ጦቢት) መጽሐፈ ዮዲት፣ አቡቀለምሲስ መገኘታቸው ሲታይ በ85ኛ ሐዋርያት ቀኖና የተመለከቱት ሁለት መልእክታተ ቀላሚንጦስ በዚህ አብጠሊስ 80ኛ ቀኖና አልተገለበጡም::


www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህም በ85ኛ ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ያልተመዘገቡ ነገር ግን በእነዚህ ግእዝ ትርጉሞች ቀኖናት በአንዱ ወይም በሌላው ሰፍረው የሚገኙት መጻሕፍት እነዚህ ናቸው::

- ዮዲት
- ጦቢት
- ጥበበ ሰሎሞን
- ባሮክ
- ሰቆቃወ ኤርምያስ
- መልእክተ ኤርምያስ
- አቡቀለምሲስ - ራእየ ዮሐንስ
- ኩፋሌ በየትኛውም ሌላ ቀኖና ቢሆንም የማይገኝ

በሌላ በኩል በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ተመዝግበው ሳለ ከሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ቀኖና 81 ያውም ጥያቄ በስተቀር በቀሩት 3 ቀኖናት ያልተወሱ ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስ ናቸው:: ከዚህም ጋር በ85 ሐዋርያውያት 85ኛ ቀኖና 3 መጻሕፍተ መቃብያን ተመዝግበው ሲገኙ በዚህ ቀኖና ግእዝ ትርጉም አብጠሊስ 80ኛ ቀኖና፣ ሁለት መጻሕፍት ይታያሉ:: ስለዚህ በሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን - ትእዛዛት 56/57/56ኛ ቀኖና እና በዚህ አብጠሊስ 80ኛ ቀኖና ሁለት ሁለት መጻሕፍተ መቃብያን ሲዘረዘሩ በአብጠሊሳት 81ኛ ቀኖና አንድ መጽሐፈ መቃብያን ብቻ ተመዝግቦ ይገኛል ግን በሥርዐተ ሐዋርያት አንድም መጽሐፈ መቃብያን አይገኝም::::

## 2. በቀኖናት ዘላኦዶቅያ /ሎዶቅያ/ 60ኛ ቀኖና እና በቀኖናው ግእዝ ትርጉም መካከል የሚታዩት ግንኙነቶችና ልዩነቶች

ስለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ከሚናገሩት 6 ቀኖናት አንዱ 60ኛ የሎዶቅያ /ላኦዶቅያ/ ቀኖና መሆኑ ሲታወቅ ይህም



60ኛ ቀኖና ከላይ እንደተገለጸው ቆይቶ የተጨመረ እንጂ ሌሎች የሎዶቅያ ቀኖናት /59 ቀኖናት/ ሲደነገጉ እንደ አልነበረ ይተረካል::

ይህንም ከፍትሐ ነገሥት ጋር ማነጻጸር ይቻላል:: ስለዚህም ፍትሐ ነገሥትን ስንመለከት በመቅድሙ ውስጥ ከአስቀመጣቸው የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች - ሲኖዶሳት መካከል 10ኛው ጉባኤ - ሲኖዶስ የሎዶቅያ /ላኦዶቅያ/ ጉባኤ - ሲኖዶስ ነው:: በዚህም ሲኖዶስ 19 ኤጴስ ቆጶሳት ተካፍለውና ስለ ክህነት፣ አገልግሎት፣ ጋብቻና ስለመሰሉት ጉዳዩች 59 ቀኖናትን ሠርተው ተለያይተዋል[1]::

ስለዚህም ፍትሐ ነገሥት ይህን ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚናገረውን የሎዶቅያ 60ኛ ቀኖና/ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት/ አያውቁም ማለት ነው:: 59ኛው የመጨረሻው ቀኖና የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝር አይናገርም:: ነገር ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጪ የሆነ መጽሐፍ እንዳይነበብ ይከለክላል[2]::

## 3. በቀኖናት ዘካርታጌኒስ(ቅርጣግና) 24ኛ/32ኛ ቀኖና እና በቀኖናው ግእዝ ትርጉም መካከል የሚታዩት ግንኙነቶችና ልዩነቶች

ስለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ከሚደነግጉት 6 ቀኖናት (6 ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት) መካከል አሁንም አንዱ ከቀኖናተ /ካርታጌኒስ/ ቅርጣግና /24ኛ /32ኛው ቀኖና መሆኑ ይታወቃል::

በካርታጌኒስ/ሰሜን አፍሪካ ክልል/ በተለያዩ ጊዜያት ሦስት ጉባኤያት /ሲኖዶሳት/ በኤፖን 393፣ በካርኪዶና-ካርታጌኒስ 397

1. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
2. ሲኖዶስ ገጽ 136 - 154::



www.ethiopianorthodox.org

እና በካርታጌኒስ 419 መደረጋቸው ሲታወቅ ስለቅዱሳት መጻሕፍት የሚናገሩት ቀኖናት /24ኛ/ 32ኛ ቀኖናት) የተደነገጉት በ419 በተደረገው 3ኛው የካርታጌኒስ ጉባኤ - ሲኖዶስ ነው[3]::

ነገር ግን ፍትሐ ነገሥትን ስንመለከት በመቅድሙ ላይ ከተቀመጡት ጉባኤያት - ሲኖዶሳት ቅደም ተከተል 6ኛውን ተራ ይዞ የሚገኘው የቅርጣግና /ቀጠግ/ ካርታጌኒስ ሲኖዶስ ሲሆን ይህም በቅርጣግና /ካርታጌኒስ/ ከተጠሩት ሲኖዶሳት 2ኛው መሆኑ ተጠቅሏል:: በዚህም ሲኖዶስ 50 ኤጲስ ቆጶሳት መካፈል የቻሉ ሲሆን ጋብቻንና አሠረ ክህነትን የሚመለከቱ 14 ቀኖናትን ጽፈው ተለያይተዋል[4]::

እንግዲህ በአንድ በኩል ስለቅዳሳት መጻሕፍት የሚደነግጉት ቀኖናት /24/32 ቀኖናት/ የተሠሩት በቅርጣግና በ419 በተሰበሰበው 3ኛው ሲኖዶስ ሲሆን ፍትሐ ነገሥቱ ግን የሚናገረው በ397 ስለተጠራው 2ኛው ሲኖዶስ ስለሆነ ይህን 24/32 ቀኖና መጻሕፍትን አልተጠቀመበትም ማለት ነው::

ወደ ግእዝም ተተርጉመው የሚገኙት ቀኖናት ዘቅርጣግና እነዚሁ 14 ቀኖናት ናቸው[5]::

## 4. በቀኖናት አበውና በቀኖናቱ ግእዝ ትርጉሞች መካከል የሚታዩ ግንኙነቶችና ልዩነቶች፣

ከታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል ሦስት:

1. ታላቁ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ
2. ጎርጎርዮስ ታኦጎሎስ(ታኦሎጎስ-ቴኦሎጎስ) ነባቤ መለኮት

3. አምፊሎኪዮስ ዘኢንቅዮን

---

3. Mansi: Sacrorum Conciliorum. . T 3, ዐምድ 723-724 A- C.
4. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
5. ሲኖዶስ ገጽ 105 - 107::



ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው - ትምህርተ መለኮትን የምታስተምርባቸው፣ ሥርዐተ አምልኮትን የምትፈጽምባቸው ለሥርዐተ ቅዳሴ የምትገለገልባቸው ሆነው የተደነገጉትን ወይም መደንገግ የሚኖርባቸውን - የሚገባቸውን አምላካውያት መጻሕፍት ዝርዝር የሚመለከት መልእክትን በማስተላለፍና ቀኖናትን በመሥራት አልፈዋል::

### 4.1 መልእክተ አትናቴዎስ

ታላቁ ቅዱስ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእለእስክንድርያ ስለሩሲ[?]ነ ዕለት-በዓለ ፋሲካ - በዓለ ትንሣኤ በአስተላለፈው 39ኛ መልእክት /367/ ስለ አምላካውያት መጻሕፍትም ዝርዝር ይናገራል::

ነገር ግን ቅዱስ አትናቴዎስ የጻፋቸው መጻሕፍት ብዙዎችም ቢሆኑ ወደ ግእዝ ተተርጉመው የሚገኙት የተወሰኑ ናቸው::

በዚህም መልክ ይህ 39ኛ የፋሲካ መልእክቱ ወደ ግእዝ ተተርጉሞ እንደሆነ በተለይ በቅርቡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አሳታሚ ድርጅት በታተመ ሃይማኖተ አበው ለመመልከት ቢሞከርም ሊገኝ አልቻለም::

ስለዚህ ፈጽሞ አልተተረጎመም ወደ ማለት መደምደሚያ ለመድረስ ግን በልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት ብዙ ያልታወቁ መጻሕፍት እንደሚገኙ ስለሚታወቅ ምን አልባት ይህም ይገኝ እንደሆነ ላያስችል ይችላል::

### 4.2 ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት - ታአጎሎስ

ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት - ታኦጎሎስ (ፊደሎች «ሎ» እና «ጎ» ተዛውረዋል ታኦሎጎስ የተሻለም ቴኦሎጎስ ማለት ነበረበት) ዘእንዚናዙ ከልዩ ልዩ አርእስትና ይዘቶች ላይ በመነሳት እጅግ

www.ethiopianorthodox.org

ብዙ መጻሕፍትን ከመጻፉ ጋር ስለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚናገር - የሚቀንን ቀኖናንም በግጥም መልክ - 34 ስንኞች ቀርጾ ይገኛል::

አሁንም የቅዱስ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ድርሰቶች በሙሉ ወደ ግእዝ እንደ አለመተርጎማቸው መጠን /ምን አልባት ተተርጉመዋል የሚል ማስረጃ የሚቀርብ ከሆነ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ /ይህስ ባለ 34 ስንኝ ግጥም[6] ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ ተተርጉሞ ይሆን እንደ ሆነ በማለት አሁንም በቅርብ የሚገኘውን ከላይ የተጠቀሰውን ማለትም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤት ክርስቲያን አሳታሚ ድርጅት ታትሞ የሚገኘው ሃይማኖተ አበው ቢገላበጥም አልተገኘም::

ስለዚህም አልተተረጎመም ወደ ማለት መደምደሚያ ከመድረስ በፊት አሁንም ምን አልባት በገዳማት ወይም አድባራት ተወስኖ ይገኝ እንደሆነ የሚለው ጥርጣሬ የሚታለፍ አይሆንም።

## 4.3 ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን

የኢቆንዮን ሊቀ ጳጳሳት የነበረ አምፊሎኪዮስ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚደነግግ ቀኖናን በ59 ስንኞች ደርድሮና ጽፎ ማስተላለፉን ተመልክተናል[7]::

ነገር ግን በዚህ አባት ስም ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚናገር ቀኖና ወደ ግእዝ ተተርጉሞ ይገኝ እንደሆነ አሁንም ከላይ ከተጠቀሰው አዲስ ኅትመት ሃይማኖተ አበው ቢፈለግ አልተገኘም:: አሁንም ምን አልባት በአንድ ወይም በሌላ ገዳም ወይም ደብር ቢሆንም አይገኝም ወደ ማለት መደምደሚያ

---

6. ከእኛ ኢትዮጵያውያን በስተቀር ግጥም ማለት ሁልጊዜ ቤት ይመታል ማለት አይደለም:: የዓረፍተ ነገሩ አቀማመጥ - ስንኙ ነው ግጥም የሚያሰኘው ለምሳሌ መዝሙረ ዳዊት የግጥም መጽሐፍ ነው የሚባለው፤ ነውም::
7. ከዚሁ ገጽ 52 - 56::



www.ethiopianorthodox.org

ለመድረስ ቢያስቸግርም ቅሉ በመሠረቱ አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን በኢትዮጵያ የታወቀ አባት አይደለም::

## 5. ፍትሐ ነገሥት

በፍትሐ ነገሥት ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስም ሆኑ ስምንቱ ትእዛዛት ሐዋርያውያት ምስለ ቀለሚንጦስ፣ ከብሉይ ኪዳን መቃብያን /2መጻሕፍተ መቃብያን እንጅ) 3ኛ መቃብያን አልተመለከቱም:: ምን አልባት መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን እሱም መጽሐፈ መቃብያን የሚለው እንደሆነም አይታወቅም:: ማመሳከር ያስፈልጋል:: መጽሐፈ ነህምያ የለም::

ከ5ቱ መጻሕፍተ ሰሎሞን አንዱ ጥበበ ባጎር እንደሆነ ይመለከታል:: አምስት ቁጥርን ለመሙላት ካልሆነ በስተቀር ግልጥ አይደለም::

በአጋጣሚ በየቀኖናቱ 5 መጻሕፍተ ሰሎሞን እየተባለ ሲነገር – ሲጻፍ ቢገኝም ቅሉ በቁጥር ግን ከ4 ላይ ነው የሚያቆሙት::

ጥበበ ሲራክ ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበለው ከታዘዙት አምላካውያት መጻሕፍት ውጪ ወይም የተውጣጣ ተብሎም ይተረጎማል፣ ሆኖም ተቀምጧል::

# የ6ቱ /ስድስቱ/ ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍትና የአራቱ ግእዝ ትርጉሞች ቀኖናት መነጻጸርያ

## ሰንጠረዥ - ሠሌዳ 3[8]

| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/56/ | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሎዶቅያ) | ቀኖናት ዘቅርጣግና /ካርታጌኒስ | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆ መጻሕፍት | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኖና 85 | ቀኖና 56 | ቀኖና 81 | ቀኖና 80 | ቀኖና 80 | 60ኛ ቀኖና | ቀኖና 24/32 | መልእክት 39ኛ | ቀኖና 1 | ቀኖና 1 | አን ቀጽ 2 | ይዘት |
| ዘፍጥረት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዘጸአት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዘሌዋውያን | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዘኍልቁ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዘዳግም | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ኢያሱ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| መሳፍንት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ሩት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |

8. ከ6ቱ ቀኖናት፡ 60ኛው ቀኖና ዘላኦዶቅያ፣ ቀኖናት ዘካርታጌኒስ፣ መልእክተ አትናቴዎስ፣ ቀኖና ጎርጎርዮስና ቀኖና አምፊሎኪዮስ ወደ ግእዝ አልተመለሱም ወደ ማለት ደርሰናል፡፡



| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/56/ | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሎዶቅያ) | ቀኖናት ዘቅርጣግና /ካርታጌኒስ | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆ መጻሕፍት | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኖና 85 | ቀኖና 56 | ቀኖና 81 | ቀኖና 80 | ቀኖና 80 | 60ኛ ቀኖና | ቀኖና 24/32 | መልእክት 39ኛ | ቀኖና 1 | ቀኖና 1 | አን ቀጽ 2 | ይዘት |
| 1ኛነገሥት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 2ኛነገሥት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | – | ✓ | ✓ | ✓ |
| 3ኛነገሥት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 4ኛነገሥት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | – | ✓ | ✓ | ✓ |
| 1ኛትሩፋት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 2ኛትሩፋት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 1ኛ ዕዝራ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| 2ኛ ዕዝራ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | | ✓ | ✓ |
| ነህምያ | -- | X | X | X | X | -- | -- | -- | -- | -- | -- | ✓ |
| አስቴር | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | -- | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዮዲት | X | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | ✓ | ✓ | X | X | ✓ | ✓ |
| ጦቢት | X | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | ✓ | ✓ | X | X | ✓ | ✓ |
| 1ኛ መቃብያን | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | ✓ | X | X | X | ✓ | ✓ |
| 2ኛ መቃብያን | ✓ | ✓ | X | X | ✓ | X | ✓ | X | X | X | ✓ | ✓ |
| 3ኛ መቃብያን | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ | ✓ |



www.ethiopianorthodox.org

| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀኖና 85 | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/56/ ቀኖና 56 | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 ቀኖና 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81 ቀኖና 80 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሎዶቅያ) 60ኛ ቀኖና | ቀኖናት ዘቅርጣግና ክርታጌኒስ ቀኖና 24/32 | መልእክት አትናቴዎስ መልእክት 39ኛ | ቀኖና ጎርጎርዮስ ቀኖና 1 | ቀኖና አምፊሎክዮስ ዘኢቆንዮን ቀኖና 1 | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆ መጻሕፍት አን ቀጽ 2 | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ ይዘት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መዝሙር | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ኢዮብ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ምሳሌ ሰሎሞን | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ተግሣጽ | X | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| መክብብ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| መሓልይ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ጥ/ሰሎሞን | X | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | ✓ | X | X | ✓ | ✓ |
| ጥበበ ባኅር | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ | X |
| ጥ/ሲራክ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | ✓ | X | X | ✓ | ✓ |
| ሆሴዕ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| አሞጽ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ሚክያስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ኢዩኤል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| አብድዩ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዮናስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ናሆም | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዕምባቆም | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ሶፎንያስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |



| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀኖና 85 | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/56/ ቀኖና 56 | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 ቀኖና 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81 ቀኖና 80 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሎዶቅያ) 60ኛ ቀኖና | ቀኖናት ዘቅርጣግና ክርታጌኒስ ቀኖና 24/32 | መልእክት አትናቴዎስ መልእክት 39ኛ | ቀኖና ጎርጎርዮስ ቀኖና 1 | ቀኖና አምፊሎክዮስ ዘኢቆንዮን ቀኖና 1 | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆ መጻሕፍት አን ቀጽ 2 | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ ይዘት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሐጌ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዘካርያስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ሚልክያስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ኢሳይያስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ኤርምያስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ባሮክ | X | X | X | X | X | ✓ | X | ✓ | | X | X | ✓ |
| ሰ/ኤርምያስ | X | X | X | X | X | ✓ | X | ✓ | X | X | X | ✓ |
| መ/ኤርምያስ | X | X | X | X | X | ✓ | X | ✓ | X | X | X | ✓ |
| ሕዝቅኤል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዳንኤል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዕዝራ ሱቱኤል | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |



www.ethiopianorthodox.org

| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/ 56/ | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሉዶቅያ) | ቀኖናት ዘቅርጣግና ካርታጊኒስ | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆ መጻሕፍት | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኖና 85 | ቀኖና 56 | ቀኖና 81 | ቀኖና 80 | ቀኖና 80 | 60ኛ ቀኖና | ቀኖና 24/32 | መልእክት 39ኛ | ቀኖና 1 | ቀኖና 1 | አንቀጽ 2 | ይዘት |
| ጸሎተ ምናሴ | | | | | | | | | | | | ✓ |
| ተ/ኤርምያስ | | | | | | | | | | | | ✓ |
| ሶስና | | | | | – | | | | | | | ✓ |
| ሠለስቱ ደቂቅ | | | | | | | | | | | | ✓ |
| ተ/ዳንኤል | | | | | | | | | | | | ✓ |
| ኩፋሌ | X | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| ሄኖክ | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | ✓ |
| ሐዲስ ኪዳን | | | | | | | | | | | | ✓ |
| ማቴዎስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ማርቆስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |



| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/ 56/ | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሉዶቅያ) | ቀኖናት ዘቅርጣግና ካርታጊኒስ | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆ መጻሕፍት | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኖና 85 | ቀኖና 56 | ቀኖና 81 | ቀኖና 80 | ቀኖና 80 | 60ኛ ቀኖና | ቀኖና 24/32 | መልእክት 39ኛ | ቀኖና 1 | ቀኖና 1 | አንቀጽ 2 | ይዘት |
| ሉቃስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዮሐንስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ግ/ሐዋርያት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ጳውሎስ ወደ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ሮሜ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ቆሮንቶስ 1 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ቆሮንቶስ 2 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ገላትያ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ኤፌሶን | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ፊሊጵስዩስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ቆላስይስ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |

www.ethiopianorthodox.org

| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/56/ | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጠሊሳት 82 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጠሊስ 81 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሉዶቅያ) | ቀኖናት ዘቅርጣግና /ካርታጌኒስ | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎክዮስ ዘኢቆንዮን | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆመ መጻሕፍት | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኖና 85 | ቀኖና 56 | ቀኖና 81 | ቀኖና 80 | ቀኖና 80 | 60ኛ ቀኖና | ቀኖና 24/32 | መልእክት 39ኛ | ቀኖና 1 | ቀኖና 1 | አንቀጽ 2 | ይዘት |
| ተሰሎንቄ1 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ተሰሎንቄ2 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ጢሞቴዎስ 1 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ጢሞቴዎስ 2 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ቲቶ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ፊሊሞና | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዕብራውያን | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ጴጥሮስ1ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ጴጥሮስ2ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዮሐንስ1ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዮሐንስ2ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ዮሐንስ3ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |



| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/56/ | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጠሊሳት 82 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጠሊስ 81 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሉዶቅያ) | ቀኖናት ዘቅርጣግና /ካርታጌኒስ | መልእክተ አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎክዮስ ዘኢቆንዮን | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆመ መጻሕፍት | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኖና 85 | ቀኖና 56 | ቀኖና 81 | ቀኖና 80 | ቀኖና 80 | 60ኛ ቀኖና | ቀኖና 24/32 | መልእክት 39ኛ | ቀኖና 1 | ቀኖና 1 | አንቀጽ 2 | ይዘት |
| ያዕቆብ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ይሁዳ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| አቡቀለምሲስ | X | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | ✓ | ✓ | X | X | ✓ | ✓ |
| ቀለሚንጦስ 1ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |
| ቀለሚንጦስ 2ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |
| ቀለሚንጦስ 3ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |
| ቀለሚንጦስ 4ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |
| ቀለሚንጦስ 5ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |

www.ethiopianorthodox.org

| በ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍት (88) | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57/56/ | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት አብጥሊሳት 82 | ሥርዐተ ሐዋርያት ቅዱሳን ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጥሊስ 81 | ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሉዶቅያ) | ቀኖናት ዘቅርጣግና /ካርታጌኒስ | መልእክት አትናቴዎስ | ቀኖና ጎርጎርዮስ | ቀኖና አምፊሎክዮስ ዘኢቆንዮን | ፍትሐ ነገሥት ጉልቆ መጻሕፍት | አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ /1980/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀኖና 85 | ቀኖና 56 | ቀኖና 81 | ቀኖና 80 | ቀኖና 80 | 60ኛ ቀኖና | ቀኖና 24/32 | መልእክት 39ኛ | ቀኖና 1 | ቀኖና 1 | አን ቀጽ 2 | ይዘት |
| ቀለሚንጦስ 6ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |
| ቀለሚንጦስ 7ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |
| ቀለሚንጦስ 8ኛ | ✓ | ✓ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X |
| መ/ቀለሚ. ንጦስ 1ኛ | ✓ | X | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | X |
| መ/ቀለሚ. ንጦስ 2ኛ | ✓ | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X | X |
| ት/ሐዋርያት | X | X | X | X | X | X | X | ✓ | X | X | X | X |
| ኖላዊ | X | X | X | X | X | X | X | ✓ | X | X | X | X |
| ድምር 88 | 78/79 | 81 | 81 | 63 | 81 | 67 | 70 | 74 | 63 | 65 | 73 | 85 |



# ምዕራፍ አምስት

# ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ቀኖናውያን ገላጭ ቅጽሎችና ሥርጭቶች

## 1. የቀኖናውያን ገላጭ ቅጽሎች ዓይነቶች

በቅዱሳት ሲኖዶሳት ቀኖናትም ሆነ በቀኖናተ አበው ቤተ ክርስቲያን ለትምህርተ መለኮት፣ ሥርዐተ አምልኮትና ለሕግ ቀኖናዊ መመሪያ፣ ማስተማርያና ማስፈጸሚያ ይሆንዋት ዘንድ እንድትቀበላቸው የታዘዙ በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝተው የተጻፉ ወይም መንፈስ እግዚአብሔር ሰፈኖባቸው - የሚገኙ:

1. ክቡራት/Σεβάσμια/
2. ቅዱሳት /Ἅγια/
3. ንባባውያት - መነበብ ያለባቸው/Ἀναγνωστέα/
4. ምንባባውያት-መነበብ የሚኖርባቸው/Ἀναγινωσκόμενα
5. ቀኖናውያት-ተደንግገው የሚገኙ/Κανονικά-Κεκανονισμένα/
6. ምቅናናውያት-መደንገግ የሚኖርባቸው/Κανονιζόμενα/
7. እሙራት/Γνήσια/
8. አምላካውያት/Θεῖα/
9. መንፈስ እግዜአብሔር ያለባቸው መጻሕፍት /Θεόπνευστα/[1]

---

1. 2ኛ ጢሞ. 3. 16-17. «...የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ተግሣጽ፣ ልብንም ለማንቃት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል»

እነዚህ ቃላት በቀኖናቱ ለቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጡ ቅጽሎች ሲሆኑ የእያንዳንዱ ቅጽል ትርጉምና ትንተና ጥልቅና ሰፊ በመሆኑ አንድ በአንድ እያንዳንዱን ቅጽል በሥነ መለኮት ትርጉምና ትንተና ለመመልከት ምናልባት ከዚህ መጽሐፍ መነሻ ዓላማ ውጪ ሊሆን ባይችልም ራሱን ችሎ በሰፊው የሚታይ በመሆኑ ለጊዜው ታልፍዋል:: ስለ ቅጽሎቹ በመጠኑም ቢሆን ሥነ ትርጓሜና ትንተና ከዚሁ ገጽ 225 - 234 ተመልከት::



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህንና እነዚህን መሰል ቅጽሎች ይዘውና በ6 ሲኖዶሳውያት ቀኖናትና ቀኖናተ አበው ተመልክተው የሚገኙት መጻሕፍት 88 ሲሆኑ ከእነዚህም አብዛኞቹ በ6ቱም ቀኖናት[2] ሲሎች የተወሰኑት ከ6ቱ ቀኖናት በ5ቱ[3]፣ በ4ቱ[4] ወይም በ3ቱ[5] ቀኖናት ከዚያም አንዳንዶቹ በሁለቱ ቀኖናት[6] ወይም በአንዱ ቀኖና ብቻ[7] እየተያዙ እንደሚገኙ ቷመልክተናል።

ሆኖም እነዚህ መጻሕፍት አንድም በተናጠል ወይም በመጣመር እየተቀዱ ይገኙ እንደነበር ሲታወቅ ግን እያደር ከይዘት፣ ከታሪክ፣ ከጽሑፍ ወይም መሰልነት በመነጨ እየተጣመሩ - በአንድ ወጥ ሰነድ እየተጠረዙ መገኘት አስፈላጊ እየሆነ ተገኘ። ለምሳሌ 5ቱ ወይም 8ቱ ብሔረ ኦሪት፣ አርባዕቱ ወንጌላት፣ ወዘተ.። የኅትመት ሥራ እየተፋጠነ በሄደ መጠን የመጻሕፍት ቅጅዎች መባዛት ከመፋጠን ጋር ብዙዎችን በአንድ መጽሐፍ አዋሕዶ መጠረዙ በጣም ቀላል እየሆነ በመገኘቱ እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት አንድም እንደ ይዘቶቻቸው በሁለት ክፍል ብሉይ ኪዳንን ለብቻና አዲስ ኪዳንን ለብቻ አድርጎ መጠረዙ አንዱ ዘዴ ሲሆን ወይም የኅትመት ወረቀት መጠን እየተሻሻለ በመመጣቱ 2ቱን ዓይነት መጻሕፍት - ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን በአንድ ላይ ጠርዞ ማሠራጨቱ ቀላል ሊሆን ቻለ።

ስለዚህ ለአምልኮት አመቺነትም ሆነ ለማስተማር ምንጨ ፍለጋ መንገድ ቀላል መሣሪያ ሆኖ ተገኘ። ሆኖም ግን ባለፉት 6 ቀኖናት የተዘረዘሩት መጻሕፍት ሁሉ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን አገኙ ማለት አይደለም። ሌላው ቀርቶ ራሳቸው ቅዱሳት መጻሕፍትም ቢሆኑ በሁለት ተከፍለው ነው የሚገኙት፣

1. የአንደኛ ቀኖና መጻሕፍት - መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና /Protocanonical Books- Πρωτοκανονικὰ βιβλία/ እና

2. የሁለተኛ ቀኖና መጻሕፍት - መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና /Deuterocanonical Books- Δευτεροκανονικά βιβλία/

በዚህ መልክ የአንደኛ ቀኖና መጻሕፍት - መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና እና የሁለተኛ ቀኖና መጻሕፍት - መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና የሚለው ክፍፍል የሚታየው በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአሁኑ ጊዜ በሁለት ክፍሎች ተከፍለው ይገኛሉ፣ 1ኛ. የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን - ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን እና ሌላው የሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል የአንደኛው ቀኖና መጻሕፍት - መጻሐፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ሲባሉ የሁለተኛው ቀኖና መጻሕፍት -መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተብለው ተለይተው

---

2. ከዚሁ ገጽ 68 የግርጌ ማስታወሻ 27።
3. ከዚሁ ገጽ 70 የግርጌ ማስወሻ 28።
4. ከትርጉም ይደረስባቸዋል ተብለው ከሚታሰቡት በስተቀር (ባሮክ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስና መልእክተ ኤርምያስ) ከ6ቱ ቀኖናት በ4ቱ ቀኖናት ተይዘው የሚገኙ መጻሕፍት የሉም። ከዚሁ ገጽ 71 የግርጌ ማስታወሻ 29።
5. ከዚሁ ገጽ 71 የግርጌ ማስታወሻ 30።
6. ከዚሁ ገጽ 72 የግርጌ ማስታወሻ 31።
7. ከዚሁ ገጽ 73 የግርጌ ማስታወሻ 32።

www.ethiopianorthodox.org

ይታያሉ[8]:: በሌላ በኩል በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ታቅፈው የሚገኙት መጻሕፍት በሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን - መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ሲሆኑ መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ግን በዕብራይስጥ አይገኙም::

አዲስ ኪዳንን በሚመለከት መሠረቱ የተጻፈበት ቋንቋ ጽርእ ሲሆን አሁንም በሁለቱ መጻሕፍተ ሐዲስ ኪዳን መካከል የልዩነት ጥያቄ የለም:: ግን በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና «ብእኔ በቀለሚንጦስ እጅ የተላኩ 8 መጻሕፍትን - ሐዋርያውያት ትእዛዛትን» በሚመለከት ግን ልዩነት አለ:: ከእነዚህ 8 መጻሕፍት - ሐዋርያውያት ትእዛዛት ጋር ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስን ተመልክተናል:: እነዚህ መጻሕፍት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንደ ሐዲስ ኪዳን

---

8. መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ሲዘረዘሩ ባያስፈልግም መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና የሚከተሉት ናቸው::

| በቀኖናተ መጻሕፍት የሚገኙት | በቀኖናተ መጻሕፍት የማይገኙ |
| --- | --- |
| - ዕዝራ ካልዕ | - ዕዝራ ሰቱኤል |
| - ባሮክ | - ጸሎተ ምናሴ |
| - ዮዲት | - ተረፈ ኤርምያስ- መጽሐፈ ኤርምያስ |
| - አስቴር-በከፊል | - ኩፋሌ |
| - ጥበበ ሰሎሞን | - ሄኖክ |
| - ጥበበ ሲራክ | |
| - ሶስና | |
| - ቤልና ደራጎን-(ምስልና ዘንዶ) ተረፈ ዳንኤል | |
| - ጸሎተ-መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ | |
| - መልክተ ኤርምያስ | |
| - 3 መቃብያን | |

የማቴዎስ ወንጌል በዕብራይስጥ/አዲስ አረማይስጥ/ እንደተጻፈና ግን ወዲያውኑ ወደ ጽርእ እንደተመለሰ ሊቃውንት ያስተምራሉ:: አውሳብዮስ ዘቂሳርያ:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከዚሁ ገጽ 174 የግርጌ ማስታወሻ 24::



መጻሕፍት ተቆጥረው ተቀባይነት የላቸውም:: ምክንያቱም በ691 በትሩሎ በተሰበሰበው 5ኛ-6ኛ ሲኖዶስ ከቤተክርስቲያን ትምህርት ጋር የሚቃረኑ ድንጋጌዎችን ይዘው በመገኘታቸው እንዳልጸደቁ ይታወቃል:: ሁለቱ መልእክታትም (መልእክታተ ቀለሚንጦስ) በዚሁ ድንጋጌ እንደተሻፈኑ ይታመናል:: ደጋግመን እንደተረዳነው ከመለያየት በኋላ የተጠራ ጉባኤ በመሆኑ በዚህ ጉባኤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አልተካፈለችም:: ውሳኔውም አያስራትም:: እነዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት ከትምህርትዋ እና እምነትዋ ጋር አብረው የማይሄዱ ወይም የሚቃረኑ ሁነው ከአልተገኙ በስተቀር::

በፍትሐ ነገሥት መተርጉማንም ሆነ በሊቃውንት ጉባኤ በፍትሐ ነገሥቱ ከተዘረዘሩት 73 መጻሕፍትም ላይ የተጨመሩት የተለያዩ 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥርን ወደ 81 የሚያደርሱት አለመሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምታስተምረው 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን ከ27 ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በመደመር /27+8=35/ 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንዳሉ መሆኑን መቀበል ግዴታ ይሆናል:: ስለዚህም ነው 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 81 መጻሕፍት የሚሆኑት:: ይህን በዝርዝር ለማመልከት ተሞክሯል:: ቢሆንም እስከ 1918 - 1980 በታተሙት ቅዱሳት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አልገቡም::

እንግዲህ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ታትመው በሥርጭት ላይ የሚገኙትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት - ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን፣ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናትና ከ1918 - 1980 በተከታታይ በኢትዮጵያ የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሐዲስ ኪዳንን በሚመለከት የግሪክና የግእዝ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በማነጻጸር ግንኙነትን ወይም ልዩነትን እንመለከታለን::



www.ethiopianorthodox.org

## 2. የቅዱሳት መጻሕፍት ሥርጭቶች

### 2.1 ማሶራዊ - ብሉይ ኪዳን - የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት/Masoretic old testament/[9]

በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ በአገልግሎትና ጥናት ላይ የሚገኘው ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን «ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን» ተብሎ የሚታወቀው ሰነድ ነው::

ይህም ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ቀደም ከአለ ጊዜ ጀምሮ በተለያየ መልክ እየታተመ ወደጊዜያችን ደርሷል:: ይህን ብሉይ ኪዳን ከሰብዐ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን ጋር በማነጻጸር ልዩነቱን መገንዘብ ይቻላል:: በዚህም መልኩ ማሶራዊ - ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ከኦርቶዶክስ እና ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር አብሮ አይሄድም ምክንያቱም እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ዳግማውያት ቀኖናውያት መጻሕፍትን ስለሚቀበሉ ሲሆን ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን ግን እነዚህን አይሸፍንምና ነው::

የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት /Masoretic old testament/ ዝርዝር[10]

1. አምስቱ ብሔረ ኦሪት /Pentateuchus/
   - 1.1 ዘፍጥረት
   - 1.2 ዘጸአት
   - 1.3 ዘሌዋውያን
   - 1.4 ዘኍልቁ
   - 1.5 ዘዳግም
2. ቀደምት ነቢያት /Prophetae Priores/
   - 2.1 ኢያሱ ወልደ ነዌ
   - 2.2 መሳፍንት
   - 2.3 ሳሙኤል 1ኛ
   - 2.4 ሳሙኤል 2ኛ
   - 2.5 ነገሥት 1ኛ
   - 2.6 ነገሥት 2ኛ
3. ደኅርት ነቢያት /Prophetae posteriores/
   - 3.1 ኢሳይያስ
   - 3.2 ኤርምያስ
   - 3.3 ሕዝቅኤል
   - 3.4 ሆሴዕ
   - 3.5 ኢዮኤል
   - 3.6 አሞጽ
   - 3.7 አብድዩ
   - 3.8 ዮናስ
   - 3.9 ሚክያስ
   - 3.10 ናሆም
   - 3.11 ዕንባቆም
   - 3.12 ሶፎንያስ
   - 3.13 ሐጌ
   - 3.14 ዘካርያስ
   - 3.15 ሚልክያስ
4. የዕብራይስጥ ቅዱስ ሥነ ጽሑፍ /Hebrew Hagiographa/
   - 4.1 መዝሙራት
   - 4.2 ምሳሌያት
   - 4.3 ኢዮብ
   - 4.4 ማሕልየ መሓልይ
   - 4.5 ሩት
   - 4.6 ሰቆቃወ ኤርምያስ
   - 4.7 መክብብ
   - 4.8 አስቴር
   - 4.9 ዳንኤል
   - 4.10 ዕዝራ
   - 4.11 ነህምያ
   - 4.12 ዜና መዋዕል 1ኛ
   - 4.13 ዜና መዋዕል 2ኛ

የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 39

### 2.2 ጽርእ - ግሪክ ቅዱሳት መጻሕፍት

#### 2.2.1 ጽርእ - ግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት

« የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ በውስጡ የተጻፈውን ቀንም ሌሊትም ታጠናለህ»[11]

9. ማሶራዊ ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን /Masoretic old testament / በሚል የሚታወቀው ብሉይ ኪዳን በ8ኛው - 9ኛው ምዕተ ዓመት በአይሁድ ሊቃውንት ፊደሉቹ፣ የፊደሉቹ ድምጾች አናጋሪዎች፣ ምልክቶች ቁጥሮቹም ተስተካክለው የተዘጋጀው ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ነው:: ማሶራህ - Massorah በዕብራይስጥ ልምድ-ትውፊት ማለት ነው::
10. Norman Henry Snaith-printed in Great Britain by Lowe and Brydone(Printers) LTD. London N.W.10 1966 (1958)
11. ኢያሱ ወልደ ነዌ 1:8::



www.ethiopianorthodox.org

አሁንም የሚመሩትና ቀጥሎም ከማሶራዊ - ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳንና ግእዝ - አማርኛ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር የሚመሳከሩት የጽርእ-ግሪክ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በ1950(እ.አ) ታትመው የሚገኙ ናቸው:: ወይም በጥቅል ርእሳቸው ወደፊትም እንደሚጠቀሱበት «ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት (Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τούς έβδομήκοντα)

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በመጀመሪያ የተጻፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜም የተተረጎሙት ወደ ግሪክ ቋንቋ ነው:: ይህም ትርጉም «የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም» ተብሎ ይታወቃል /ሰብዓሊቃናት- ሊቃውንት ስለተረጎሙት ነው/:: የሰብዓ ሊቃናት ትርጉመ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን ተብሎ ከሚታወቀው ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ሲተያይ የሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በማሶራዊ ብሉይ ኪዳን የማይገኙ መጻሕፍትን ይዞ ይገኛል:: ይህም ሁለቱንም ብሉይ ኪዳኖች በማነጻጸር ይታያል::

በዚህ መልክ የሚገኘው የሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን እንደሚታወቀው ሁለት ንዑሳት - ክፍላተ መጻሕፍትን: ቀዳሚያውያት ቀኖናውያት መጻሕፍትን - መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና እና ዳግማውያት ቀኖናውያት - ምንባባውያት መጻሕፍትን -መጻሕፍትን ዘዳግም (ካልዕ) ቀኖና ይዞ ይገኛል:: ዳግማውያት ቀኖናውያት መጻሕፍት - መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተብለው የሚታወቁ በማሶራዊ ብሉይ ኪዳን አይገኙም:: በዚህ ብቻ ሳይሆን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቀኖናተ መጻሕፍትም አይገኙም::

ስለዚህ እነዚህ መጻሕፍት እንዲነጻጸሩ ተደርጐ ልዩነቶቻቸው ይመለከታሉ::



የሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኁልቁ
5. ዘዳግም
6. ኢያሱ
7. መሳፍንት
8. ሩት
9. 1ኛ ነገሥት
10. 2ኛ ነገሥት
11. 3ኛ ነገሥት
12. 4ኛ ነገሥት
13. 1ኛ ትሩፋት
13. 2ኛ ትሩፋት
15. 1ኛ ዕዝራና
16. 2ኛ ዕዝራ
17. ነህምያ
18. ጦቢት
19. ዮዲት
20. አስቴር
21. 1ኛ መቃብያን
22. 2ኛ መቃብያን
23. 3ኛ መቃብያን
24. መዝሙራተ ዳዊት
25. ኢዮብ
26. ምሳሌያተ ሰሎሞን
27. መክብብ
28. ማሕልየ መሓልይ
29. ጥበበ ሰሎሞን
30. ጥበበ ሲራክ
31. ሆሴዕ
32. አሞጽ
33. ሚክያስ/ሚኬያስ/
34. ኢዩኤል
35. አብድዩ/አብዩድ/
36. ናሆም/ናሑም/
37. ዮናስ
38. ዕንባቆም/አባኩም/
39. ሶፎንያስ
40. ሐጌ/አንጌዮስ/
41. ዘካርያስ
42. ሚልክያስ/ማላኪያስ/
43. ኢሳይያስ
44. ኤርምያስ
45. ባሮክ
46. ሰቆቃወ ኤርምያስ
47. መልእክተ ኤርምያስ
48. ሕዝቅኤል
49. ዳንኤል
50. አባሪ መቃብያን 4ኛ

www.ethiopianorthodox.org

በሰብዓ ሊቃናት ዘንድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 49/ወይም 49 + 1 = 50 ናቸው::

### 2.2.2 ጽርእ-ግሪክ ሐዲስ ኪዳን - ΚΑΙΝΗ ΔΙΑΘΗΚΗ

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከማቴዎስ ወንጌል በስተቀር የተጻፉበት ቋንቋ ግሪክ/ልሳነ ጽርእ/ እና ቁጥራቸውም /ብዛታቸውም/ 27 መሆኑ በአብዛኞቹ ዘንድ ተቀባይነት እንደአለው ይታወቃል::

በዚህ በኩል በግሪክ ቋንቋ ለመጻፋቸው ልዩነት ባይኖርም ቁጥራቸውን /ብዛታቸውን/ በሚመለከት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ:: ይህም ልዩነት ሊመነጭ የቻለው በመጀመሪያ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና 2 መልእክታተ ቀላሚንጦስ እና 8 ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በ«ሐቡራትና ቅዱሳት» መጽሕፍት ዝርዝር ውስጥ ተመዝግበው ስለሚገኙ በዚህ ጊዜ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 37/27+2+8 = 37/ መጻሕፍት ሆነው ሊታሰቡ ችለዋል:: ነገር ግን በአንድ በኩል እነዚህ ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ መልእክታትን ጨምረው በውስጣቸው ባሉት ምሥጢራት ምክንያት ለሕዝብ እንዳይሰራጩ[12] የሚል ሐረግን ቀኖናው ይዞ ከመገኘቱ ጋር በሌላ በኩል በሌሎች ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ተወስነው አይገኙም:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ 2 መልእክታተ ቀለሚንጦስም ሆኑ 8 ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ገብተው አይቆጠሩም:: ምክንያቱም በ692 5ኛ - 6ኛ የትሩሎ ሲኖዶስ እንደሌሎች 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተቆጥረው ሳይጸድቁ አልፈዋል:: በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በኩል ግን በአንድ በኩል ይህንን ሲኖዶስ እንደማትቀበለው ሲታወቅ በሌላ በኩል የሁለቱም መልእክታተ ቀለሚንጦስ ሁኔታ ባይወሳም 8ቱ ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ /መጻሕፍተ



ቀለሚንጦስ/ 8 ብሔር ዘቀለሚንጦስ/ እንደ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተቆጥረው ይኸው 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንዳሉ ይታመናል:: ግን የፍትሐ ነገሥት መተርጉማንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ የራሳቸው አመለካከት አላቸው:: ወደፊት እንመለከተዋለን::

ግሪክ አዲስ ኪዳን

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. የሐዋርያት ሥራ

የጳውሎስ መልእክታት:

6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
8. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17. ወደ ቲቶ
18. ወደ ፊልሞና
19. ወደ ዕብራውያን
20. ጴጥሮስ 1ኛ
21. ጴጥሮስ 2ኛ
22. ዮሐንስ 1ኛ
23. ዮሐንስ 2ኛ
24. ዮሐንስ 3ኛ
25. መልእክተ ያዕቆብ
26. መልእክተ ይሁዳ
27. መልእክተ ይሁዳ
28. አቡቀለምሲስ

### 2.2.3 የግእዝ - አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ የተተረጎሙት ወደ ጥቂቶች ሌሎች የጥንት ቋንቋዎች

---

12. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ቃል በቃል እንኳን ባይሆን ሰፋ በሚል ዝርዝር ሥልጠን ከተሰጣቸው ካህናት በስተቀር::

www.ethiopianorthodox.org

ከመተርጎማቸው አስቀድሞ ነው:: ሆኖም በእጅ ጽሑፎች እየተገለበጡ በአድባራትና ገዳማት፣ በሊቃውንት እጆች ከመገኘታቸው በስተቀር ወደ ሕዝብ እጅ የመግባታቸው ጉዳይ እጅግ ጠባብ ነበር:: ቢሆንም በየወቅቱ ይደረግ የነበረው የሊቃውንት ድካም ቀላል አልነበረም:: ስለዚህ ወደ ቅርቡ የዚህ ምዕተ አመት መጀመሪያ ብንመለስ የድካም ውጤት ፍሬን እንመለከታለን::

### 2.3.1 የ1918 የእጅ ጽሑፎች ቅዱሳት መጻሕፍት ሥርጭት

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተለይ በራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ቅዱሳት መጻሕፍትም ሆኑ ሌሎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የምታስተምረባቸውና የምትጠቀምባቸው - የምትገለ ገልባቸው መጻሕፍት በእጅ እየተቀዱ - እየተገለበጡ እንዲሠራጩ የተደረገው ጥረት ከፍተኛ ቢሆንም የበለጠ ግን እየታተሙ ቢሠራጩ ለተጠቃሚዎች በቀላሉ እንደሚደርሱ በማመን የኅትመት ሥራንና ዘዴን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት እነዚህ የቤተክርስቲያኗ ቅዱሳት መጻሕፍት እየታተሙ በፍጥነት እንዲሠራጩ አድርገዋል:: በዚህም መሠረት የሌሎች የቤተክርስቲያን የትምህርትና የአገልግሎት መጻሕፍት ተባዝተው የመሠራጨታቸው ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ብንመለከት በመጀመሪያ 5ቱ መጻሕፍተ ሰሎሞን፣ መጽሐፈ - ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ አርባዕቱ ወንጌላት ከነትርጓሜአቸው እንዲታተሙ ተደርጎ የሌሎችም መጻሕፍት ኅትመት እንዲቀጥል እየተደረገ እያለ ይህን ጥረት የጠላት ወረራ አሰናከለው:: በተለይ ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ከፍተኛ ድካምን ጠይቀው የተዘጋጁት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ትርጓሜ የእጅ ጽሑፎች መጥፋታቸው ነበር::

ይህም እንድምታ ትርጓሜን በሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ጥረት ግእዝን የማያውቀው ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ እንዲረዳ ለማድረግ በማሰብ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በ1918 በነጠላ ትርጓሜ /ትርጉም/ ተተርጉመው እንዲገኙ አስደርገው ነበር[13.1]::

ነገር ግን ግእዝ ሐዲስ ኪዳንን በሚመለከት ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ገና በጣም ቀደም ብሎ በተለያዩ የውጪ አገሮች ከተሞች: በ1548 - 1549 በሮም በ1826 በለንደንና ተሻሽሎ በ1899 ላይፕዚግ (Leipzig) እየታተመ ተሠራጭቶ እንደነበር ይታወሳል[13.2] ::

የ1918 የእጅ ጽሑፎች ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚከተለው ነው::

1ኛ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኁልቁ
5. ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ
10. መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ
11. መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ
12. መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ
13. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳሚ
14. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ

13.1 መጽሐፈ ቅዳሴ በግእዝና በአማርኛ 1942 ገጽ 3 - 4::
13.2 Petrus Ethiops: The Ethiopic New testament, 1548-1549. Rome, Platt T. Pell: The Ethiopic New Testament, 1826, London. F. Praetorius: The Ethiopic New Testament; 1899, Leipzig.

www.ethiopianorthodox.org

15. መጽሐፈ ዕዝራ
16. መጽሐፈ ነህምያ
17. መጽሐፈ አስቴር
18. መጽሐፈ ኢዮብ
19. መጽሐፈ መዝሙራት ዘዳዊት
20. መጽሐፈ ምሳሌ
21. መጽሐፈ መክብብ
22. መጽሐፈ ማሕልየ መሓልይ
23. ትንቢተ ኢሳይያስ
24. ትንቢተ ኤርምያስ
25. ሰቆቃወ ኤርምያስ
26. ትንቢተ ሕዝቅኤል
27. ትንቢተ ዳንኤል
28. ትንቢተ ሆሴዕ
29. ትንቢተ አሞጽ
30. ትንቢተ ሚክያስ
31. ትንቢተ ኢዩኤል
32. ትንቢተ አብድዩ
33. ትንቢተ ዮናስ
34. ትንቢተ ናሆም
35. ትንቢተ ዕንባቆም
36. ትንቢተ ሶፎንያስ
37. ትንቢተ ሐጌ
38. ትንቢተ ዘካርያስ
39. ትንቢተ ሚልክያስ
40. መጽሐፈ ኩፋሌ
41. መጽሐፈ መቃብያን (3 መቃብያን)
42. መጽሐፈ ሄኖክ
43. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል
44. መጽሐፍ ዕዝራ ካልእ
45. መጽሐፈ ጦቢት
46. መጽሐፈ ዮዲት
47. መጽሐፈ ጥበብ/ዘሰሎምን/
48. መጽሐፈሲራክ/ጥበበ ሲራክ
49. መጽሐፈ ባሮክ
50. መጽሐፈ ኤርምያስ (ተረፈ ኤርምያስ)
51. መጽሐፈ ሶስና
52. ተረፈ ዳንኤል

ድምር 52

2ኛ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1. ወንጌል ዘማቴዎስ
2. ወንጌል ዘማርቆስ
3. ወንጌል ዘሉቃስ
4. ወንጌል ዘዮሐንስ
5. ግብረ ሐዋርያት
6. መልእክተ ጳውሎስ -ኀበ ሰብአ ሮሜ
7. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ
8. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ካልዕ
9. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ገላትያ
10. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ኤፌሶን



11. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ፊልጵስዩስ
12. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆላስይስ
13. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ተሰሎንቄ ቀዳማዊ
14. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ተሰሎንቄ ካልዕ
15. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ጢሞቴዎስ ቀዳማዊ
16. መልእክተጳውሎስ ኀበ ጢሞቴዎስ ካልዕ
17. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ቲቶ
18. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ፊልሞና
19. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ዕብራውያን
20. መልእክተ ጴጥሮስ ቀዳሚት
21. መልእክተ ጴጥሮስ ካልዒት
22. መልእክተ ዮሐንስ ቀዳሚት
23. መልእክተ ዮሐንስ ካልዒት
24. መልእክተ ዮሐንስ ሣልሲት
25. መልእክተ ያዕቆብ
26. መልእክተ ይሁዳ
27. ራእየ ዮሐንስ/ አቡቀለምሲስ

ድምር 27

ስለዚህም 52 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር 79(52+27=79) ግን 52 + 2 +27 =81 ነው።

## 2.3.2 የ1929 የፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት

ጠላት ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት /1928 1933/ ብዙዎች የእጅ ጽሑፎችም ሆኑ የታተሙ መጻሕፍት በጠላት እጅ እየገቡ ወደ ባዕድ አገር ቢወሰዱምና ሌሎችም ቢወድሙም ከእነዚህ መካከል ግን ንጉሠ ነገሥቱ በ1918 በነጠላ ትርጓሜ/ትርጉም/ አስተርጉመው በብራና በእጅ አጽፈውና በአንድነት አስጠርዘዋቸው የነበሩት የተጠቀሱት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በጠላት እጅ ወድቀው ድራሻቸው ሳይጠፋ ቆይተው በአጋጣሚ ወደ ለንደን ተወስደው በስደት ላይ

www.ethiopianorthodox.org

ለነበሩት ንጉሠ ነገሥት ደረሷቸው:: ስለዚህም እነዚህ መጻሕፍት በለንደን በ1929 በአራት ክፍል ተከፍለው /በአራት ጥራዝ ተጠርዘው/ በፎቶ ኦፍ ሴት ተባዝተው ሊሠራጩ ችለዋል:: የዚህም ፎቶ ኦፍ ሴት መጻሕፍት 52 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት = 79 መጻሕፍት /52+27 = 79/ ወይም 52 + 2 + 27 =81 ናቸው[14]::

እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት የተዘረዘሩት የ1981 እጅ ጽሑፎች ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት በመሆናቸው ልዩነት ባይኖራቸውም በ4 ክፍሎች እንደሚከተለው ተጠርዘው ይታያሉ::

1ኛ ክፍል/ብሉይ ኪዳን - ጥራዝ 1/

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ
10. መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ
11. መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ
12. መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ
13. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
14. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ
15. መጽሐፈ ዕዝራ
16. መጽሐፈ ነህምያ
17. መጽሐፈ አስቴር

---

14. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 52 ናቸው ሊባሉ የቻሉበት ምክንያት 3 መጻሕፍተ መቃብያን እንደአንድ መጽሐፍ ሆነው ስለተቆጠሩ ነው ነገር ግን ስለዚህ በዚህ ኅትመት ተባዝተው የሚገኙት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 52 እና 2(52+2 = 54) 54 ናቸው:: በዚህም በመነጨ በዚህ ኅትመት የሚታዩት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 52+27 = 79 ሳይሆኑ 54 + 27 = 81 ናቸው::

2ኛ ክፍል/ብሉይ ኪዳን ጥራዝ 2/

18. መጽሐፈ ኢዮብ
19. መጽሐፈ መዝሙራት ዘዳዊት
20. መጽሐፈ ምሳሌ
21. መጽሐፈ መክብብ
22. መጽሐፈ ማሕልይ መሓልይ
23. ትንቢተ ኢሳይያስ
24. ትንቢተ ኤርምያስ
25. ሰቆቃው ኤርምያስ
26. ትንቢተ ሕዝቅኤል
27. ትንቢተ ዳንኤል
28. ትንቢተ ሆሴዕ
29. ትንቢተ አሞጽ
30. ትንቢተ ሚክያስ
31. ትንቢተ ኢዩኤል
32. ትንቢተ አብድዩ
33. ትንቢተ ዮናስ
34. ትንቢተ ናሆም
35. ትንቢተ ዕንባቆም
36. ትንቢተ ሶፎንያስ
37. ትንቢተ ሐጌ
38. ትንቢተ ዘካርያስ
39. ትንቢተ ሚልክያስ

3ኛ ክፍል/ብሉይ ኪዳን-ጥራዝ 3/

40. መጽሐፈ ኩፋሌ
41. መጽሐፈ መቃብያን
42. መጽሐፈ ሄኖክ
43. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል
44. መጽሐፍ ዕዝራ ካልዕ
45. መጽሐፈ ጦቢት
46. መጽሐፈ ዮዲት
47. መጽሐፈ ጥበብ/ዘሰሎሞን/
48. መጽሐፈ ሲራክ/ጥበበ ሲራክ/
49. መጽሐፈ ባሮክ
50. መጽሐፈ ኤርምያስ
51. መጽሐፈ ሶስና
52. ተረፈ ዳንኤል

4ኛ ክፍል/ሐዲስ ኪዳን ጥራዝ 4/

1. ወንጌል ዘማቴዎስ
2. ወንጌል ዘማርቆስ
3. ወንጌል ዘሉቃስ
4. ወንጌል ዘዮሐንስ
5. ግብረ ሐዋርያት
6. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ሮሜ
7. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ
8. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆሮንቶስ ካልዕ
9. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ገላትያ
10. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ኤፌሶን

www.ethiopianorthodox.org

11. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ፊልጵስዩስ
12. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ቆላስይስ
13. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ተሰሎንቄ ቀዳማዊ
14. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ተሰሎንቄ ካልዕ
15. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ጢሞቴዎስ ቀዳማዊ
16. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ጢሞቴዎስ ካልዕ
17. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ቲቶ
18. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ፊልሞና
19. መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ዕብራውያን
20. መልእክተ ጴጥሮስ ቀዳሚት
21. መልእክተ ጴጥሮስ ካልዒት
22. መልእክተ ዮሐንስ ቀዳሚት
23. መልእክተ ዮሐንስ ካልዒት
24. መልእክተ ዮሐንስ ሣልሲት
25. መልእክተ ያዕቆብ
26. መልእክተ ይሁዳ
27. ራእየ ዮሐንስ/አቡቀለምሲስ

ድ ም ር 27

ስለዚህ 52 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር= 79 (52+27 =79/ ግን 52 + 2 + 27 = 81 መሆኑን ገልጠናል::

## 2.3.3 የ1947/1953/ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት

በ1929 ቅዱሳት በአራት ክፍሎች ተከፍለውና በፎቶ አፍ ሴት ተባዝተው መሠራጨታቸው ቢታወቅም በአንድ በኩል በቀላሉ ለሕዝብ ሊዳረሱ ካለመቻላቸው በሌላም በኩል በአራት ክፍሎች ተጠርዘው እንደመሠራጨታቸው መጠን ሁሉንም በአንድነት አግኝቶ ለመጠቀም ወይም ለመገልገል ካለመቻል የተነሳ እንደገና የማሳተሙ አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን በአንድ ጥራዝም አጠቃሎ ማሠራጨቱ እጅግ ተፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ግልጽ ነበር::

ስለዚህም ንጉሠ ነገሥቱ ቅዳሳት መጻሕፍቱ ከተተረጐሙባቸው ቋንቋዎች ዕብራይስጥና ጽርእ-ግሪክ ጋር እየተያዩ ወይም እየተመሳከሩ ታርመው እንዲታተሙ ለማድረግ በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ተገቢ ዕውቀት ያላቸውን ሊቃውንት መርጠው በማሳባሰብ የካቲት 27 ቀን 1939 ዓ.ም. አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ እንዲቋቋም አደረጉ፤ ኮሚቴውም በትጋትና በቅንነት 5/አምስት/ ዓመት ያህል በተፈለገ መጠን ሠርቶ የሥራውን ውጤት - ታርመው የተዘጋጁት ቅዱሳት መጻሕፍትን በ1940 ዓ.ም. አቅርቦ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ በ1947/1953/ በአንድ ጥራዝ ታትመው ሊሠራጩ ችለዋል[15]::

በ1947 /1953/ የታተሙት ቅዳሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚከተለው ነው::

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት:-

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኍልቁ
5. ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. መጽሐፈ ሳሙኤል
10. መጽሐፈ ሳሙኤል
11. መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ
12. መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ
13. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
14. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ
15. መጽሐፈ ኩፋሌ
16. መጽሐፈ ሄኖክ
17. መጽሐፈ ዕዝራ
18. መጽሐፍ ነህምያ
19. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል
20. መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ
21. መጽሐፈ ጦቢት
22. መጽሐፈ ዮዲት
23. መጽሐፈ አስቴር
24. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
25. መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ
26. መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ

15. ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በመቅድሙ ላይ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ በዘመነ መንግሥታቸው 25ኛ ዓመት 1947 እንዲታተም መታዘዙ ሲታይ ሽፋኑ ግን በ1953 [illegible]



www.ethiopianorthodox.org

27. መጽሐፈ ኢዮብ
28. መዝሙረ ዳዊት
29. መጽሐፈ ምሳሌ
30. ተግሣጽ
31. መጽሐፈ ጥበብ
32. መጽሐፈ መክብብ
33. ማሕልየ መሓልይ
34. መጽሐፈ ሲራክ
35. ትንቢተ ኢሳይያስ
36. ትንቢተ ኤርምያስ
37. መጽሐፈ ባሮክ
38. ሰቆቃወ ኤርምያስ
39. ትንቢተ ሕዝቅኤል
40. ትንቢተ ዳንኤል
41. ትንቢተ ሆሴዕ
42. ትንቤተ አሞጽ
43. ትንቢተ ሚክያስ
44. ትንቢተ ኢዩኤል
45. ትንቢተ አብድዩ
46. ትንቢተ ዮናስ
47. ትንቢተ ናሆም
48. ትንቢተ ዕንባቆም
49. ትንቢተ ሶፎንያስ
50. ትንቢተ ሐጌ
51. ትንቢተ ዘካርያስ
52. ትንቢተ ሚልክያስ

<u>የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት</u>

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. ግብረ ሐዋርያት
   የጳውሎስ መልእክታት
6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
8. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17. ወደ ቲቶ
18. ወደ ፊልሞና
19. ዕብራውያን
20. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ
21. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
22. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
24. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
25. የያዕቆብ መልእክት
26. የይሁዳ መልእክት
27. የዮሐንስ ራዕይ



## 2.3.4 የ1980 ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት

በ1947(1953) ታትሞና ተሠራጭቶ የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ በማለቁ እንደገና እንዲታተም የማድረጉ አስፈላጊነት በማስገደዱ በዚያን ወቅት ኅትመት ከቤተ ክርስቲያን ሥነ ቃል ውጭና የማይስማሙ፣ ቅርጸም ጋር የማይጣጣሙ ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን ቅዱስ ሲኖዶስ ተመልክቶና አስተካክሎ እንዲታተም አድርጓል:: ከዚህም በስተቀር ብሉይ ኪዳን ከእናት ቋንቋው ዕብራይስጥና ሐዲስ ኪዳንም ከእናት ቋንቋው ግሪክ/ጽርእ/ ጋር እንዲታያዩ እና የተከሰቱ ልዩነቶች እንዲመለከቱ ተደርገው ይገኛሉ[16]::

ሆኖም ግን ተገቢው ጥንቃቄ ተደርጎ የታተሙ መሆናቸው ምን ያህል ልክ ነው? ነገር ግን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንጂ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በስብዓ ሊቃናትም ሆነ ማሶራዊ-ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር እንዳልተመሳከሩ ታውቋል:: ቢያስፈልግ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን ከ1947 ኅትመት ብሉይ ኪዳን ጋር አመሳክሮ መረዳት ይቻላል:: መጻሕፍቱ በሁለት ተከፍለው ማለትም የ1ኛ ቀኖና መጻሕፍትና የ2ኛ ቀኖና መጻሕፍት ተብለው ተጠርዘው ይገኛሉ:: በትክክል በሁለቱም ክፍሎች የተደረደሩት መጻሕፍት በየቦታው ነው ወይ የተደረ ደሩት? ወደፊት አንድ በአንድ ይታያሉ:: አንድ አንድ ምንጭ እንኳን ቢቀር መሰል የሌላቸው መጻሕፍት አብረው ታትመዋል:: ዕዝራ ሱቱኤል

---

16. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1980 አዲስ በታተመ መጽሐፍ ቅዱስ (Amharic Bible DC R083 UBS-EPF 1988), መቅድም::

www.ethiopianorthodox.org

ወይም በሰብዓ ሊቃናት አንደኛ መጽሐፈ ዕዝራ የሚባለው በዚህ ኅትመት 2ኛ መጽሐፈ ዕዝራ ተብሎ ይገኛል:: የሰብዐ ሊቃናት ዕዝራ ቀዳማዊ በግእዝ ዕዝራ ካልዕ ሆኖ ይገኛል:: ሌሎችም ችግሮች አሉበት::

<u>የብሉይ ኪዳን የ1ኛ ቀኖና መጻሕፍት -</u>

<u>መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና</u>

1. ዘፍጥረት
2. ዘጸአት
3. ዘሌዋውያን
4. ዘኁልቁ
5. ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ
10. መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ
11. መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማማዊ
12. መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ
13. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
14. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ
15. መጽሐፈ ዕዝራ
16. መጽሐፈ ነህምያ[17]
17. መጽሐፈ አስቴር
18. መጽሐፈ ኢዮብ
19. መዝሙረ ዳዊት
20. መጽሐፈ ምሳሌ
21. መጽሐፈ ተግሣጽ
22. መጽሐፈ መክብብ
23. ማሕልየ መሓልይ
24. ትንቢተ ኢሳይያስ
25. ትንቢተ ኤርምያስ
26. ሰቆቃወ ኤርምያስ
27. ትንቢተ ሕዝቅኤል
28. ትንቢተ ዳንኤል
29. ትንቢተ ሆሴዕ

---

17. መጽሐፈ ዕዝራ በዚህ ስም «ነህምያ» በማንኛውም ቀኖና አልተመለከተም::



30. ትንቢተ አሞጽ
31. ትንቢተ ሚክያስ
32. ትንቢት ኢዩኤል
33. ትንቢተ አብድዩ
34. ትንቢተ ዮናስ
35. ትንቢተ ናሆም
36. ትንቢተ ዕንባቆም
37. ትንቢተ ሶፎንያስ
38. ትንቢተ ሐጌ
39. ትንቢተ ዘካርያስ
40. ትንቢተ ሚልኪያስ

<u>የብሉይ ኪዳን 2ኛ ቀኖና መጻሕፍት-</u>

<u>መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና</u>

41. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል
42. መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ
43. መጽሐፈ ጦቢት
44. መጽሐፈ ዮዲት
45. መጽሐፈ አስቴር
46. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
47. መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ
48. መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ
49. መጽሐፈ ሲራክ
50. ጸሎተ ምናሴ
51. ተረፈ ኤርምያስ
52. ሶስና
53. መጽሐፈ ባሮክ
54. መጽሐፈ ጥበብ-ዘሰሎሞን
55. መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ
56. ተረፈ ዳንኤል
57. መጽሐፈ ኩፋሌ
58. መጽሐፈ ሄኖክ

<u>የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት</u>

<u>ብዛት 58</u>

2.<u>የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት</u>

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል
5. የሐዋርያት ሥራ
6. የጳውሎስ መልእክታት
6. ወደ ሮሜ ሰዎች
7. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
8. ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9. ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14. ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15. ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16. ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17. ወደ ቲቶ



www.ethiopianorthodox.org

18. ወደ ፊልሞና
19. ወደ ዕብራውያን
20. የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ
21. የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
22. የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
23. የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
24. የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
25. የያዕቆብ መልእክት
26. የይሁዳ መልእክት
27. የዮሐንስ ራእይ-አቡቀለምሲስ

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 27

ስለዚህ 58 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር (58+27 = 85) 85 ይሆናል::



## የ1918 የእጅ ጽሑፎች፣ የ1929 ፎቶኦፍሴት ኅትመት፣ የ1947 /1953/ ኅትመትና የ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማነጻጸርያ ሰንጠረዥ-ሰሌዳ 4

| የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተራ ቁ. | የ1918 የእጅ ጽሑፎች | የ1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት | የ1947/1953 ኅትመት | የ1980 ኅትመት |
| 1 | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት |
| 2 | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት |
| 3 | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን |
| 4 | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ | ዘኁልቁ |
| 5 | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም |
| 6 | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ |
| 7 | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት |
| 8 | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት |
| 9 | ሳሙኤል 1ኛ | ሳሙኤል 1ኛ | ሳሙኤል 1ኛ | ሳሙኤል 1ኛ |
| 10 | ሳሙኤል 2ኛ | ሳሙኤል 2ኛ | ሳሙኤል 2ኛ | ሳሙኤል 2ኛ |
| 11 | ነገሥት 1ኛ | ነገሥት 1ኛ | ነገሥት 1ኛ | ነገሥት 1ኛ |
| 12 | ነገሥት 2ኛ | ነገሥት 2ኛ | ነገሥት 2ኛ | ነገሥት 2ኛ |
| 13 | ዜና መዋዕል 1ኛ | ዜና መዋዕል 1ኛ | ዜና መዋዕል 1ኛ | ዜና መዋዕል 1ኛ |
| 14 | ዜና መዋዕል 2ኛ | ዜና መዋዕል 2ኛ | ዜና መዋዕል 2ኛ | ዜና መዋዕል 2ኛ |
| 15 | ዕዝራ | ዕዝራ | ዕዝራ | ዕዝራ |
| 16 | ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ |
| 17 | አስቴር | አስቴር | አስቴር | አስቴር |
| 18 | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ |
| 19 | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር |



www.ethiopianorthodox.org

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

| ተራ ቁ. | የ1918 የእጅ ጽሑፎች | የ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት | የ1947/1953 ኅትመት | የ1980 ኅትመት |
|---|---|---|---|---|
| 20 | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ |
| 21 | - - | - - | ተግሣጽ | ተግሣጽ |
| 22 | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ |
| 23 | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ |
| 24 | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ |
| 25 | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ |
| 26 | ሰቆቃው | ሰቆቃው | ሰቆቃው | ሰቆቃው |
| 27 | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል |
| 28 | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል |
| 29 | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| 30 | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ |
| 31 | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ |
| 32 | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| 33 | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ |
| 34 | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ |
| 35 | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም |
| 36 | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም |
| 37 | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ |
| 38 | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ |
| 39 | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ |
| 40 | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ |
| 42 | መቃብያን 1ኛ | መቃብያን 1ኛ | መቃብያን 1ኛ | መቃብያን 1ኛ |

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

| ተራ ቁ. | የ1918 የእጅ ጽሑፎች | የ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት | የ1947/1953 ኅትመት | የ1980 ኅትመት |
|---|---|---|---|---|
| 43 | መቃብያን 2ኛ | መቃብያን 2ኛ | መቃብያን 2ኛ | መቃብያን 2ኛ |
| 44 | መቃብያን 3ኛ | መቃብያን 3ኛ | መቃብያን 3ኛ | መቃብያን 3ኛ |
| 45 | ሄኖክ | ሄኖክ | ሄኖክ | ሄኖክ |
| 46 | ዕዝራ ሱቱኤል | ዕዝራ ሱቱኤል | ዕዝራ ሱቱኤል | ዕዝራ ሱቱኤል |
| 47 | ዕዝራ ካልዕ | ዕዝራ ካልዕ | ዕዝራ ካልዕ | ዕዝራ ካልዕ |
| 48 | ጦቢት | ጦቢት | ጦቢት | ጦቢት |
| 49 | ዮዲት | ዮዲት | ዮዲት | ዮዲት |
| 50 | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን |
| 51 | ጥበበ ሲራክ | ጥበበ ሲራክ | ጥበበ ሲራክ | ጥበበ ሲራክ |
| 52 | ባሮክ | ባሮክ | ባሮክ | ባሮክ |
| 53 | መ/ኤርምያስ | መ/ኤርምያስ | - - | ተ/ኤርምያስ |
| 54 | ሶስና | ሶስና | - - | ሶስና |
| 55 | ተረፈ ዳንኤል | ተረፈ ዳንኤል | - - | ተረፈ ዳንኤል |
| 56 | - - | - - | - - | መዝ/3ቱ ደቂቅ |
| 57 | - - | - - | - - | አስቴር |
| 58 | - - | - - | - - | ጸሎተ ምናሴ |
| 58 | 54 | 54 | 52 | 58 |

## የ ሐ ዲ ስ ኪ ዳ ን መ ጻ ሕ ፍ ት

| ተራ ቁ. | የ1918 የእጅ ጽሑፎች | የ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት | የ1947/1953 ኅትመት | የ1980 ኅትመት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ |
| 2 | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ |
| 3 | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ |
| 4 | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ |
| 5 | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት |
| | ጳውሎስ ወደ: | ጳውሎስ ወደ: | ጳውሎስ ወደ: | ጳውሎስ ወደ: |
| 6 | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ |
| 7 | ቆሮንቶስ 1ኛ | ቆሮንቶስ 1ኛ | ቆሮንቶስ 1ኛ | ቆሮንቶስ 1ኛ |
| 8 | ቆሮንቶስ 2ኛ | ቆሮንቶስ 2ኛ | ቆሮንቶስ 2ኛ | ቆሮንቶስ 2ኛ |
| 9 | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ |
| 10 | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን |
| 11 | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ |
| 12 | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ |
| 13 | ተሰሎንቄ 1ኛ | ተሰሎንቄ 1ኛ | ተሰሎንቄ 1ኛ | ተሰሎንቄ 1ኛ |
| 14 | ተሰሎንቄ 2ኛ | ተሰሎንቄ 2ኛ | ተሰሎንቄ 2ኛ | ተሰሎንቄ 2ኛ |
| 15 | ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጢሞቴዎስ 1ኛ |
| 16 | ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጢሞቴዎስ 2ኛ |
| 17 | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ |



## የ ሐ ዲ ስ ኪ ዳ ን መ ጻ ሕ ፍ ት

| ተራ ቁ. | የ1918 የእጅ ጽሑፎች | የ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት | የ1947/1953 ኅትመት | የ1980 ኅትመት |
|---|---|---|---|---|
| 18 | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና |
| 19 | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን |
| 20 | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ |
| 21 | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ |
| 22 | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ |
| 23 | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ |
| 24 | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ |
| 25 | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ |
| 26 | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ |
| 27 | አቡቀለምሲስ | አቡቀለምሲስ | አቡቀለምሲስ | አቡቀለ[illegible]ሲስ |
| 27 | 27 | 27 | 27 | 27 |
| ድምር | 81 | 81 | 79 | 85 |

www.ethiopianorthodox.org

## 3. በ1918፣ 1929፣ 1947(1953) እና 1980 ዕርጭቶች ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል የሚታዩ ልዩነቶች

በተከታታይ በእጅ ተገለብጠውም ሆነ ታትመው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት የአንዱ ኅትመት መጻሕፍት ከሌላው ኅትመት መጻሕፍት ጋር ሲተያዩ በመጠኑም ቢሆን ልዩነት ይታያል።

የመጀመሪያው በ1918 የእጅ ጽሑፎች በ1929 ፎቶ አፍሴት ኅትመት መጻሕፍት መካከል የሚታይ ልዩነት የለም። ምክንያቱም በ1929 ፎቶ አፍሴት የተነሱት ቅዱሳት መጻሕፍት የ1918 የእጅ ጽሑፎች ናቸውና።

በእነዚህ የ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም የ1929 ፎቶ አፍ ሴት ኅትመትና የ1947 /1953/ ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል የሚታዩ ልዩነቶች በ1929 ፎቶ አፍ ሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት በአራት ክፍሎች /4 ጥራዞች/ ተከፍለው በተለይ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በ3 ክፍሎች /3 ጥራዞች/ ተመድበው መገኘታቸው ነው። ከእነዚህም 3ኛውን ክፍል /ጥራዝ 3ን/ ይዘው የሚገኙት መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ሲሆኑ በ1947/1953/ ኅትመት ግን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና እና እንደ መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ሁነው ተከፍለው ሳይሆን እንደ ግሪክ ብሉይ ኪዳን - ሰብዓ ሊቃናት ተራ ቅደም ተከተልን ይዘው ይገኛሉ። በዚህ መልካቸው መጽሐፈ አስቴር በሁለት ማለትም እንደ መጽሐፍ ዘቀዳሚ ቀኖና እና እንደ መጽሐፍተ ዘዳግም ቀኖና ተብሎ ሳይለይ፣ መጽሐፈ ሶስና ፣ ጸሎተ ወይም መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ እና ተረፈ ዳንኤል /ምስልና ዘንዶ/ ከትንቢተ ዳንኤል ሳይለዩ ታትመው ይገኛሉ። በሌላም በኩል በ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ አፍ ሴት ኅትመት የሚገኘው



መጽሐፈ ኤርምያስ በ1947 /1953/ ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተይዞ አይገኝም። በ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ አፍ ሴት ኅትመት የሚገኘው ተግሣጽ ዘሰሎሞን በ1947 (1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት አይገኝም።[18]።

ቀጥሎም በእነዚህ ሶስቱ: የ1918 የእጅ ጽሑፎች፣ በ1929 ፎቶ አፍ ሴት ኅትመት፣ በ1947 /1953/ ኅትመትና በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝሮች ውስጥ መጠነኛ ልዩነት ይታያል።

ስለዚህ በፊትኞቹ 3ቱ ወይም ሁለቱ የማይገኙ ጸሎተ ምናሴና 2ኛ መጽሐፈ አስቴር በ1980 ኅትመት ቅዱሳን መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና መካከል ይገኛሉ።

በሌላ በኩል የ1980 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ 1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም 1929 ፎቶ አፍ ሴት ኅትመት መጻሕፍት 3ኛውን ክፍል /ጥራዝ 3ን/ ግን የሁለተኛ ቀኖና መጻሕፍት /መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና/ በሚል ርእስ ለይቶ ይዞ ይገኛል።

በዚህም መሠረት የቀደሙት ሦስት ወይም ሁለት ክፍሎች: የ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም የ1929 ፎቶ አፍሴት ኅትመትና የ1947/1953/ ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት: 52 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር /52 + 27 = 79/ = 79 ወይም 52 + 2 = 54 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር /54 + 27 = 81/ = 81 ሲሆን[19] የ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት 58 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍተና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር /58 + 27 = 85/ = 85 ይሆናል።

---

18. ተግሣጽ የምሳሌ ሰሎሞን ዘር ሆኖ በመቆጠሩ ስለነበር ነው።
19. በዚሁ ገጽ 44 የግርጌ ማስታወሻ 14
20. ስለ 3 መጻሕፍት መቃብያን ከዚሁ ገጽ 201 212 ተመልከት።

www.ethiopianorthodox.org

## 4. ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት ከመሠረታውያን ምንጮቻቸው ጋር ሲነጻጸሩ

ቅዱሳት መጻሕፍት 1/ በተለይ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከአንድአንዶች መጠነኛ ቁጥር ከአላቸው መጻሕፍት በስተቀር[20] በሙሉ የተጻፉበት ቋንቋ ዕብራይስጥ ነው[21]::

ሆኖም በጣም ቀደም ብለው በሰብዓ ሊቃናት (ሰብዓ ሊቃውንት) ወደ ጽርእ (ግሪክ ቋንቋ) መመለሳቸውን እናውቃለን[22]::

በኢትዮጵያ እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ የተተረጎሙት ከእናቱ ዕብራይስጥ ሳይሆን በጽርእ መሆኑ በግልጥ ይታያል:: ከዕብራይስጥ ነው ብለው በድርቅና የሚከራከሩ ሊቃውንት እንደ አሉ ይሰማል:: ነገር ግን የግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት ውለውና አድረው ከዕብራይስጥም ጋር አልተመሳከሩም ማለት ባይቻልም ግእዙ ቅዱሳት መጻሕፍት በቅርጽ፣ በቃላት፣ በሐረግ፣ ወዘተ. በቅርብ የበለጠ የሚመሳከሩት ከጽርእ(ግሪክ) ምንጮቻቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ነው[23]::

በመጠኑም ቢሆን በሦስቱም ቋንቋዎች: ዕብራይስጥ፣ ጽርእና ግእዝ የሚገኙትን መጻሕፍት ለማመሳከር እንደ መቻሌ መጠን ይህን ለማለት የምችል ይመስለኛል:: ወደ ዝርዝር ለመግባትና ሁኔታዎችን-ልዩነቶችን በግልጥ ማሳየት ይቻል ነበር ግን ቦታው አይደለም:: ሌላው ችግር መጻሕፍት ዘዳግም (ካልዕ) ቀኖና ተብለው የሚታወቁት በጽርእ - እንደ ሰብዓ ሊቃናትና ግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት ተይዘው ሲገኙ በዕብራይስጥ አይገኙም:: ይህ ሁኔታ ግን እንዴት ተፈጠረ የታሪክ ጉዳይ ነው::

2/ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከማቴዎስ ወንጌል በስተቀር ሆኖም ማርቆስም ወንጌሉን በጣሊያን (ላቲን ቋንቋ) እንደጻፈው ይነገራል[24] በጽርእ (ግሪክ ቋንቋ) ተጽፈው ቀደም ብለው ከተተረጎሙባቸው የጥንት ቋንቋዎች አንዱ ግእዝ ነው::

ስለዚህ በአንድ በኩል የዕብራይስጥ፣ የጽርእ ሰብዓሊቀናትና የግእዝ-አማርኛ ብሉይ ኪዳን መጻሐፍት በሌላም በኩል ቀጥሎ የጽርእና የግእዝ -አማርኛ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይነጻጸራሉ:: ለዚህም ንጽጽር ሥራ የተጠቀምንባቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ሰነዶች:

የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን (Masoretic Old testament) በ1961 (እ.አ) በNorth Henry snaith = የታተመ ብሉይ ኪዳን፣ ጽርእ (ሰብዓ ሊቃናት) = በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በ1950 (እ.አ) የታተመ ብሉይ ኪዳን እና ግእዝ - አማርኛ ብሉይ ኪዳን = በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የታተመ መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እና ግሪክና ግእዝ - አማርኛ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው::

21. ከዚሁ ገጽ 150::
22. ከዚሁ ገጽ 178-179
23. አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ: መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ 17-22::

24. አውሳብዮስ ዘቂሳርያ: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 3ኛ መጽሐፈ ምዕራፍ 24.6፤ 5ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 8.2:: S.Eus. Hieronymi: Comentariorum in Evangelium Matthaei J.P. Migne: Patrologiae ... Latina T.26. ዐምድ 18::

www.ethiopianorthodox.org

## የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

1/ (Masoretic old testament)፣ የሰብዓ ሊቃናት /ግሪክ ትርጉም/ ብሉይ ኪዳንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሐዲስ ኀትመት መጽሐፍ ቅዱስ፡ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

2/ የግሪክና የግእዝ - አማርኛ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማነጻጸርያ ሠንጠረዥ-ሠሌዳ 5

| ተራ.ቁ | ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን | ሰብዓ ሊቃናት-ብሉይ ኪዳን | የአማርኛ 1980 መጽሐፍ ቅዱስ፡ ብሉይ ኪዳን |
|---|---|---|---|
| 1 | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት |
| 2 | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት |
| 3 | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን |
| 4 | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ |
| 5 | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም |
| 6 | ኢያሱ ወልደ ነዌ | ኢያሱ ወልደ ነዌ | ኢያሱ ወልደ ነዌ |
| 7 | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት |
| 8 | ሩት | ሩት | ሩት |
| 9 | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት |
| 10 | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት |
| 11 | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት |
| 12 | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት |
| 13 | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት |
| 14 | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት |
| 15 | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ |
| 16 | - - | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ |
| 17 | ነህምያ | ነህምያ | ነህምያ |



| ተራ.ቁ | ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን | ሰብዓ ሊቃናት-ብሉይ ኪዳን | የአማርኛ 1980 መጽሐፍ ቅዱስ፡ ብሉይ ኪዳን |
|---|---|---|---|
| 18 | - - | ጦቢት | ጦቢት |
| 19 | - - | ዮዲት | ዮዲት |
| 20 | - - | አስቴር | አስቴር |
| 21 | - - | 1ኛ መቃብያን | 1ኛ መቃብያን |
| 22 | - - | 2ኛ መቃብያን | 2ኛ መቃብያን |
| 23 | - - | 3ኛ መቃብያን | 3ኛ መቃብያን |
| 24 | መዝሙራተ ዳዊት | መዝሙራተ ዳዊት | መዝሙራተ ዳዊት |
| 25 | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ |
| 26 | ምስሌያተ ሰሎሞን | ምስሌያተ ሰሎሞን | ምስሌያተ ሰሎሞን |
| 27 | - - | - - | ተግሣጽ |
| 28 | መክብብ | መክብብ | መክብብ |
| 29 | ማሕልየ መሓልይ | ማሕልየ መሓልይ | ማሕልየ መሓልይ |
| 30 | - - | ጥበበ ሰሎሞን | ጥበበ ሰሎሞን |
| 31 | - - | ጥበበ ሲራክ | ጥበበ ሲራክ |
| 32 | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| 33 | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ |
| 34 | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| 35 | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ |
| 36 | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ |
| 37 | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ |
| 38 | ናሆም | ናሆም | ናሆም |



www.ethiopianorthodox.org

| ተራ.ቁ | ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን | ሰብዓ ሊቃናት-ብሉይ ኪዳን | የአማርኛ 1980 መጽሐፍ ቅዱስ፡ ብሉይ ኪዳን |
|---|---|---|---|
| 39 | ዕምባቆም | ዕምባቆም | ዕምባቆም |
| 40 | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ |
| 41 | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ |
| 42 | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ |
| 43 | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ |
| 44 | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ |
| 45 | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ |
| 46 | - - | ባሮክ | ባሮክ |
| 47 | ሰቈቃወ ኤርምያስ | ሰቆቃወ ኤርምያስ | ሰቆቃወ ኤርምያስ |
| 48 | - - | መልእክተ ኤርምያስ | - - |
| 49 | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል |
| 50 | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል |
| 51 | - - | አስቴር | አስቴር |
| 52 | - - | - - | መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል |
| 53 | - - | ሶስና | ሶስና |
| 54 | - - | ተረፈ ዳንኤል | ተረፈ ዳንኤል |
| 55 | - - | - - | ጸሎተ ምናሴ |
| 56 | - - | - - | ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ |
| 57 | - - | - - | ተረፈ ኤርምያስ |



| ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን | 2. ግሪክ ሐዲስ ኪዳን | የአማርኛ የ1980 መጽሐፍ ቅዱስ፡ ሐዲስ ኪዳን |
|---|---|---|
| | የማቴዎስ ወንጌል | የማቴዎስ ወንጌል |
| | የማርቆስ ወንጌል | የማርቆስ ወንጌል |
| | የሉቃስ ወንጌል | የሉቃስ ወንጌል |
| | የዮሐንስ ወንጌል | የዮሐንስ ወንጌል |
| | ግብረ ሐዋርያት | ግብረ ሐዋርያት |
| | የጳውሎስ መልእክት | የጳውሎስ መልእክት |
| | ወደ ሮሜሰዎች | ወደ ሮሜሰዎች |
| | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ |
| | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ | ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ |
| | ወደ ገላትያ ሰዎች | ወደ ገላትያ ሰዎች |
| | ወደ ኤፌሶን ሰዎች | ወደ ኤፌሶን ሰዎች |
| | ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች | ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች |
| | ወደ ቆላስይስ ሰዎች | ወደ ቆላስይስ ሰዎች |
| | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ |
| | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ | ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ |
| | ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ | ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ |
| | ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ | ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ |
| | ወደ ቲቶ | ወደ ቲቶ |
| | ወደ ፊልሞና | ወደ ፊልሞና |
| | ወደ ዕብራውያን | ወደ ዕብራውያን |
| | የጴጥሮስ መልእክት1ኛ | የጴጥሮስ መልእክት1ኛ |



www.ethiopianorthodox.org

| ማሶራዊ ብሉይ ኪዳን | ግሪክ ሐዲስ ኪዳን | አማርኛ የ1980 መጽሐፍ ቅዱስ: ሐዲስ ኪዳን |
|---|---|---|
| | የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ | የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ |
| | የዮሐንስ መልእክት 1ኛ | የዮሐንስ መልእክት 1ኛ |
| | የዮሐንስ መልእክት 2ኛ | የዮሐንስ መልእክት 2ኛ |
| | የዮሐንስ መልእክት 3ኛ | የዮሐንስ መልእክት 3ኛ |
| | የያዕቆብ መልእክት | የያዕቆብ መልእክት |
| | የይሁዳ መልእክት | የይሁዳ መልእክት |
| | የዮሐንስ ራእይ-አቡቀለምሲስ | የዮሐንስ ራእይ-አቡቀለምሲስ |
| | - - | ቀለሚንጦስ[25] |

ነገር ግን ከግሪክ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ የቀረ ነገር ባይኖርም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ በታሪክና በትውፊት ስምንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ - ስምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ (8ቱ ብሔር ዘቀለሚንጦስ) ወይም እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ የሚታሰቡት ሌሎች ስምንት መጻሕፍት ገብተው አለመገኘታቸው ግልጥ አይደለም::

25. መልሱ ምን አልባት ከሊቃውንት ይጠበቅ ይሆን?



# ምዕራፍ ስድስት

## በግእዝ - አማርኛ ቅዱሳት መጻሕፍት - ብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና በግሪክ-ጽርእ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደሰብዓ ሊቃናት መካከል አንድነትና ልዩነት

በግእዝ - አማርኛ ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚመለከት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ሲተያዩ በይዘት እንኳን ባይሆን በአከፋፈል ወይም አቀማመጥ ተመሳሳይነት ወይም ልዩነት ይታያል:: በተለይ መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተብለውና ተለይተው[26] በሚታወቁት መጻሕፍት መካከል: መጽሐፈ ሶስና፣ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ (ጸሎተ አዛርያስ ወሠለስቱ ደቂቅ)፣ ተረፈ ዳንኤል፣ መጽሐፈ አስቴር (መጽሐፍ ዘቀዳሚ ቀኖናም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ)፣ መጽሐፈ ኤርምያስ (ተረፈ ኤርምያስ)፣ ጸሎተ ምናሴ፣ መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል፣ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ፣ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሄኖክ፣ መጻሕፍተ መቃብያን ይገኙባቸዋል::

### 1 መጽሐፈ ሶስና

መጽሐፈ ሶስና (ዘዳንኤል ነቢይ) በ1918 የእጅ ጽሑፎችና በ1929[27] እና በ1980[28] ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ራሱን

26. በ1918 የእጅ ጽሑፎችና በ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኀትመት 3ኛ ክፍል (ብሉይ ኪዳን ጥራዝ 3) በ1980 ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት የብሉይ ኪዳን 2ኛ ቀኖና:: (የግርጌ ማስታወሻ ቁጥሮች ከምዕራፍ አምስት እስከ ምዕራፍ ሰባት ተከታታይ 1-148 ናቸው)::
27. የ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ጥራዝ 3 ገጽ 1118-1119::
28. የ1980 ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ገጽ 900-902::



www.ethiopianorthodox.org

ችሎና የመጻሕፍት ክዳን ቀኖና ክፍል ሆኖ ቢገኝ በ1947 ኅትመት ቅዱሳን መጻሕፍት[29] ይህ መጽሐፈ ሶስና ራሱንም ችሎ ለማለት ቢቻልም ግን ልክ እንደሰብዓ ሊቃናት[30] «መጽሐፈ ሶስና» ትንቢተ ዳንኤል ብሎ በመነሳት ሆኖም ከትንቢተ ዳንኤል ከምዕራፍ 1 በፊት ያለውን ክፍል ይዞ ይገኛል::

እንግዲህ በሁለቱም ክፍሎች (ግእዝ-አማርኛ ቅዱሳትም ሆነ ሰብዓ ሊቃናት) መጽሐፈ ሶስና ከምዕራፉ ውጪ በመሆኑ የትንቢተ ዳንኤል ዘር ነው ማለት አያስችልም ማለትም አይሆንም::

በይዘቱ ግን ግእዝ-አማርኛው መጽሐፈ ሶስና ከግሪኩ ሰብዓ ሊቃናት መጽሐፈ ሶስና እንደተተረጎመ ይታያል:: መጽሐፈ ሶስና በዕብራይስጥ እንደሌለም ይታወቃል::

## 2 ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ(ጸሎተ አዛርያስ ወመዝሙር ዘ ሠለስቱ ደቂቅ

ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ በ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1919 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሐፍትና በ1947(1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ተለይቶ ተመልክቶ አይገኝም:: ሆኖም ግን በሰብዓ ሊቃናት «ጸሎተ አዘርያስ ወሠለስቱ ደቂቅ» በሚል ርእስ ግን ራሱን ችሎና ተለይቶ ሳይሆን በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 3 በቁጥር 23 እና 24 መካከል ሰፍሮና ከ1-60 ቁጥሮችን ይዞ እንደሚገኘው መጠን[31] በ1947 (1953) ኅትመት መጻሕፍት ቅዱሳትም ይገኛል[32]:: በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ከትቢተ ዳንኤል

---

29. የ1947 (1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ገጽ 967-968::
30. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατα τους ἑβδομήκοντα ,(ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 834 - 835::
31. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τούς ἑβδομηκοντα ,(ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 839 - 840::
32. የ1947(1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ገጽ 972 - 994::



ተለይቶ ራሱን ችሎ በመጻሕፍት ክዳንም ቀኖና (የብሉይ ኪዳን 2ኛ ቀኖና መጻሕፍት) ተመዝግቦ ይገኛል[33]::

ሆኖም ዐረፍተ ነገሮች በትንቢተ ዳንኤል በምዕራፍ 3 ቁጥር 23 እና 24 ጸሎተ አዛርያስ ወሠለስቱ ደቂቅ ጋር ሲያያዙ:

«እነዚህም ሶስቱ ሰዎች ሲድራቅና ሚሳቅ፣ አብደናጎም ታስረው በሚነድደው በአቶነ እሳት ውስጥ ወደቁ[34]::

በነጎድጓድ እሳትም መካከልም ተመላለሱ፣ እግዜአብሔርን ፈጽመው አመሰገኑት:: አዛርያስም በእሳቱ መካከል ቆሞ እንዲህ ብሎ ጸለየ፣ በእሳቱ መካከልም ምስጋናን ጀመረ[35]::

«እግዚአብሔርን የምትፈሩ አሕዛብ ሁላችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት፣ ከአማልክት በላይ ለአምላክ ተገዙ፣ አመስግኑት፣ ቸርነት ለዘላለም ነውና ተገዙለት[36]:: የዚያን ጊዜም ናቡከደነጾር ተደነቀ፣ ፈጥኖም ተነሳ፣ አማካሪዎቹንም ሶስት ሰዎችን አስረን በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረምን? ብሎ

---

33. የ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት: መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 922-924::
34. ዳንኤል 3:23 Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τούς ἑβδομήκοντα ,( የብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 839፣ መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 672::
35. ጸሎተ አዛርያስ ወሠለስቱ ደቂቅ ቁጥር 1 Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τούς ἑβδομήκοντα , (ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 839: መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገጽ 922::
36. ጸሎተ አዛርያስ ወሠለስቱ ደቂቅ ቁጥር 66 /ግሪክኛ 67/ Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα ,/ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ገጽ 840፣ መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 894::



www.ethiopianorthodox.org

ተናገራቸው እነሱም ንጉ... ሆይ እውነት ነው ብለው ለንጉሡ መለሱለት»[37]::

ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ የሰብዓ ሊቃናት ጸሎተ አዛርያስ ወ ሠለስቱ ደቂቅ ግልባጩ መሆኑ አያጠራጥርም::

ነገር ግን ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ ራሱን ችሎ የሚቆጠር መጸሐፍ ሳይሆን ምንም እንኳን የትንቢቱ ምዕራፍና ቁጥር ተከታይ ባይሆንም በአንድ መጽሐፈ ዳንኤል እንደሚሸፈን ነው ሊታይ የሚችለው::

## 3 ተረፈ ዳንኤል

በ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት 3ኛ ክፍል (ብሉይ ኪዳን ጥራዝ 3)[38] እና በ1980 ኅትመት (የብሉይ ኪዳን 2ኛ ቀኖና መጻሕፍት) ኅትመት[39] ቅዱሳት መጽሐፍት ሌላ አንድ ራሱን ችሎና ተረፈ ዳንኤል በሚል ርእስ ግን ምዕራፍ 13 ብሎ ተነስቶ ከ1-42 ቁጥሮችን ይዞ ይገኛል::

ነገር ግን በ1947(1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን ተረፈ ዳንኤል ከትንቢተ ዳንኤል ተለይቶና ራሱን ችሎ ተይዞ አይገኝም[40]::

ተረፈ ዳንኤል በሰብዓ ሊቃናት በዚህ ርእስ «ተረፈ ዳንኤል» ሳይሆን ምስልና ዘንዶ /ቤልና ደራጎን/ በሚል ርእስ

37. ዳንኤል 3.24 Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τούς ἑβδομήκοντα, (ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 672::
38. የ1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት ገጽ 1120-1121::
39. የ980 የኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ገጽ 824 - 825::
40. የ1947 (1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ገጽ 984 - 985::



ከትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 12 ቀጥሎ ምዕራፍ ሳይሰጠው ግን ከ1 - 42 የሚደርሱ ቁጥሮችን ይዞ ይገኛል[41]::

አሁንም የግእዝ-አማርኛ ተረፈ ዳንኤል እና የሰብዓ ሊቃናቱ ምስልና ዘንዶ/ቤልና ደራጎን/ በሚል ርእስ አሰጣጥ ከመለያየታቸው በስተቀር አንድ መጽሐፍ ናቸው ማለት ግሪክኛው መጽሐፍ ግእዙ መጽሐፍ የተተረጎመባት እናት ምንጩ ነው:: ሆኖም ግን በግእዝ-አማርኛ ራሱን ችሎ ተቀርጾና በ2ኛ ቀኖና መጻሕፍት በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተይዞ መግኘቱ ሲታይ[42] በሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን ግን የትንቢተ ዳንኤል አካል ሆኖ እና ምዕራፍንና ቁጥርን ይዞ ባይገኝና አሁንም እንደ አለፉት ሁለት መጻሕፍት/ሶስና እና ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ/ ይህም አንድ ዳንኤል ሆኖ ነው የሚገኘው:: ምን አልባት ግእዝ-አማርኛው ተረፈ ዳንኤል ብሎ 13ኛን ምዕራፍ የሰጠው በአንድ በኩል ከምዕራፍ 12 መቀጠሉን ሲያሳይ በሌላ በኩል ከምዕራፍ ውጪ መጨረሻ በመሆኑ ተረፈ ዳንኤል ሊለው ችሏል[43]:: እንግዲህ ከመጻሐፍት ቁጥር አንጻር እነዚህ:

1. ሶስና
2. ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ
3. ተረፈ ዳንኤል

አሁን በታዩበት መልካቸው ተለያይተው ሳይሆን ከትንቢተ ዳንኤል ጋር በመጣመር እንደ አንድ መጽሐፍ ነው የሚቆጠሩት[44]::

41 Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατα τούς εβδομηκοντα ,(ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት /ገጽ 850 - 851)::
42. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 924-925::
43. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 924::
44. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τούς ἑβδομήκοντα /ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 850::



www.ethiopianorthodox.org

## 4 አስቴር /መጽሐፈ አስቴር/

በ1980 መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአስቴር ስም ሁለት መጻሕፍት ታትመው ይገኛሉ:: ከእነዚህም አንዱ መጽሐፈ አስቴር በመጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ተመዝግቦ ሲገኝ[45] ሌላው መጽሐፈ አስቴር በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተይዞ ይታያል[46]:: ነገር ግን ሁለቱ መጻሕፍት ልዩነት እንደአላቸው ለመመልከት ሲሞክር ምንም ትርጉም አልነበራቸውም::

በአጭሩ በመጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና የተያዘው መጽሐፈ አስቴር በብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት የሚገኝ መጽሐፈ አስቴር ትርጉም ነው:: ነገር ግን በአርጤክስስም ዘመን እንዲህ ሆነ፣ ይህም አርጤክስስ ከሕንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሃያ ሰባት አገሮች ላይ ነገሠ[47] ብሎ ይህንም ምዕራፍ አንድ ብሎ ጀምሮ በምዕራፍ 10 ይጨርሳል[48]:: ነገር ግን ይህ ምዕራፍ 10 በ3 ቁጥሮች ተወስኖ ይገኛል[49]::

እንግዲህ ይህ በ1ኛ ቀኖና መጻሐፍት - መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ሥር የሚገኘው መጽሐፈ አስቴር ከግሪኩ ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን ጋር ሲተያይ-ሲመሳከር:

45. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 400-406፣ Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα, /ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 834-851::

46. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 785-794፣ መጽሐፈ አስቴር በ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ አፍሴት ኅትመት በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና በግልጽ ሰፍሮ አይገኝም::

47. አስቴር 1.1 መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 400፣ 785::

48. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 400-406::

49. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 406::



- በአንድ በኩል ግእዙ-አማርኛው መጽሐፈ አስቴር ከሰብዓ ሊቃናት መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ አንድ ቁጥር 2 ላይ ነገር ግን ቁጥር አንድ ብሎ ይነሳል[50]:: በሌላ በኩል ግእዙ-አማርኛው መጽሐፈ አስቴር የሚጨርስበት ምዕራፍ 10 ሲሆን ይህም ከሰብዓ ሊቃናት መጽሐፈ አስቴር 10: 1-3 ጋር አንድ ነው:: ነገር ግን የሰብዓ ሊቃናቱ መጽሐፈ አስቴር ቁጥር 3 ከዚያም በኋላ 3 አልፋ፣ 3 ቤታ፣ 3 ጋማ፣ 3 ዴልታ፣ 3 ኤፕሲሎን፣ 3 ዜታ፣ 3 ኢታ፣ 3 ቴታ፣ 3 ዮታ፣ 3 ካፖ፣ 3 ላምዳ ብሎ ሲጨመር[51] በግእዝ-አማርኛው መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ 10 እነዚህ ቁጥርን አልፎ ከ3 አልፋ - 3 ላምዳ = 11 ቁጥሮች ተለይተው አይታዩም::

በዚህ በኩል ያለው ልዩነት ይህን ሲመስል ሌላው መጽሐፈ አስቴር በ2ኛ ቀኖና መጻሕፍት-መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና የተመደበው ነው::

ይህን መጽሐፈ አስቴር በሚመለከት ከላይ እንደ አለው የሰብዓ ሊቃናት መጽሐፈ አስቴር «ከፍ ያለ ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት በኒሳን መባቻ የኢያዕር የሰሜኢ፣ የቂስ ልጅ ከብንያም የተወለደ አይሁድ ወገን ሰው የሚሆን መርዶክዮስ ሕልምን አየ . . .»[52] ብሎ ሲነሳ ግን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ግሪክኛው መጽሐፈ አስቴር በመጀመሪያ ቁጥር 1ን በሁለት መልክ አላስቀመጠም: 1 አልፋ፣ 1 ቤታ፣ 1 ጋማ፣ 1 ዴልታ፣ 1 ኤፕሲሎን፣ 1 ዚታ፣ 1 ኢታ፣ 1 ቴታ፣ 1 ዮታ፣ 1 ካፓ፣ 1 ላምዳ፣ 1 ሚ፣ 1 ኒ፣ 1 ኤክሲ፣ 1 ኦሚክሮን፣

50. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 400::

51. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα , (የብሉይ ኪዳን ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 464::

52. የ1980 መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 785::



www.ethiopianorthodox.org

1 ፒ፣ 1 ሮ እስከ 1-17 ከቆጠረ በኋላ እንደገና በነጠላ 1 ብሎ ደግም እስከ ቁ. 22 መሄዱን ሳይከተል[53] እነዚህን ቁ. 1 አልፋ - 1 ሮ ቁጥር የያዘውን ክፍል በመጀመርያ እንደ መግቢያ አስቀምጦ ከመደበኛው ቁጥር 1 ላይ ቁጥር 1 ብሎ ይነሳል[54]:: ነገር ግን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ግሪክኛው መጽሐፈ አስቴር በምዕራፍ 10 ሳይሆን በምዕራፍ 11 ነው የሚጨርሰው[55]::

ከዚህ ላይ በመጻሐፍት ዘቀዳሚ ቀኖና መጽሐፈ አስቴር እንደተመለከተው 10ኛው ምዕራፍ በ3 ቁጠሮች እንደመጨረሱ ሳይሆን በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና የተያዘው መጽሐፈ አስቴር እንደ ግሪኩ-ሰብዓ ሊቃናት መጽሐፈ አስቴር በይዘት ትርጉሙ መሆኑ ቢታወቅም ግሪኩ መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ 10ን በመደበኛ ሥርዐት ከ1-3 ቁጥሮችን ከቆጠረ በኋላ ቀጥሎ ቁጥር 4 በማለት ፋንታ 3 አልፋ፣ 3 ቬታ፣ 3 ጋማ፣ 3 ዴልታ፣ 3 ኤኘሲሎን፣ 3 ዚታ፣ 3 ኤታ፣ 3 ቲታ፣ 3 ዮታ፣3 ካፖ፣ 3 ላምዳ ብሎ ሲያቆም[56] ግእዙ-አማርኛው መጽሐፈ አስቴር ግን ይህን ሳይከተል 4-13 ቁጥሮችን ከቆጠረ በኋላ 3 ላምዳን ምዕራፍ 11 ብሎ ይከፍለዋል:: ቁጥር ግን አልተሰጠውም[57]:: ምዕራፍ ስምንትን አስመልክቶ የብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ 8 ቁጥር 1 ብሎ ተነስቶ ቁጥር 12 ላይ ሲደርስ አሁንም 13ን በመቀጠል ፋንታ 12 አልፋ፣ 12 ቬታ፣ 12 ጋማ፣ 12 ዴልታ፣ 12 ኤኘሲሎን፣ 12 ዜታ፣ 12 ኢታ፣ 12 ቲታ፣ 12 ዮታ፣ 12 ካፖ፣ 12 ለምዳ፣ 12 ሚ፣ 12 ኒ፣ 12 ኤክሲ፣ 12 አሚክሮን፣ 12 ፒ፣ 12 ሮ፣ 12 ሲግማ፣ 12 ታፍ፣ 12 ኢኘሲሎን፣ 12 ፊ/12.1 - 12.21 = 21/ የሚሉ ቁጥሮች ጣልቃ ካስገባ በኋላ ወደ ተራ ቁጥር 13 ተመልሶ በቁጥር 17 ይጨርሳል::

በ1980 የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ በመጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና የሚገኘው 1ኛው መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ 8 ቁጥር 1 ብሎ ጀምሮ በቁጥር 12 እና 13 መካከል ምንም ዓይነት ጣልቃ ቁጥሮች ሳይኖሩት በቁጥር 17 ጨርሶ ያቆማል:: ነገር ግን በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና የሚገኘው 2ኛው መጽሐፈ አስቴር እንደሰብዓ ሊቃናቱ መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ 8 ቁጥር 1 ብሎ ተነስቶ ከቁጥር 12 ላይ ሲደርስ አሁንም እንደ ሰብዓ ሊቃናቱ መጽሐፈ አስቴር 12 ሀ፣ 1 ለ፣ ወዘተ. ሳይል ግን ከቁጥር 1 - 24 ቆጥሮ አሁንም ወደ 13 ቁጥር ተመልሶ በቁጥር 17 ይጨርሳል:: ነገር ግን በሌላ በኩል ሶስናን፣ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅን፣ ተረፈ ዳንኤልን ከትንቢተ ዳንኤል ለይቶና መጽሐፈ አስቴርንም ከሁለቱ ቦታ ላይ አስቀምጦ የሚገኘው የ1980 ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሲሆን የ1947/1953/ ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ልክ

53. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα ,(ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 456፣ መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 785::

54. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 456፣ መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 785::

55. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα ,(ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 785::

56. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα , ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 464 መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 794::

57. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 794::



www.ethiopianorthodox.org

እንደሰብዓ ሊቃናት የተጠቀሱትን 3 መጻሕፍት ከትንቢተ ዳንኤል ሳይለይና መጽሐፈ አስቴርንም በሁለት ቦታ ሳያስቀምጥ ይዞ ይገኛል[58]::

በሌላም በኩል እንደተባለው መጽሐፈ አስቴር እንደ መጽሐፍ ዘቀዳሚ ቀኖና በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት በምዕራፍ 10 ቁ. 1 - 3 ሲጨርስ እንደ መጽሐፍ ዘዳግም ቀኖና በምዕራፍ 11 ግን ያለ ቁጥር ሲጨርስ በ1947 (1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ይህ መጽሐፈ አስቴር በሁለት መጽሐፍ ዘቀዳሚ ቀኖና (1980) በምዕራፍ 10 ቁ. 1 - 3 እና ወይም እንደ መጽሐፍ ዘዳግም ቀኖና በምዕራፍ 11 ግን ቁጥር አልባ የሚጨርስ ሳይሆን ምዕራፍ 10ን ቁጥሮችን 1 - 21 ከመያዙ ጋር በተጨማሪ ምዕራፍ 11ን ቁ. 1 - 45፣ ምዕራፍ 12 ቁ. 1 - 13 እና ምዕራፍ 13ን ቁ. 1 - 42 ይዞ ይገኛል[59]:: እንግዲህ አንድ አንድ በጣም መጠነኛ ልዩነቶች ቢኖሩም አንድ መጽሐፍ አንድ ጊዜ በ1ኛ ቀኖና መጻሕፍት ሌላ ጊዜ በ2ኛ ቀኖና መጻሕፍት ተመድቦ መገኘቱ በዚህ መጽሐፍ መደምደሚያ ላይ ተመልክቷል:: በዚህ መልኩ እንዲታተም ከፈቀደው ቅዱስ ሲኖዶስ መልስ ባይጠበቅም ከሊቃውንት ጉባኤ ይህ መልስ ይጠበቃል::

58. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τους ἑβδομηκοντα . . . ብሉይ ኪዳን /እንደሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 452 - 452 መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት /1980/ ገጽ 404 - 405፣ 791 - 792፣ መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻፍት /1947/ ገጽ 967 - 968 971 - 974፣ 888 - 895፣ 573 - 582::

59. የ1947(1953) ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገጽ 982-983፣ 983፣ 984 - 985::



## 5 ተረፈ ኤርምያስ

በ1918 የአጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት መጽሐፈ ኤርምያስ[59] ወይም በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ተረፈ ኤርምያስ[60] በሚል ርእስ የሚነሳ መጽሐፍ ሲኖር በ1947 (1953) ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ግን አይገኝም::

መጽሐፈ ኤርምያስ ወይም ተረፈ ኤርምያስ ከ6 - 11 ያሉ ምዕራፎችን ይዞ ይገኛል::

የዚህንም መጽሐፍ ምንጩ ለማግኘት አሁንም ከግሪክ ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል መፈለግ ይሆናል::

ተረፈ ኤርምያስ ሲጀምር «እግዚአብሔር ያዘዘውን ይነግራቸው ዘንድ የባቢሎን ንጉሥ ማርኮ ወደ ባቢሎን አገር ወደ ወሰዳቸው ሰዎች ኤርምያስ የላከው የጣኦቱን መልክ የሚናገር መጽሐፈ ይህ ነው[61]» ብሎ የሚጀምርበት ዐረፍተ ነገር የመልእክተ ኤርምያስ መግቢያ ግልባጭ ሆኖ ሲገኝ ከዚህ በኋላ ይህ ተረፈ ኤርምያስ እና መልእክተ ኤርምያስ አይገናኙም:: በሌላም በኩል መልእክተ ኤርምያስ በአንድ ምዕራፍ ተወስኖና ከ1 - 72 ያሉ ቁጥሮችን ብቻ ይዞ የሚገኝ መጽሐፍ ነው[62]:: ምን አልባት ወደ ግእዝ አልተተረጎመም ይሆን? ምክንያቱም በዚህ አዲስ እትም መጽሐፍ ቅዱስ አይታይምና::

60. የ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ ገጽ 1107 - 1108፣ መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 982 - 900::

61. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 892::

62. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατα τους εβδομηκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 791-792::

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ ይህ ተረፈ ኤርምያስ ከወዴት መጣ? አሁንም ከየት ተገኝና ሊታተም ቻለ? በምርምር እስከ አልተደረሰበት ጊዜ ሌላ መልስ ይጠበቃል::

ነገር ግን ምዕራፍ 6 ብሎ ጀምሮ በመጨረሻ ምዕራፍ «. . . ባሮክ በዚህ መጽሐፍ የተናገረው ነገር ተፈጸመ» ብሎ ስለሚያሳርግ[63] የመጽሐፈ ባሮክ ተከታይ መስሎ ይታያል:: የመጽሐፈ ባሮክ የመጨረሻ ምዕራፈ 5 ነውና[64]::

በሌላ በኩል መልእክተ ኤርምያስ ከ6ቱ ቀኖናት በሁለቱ ቀኖናት ተመዝግቦ ሲገኝ[65] በግእዝ ትርጉም ቀኖናት ተይዞ የሚገኘው አይደለም::

## 6. ጸሎተ ምናሴ

ጸሎተ ምናሴ በመባል የሚጠራ መጽሐፍ ከ1980 ኀትመት መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በስተቀር[66] በሌሎች (በ1918 የእጅ ጽሑፎች፣ ወይም በ1929 የፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመትና በ1947 ኅትመት) ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል የሚገኝ አይደለም::

ጸሎተ ምናሴ በግሪክ - ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም አይገኝም:: በቀኖናተ ቅዱሳት

63. ምዕራፍ 11.63 መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 900::

64. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 902 - 905:: Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα. (ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 783-786)::

65. - ቀኖናት ዘላኦዶቅያ /ሉዶቅያ/ 60ኛ ቀኖና
- መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ

66. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዱስን ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 891-892::



መጻሕፍት ተመልክቶ የማይገኝ መሆኑም ይታወቃል::

ጸሎተ ምናሴ በጥንት ቀኖናተ መጻሕፍትም ሆነ በቀኖናቱ ግእዝ ትርጉሞች ተመዝግቦ አለመገኘቱ ሲገለጥና በአዲሱ የ1980 ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖናም እንኳን ቢሆን ተይዞ ተገኘ? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ከጥንታውያት መጻሕፍት አንዱ መሆኑ ግን ይታወቃል: ለምሳሌ ቀደም ብለው ከሚታወቁት መጻሕፍት መካከል በአንዱ «ሐዋርያውያት ትእዛዛት» (Constitutiones Apostolicae-Ἀποστολικαὶ διαταγαί) ወይም «ትእዛዛት ዘሐዋርያት» (Constitutiones Apostolorum - Διαταγαὶ τῶν Ἀποστόλων) እንዲህ ሲባል ተጠቅሶ ሳይሆን ቃል በቃል ተገልብጦ - ተቀድቶ ይገኛል[67]::

ተደጋግሞ እንደተመለከተው ወደ ፊትም እንደሚገለጠው ትእዛዛት ዘቅዱሳት ሐዋርያት ወይም ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የእናንተ ኤጴስ ቆጶሳት በእኔ በቀለሚንጦስ እጅ የተላኩ ስምንት መጻሕፍት - ትእዛዛት . . ./ ተብለው ተመዝግበው የሚገኙ ትእዛዛት ዘሐዋርያት ወይም ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ናቸው[68]::

## 7. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል በሚል ስም የሚታወቀው መጽሐፍ በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት (በ1918 የእጅ ጽሑፎች፣

67. ትእዛዘተ ቅዱሳን ሐዋርያት ምስለ ቀለሚንጦስ Διαταγαὶ τῶν Ἁγίων Ἀποστόλων διὰ Κλήμεντος 2ኛ መጽሐፍ ስለ ኤጲስ ቆጳሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ምዕራፍ 22፣ ቁ. 12 - 14 (2ኛ ዜና መዋዕል 33.13 - 22::

68. F. Funk: Didascalia et Constitutiones Apostolorum. paderborn 1906. Διαταγαὶ τῶν Ἁγίων Ἀποστόλων διὰ Κλήμεντος

www.ethiopianorthodox.org

በ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት፣ በ1947 እና በ1980 ኅትመቶች ቅዱሳት መጻሕፍት ግን በመጀመሪያዎቹ፣ (በ1918 እና 1929) መጻሕፍት 3ኛ ክፍል (ብሉይ ኪዳን ጥራዝ 3)፣ በ1947 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ያለምንም ልዩነት እና በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ግን በብሉይ ኪዳን 2ኛ ቀኖና መጻሕፍት ይገኛል[69]:: ነገር ግን በዚህ ስምና ይዘት በሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ከአለመታየቱም በላይ በቀኖናተ አምላካውያት መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚገኝ መጽሐፍ የለም:: አሁንም የዚህን መጽሐፍ ምንጭ ማግኘት ማስቸገሩ ግልጽ ነው::

## 8. መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

ስለ መጻሕፈ ዕዝራ ቀደም ብለን አውስተን ነበር:: በመሠረቱ በአዲሱ 1980 ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት መጻሕፍተ ዕዝራ ሲኖሩት አንደኛው መጽሐፈ ዕዝራ በመጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና[70] እና ሁለተኛው መጽሐፈ ዕዝራ በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና[71] መካከል ተይዘው ይገኛሉ:: ሁለቱም መጻሕፍተ ዕዝራ በግሪክ-ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳንም ይገኛሉ[72]::

እንግዲህ ሁለቱ ግእዝ-አማርኛና ግሪክ መጻሕፍት ሲመሳከሩ ልዩነታቸው የግእዝ-አማርኛው መጽሐፈ ዕዝራ

69. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 723 -746::
70. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 379 - 387::
71. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 746 - 762:: 2ኛ ዕዝራ እንደ 3ኛ ዕዝራ ተቆጥሮና 4ኛ ዕዝራም እንደ አለ ተጽፎ ሲገኝ ሁለቱም መጻሕፍተ ዕዝራ-መጽሐፈ ዕዝራ ራብዕና መጽሐፈ ዕዝራ ሣልስ ከቁጥር ውጭ ይገኛሉ:: አባ ፍራንቸስኮስ ዘባኄኖ: ነቢያት ወመቃብያን-መጽሐፈ ራብዕ፣ አሥመራ 1918::
72 Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα.(ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 1ኛ ዕዝራ ገጽ 401-414 2ኛ እዝራ ገጽ 114 - 422::



ቀዳማዊ የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ሆኖ እና የግእዝ-አማርኛው መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ የግሪኩ መጽሐፈ ዕዝራ ቀዳማዊ ሆኖ መገኘቱ ነው::

ከዚህ ጋር መጽሐፈ ነህምያ[73] ከመጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ተከፍሎ የወጣ መጽሐፍ መሆኑ ተገልጧል:: ስለዚህም በግእዝ-አማርኛው የመጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ክፍል ሆኖ ይገኛል:: ሆኖም የግሪኩ መጽሐፈ ዕዝራ ግልባጭ ትርጉም መሆኑ አያጠራጥርም::

## 9. መጽሐፈ ኩፋሌና መጽሐፈ ሄኖክ

መጽሐፈ ኩፋሌና መጽሐፈ ሄኖክ በሁሉም ሥርጭቶች ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል መገኘታቸው ይታወቃል[74]::

በመሠረቱ በግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት መጻሕፍት መካከል አይገኙም:: ቆይቶም በቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት አልተመለከቱም:: ነገር ግን በተለይ መጽሐፈ ኩፋሌ በእነዚህ ቀኖናት ግእዝ ትርጉሞች በአብዛኞቹ(ጎቱ) ተመልክቶ ይገኛል[75]:: እነዚህስ ቀኖናት ቢሆን ከወዴት አመጡት? ብሎ ለማስረዳት የሚቻል አይደለም::

መጽሐፈ ሄኖክን በሚመለከት ከላይ እንደተመለከተው በሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ከአለመኖሩም የተነሳ ከፊቱ ቀኖናት መጻሕፍት በአንዱም አልተወሳም:: ከዚያም በእነዚህ ቀኖናት ቅዱሳት መጻሕፍት ግእዝ ትርጉሞች አልተመለከተም:: ስለዚህም በቅዱሳት መጻሕፍት መካከል አንዱ ሆኖ እንዴት ተመዝግቦ ተገኘ?

እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማን ግን ሄኖክን በሚመለከት ሐዋርያት በመጀመሪያ በቀኖናት አስገብተውት

73. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት(1980) ገጽ 387 - 394::
74. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ መጻሕፍት(1980) ገጽ 926-1037::
75. ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን(ረስጠጅ)፣ ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት(ረስጠአ)፣ ሲኖዶስ [illegible]::



www.ethiopianorthodox.org

እንደነበር /ሃምናልባት የ.ስ5ቱ ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ማለታቸው ይሆን?/ እና ቆይቶ ግን ፈላስፎች ሐዋርያት የእኛን ፍልስፍና ይቀበላሉ ስለአሉዋቸው እንደአወጡት ይተረጎማል[76]፡ ይህስ ቢሆን ቅዱስ ትምህርትን ይዟል ብለው ተቀብለው በቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር አስገብተውት ይሆን ከሆነ እንዴት እንደዚህ ተባልን ብለው ከቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ ይፍቁታል? መቀበሉ አስቸጋሪ ይመስለኛል:: ነገር ግን ሄኖክ በቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ገብቶ በቀኖናተ መጻሕፍት ተመዝግቦ ባይገኝም ቅሉ ቃል በቃልም እንኳን ባይሆን ወይም ይመስላል ተብሎ በሚተረጎምበት መልክም ቢሆን ቅሉ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እየተጠቀሰ መገኘቱ ይታወቃል::

ስለዚህ በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት[77] የታተመ መጽሐፍ ቅዱስን[78] ብንመለከት የሚከተሉትን ጥቅሶች እናገኛለን[79]

76. ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ገጽ 43::
77. United Bible Societies: The American Bible Society N.Y, The British and Foreign Bible Society, London., The National Bible Society of Scotland, Edinburgh, The Netherlands Bible Society, Amesterdam and The Wurttemberg Bible Society, Stuttgart (Published) 1966.
78. The Greek New Testament edited by Kurt Aland, Matthew Black, Bruce M. Metzger and Allen wikgren
79.

| | |
|---|---|
| ሄኖክ 1.2 | 1ኛ ጴጥሮስ 1.12 |
| ሄኖክ 1.9 | የይሁዳ መልእክት ከ14 - 15 |
| ሄኖክ 9.4 | አቡቀለምሲስ 15.3 |
| ሄኖክ 46.3 | ቆላስይስ 2.3 |
| ሄኖክ 51. 2 | ሉቃስ 21.28 |
| ሄኖክ 64.27 | ዮሐንስ 5.22 |

ከፊሎች ናቸው::



በሌላ በኩል በዚህ ሐዲስ ኪዳን ሄኖክ እስከ ምዕራፍ 70 ድረስ ተጠቅሶ ሲገኝ[80] በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ግን በምዕራፍ 42 ላይ ይቆማል[81]::

ኩፋሌን በሚመለከት በፍትሐ ነገሥት ያልተያዘው ከብሔረ ኦሪት የወጣ በመሆኑ እንደሆነ ይተረጎማል[82]:: ይህም ቢሆን አሳማኝነቱ አይታይም::

## 10. 3 መጻሕፍተ መቃብያን

3 መጻሕፍተ መቃብያን በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት: በ1918 የእጅ ጽሑፎች፣ በ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት፣ በ1947(1953) እና በ1980 ኅትመቶች ቅዱሳት መጻሕፍት ተይዘው ይገኛሉ::

በብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት 4 መቃብያን ናቸው የሚገኙት[83]::ወደ ቀኖናተ መጻሕፍት ስንመለከት ከላይ

80 Greek New Testament ......ገጽ 918 - 919::
81. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 1037::
82. ኩፋሌ በመሠረቱ ከአምስቱ ወይም ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ከመጀመሪያዎቹ ሁለት: ዘፍጥረትና ዘጸአት ተከፍሎ የተቀነባበረና ይዘቱም የዘመን አከፋፈልን -ክፍለ ዘመናትን የሚናገርና በኢዮቤልዩ የሚቆጥር መጽሐፍ መሆኑ ይታያል:: አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍል 2 መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ 543:: ነገር ግን እንዲያውም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የመጀመሪያዎች መጻሕፍት አምስቱ ብሔረ ኦሪት ወይም ስምንቱ ብሔረ ኦሪት እየተባሉ እንደሚለዩ ሲታወቅ መጽሐፈ ኩፋሌም ተጨምሮ ዘጠኙ ብሔረ ኦሪት ተብለው የሚገኙበት ሁኔታም ይገጥማል:: ብዙ ጊዜ ከእነዚህ ስምንት ብሔረ ኦሪት እየቀጠለም ነው ተይዞ የሚገኘው:: Abbadie A.d: Catalogue ቁ. 117 ገጽ 132 - 133::
83. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) 1ኛ መቃብያን ገጽ 795 - 827፣ 2ኛ መቃብያን ገጽ 827 - 848፣ 3ኛ መቃብያን ገጽ 844 - 853፣ ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ገጽ 43:: ሌላም ታሪክ አለቃ ኪዳነ ወልድ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ 19::



www.ethiopianorthodox.org

ከተጠቀሱት 6 ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና እና በቀኖናተ ካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ 24ኛ/ 32ኛ ቀኖና (ግን ላቲን ትርጉም 2 መጻሕፍተ መቃብያን: 1ኛ መጽሐፈ መቃብያን እና 2ኛ መጽሐፈ መቃብያን) 3 መጽሐፍተ መቃብያን ተዘርዝረው ይገኛሉ:: ነገር ግን በእነዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ግእዝ ትርጉሞች ከአራቱ በሦስቱ መጻሕፍተ ቀኖናት ሁለቱ መጻሕፍተ መቃብያን ብቻ ናቸው ተመዝግበው የሚገኙት::

ታድያ በተከታታይ (1918፣ 1919፣ 1947 እና 1986) በታተሙት ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ይህ 3ኛው መጽሐፈ መቃብያን ከምን ላይ ተመርኩዞ ታትሞ ሊገኝ ቻለ? ይህንም ምክንያት ማስረዳት በምርምር ዘዴ ከሆነ ከዚህ ውጪ ለመሄድ መንገድ የለም:: ስለ አንድ የቆየና ያለ ነገር ለመናገር ምንጩ ያስፈልጋል::

ሐዋርያውያት ቀኖናት ግእዝ ትርጉሞች 3ኛውን መጽሐፍ ለምን አልመዘገቡትም? ምንአልባትም ትልቁ ችግር ግእዝ ሰነዶች ሂሳዊ ጥናት ስለአልተደረገባቸው ከአንድ ሰነድ ወደ ሌላው ሰነድ በእጅ ጽሑፍ በሚገለባበጡበት ጊዜ እየተዘለለ መጥቶ ሊሆንም ይችላል::

ሆኖም ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በታተሙት ቅዱሳት መጻሕፍት 3 መጻሕፍተ መቃብያንና የግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት 3 መጻሕፍተ መቃብያን ሲመሳከሩ በትክክል የግእዙና አማርኛው መጻሕፍተ መቃብያን የግሪኩ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዐ ሊቃናት ትርጉሞች ናቸው? ከሚለው ጥያቄ መነሳት ግድ ይሆናል::

በእውነት እንደ ሰብዓ ሊቃናት ግሪኩ ብሉይ ኪዳን ይዞአቸው የሚገኙት 3 መጻሕፍተ መቃብያን:



1ኛ መጽሐፈ መቃብያን 16 ምዕራፎችን[84]
2ኛ መጽሐፈ መቃብያን ምዕራፎችን[85]
3ኛ መጽሐፈ መቃብያን 7 ምዕራፎችን[86]

ይዘው የሚገኙ ሲሆን በግእዝ - አማርኛ ኅትመቶች ቅዱሳን መጻሕፍት

- መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ 36 ምዕራፎችን[87]
- መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ 21 ምዕራፎችንና[88]
- መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 10 ምዕራፎችን[89] ይዘው ይገኛሉ::

እንግዲህ በያሏቸው ምዕራፎች እንኳን ቢተያዩ

1. 1ኛ መጽሐፈ መቃብያን እንደ ሰብዓ ሊቃናት 16 ምዕራፎች ሲኖሩት[90] በግእዝ-አማርኛ ኅትመቶች ቅዱሳት መጻሕፍት 1ኛ መጽሐፈ መቃብያን 36 ምዕራፎች አሉት[91]:: ልዩነት 20 መጻሕፍት::

2. 2ኛ መጽሐፈ መቃብያን እንደ ሰብዓ ሊቃናት 13 ምዕራፎች ሲኖሩት[92] በግእዝ-አማርኛ ኅትመቶች ቅዱሳት መጽሐፍት 2ኛ

---

84. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τούς ἑβδομήκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት /ገጽ 465 - 491::
85. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τὸυς ἑβδομὴκοντα /ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 492 - 510::
86. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τὸυς ἑβδομὴκοντα /ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 511-519::
87. መጽሐፈ ቅዱስ: ብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 795-827::
88. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 827-844
89. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 844-853::
90. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τὸυς ἑβδομὴκοντα /ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 465-491::
91. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 795-827::
92. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τὸυς ἑβδομὴκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት ገጽ 472-510::


www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፈ መቃብያን 21 ምዕራፎች አሉት፣ የ8 ምዕራፎች ልዩነት ይታያል[93]::

3. 3ኛ መጽሐፈ መቃብያን እንደ ሰብዓ ሊቃናት 7 ምዕራፎችን ይዞ ሲገኝ[94] በግእዝ- አማርኛ ኀትመቶች ቅዱሳት መጻሕፍት 3ኛ መጽሐፈ መቃብያን 10 ምዕራፎችን ያቅፋል[95]:: አሁንም የ3 ምዕራፎች ልዩነት ይታያል::

ምን አልባት የሰብዓ ሊቃናት መቃብያን ምዕራፎች ቁጥር ወደ ግእዝ ሲተረጎም ተዛብቶ ይሆናል የሚል አስተሳሰብ ሊኖር ይችላል::

በሌላም በኩል ፍትሐ ነገሥትን ስንመለከት በፍትሐ ነገሥት ሁለት መቃብያን ብቻ ወይም ሦስትም ለማለት ይቻላል ተመዝግበው ሲታዩ እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማን ግን እነዚህ ሁለት ወይም ሦስት መቃብያን ወደ አራት መቃብያን ተቃርበው ይገኛሉ::

በዚህ መሠረት:

1ኛ. መቃብያን የመቃቢስ ዘአልአዛር /ኤሌአዛር/ መቃብያን[96]

2ኛ. መቃብያን የመቃቢስ ዘምዓብ መቃብያን[97]

3ኛ. መቃብያን የመቃቢስ ዘብንያም መቃብያን[98]

መሆናቸው ሲተረክ ከእነዚህም እምዘረከቦሙ ለአይሁድ

---

93. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 827-844::
94. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τους ἑβδομηκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 510-519::
95. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 844-853::
96. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα ከ1ኛ መቃብያን 2.5 ጋር አስተያይ::
97. 2ኛ መቃብያን 1.2፤ 2.6::
98. 1ኛ መቃብያን 2.1::



አሜሶጶጣሚያ ዘሶርያ[99] እና ይትነሡያ ደሴያተ ግብጽ[100] አንደኛ መቃብያን ሲባሉ በመዋዕለ ጽርዓውያን ወሜዶናውያን ሀሎ አሐዱ ንጉሥ ዘስሙ ጺሩፃዕይዳን[101] 2ኛ መቃብያን ሆኖ 3ኛ መቃብያን መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ዘውእቱ መቃብያን[102] የተባለው እንደሆነ ተደርጎ ተተርጉሟል[103]::

ስለዚህ:

1ኛ መቃብያን ዘመቃቢስ ዘአልአዛር

2ኛ መቃብያን ዘመቃቢስ ዘሞዓብ

3ኛ መቃብያን ዘመቃቢስ ዘብንያም

4ኛ መቃብያን መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን ዘውእቱ መቃብያን

ወደ ታሪክ ስንመለስ በርግጥ መቃብያን በሚል ርእስ 4 መጻሕፍት ይገኛሉ:: እነዚህም አራት መጻሕፍት 3ቱ /1-3/ ወይም በቡልጋታን ፤1-2/ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ሰብዓ ሊቃናት በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተይዘው የሚገኙ ሲሆን[104] አራተኛው መቃብያን በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በታተመው ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት በአባሪነት ተቀርጾ ይገኛል[105]:: በመጠኑም ቢሆን እነዚህን መቃብያን ስንመለከት እነዚህን ይመስላሉ::

---

99. ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ገጽ 43::
100. ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ገጽ 43::
101. 1ኛ መቃብያን 1.1::
102. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ቁጥር 17::
103. ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ገጽ 43::
104. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατα τοὺς ἑβδομηκοντα /ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃውንት/ ገጽ 445-519::
105. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατα τοὺς ἑβδομήκοντα /ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 852-864::



www.ethiopianorthodox.org

1ኛ መቃብያን በመጀመሪያ ከይዘቶቹ አንጻር መቃብያን- አይሁድ በአገራቸው ላይ ሰፍኖ የነበረን ግሪክ ፍልስፍና፣ ባህልና እምነት ለማስወገድ በአጭሩ ስለ አገራቸው ብሔራዊ እምነታቸው ያደረጉት ትግል ታሪክ ነው:: ማቃቤዎስ - መቃቢስ- መቃብያን የሚለው ቃል በካህን ማታትያስ እና ቀጥሎም በልጆቹ በይሁዳ መቃቤዮስ[106]፣ ዮናታን ታሲ[107]፣ ስምዖን አኙሩስ[108] መሪነት በሴዴቃውያን /የሴዴቅ ወገኖች/ ላይ ለተነሱት ቀናዒያን አይሁድ የተሰጠ ስያሜ ነው::

ቃሉ ራሱ ማቃቢ /ስ/ ማቃቤዎስ በዕብራይስጥ ቋንቋ «ማቃባ» ማለት ቀስት ማለት ሲሆን በዚሁ መልኩ ፀረ ጠላት ቀስት ማለት ይሆናል:: በመጀመሪያ መቃቢስ /ማቃቤዎስ/ ተብሎ የተሰየመው- የተጠቀሰው ይሁዳ[109] ነው:: አንደኛ መቃብያን የሚተርከው ታሪክ የ40 ዓመት /175 እስከ 135 ቅ.ክ/ ትግል ታሪክን ሲሆን ይህም በትልቁ እስክንድርና ወራሾቹ ዘመናት የነበረው ዘመን ታሪክ ነው::

የመጽሐፉ ዓላማ በአይሁድ ላይ ተንሰራፍቶ የነበረው የግሪክ ሥልጣኔ /ፍልስፍና/፣ እምነትና ባህል እንዲጠፋ በዚህ ምክንያት ሊጠፋ ተቃርቦ የነበረው የአይሁድ ብሔራዊ እምነት እንዲጠበቅና የፖለቲካ ነፃነታቸው እንዲሳካ ለማድረግ የተደረጉትን የመቃብያን የትግል ውጤቶች መዝግቦ ለትውልድ ማስተላለፍ ነው::

106. 1ኛ መቃብያን 2.4 2ኛ መቃብያን 8.1 (ይሁዳ መቃቢስ የተባለ)::
107. 1ኛ መቃብያን 2.5 (ዮናታን አኙፋስ የተባለ)::
108. 1ኛ መቃብያን 2.3 (ስምዖን ታሲ የተባለ)
109. 1ኛ መቃብያን 2.4፣ 3.1- 9፣ 22::



ስለዚህ በመጀመሪያ ስለ ታላቁ እስክንድርና[110] አልጋወራሾቹ[111] ይተረካል:: ቀጥሎም በካህን ማታትያስ[112] ከዚያም በመቃብያን ልጆቹ ይሁዳ[113]፣ ዮናታን[114] እና ስምዖን[115] መሪነት የተደረጉ ትግሎች ይተረካሉ::

1ኛ መቃብያን በመጀመሪያ የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ በአንድ ፍልስጤማዊ ይሁዳዊ ሲሆን ይህም ከ103 ቅ.ክ በፊት እንደነበር ይታወቃል:: ይህም ታሪክ የሚደገፍበት ምክንያት ይህን መጽሐፍ የጻፈው ሰው በ103 ከሞተ ዮሐንስ ዘይርካኖስ ጋር አብሮ እንደነበር መታወቁ ነው:: ሆኖም ይህ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ 1ኛ መቃብያን ጠፍቶ ግን በግሪክ ቋንቋ ትርጉሙ ሊገኝ ችሏል::

2ኛ መቃብያን በ1ኛ መቃብያን ዘመናት መካከል የነበረ የ15 ዓመታት /186-161/ቅ.ክ/ ታሪክን ከመተረኩ በመነጨ ከ1ኛ መቃብያን ተለይቶ ቢጻፍም ቅሉ በመሠረቱ በይዘቱ ብዙ ፍሬ ነገር ቢመሳሰልም አንዳንድ ነገሮች ይለያሉ:: የ2ኛ መቃብያን ዓላማ የእግዚአብሔር ርስት - ርስተ እግዚአብሔር ለሆነ ሕዝብ መሣሪያ ሆኖ በመነሳት የይሁዳ መቃቢስን የተሳካ አርበኝነት ውጤቶች መተረክ ሲሆን በይዘቱም ቢሆን ቄርኔዎስ ያሶን መቃብያን ስለአደረጋቸው ጦርነቶች ዝርዝር የአምስት ብሔረ መጻሕፍት ተዋጽኦን ይዞ እንደሚገኝ ይተረካል:: ይህ አስተዋጽኦ በአንድ እስክንድራዊ ይሁዳዊ ሰው በሁለተኛው ምዕተ

110. 1ኛ መቃብያን 1.1-4::
111. 1ኛ መቃብያን 1.4-9::
112. 1ኛ መቃብያን 1.10-2.7::
113. 1ኛ መቃብያን 3.1-9.22 = 2ኛ መቃብያን
114. 1ኛ መቃብያን 9.23-12.53::
115. 1ኛ መቃብያን 13.1-16.24::



www.ethiopianorthodox.org

ዓመት መጨረሻ ወይም በአንደኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ቅ.ክ እንደተዘጋጀ ይነገራል:: ሆኖም በይዘቱ በመግቢያው ላይ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ አገር የሚኖሩ አይሁድ በግብጽ ለሚገኙ ወንድሞቻቸው የላኩት መልእክት[116]፣በሊቀ ካህናቱ ላይ የተደረጉ የስም ማጥፋት ዘመቻዎች[117]፣ በአንጥያክስ ኤጲፋኒስ የተካሄደ የአይሁድ መሳደድ ስለዚህም የመቃብያን አመጽን ለማካሄድ መነሳሳት[118]፣ ከዚያም የይሁዳ መቃቢስ ዘመቻዎችና ድሎች[119]፣ ከአንጥያክስ ኤጴፋኒስ ሞት በኋላ ቤተ መቅድሱ ነጽቶ የምረቃው በዓል መደረግ ይታያል[120]::

2ኛ መቃብያን በመጀመሪያ ተጽፎ የሚገኘው በግሪክ ቋንቋ ነው::

3ኛ መቃብያን ካለፉት ሁለት መቃብያን የተለየ አጭር መጽሐፍ ሲሆን የተጻፈውም የሚተርከውም ታሪክ ከመቃብያን በፊት የነበረን ታሪክ ነው:: ግን ከመቃብያን ትግል ጋር ተመሳሳይ ታሪክ ነው:: ከዚህም በመነጨ ማለትም አስቀድሞ ቢጻፍም ቅሉ ከዓላማውና ይዘቱ አንጻር እሱም 3ኛ መቃብያን የሚለውን ስያሜ ሊይዝ እንደቻለ ይተረካል:: ይዘቱም ሲታይ ንጉሥ አንጥያክስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት እንደተነሳ[121] ግን ይህ የንጉሡ ምኞት እንዳልተሳካ[122]፣ ስለዚህ ንጉሡ አይሁድን ለመቀበል ርምጃን ለመውሰድ እንደወሰነ[123] እና በንጉሡ ትእዛዝ የአይሁድ መረሽን ቢተላለፍም[124] በተአምር መዳናቸው[125]፣ ከዚያም የአይሁድ ድልን መጐናጸፍ[126] ነው::

3ኛ መቃብያን የተጻፈበት ዘመን በአንደኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ክፍለ ዘመን ሲሆን የተጻፈበትም ቋንቋ ግሪክ ነው:: ጸሐፊው ግን አይታወቅም::

4ኛ መቃብያን:- በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በታተመ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት በአባሪነት ተይዞ መገኘቱ ይታያል[127]:: ስለዚህም እንደሌሎች 3 መቃብያን መጻሕፍት በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ተመዝግቦ አይገኝም:: ሆኖም ይህ መጽሐፍ ከሌሎች መቃብያን ጋር ሳይታተም የሚታለፍበት ጊዜ እምብዛም አያጋጥምም:: ለዚህም ምክንያት ሆኖ የሚታየው በአንድ በኩል በጥንት የሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን የእጅ ጽሑፎች እየተያዘ መገኘቱ በሌላም በኩል የይዘቱ አስፈላጊነት ነው::

በመሠረቱ አራተኛ መቃብያን የፍልስፍና ዓይነት መጽሐፍ ነው:: ጸሐፊው ግሪክ-ጽርዓዊ ይሁዳዊ ሲሆን የተጻፈበት ዘመን በአንደኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ቅ.ክ

116. 2ኛ መቃብያን 1.1-2.32::
117. 2ኛ መቃብያን 3.1-4.50::
118. 2ኛ መቃብያን 5.1-7.42::
119. 2ኛ መቃብያን 8.1-10.9::
120. 2ኛ መቃብያን 10.10-15.36::
121. 3ኛ መቃብያን 1.1-29::
122. 3ኛ መቃብያን 2.1-38::

123. 3ኛ መቃብያን 3.1-4.24::
124. 3ኛ መቃብያን 5.1-51::
125. 3ኛ መቃብያን 6.1-41::
126. 3ኛ መቃብያን 7.1-23::
127. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα /ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት/ ገጽ 1259-1273:: ነገር ግን በአንድአንድ የጥንት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእጅ ጽሑፎችና በአንድ አንድ ኅትመቶች ከመገኘቱ ጋር በግሪክ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቀው በታተሙ ቅድሳት መጻሕፍትም (1944 እና 1892) መካከል ተይዞ እንደሚገኝ መረዳት ይቻላል::


www.ethiopianorthodox.org

ወይም በአንደኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ጅ.ክ ነው:: ኢዮሲጶስ የሚባል ሰው ጽፎት እንደነበር በኤሮኒሞስና በሌሎች ጸሐፍት ይተረክ ነበር:: ምክንያቱም በሰብአውያን ስሜቶች ላይ የቅዱስ ሐሳብ ገዥነትን ለማሳየት ነበር አንዱ ገጽታው:: ስለዚህም ከአራት ዋና ዋና ቁም ነገሮች: ጨዋነት፣ ፍትሕ፣ ጀግንነትና ጥበብ-ማስተዋል ሲሆኑ ከእነዚህ አንዱ ጨዋነት ከመሆኑ ተነስቶ ቅዱስ ሐሳብን ይተነትናል:: ከዚህም በመነጨ ይዘቱ ከመግቢያው[128] ቀጥሎ ደግ ሐሳብ - ቀና ሐሳብን እና ስሜቶችን ሲያመለክት[129]፣ አንጥያክስ ኤጲፋኒስ አይሁድ የግሪክን ሥልጣኔ /ፍልስፍና/፣ ባህልና እምነት-አምልኮት/ እንዲቀበሉ መጠየቁን ይገልጣል[130]፣ ከዚያም የኤሌአዛር-አልአዛር መስዋዕትነት- ሰማዕትነት[131] የአምስት ወንድማማቾች መቃብያን መስዋትነት[132]፣ የአምስት ወንድማማቾች መቃብያን እናቶች ሰማዕትነት[133]፣ መደምደሚያ ነው[134]:: 4ኛ መቃብያን የተጻፈበት ቋንቋ ግሪክ ሲሆን ጸሐፊውም አንድ ጽርአዊ አይሁዳዊ እንደነበር ተገልጿል::

በመሠረቱ 4ኛ መቃብያን ጤናማ አስተሳሰብ በእምነት ላይ የተመሠረተ አስተሳሰብ ሲሆን በዚህም መሠረት ደካማ ስሜቶችን ማስወገድ፣ ከጊዜያዊ ሕይወት የዘላለም ሕይወትን መምረጥ መሆኑ የተገለጠበት መጽሐፍ እንደመሆኑ መጠን የሃይማኖት መጻሕፍነት ገጽታ ጎልቶ ይታያል::

---

128. 4ኛ መቃብያን 1.1-12::
129. 4ኛ መቃብያን 1.13-3.18::
130. 4ኛ መቃብያን 3.39-4.26::
131. 4ኛ መቃብያን 5.1-7.23::
132. 4ኛ መቃብያን 8.1-14.20::
133. 4ኛ መቃብያን 14.11-17.24::
134. 4ኛ መቃብያን 18.1-24::



እንግዲህ ሦስት ወይም አራት መቃብያን ከቅርጽ አንጻር በሁለቱም በኩል/ ግእዝና ሰብዓ ሊቃናት = ግሪክ/ ይህን መሰል ሰፊ ልዩነት ሲታይ ከይዘት አንጻርስ አንድ ናቸው ወይስ መሰል ልዩነት ይታይ ይሆን?

በመሠረቱ የታሪኩ አቀራረብ፣ ስምና ቦታ፣ የታሪኩ ባለቤቶች ብዙ ልዩነት እንዳላቸው ይታያል:: ሆኖም ግን የሚተረከው ታሪክ ይዘት አንድ አቅጣጫነት አለው:: ይህም ሲባል በአጭሩ በራስ በይሁዳ ክልልም ሆነ በአጠቃላይ በመካከለኛው ምሥራቅ ቀበሌዎች /ሜዶን፣ ሚሶጶጣምያ፣ ግብጽ፣ ወዘተ./ ተንሰራፍቶ - ሰፍቶና ሰፍኖ ይገኝ የነበረውን የግሪክ ሥልጣኔ /ፍልስፍና፣ ባህልና አመልኮት/ የበለጠ ለአይሁድነት እምነትና ባህል ውድቀት በጣም ጫና ሆኖ ከመገኘቱም ጋር አይሁድም በግድ ይህን የግሪክን ፍልስፍና፣ ባህልና አምልኮት እንዲቀበሉ እየተገደዱ በማይስማሙበት ጊዜም እየተገደሉ ወዘተ. ተመሳሳይ ግፍ እየደረሰባቸው-ቤት ንብረታቸው እየተደፈረ፣ ካህናቱም እየተገፉ፣ ወዘተ. ስለነበር ይህን ግፍና መከራ ለመቋቋም በወል ስም መቃብያን /ግእዝና ሰብዓ ሊቃናት-ግሪክ/ ግን በተለያየ ቅርጽ/ ይሁዳ መቃቢስ፣ ዮናታንና ስምዖን፣ ወዘተ/ በአንድ በኩል /እንደ ሰብዓ ሊቃናት/ በሌላ በኩል መቃብያን: መቃብቢስ ዘአልአዛር፣ መቃቢስ ዘሞዓብና መቃቢስ ዘብንያም/ግእዝ/ ያደረጉት ትግልና የተጎናጸፉት ድል ታሪክ /የአርበኝነት ታሪክ/ ነው::

የሚቀረው ጥያቄ የግእዝ መቃብያን የሰብዓ ሊቃናት መቃብያን ትርጉሞች ናቸው? ወይስ አይደሉም? የሚለው ነው:: ትርጉሞች አይደሉም የሚባል ከሆነ ከወዴት መጡ? ናቸው የሚባል ከሆነ ይህ ሰፊ ልዩነት እንዴት ተፈጠረ?

ይህ እንግዲህ በጥናት በኩል መልስ የሚገኝለት ጥያቄ ነው:: ቢቻል ራሱን በቻለ ጥናት ለማመሳከር ሙከራ ይደረጋል::



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን በሌላ ጠኩል ከአንጥያክስ ኤጲፋኒስ በፊት መቶ ዓመት በነበረ በጠሎሚዎስ ፊልአጼልፎስ ዘመነ ሥልጣን በሰብዓ ሊቃናት በተመለሱት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (ሰብዓ ሊቃናት) ያልነበሩ ሁለት መቃብያን ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደ አለነበሯት፣ በዚህም መጽሐፍ (በእነዚህም መጻሕፍት) አንጥያክስ አይሁድን እንደ አሳደደ ተጽፎ ስለሚገኝ በርግጥም ይህ መጽሐፍ (እነዚህ መጻሕፍት) ከሰብዓ ሊቃናት በኋላ የተጻፉ (የተጻፈ) ለመሆኑ (ለመሆናቸው)[135] ነገር ግን በለንደን መዝገበ መጻሕፍት የሚገኝ ግእዝ መቃብያን ከዚህ መቃብያን (እነዚህ መቃብያን) ጋር እንደማይመሳሰል:: በዚህም አገር ይገኝ እንደሆን ቢፈለግ ሲገኝ ካለመቻሉ የተነሳ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሁለት መቃብያን እንዳታጣቸው በማሰብ ከዩናኒ-ግሪክ ወደ ግእዝ እንደተመለሱ ይገልጣል[136]:: ነገር ግን ከላይ እንደተገለጠው በሥርጭት በሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት የሚገኙት 3 መቃብያን ከግሪክ - ሰብዓ ሊቃናት 3 መቃብያን ጋር አይመሳሰሉም:: ሆኖም ሁለቱ መቃብያን በኢትዮጵያ አልነበሩም ነበር ለማለት ያስቸግራል (አሁን የተተረጎሙት ከሆነ ጥያቄ አይነሳም):: ምክንያቱም ከሲኖዶሶቱ በሁለቱ (በሦስቱም ማለት ይቻላል) ሁለት መቃብያን ተይዘው ይገኛሉ:: ግን ሲኖዶሳቱ ይዘዋቸዋል ማለት የግድ ወደ ግእዝ ተተርጉመዋል የሚያስኝም አይሆንም:: የሆነ ሆኖ አሁን በሥርጭት ላይ የሚገኙት መቃብያን ከዩናኒ - ግሪክ ወደ ግእዝ ከተተረጎሙ መቃብያን ጋር አንድ አይደሉም[137]::

---

135. ከዚሁ ገጽ 201 - 209፣ 262 - 264::
136. አባ ፋራንቺስኮስ ዘባሳኖ: ሰመንቱ ብሔረ አሪት፣ አሥመራ 1915 መጽሐፍ ቀዳማዊ: መቅድም ገጽ IX -X::
137. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1980) ገጽ 795 - 853 =አባ ፍራንቺስኮስ: ነቢያት ወመቃብያን - መጽሐፍ ራብዕ፣ አሥመራ 1918 ገጽ 403 - 499::



## በሐዲስ ኪዳን የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና፣ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስና ስምንቱ ግእዝ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ

በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ላይ እንደ ተመለከትነው እስከ አሁን ከተዘረዘሩት ክቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ 2 መልእክታተ ቀለሚንጦስና በ8 መጻሕፍት የተቀነባበሩ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ይገኛሉ::

እነዚህም ትእዛዛት «ለሁላችሁም ካህናትና ምእመናን . . . የእኛ ብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት . . . በእኔ ቀለሚንጦስ እጅ ለእናንተ ኤጲስቆጶሳት የተላኩ ሁለት መልእክታተ ቀላሚንጦስና በስምንት መጻሕፍት ትእዛዛት ክቡራትና ቅዱሳት ይሁኑ»:: ከሚለው ሐረግ በመነጨ ሐዋርያውት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ወይም በአጭሩ ቀለሚንጦስ በመባል ይታወቃሉ::

ከዚህም በመነሳት እነዚህ ትእዛዛት ወይም ከእነሱ ላይ ተነስተው የተዘጋጁ ወይም ሳይሆኑም የተለያዩ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ወይም በብዛት ሰመንቱ ብሔር ዘቀለሚንጦስ በመባል የሚታወቁ መጻሕፍት ወይም የተሻለ መድበለ ቀኖናት: ሰሜንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ይገኛሉ[1]::

## 1. ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

በብሔረ ሕግ ወቀኖና (NOMOKANON) ጥናት ቀለሚንጦስ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት በሱርስጥ፣ ቅብጥ፣ ዐረብኛ እና ግእዝ ትርጉሞች ግን በአንድ ወጥነት-ተመሳሳይነት ሳይሆን ከተለያየ ይዘትና አቀማመጥ ልዩነት ጋር ይገኛሉ::

---

1. F. Funk: Didascalia et Constitutiones Apostolorum, Paderborn 1905, Βιβλιοθήκη Ελλήνων πατερων κάι'Εκκλησιαστικων συγγραφεων T.B. ገጽ 5-172፣ G.Bardv: Dictionaire de droit canonique T.IV., 149 ገጽ 453-460::



www.ethiopianorthodox.org

## 1.1 ሱርስጥ - ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ በ687 በኤጴ እንደተዘጋጀ ሲገመት በዚህ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት የተያዙ ሰነዶች ከ6ኛው ምዕተ ዓመት አስቀድሞ የነበሩ ሲሆን ስምሳ የመጀመሪያዎቹ ሁለት መጻሕፍት - ኪዳናት ዘእግዚእ በ52 በአንጾኪያ ሊቀ ጳጳሳት ሳዊሮስ መጠቀሳቸው ሲታወቅ ሱርስ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ከግሪክ እናቱ ሰነድ ጋር በመተያየ በ1956 ሊታተም ችሏል[2]::

በዚህም ኅትመት መሠረትነት ሱርስጥ ስምንቱ ብሔ ቀኖናት ይዞአቸው የሚገኙት ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው፡:

1. ኪዳን ዘእግዚእ 3
2. ኪዳን ዘእግዚእ[3]
3. ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት[4]
4. ስለ ሲመትና ሀብተ ክህነት ትእዛዛትና ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት[5]
5. ስለ አሥረ ክህነት ትእዛዛት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ዘበእደ አቡሊዲስ[6]
6. ስለ ካህናትና ምእመናን ትእዛዛት ዘሐዋርያት[7]

---

2. A. Baumstrak: ueber den Octateuchus Clement Römische Quartalschrift T. XIX 1906 ገጽ 291-300:
3. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 240-246::
4. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 168-181::
5. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕገ ወቀኖና ገጽ 206 የግርጌ ማስታወሻ 216::
6. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 206፣ የግርጌ ማስታወሻ 917::
7. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 207፣ የግርጌ ማስታወሻ 918::



7. ስለ ቅዱስ ቁርባንና ምሥጢረ አምልኮት ትእዛዛት ዘቅዱሳን ሐዋርያት[8]
8. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት[9]

## 1.2 ዐረብኛ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

ቀለሚንጦስ - ዐረብኛ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት የሚከተሉትን ስምንት (8) መጻሕፍት ይዞ ይገኛል::

1. 1ኛ እና 2ኛ ኪዳናት ዘእግዚእ[10]፤
2. ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት ዘቅዱሳን ሐዋርያት[11]
3. ቅብጣዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ[12]፤
4. ስለ ሲመት-ስጦታና ሀብት ክህነት ትእዛዛትና ቀኖናት ቤተ ክርስቲያናውያት[13]፤
5. ስለ አሥረ ክህነት ትእዛዛት ሐዋርያውያት ዘበእደ ቀለሚንጦስ[14]፤

---

8. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 207፣ የግርጌ ማስታወሻ 919::
9. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 137-166::
10. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 207 የግርጌ ማስታወሻ 922::
11. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 207 የግርጌ ማስታወሻ 923::
12. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 186-192 የግርጌ ማስታወሻ 924::
13. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 207 የግርጌ ማስታወሻ 925::
14. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 207 የግርጌ ማስታወሻ 926::



www.ethiopianorthodox.org

6. ስለ ካህናትና ምእመናን ትእዛዛት[15]፤
7. የቀኖና 32 የመጀመሪያ ሐረግ ብቻ[16]፤
8. 81 ሐዋርያውያት ቀኖናት[17]፤

በሱርስጥ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናትና በዐረብኛ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት መካከል ያለው ልዩነት ሱርስጥ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት 2 መጻሕፍት ኪዳናትን ሲይዝ ዐረብኛው ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ሁለቱን ኪዳናት አንድ አድርጎ ነው ይዞ የሚገኘው። ሱርስጥ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ሐዋርያውያትን በሚመለከት ሱርስጥ ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት 85ቱን ሲይዝ ዐረብኛው 81ቱን ነው ይዞ የሚገኘው::

ስለዚህ 8 መጻሕፍትን ለማሟላት በሱርስጥ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት የማይገኘውን ቅብጣዊ ቤተ ክርስቲያናዊ ትእዛዝ ይዞ ይገኛል[18]:: የቀረው ልዩነት በሌሎች የሰነዶች ምልዓትና እድገት ብቻ ነው[19]::

## 1.3 ቅብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

ቀለሚንጦስ ቅብጣዊ ሰብዓተ ብሔረ ቀኖናት የዐረብኛው ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ሰባቱ መጻሕፍት ግልባጭ ነው ማለትም የዐረብኛውን ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት የመጀመሪያውን መጽሐፍ /ኪዳን ዘእግዚእን/ ስለማይዝ ነው[20]:: በሌላም በኩል ዐረብኛው ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት 81 ሐዋርያውት ቀኖናትን ሲይዝ ቅብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት 56 ሐዋርያውያት ቀኖናትን-ረስጠጅን ነው ይዞ የሚገኘው[21]::

በአጭሩ አሁንም በሱርስጥ፣ ዐረብኛና ቅብጥ ብሔራተ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ የጎላ ልዩነት እምብዛም አይታይም::

## 1.4 የግእዝ ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን «ሲኖዶስ ዘአበው ሐዋርያት ቅዱሳን» በሚል ርእስ በሚታወቅ መድበለ ቀኖናት ስመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ተመዝግበው ይገኛሉ::

በአጭሩም ይህ ሲኖዶስ በውስጥ ከያዛቸው ልዩ ልዩ ቀኖናት የመጀመሪያዎች ልዩ ልዩ ስምንቱ ሐዋርያውያት ቀኖናት ናቸው:: እነሱም የሚከተሉት ናቸው::

1. 72 ቀኖናት ዘአበው[22]፤
2. 56/57/ ቀኖናት-ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን[23]፤
3. ቀኖናት - ሲኖዶስ ዘቀለሚንጦስ ዘጸሐፈ ጴጥሮስ ረድእ ርእሰ ሐዋርያት[24]፤
4. 30 ቀኖናት-ሲኖዶስ መጽሐፈ ዜናሆሙ ለሐዋርያት[25]፤

---

15. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ: ሕግ ወቀኖና ገጽ 207 የግርጌ ማስታወሻ 297::
16. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ: ሕግ ወቀኖና ገጽ 208 የግርጌ ማስታወሻ 928::
17. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ: ሕግ ወቀኖና ገጽ 208 የግርጌ ማስታወሻ 929::
18. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ: ሕግ ወቀኖና ገጽ 186-191፣ 207::
19. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ: ሕግ ወቀኖና ገጽ 208-210::
20. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት ብሔረ: ሕግ ወቀኖና ገጽ 240-246::
21. ዲበኩሉ ዘውዴ፣ ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 208-210::
22. እነዚህ 72 ወይም 71 ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት፣ ረስጠብ ቀለሚንጦስ ዳግም ተብለው የሚጠቀሱት ቀኖናት ናቸው::
23. እነዚህም 56/57/ ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት ረስጠጅ ቀለሚንጦስ ሣልስ ተብለው የሚታወቁት ቀኖናት ናቸው:: ሲኖዶስ ገጽ 41-48::
24. እነዚህ ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት አልተመለከተም ሲኖዶስ ገጽ 48-52::
25. 30 ቀኖናተ ሐዋርያት በፍትሐ ነገሥት «ዓይን» በሚል ምኅጻረ ቃል /እንደ ሚጠቀሱ/ ተጠቅሰውም ባይገኙ ቅሉ/ የተመለከቱት ቀኖናት-ሥርዐተ ጽዮን ናቸው:: ሲኖዶስ ገጽ 54-58:: ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 212፣ 113 - 136::


www.ethiopianorthodox.org

5. 82 ቀኖናት - አብጠሊሳት ዘሐዋርያት[26]፣
6. 25 ቀኖናተ ስምኦን ቀነናዊ[27]፣
7. 80 ቀኖናት-ሥርዐተ ሐዋርያት[28]፣
8. 80/81/ ቀኖናት-አብጠሊስ ዘሐዋርያት[29]፣

## 2. ስምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ

ከዚህ ቀጥሎ ይህ ሲኖዶስ ሲኖዶሳውያትንና ሌሎችንም ልዩ ልዩ ቀኖናት ከዘረዘረ በኋላ ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን-ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስን በመጨረሻ ይዞ የሚገኝ ሲሆን እነዚህም ስምንት መጽሐፍተ ቀለሚንጦስ ከላይ ከተመለከቱት ቀኖናት-ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት የተለዩ ሆነው ይታያሉ::

ስለዚህም በመጀመርያ ቅዱስ ቀለሚንጦስ ሲል ጀምሮ የተለያዩ ርእሶችንም ሆነ ወይም ቀኖናትን ሳያመለክት በስድ ንባብ ብዙውን ክፍል ቢዘረዝርም የሚከተሉት 8 ርእሶች ለንባቡም ቢሆን መነሻ ሆነው ይገኛሉ::

1 - 2 «ቅዱስ ቀለሚንጦስ»[30] በሚል ርእስ ተነስቶ ከቀኖናውያት ትእዛዛት ጋር እምብዛም ያልተያያዘ ታሪክን በመተረክ ግን በሁለት ንዑሳን እንበላቸው ክፍሎች ተከፍሎ ስለሚጨርስ ሲሆን ይችላል: ከስምንቱ መጻሕፍት ሁለቱን እንደያዘ ሆኖ ተቆጥሮ የሚከተለው መጽሐፍ እንደ 3ኛ መጽሐፍ ተቆጥሮ ይገኛል::

---

26. 82 ቀኖናት - አብጠሊሳት በፍትሐ ነገሥት ረስጠአ - ቀለሚንጦስ ቀዳማዊ የሚባሉት ናቸው:: ሲኖዶስ ገጽ 58-70::
27. እነዚህ ቀኖናት በፍትሐ ነገሥት አልታወቁም:: ሲኖዶስ 71-81::
28. 80 ሥርዐተ- ቀኖናተ ሐዋርያት ቅዱሳን - ሲኖዶስ ገጽ 86 - 98
29. 80(81) ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን - ሲኖዶስ ገጽ 86 -98 በቁጥሮች 2፣ 5.7፣ የሰፈሩት ሐዋርያውያት ቀኖናት በተለያየ ቅርጻቸው ይሁን እንጅ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉሞች በመሆናቸው አንድ ዓይነት ናቸው::
30. ሲኖዶስ ገጽ 213-237::



3. ቀዳሚ ምሥጢራት ዘከሠተ ጴጥሮስ፡
4. ንቀድም ወንጽሕፍ ኃይለ ወተአምረ[32]፣
5. ዘነገሮ ጴጥሮስ ርእሰ ሐዋርያት ለቀለሚንጦስ[33]፣
6. ሥርዐት ዘቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘነገሮ.. ጴጥሮስ ለቀለሚንጦስ ረድእ[34]፣
7. ቀለሚንጦስ ሣልስ[35]፣
8. በትር ዘዘበጠ ለሰይጣን[36]፣

እንግዲህ እነዚህ በሌላ መልክ ስምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ በመባል የሚታዩት መጻሕፍት በጣም ዝርዝር ከመሆናቸው ጋር ሥነ ሥርዐትን ተከትለው የተቀረጹ ከአለመሆናቸውም በላይ በሌላ በኩል እነዚህ ስምንት መጻሕፍት ናቸው በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና «ክቡራት ቅዱሳት» ተብለው የተቀመሩት? ወይስ ሌሎች ናቸው? ሆኖም ቀደም ብለው የተጠቀሱት ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ራሳቸው ስምንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ባይሆኑም ቅሉ በብዛት ከእነዚህ ትእዛዛት ላይ የተቀነባበሩ መሆናቸው ይታያል::

ደግሞስ እነዚህ መጻሕፍት ከሆኑ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ተደምረው ነው የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ወደ 81 የደረሰው? ይህም ጥያቄ ይከተላል:: በሌላም በኩል ፍትሐ ነገሥት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙ 81 መጻሕፍት በማለት ቢነሳም መጻሕፍቱ ሲዘረዝሩ 73 መጻሕፍትን ቆጥሮ ነው የሚቆመው[37]:: ሆኖም የፍትሐ ነገሥት መተርጉማን እና

---

31. ሲኖዶስ ገጽ 238-253::
32. ሲኖዶስ ገጽ 254-284::
33. ሲኖዶስ ገጽ 285-308::
34. ሲኖዶስ ገጽ 309-313::
35. ሲኖዶስ ገጽ 313-324::
36. ሲኖዶስ ገጽ 325 - 339::
37. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2::



www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን የሊቃውንት ጉባኤ ይህን 73 ቁጥር ወደ 81 ለማድረስ ሁለት መጻሕፍተ ኪዳናትን፣ አራት መጻሕፍት ሲኖዶስን፣ መጽሐፈ ቀለሚንጦስንና ዲድስቅልያን ማለትም ሁለት መጻሕፍተ ኪዳንን፣ አራት መጻሕፍተ ሲኖዶሳትን፣ ቀለሚንጦስንና ዲድስቅልያን ማለትም 2 + 4 +1 + 1 = 8 (ስምንት) መጻሕፍትን በ73 መጻሕፍት ላይ በመደመር 81 መጻሕፍትን ያሳያል::

ነገር ግን በአንድ በኩል መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ስምንት መሆናቸውን ስንመለከት በሌላ በኩል እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማን እና እንደሊቃውንት ጉባኤ አንድ መጽሐፈ ቀለሚንጦስ ነው ሲባል የሚሳው ጥያቄ መጽሐፈ ቀለሚንጦስም ከስምንቱ የትኛው መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል ነው::

ሆኖም በእኛ በኩል ሁለተኛዎቹ ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ-ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ከላይ ከተመለከትናቸው ሱርስጥ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናትም ሆነ ወይም ዐረብኛ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናትና ግብጥ ሰብዓቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ጋር የሚዛመዱ ሁነው አይታዩም::

## 3. ሐዋርያውያት ትእዛዛት ዘበእደ ቀለሚንጦስ-ሰመንቱ ብሔራተ ቀኖናት

«ብእኔ ቀለሚንጦስ አማካይነት /እጅ/ በ8 መጻሕፍት ተዘጋጅተው ለእናንተ ኤጲስ ቆጶሳት የተላለፉ ትእዛዛት፣ እነዚህም በውስጣቸው በያዙአቸው ምስጢራት ምክንያት ለሁሉም አይተላለፉ»

ሐዋርያውያት ትእዛዛት (Constitutiones Apostolicae - Ἀποστολικαὶ διαταγαὶ ወይም ትእዛዛተ ሐዋርያት (Constitutiones Anostolorum -Διαταγαὶ τῶν Ἀποστόλων) በሚል ርእሶች ተቀነባብረው ሲያያዙ የመጡ ሥራዎች ይገኛሉ::



እነዚህ ሐዋርያውያት ትእዛዛት የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት፣ ሕግንና ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዘው የሚገኙ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ኋላ ከጥርጣሬ ላይ ቢወድቁም በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻና በ5ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በ8 መጻሕፍት ተከፍለው መቀነባበራቸው ሲታሰብ ከእነዚህም 8 መጻሕፍት - ሐዋርያውያት ትእዛዛት የመጀመርያዎች 6 መጻሕፍት በይበልጥ ከዲድስቅልያ ዘ 12 ሐዋርያት ላይ ተመርኩዘው፣ ተቀናጅተውና በምዕራፎች ተቀነባብረው የሚገኙት መድብላተ ቀኖናት ሲሆኑ ከእነሱም የመጀመርያው መጽሐፍ 10 ምዕራፎችን[38]፣ 2ኛው 63[39]፣ 3ኛው 20[40]፣ 4ኛው 14[41]፣ 5ኛው 20[42] እና 6ኛው 30[43] ምዕራፎችን ይዘው ይገኛሉ::

ሰባተኛው መጽሐፍ 49 ምዕራፎችን ይዞ ሲገኝ[44] ከእነዚህም ምዕራፎች በተለይ 32ቱ ምዕራፎች 1-32 /ከትምህርተ 12 ሐዋርያት ለአሕዛብ የሁለተኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ሥራ ላይ ተመስርተው የተዘጋጁ መሆናቸው ይታወቃል[45]::

ስምንተኛው መጽሐፍ አንድም 2 ምዕራፎች /1-2/ ከአቡሊዲስ ዘሮሜ ሐዋርያዊ ትውፊት/ሐዋርያዊ ትውፊት

38. መጽሐፍ አንድ: ስለምዕመናን አጠቃላይ ትምህርት /ም ከ1-10::
39. መጽሐፍ ሁለት: ስለ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት/ም ከ1-20/
40. መጽሐፍ ሦስት: ስለ መበለታት /ም. ከ1-14/
41. መጽሐፍ አራት: ስለ እጓለ ማውታ /ም ከ1-14/
42. መጽሐፍ አምስት: ስለ ሰማዕታት /ም ከ1_20/
43. መጽሐፍ ስድስት: ስለ መለየት /ም ከ1-30/
44. መጽሐፍ ሰባት: ስለመንግሥት ምሥጋናና ክርስቶስን ስለመቀበል/ም ከ1-49/
45. ዲበኩሉ ዘውዱ ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 146::



www.ethiopianorthodox.org

[illegible]
በሚል ርእስ ከሚታወቅ የአቡሊዲስ ሥራ ላይ ተመስርቶና 46 ምዕራፎችን ይዞ፣ የቀሩት 25 ምዕራፎች /3-27/ ቅዳሴ ቀለሚንጦስ ከሚባል አንጾኪያዊ ቅዳሴን እና የመጨረሻዎች 19 ምዕራፎች/38-46/ ልዩ ልዩ ቤተክርስቲያናውያት ቀኖናትን ይዞ ተቀነባብሮ የሚገኘው መጽሐፍ ሲሆን 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በአባሪነት 47ኛውን ምዕራፍ ይዘው ይገኛሉ[46]::

በሌላ በኩል ግን እነዚህ 8 መጻሕፍት - ሐዋርያውያት ትእዛዛት በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በ85ኛው ቀኖና በእነ በቀለሚንጦስ እጅ ለእናንተ ኤጲስ ቆጰሳት በ8 መጻሕፍት ተዘጋጅተው የተላኩ ግን በውስጣቸው ከሚገኙ ምስጢራት የተነሳ ለሁሉም መዳረስ እንደማይኖርባቸው ሁነው በቅዱሳትና ክቡራት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ገብተው ተመዝግበው ይገኛሉ::

እንግዲህ ሐዋርያውያት ትእዛዛት የሐዋርያውያት ሥራዎች እንደ አልሆኑና ስለዚህም የዘመነ ሐዋርያት ሥራዎች እንደአይደሉም ሲታይ ቢሆንም የጥንት ቤተ ክርስቲያን ሥራዎች መሆናቸው ሊካድ አይችልም::

በአንድ በኩል በውስጣቸው ከተያዙት ምስጢራት የተነሳ ለሁሉም እንዳይደረሱ በመታዘዙ በሰፊው ሊታወቁ ከአለመቻላቸውም በላይ በትሩሎ በ692 የተደረገ 5ኛ-6ኛ ሲኖዶስ በሲኖዶሳውያት ቀኖናትና ቀኖናተ አበው የተዘረዘሩትን ቅዱሳት መጻሕፍት በአጸደቀበት ጊዜ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና የተያዙትን መጻሕፍት ሲያጸድቅ በዚህ 85ኛ ቀኖና ዝርዝር ውስጥ ቢገኙም ቅሉ በውስጣቸው ስሕተትና ባዕድ ትምህርት

46. መጽሐፍ ስምንት: ስለ ፀጋና ሀብተ ክህነት፤ /ቀኖናት ቤተክርስቲያናውያት /ም ከ1-46/ /ም 47፤ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት አባሪ::



አለባቸው በማለት እነዚህ 8 ሐዋርያውያት ትእዛዛትን ሳያጸድቃቸው አልፍዋል[47]:: ይህን ሲኖዶስ ከመለያየት በኋላ የተጠራ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም አታውቅም:: ከዚህም የተነሳ በርግጥ በእነዚህ ትእዛዛት ውስጥ ሰፍረው የሚገኙት ስህተቶችን ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም የምትቀበላቸው አይደለም[48]::

ስመንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በ691 5ኛ-6ኛ ትሩሎ ሲኖደስ ተቀባይነት ሳያገኙ የቀሩት በውስጣቸው በያዙት ጸሎተ ሃይማኖት «ዘዕሩይ ምስለ አብ» = ከአብ ጋር እኩል የሚለው ሐረግ ወጥቶ በመገኘቱ ነው:: እንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ደምራ የምትቀበላቸው 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ እነዚህ ይሆኑ? ወይስ ሌሎች መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ናቸው? በፍተሐ ነገሥት መተርጉማንና በሊቃውንት ጉባኤ እምነት ግን አይደሉም:: ሆኖም ሁሉንም በዝርዝር ማመሳከርን ይጠይቃል:: በዚህ መጽሐፍ ይህን ለማድረግ የማይቻል ነው::

እስኪ እነዚህን በመጠኑም ቢሆን የፍትሐ ነገሥትን: ብሔረ ሕግ ወቀኖናን ገጽ 206 - 217 ግልባጭ እንመልከት::

47. 5ኛ - 6ኛ ሲኖዶስ ቀኖና 2::
48. ዲበኩሉ ዘውዱ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና ገጽ 147::



www.ethiopianorthodox.org

ሆኖም በመግቢያው መጨረሻ እንደተመለከተው እነዚህ ሐዋርያውያት ትእዛዛት የተለያዩ ሰፋፊ ምዕራፎችን በያዙ ስምንት መጻሕፍት ተከፍለውና ሥርዐተ ቤተክርስቲያንንና አሠረ ክህነትን ከእነዚህም ጋር 85 ሐዋርያውያት ቀኖናትን ይዘው የሚገኙ ሲሆኑ ወደ ግእዝ ቃል በቃል (ሰዋስዋዊ ትርጉም) እንኳን ባይሆንም በሐረግ ትርጉም ዘይቤ ሲሆን ተተርጉመው የሚገኙ ለመሆናቸው አስተማማኝ መረጃ በእኔ በኩል አልተገኘም::

እነዚህን ስምንት ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በግእዝ ከአሉት ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ጋር ለማመሳከር ያለው የተሻለ አማራጭ እነዚህን ስምንት ሐዋርያውያት ትእዛዛትን ወደ ግእዝ ወይም አማርኛ መተርጎም ሆኖ ይገኛል[49]::

49. ከዚሁ ገጽ 21::



# ምዕራፍ ስምንት
# የቅዱሳት መጻሕፍትና ምንጮች- ቀኖናት ማጠቃለያ ማገናዘቢያና መደምደሚያ

## 1. ማጠቃለያና ማገናዘቢያ

### 1.1 የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥርና ታሪካዊ ቀኖናዊነት

ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙ/እዙዛት/[1]

- «ክብራት» -ከሁሉም የላቀ ክብር ያላቸው/Σεβάσμια/[2]
- «ቅዱሳት» -ከሁሉም በላይ ቅድስና ያላቸው /Ἅγια/[3]
- «ንባባውያት» -መነበብ ያለባቸው /ግዴታ/Αναγνωστέα/[4]
- «ምንባባውያት»-መነበብ የሚኖርባቸው/Αναγινωσκόμενα/[5]
- «ቀኖናውያት»-የተቀነኑ-የተደነገጉ/Κανονικά-Κεκανονισμένα/[6]

1. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2:: ከዚሁ ምዕራፍ አንድ ገጽ 18...፣ ምዕራፍ አምስት ገጽ 142..::
2. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና::
3. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና
4. 60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ/ሎዶቅያ፣ /24/32 ቀኖና ዘካርታጌኒስ/ቅርጣግና/
5. 39ኛ መልእክተ አትናቴዎስ:: ምቅናን «ምቅናናውያን/ት/» ፈጽሞ ያልተለመደ ቅጽል ነው:: ሆኖም በልሳነ ጽርእ/ግሪክ/ ካኖኒዞሚኖን-ካኖኒዞሜና/ Κανονιζόμενον-Κανονιζόμενα /ለሚል ቀኖናዊ ቅጽል ትርጉም ሆኖ የተቀረጸ ቅጽል ነው:: «ቀኖና» ግሪክ ቃል «ካኖን»- KANΩN እንደ አለ በግእዝ የተቀዳ ቢሆንም ግስም ሊወሰድበት ችሏል:: ቀነነ= ሕግ ሥራ ፣ ደንብ አቆመ፣ /ደንባ/፣ አገገ፣ ደነገገ የሚል ግስ ተወልዷል /አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ: መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ 800:: ከዚህ በመነሳት በትክክል ግሪኩ ቀኖና የወጣበት ግስ «ካኖኒዞ» -Κανονίζω ይህን ትርጉም ይዞ ስለሚገኝ ከዚህም ግስ የወጣው መደንገግ፣ መደንባት የሚኖርበት የሚል ትርጉምን ይዞ የሚገኘውን ቅጽል የተሻለ ምትክ አማራጭ ሆኖ በመገኘቱ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

- ምቅናናውያት» -መቀነን-መደንገግ የሚኖርባቸው /Κανονιζόμενα/[7]
- «እሙራት» -ከሁሉም ይበልጥ የታወቁ-ርግጠኞች/Γνησια/[8]
- «አምላካውያት» -ስለ አምላክ የሚናገሩ /Θεία/[9]
- «ጽሑፋት በመንፈስ እግዚአብሔር» -በመንፈስ እግዚአብሔር ተቀኝተው የተጻፉ /Θεόπνευστα/[10] መጻሕፍትን ለማግኘት የሚያስችሉ ሲኖዶሳውያት ቀኖናትንና ቀኖናት አበውን ከማነጻጸሩ ጨምር ተመልክተናል::

ቤተ ክርስቲያን ለምታስተምረው ነገረ መለኮትና ለምትፈጽመው ሥርዐተ አምልኮት ምንጮች ይሆናት ዘንድ ልትገለገልባቸው እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጻሕፍት የትኞቹ መጻሕፍት መሆናቸውን ከላይ የተመለከቱትን ገጸተ ባሕርያት- የባሕርይ ቅጽሎችን ከመስጠት ጋር አባቶች በተናጠል ወይም በአንድነት ሲኖዶሳትን - በመጥራትና ቀኖናትን በመሥራት- በመደንገግ ወይም መልእክታትን በማስተላለፍና ለማመልከት - ለማሳየት ችለዋል::

በአጠቃላይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው ስለታዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የሚናገሩት(የሚቀንኑት ወይም የሚደነግጉት) ቀኖናት 6 ቀኖናት/ ሦስት ሲኖዶሳውያት እና ሦስት ቀኖናተ አበው/ ሲሆኑ እነዚህም ቀኖናት የመጻሕፍትን ዝርዝር አንድአንዶቹ በዝርዝር ሲያመለክቱ ሌሎች አንድ አንዶች ደግሞ በጥቅል በማሰባሰብ መልክ ለምሳሌ 4 ነገሥት፣

---

6. 24/32 ቀኖና ካርታጌኒስ /ቅርጣግና/
7. መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ::
8. ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት::
9. 24/32 ቀኖና ካርታጌኒስ/ግርጣግና/
10. መልእክተ አትናቴዮስ 39ኛ::



12 ንዑሳን ነቢያት በማለት ያመለክታሉ:: በሌላም በኩል ለእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ከላይ የተመለከቱትን ቅጽሎች ስንመለከት እየአንድአንዱ ቅጽል ሰፊና ጥልቅ ትርጉምና ትርጓሜ ያለው ነው:: እነዚህን ቅጽሎች በሚመለከት በመተርጉማነ ቀኖናት - በቀኖናቱ አንድምታ ትርጓሜ /በአገራችን በብዛት ባይታወቅምና ይህ ዓይነቱ ትርጓሜ ተሰጥቶአቸው ሊያጋጥም ባይቻልም/ ሰፊና ጥልቅ ትንተና ተደርጉባቸዋል:: ጥልቅ ግንዛቤም ዳብሮባቸዋል::

ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ ከላይ እንደተመለከተው መሰል ሰፊ ትንተና አካሄዶ ጥልቅ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ከመጽሐፉ ዓላማና ግብ ጋር አይሄድም ባይባልም በጣም ሊያሰፋው ስለሚችል በአጭር ሐረጎች የመወሰን ግዴታ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል::

1. ክቡራትና ቅዱሳት: «ክቡራትና ቅዱሳት» 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ለቅዱሳት መጻሕፍት የሰጣቸው ቅጽሎች ሲሆኑ እነዚህም ቅጽሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ከሁሉም የላቀ ክብር፣ ልዕልናና ቅድስና ያላቸው መጻሕፍት መሆናቸውን ያሳያሉ::

2. ንባባውያትና ምንባባውያት: 1) «ንባባውያት» የሚል ቅጽልን ለቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሙት 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና፣ 60ኛ ቀኖና ዘላኦደቅያ /ሎዶቅያ/ እና 24/32 ቀኖና ዘካርታጊኒስ /ቅርጣግና/ ሲሆኑ ለማሳየት የፈለጉት ለቤተ ክርስቲያን ትምህርትና አገልግሎት በግድ መነበብ ያለባቸውን መጻሕፍት ነው:: 2) «ምንባባውያት» የሚል ቅጽልን የተጠቀመ ታላቁ አትናቴዎስ ሲሆን ቅዱስ አትናቴዎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሁለት ክፍሎ ነው የሚያሳየው:: በመጀመርያ ለአብዛኞቹ መጻሕፍት መቀነን - መደንገግ የሚገባቸው አምላካውያትና ጽሑፋት በመንፈስ እግዜአብሔር የሚል ቅጽልን ሰጥቶ ከለየ ቡኋላ ለሌሎች ለተወሰኑ መጻሕፍት መነበብ የሚኖርባቸው -

www.ethiopianorthodox.org

ግዴታ የሌለባቸው «ምንባባውያት» የሚል ቅጽልን ሰጥቶአቸው አልፍዋል::

3. ቀኖናውያትና ምቅናናውያት: 1) ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የተደነገገ «ቀኖናውያት» የሚል ቅጽልን ለቅዱሳት መጻሕፍት ሰጥተው የሚገኙት 60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ /ሎዶቅያ/ እና 24/32 ቀኖና ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ ሲሆኑ 2) መቀነን - መደንገግ የሚገባቸው - «ምቅናናውያት» የሚለውን ቅጽል ትልቁ አትናቴዎስ ለእነዚሁ ቅዱሳት መጻሕፍት ሰጥቶ ይገኛል::

4. እሙራት: ለቅዱሳት መጻሕፍት ከሁሉም ይበልጥ የታወቁ የተረጋገጡ 1) «እሙራት» የሚለውን ቅጽል ለቅዱሳት መጽሐፍት ሰጥተው የሚገኙት ቀኖና ጎርጎርዮስና ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዮን ናቸው::

5. አምላካውያት: ስለ ትምህርተ መለኮትና ሥርዐተ አምልኮት የሚናገሩት ቅዱሳት መጻሕፍት «አምላካውያት» የሚለውን ቅጽልን ሰጥተው የሚገኙት ቀኖናት 24/32 ቀኖና ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ እና መልእክተ አትናቴዎስ ሁነው ይገኛሉ:: ይህ ቅጽል ቤተ ክርስቲያን እንደትቀበላቸው ለታዘዙ ቅዱሳት መጻሕፍት «ቅዱሳት» ከሚለው ቅጽል ጋር በአማራጭነት የምንጠቀምበት ቅጽል ነው[11]::

6. ጽሑፋት በመንፈስ እግዜአብሔር - ዘበመንፈስ እግዚአብሐኤር ተጽሕፋ:: ይህ የመጨረሻ ቅጽል በግሪክ ቋንቋ አንድ ድርብ ቃል ቴኦፕኔፍታ (Θεόπνευστα) /ሁለት ቃላት - ተደርበው/ ቴኦና ፕኔብማ - አምላክና መንፈስ (Θεός-πνεῦma) /ተጣምረው የተፈጠረ ሲሆን በግእዝ አንድ ድርብ ቃል መሆኑ ሲቀር የማይችል እንኳን ቢሆን አንድ ወጥ-ድርብ ቅጽል

11. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2::



ሲገኝ ባለመቻሉ በሐረግ ተተክቷል «ዘበመንፈስ እግዜአብሔር ተጽሕፈ»[12]:: ይህ ቅጽል ለቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጠው በታላቀ አትናቴዎስ - መልእክተ አትናቴዎስ እና 24/32 ቀኖና ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/ ሲሆን ይህ ቅጽል ለቅዱሳት መጻሕፍት ከዘረዘሩት ቅጽሎች ሁሉ የበለጠ የቅዱሳት መጻሕፍት ባሕርይ ገላጭ ቅጽል ነው::

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለትምህርተ መለኮትና ሥርዐተ አምልኮት በምንጨነት ልትገለገልባቸው የታዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ እግዜአብሔር ከተጻፉት ውጪ መሆን እንደሌለባቸው የሚያሳየው ቅጽል ነው:: ከዚህ ጋር አንድ አንድ ቀኖናት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጻሕፍት «ክቡራትና ቅዱሳት»፣ «ንባባውያትና ምንባባውያት»፣ «ቀኖውያትና ምቅናናውያት»፣ «እሙራት»፣ «አምላካውያትና ጽሐፋት በመንፈስ እግዜአብሐኤር» የሚሉ ቅጽሎችን እየሰጡ ቢገኙም ቅሉ ከተዘረዘሩት መጻሕፍት ውጪ ሌሎች መጻሕፍትም እንደይኖሩ በሩን - ዝርዝሩን አይዘጉም:: ሌሎች ደግሞ ከእነዚህ ቅጽሎች መካከል የተወሰኑትን መስጠት ግን እነዚህ መጻሐፍት እነዚህ ናቸው በማለት ከእነዚህ ከተዘረዘሩት መጻሕፍት ውጪ መጨመር ወይም መቀነስ እንደማይቻልም ይደነግጋሉ::

ሆኖም ቅዱሳት መጻሕፍት የመጨረሻ ቀኖናዊ ዝርዝራቸውን ይዘዋል ለማለት አላስቻለም:: ስለዚህም በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የቁጥር ልዩነት የሚታየው ለምሳሌ በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን ድረስ ለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝርና ልክ የመጨረሻ ውሳኔ አልተሰጠም:: ለዚህም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲጠራና

12. 2ኛ ጢሞ. 3.16-17::



www.ethiopianorthodox.org

እንዲወሰን ጥረት እየተደረገ ቢሆንም እስከ አሁን ይህ ሲኖዶስ ሊጠራ አልቻለም::

ሆኖም ወደ ዝርዝር መግባቱ የሚያስፈልግ አይመስልም:: የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት በ1441 በፍሎሬንድያ፣ በትሪንዶን በ1546[13] እና በቫቲካን በ1780[14] በተጠሩ ሲኖዶሳት አብዛኛውን የኢጳን - ካርታጌኒስ /ቅርጣግና/393፣ 397 እና 419 ሲኖዶሳት ውሳኔዎችንና የኢኖኬንድዮስ 1ኛ መልዕክትን /405/ መሠረት በማድረግ ወደ መጨረሻ ውሳኔ መድረሷ ይታወቃል::

እንግዲህ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አንድም እነዚህ ናቸው ወይም ክቡራትና ቅዱሳት፣ ወዘተ. ቅዱሳት መጻሕፍት በማለት የሚናገሩት 6 ቀኖናትን ተመልክተናል:: ከእነዚህ ቀኖናት መካከል እስከ ደረስንበት ሁኔታ ወደ ግእዝ ተተርጉመው የሚገኙት 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቢሆኑም በ85ኛው ቀኖና ዝርዝር ግን ሌሎችም ዝርሮች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ቀኖናም ባይሆን በሌሎች ቀኖናት የተያዙ መጻሕፍት አልቀሩም:: እንዲያውም ከዚህ አልፎ በትኛውም ቀኖና ያልተመለከተ መጽሐፍ ኩፋሌ ተይዞ ይገኛል::

ታሪኩ ይህ ብቻም አይደለም:: ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ተመልሰዋል የሚባሉት 4 ቀኖናት - መጻሕፍተ ቀኖናት ሁነው ይገኛሉ::

እነዚህም አንድም ርስ በራሳቸው ወይም በጠቅላላ ከ6ቱ ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በማነጻጸር እንዲታዩ ተደርጓል[15]::

አሁንም እነዚህ 4 ቀኖናት - መጻሕፍተ ቀኖናት በግእዝ ትርጉሞች ሰነዶች ግን «ሲኖዶሳት» በሚል መነሻ ይታወቃሉ::

---

13. ስለ ቅዱሳት መጻፍት ቀኖናት አዋጅ - De canonicis scripturis.
14. Constitutio dogmatico de Fide catholica.
15. የሚከተለው ሰንጠረዥ ቁ. 5 (ገጽ 232 - 236)



ይህንም ለማጠቃለል የእነዚህ ሲኖዶሳት የመጨረሻ ኖናት 56፣ 81፣ 80 እና 80በመካከላቸውና ከተመለሱበት የ85 ዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ጋር በማነጻጸር ልዩነታቸውንና ንድነታቸውን ለማሳየት ሲቻል በመጨረሻም ከእነዚህ ሲኖዶሳት ይ በመመሥረት 81 ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ መመልከት ወደምደሚያ እንደረሳለን::

www.ethiopianorthodox.org

# የአራት ግእዝ ትርጉሞች ሐዋርያውያት ቀኖናት በራሳቸውና ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ጋር ሲነጻጸሩ

## ሰንጠረዥ-ሰሌዳ -5

| ተራ ቁ. | ትእዛዝ 57 ቀኖና 56 | አብጠሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጠሊስ 81 ቀኖና 80 | 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀኖና 85 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት |
| 2 | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት |
| 3 | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን |
| 4 | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ |
| 5 | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም |
| 6 | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ |
| 7 | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት |
| 8 | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት |
| 9 | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት | 1ኛ ነገሥት |
| 10 | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት | 2ኛ ነገሥት |
| 11 | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት | 3ኛ ነገሥት |
| 12 | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት | 4ኛ ነገሥት |
| 13 | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት | 1ኛ ትሩፋት |
| 14 | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት | 2ኛ ትሩፋት |
| 15 | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ | 1ኛ ዕዝራ |
| 16 | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ | 2ኛ ዕዝራ |
| 17 | አስቴር | አስቴር | - - | አስቴር | አስቴር |
| 18 | ዮዲት | ዮዲት | - - | ዮዲት | - - |
| 19 | ጦቢት | ጦቢት | - - | ጦቢት | - - |
| 20 | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ |
| 21 | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር |
| 22 | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ |
| 23 | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ |
| 24 | ተግሣጽ | ተግሣጽ | - - | ተግሣጽ | - - |
| 25 | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ |
| 26 | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን | - - | ጥ/ሰሎሞን | - - |
| 27 | ጥበበ ሲራክ | ጥበበ ሲራክ | - - | ጥበበ ሲራክ | ጥበበ ሲራክ |
| 28 | 1ኛ መቃብያን | 1ኛ መቃብያን | - - | 1ኛ መቃብያን | 1ኛ መቃብያን |
| 29 | 2ኛ መቃብያን | - - | - - | 2ኛ መቃብያን | 2ኛ መቃብያን |
| 30 | - - | - - | - - | - - | 3ኛ መቃብያን |
| 31 | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| 32 | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ |
| 33 | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ |
| 34 | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| 35 | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ |
| 36 | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ |
| 37 | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም |





www.ethiopianorthodox.org

| ተራ ቁ. | ትእዛዝ 57 ቀኖና 56 | አብጥሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጥሊስ 81 ቀኖና 80 | 85 ሐዋርያ ውያት ቀኖናት ቀኖና 85 |
|---|---|---|---|---|---|
| 38 | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም |
| 39 | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ |
| 40 | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ |
| 41 | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ |
| 42 | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ |
| 43 | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ |
| 44 | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ |
| 45 | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል |
| 46 | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል |
| 47 | ኩፋሌ | ኩፋሌ | - - | ኩፋሌ | - - |
| | 46 | 45 | 37 | 46 | 42 |
| 1 | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ |
| 2 | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ |
| 3 | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ |
| 4 | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ |
| 5 | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት |
| | ጳውሎስ | ጳውሎስ | ጳውሎስ | ጳውሎስ | ጳውሎስ |
| | ወደ | ወደ | ወደ | ወደ | ወደ |
| 6 | ሮሜ ሰዎች | ሮሜ ሰዎች | ሮሜ ሰዎች | ሮሜ ሰዎች | ሮሜ ሰዎች |
| 7 | ቆሮንቶስ1ኛ | ቆሮንቶስ 1ኛ | ቆሮንቶስ 1ኛ | ቆሮንቶስ1ኛ | ቆሮንቶስ 1ኛ |
| 8 | ቆሮንቶስ2ኛ | ቆሮንቶስ2ኛ | ቆሮንቶስ 2ኛ | ቆሮንቶስ2ኛ | ቆሮንቶስ 2ኛ |
| 9 | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ |



| ተራ ቁ. | ትእዛዝ 57 ቀኖና 56 | አብጥሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጥሊስ 81 ቀኖና 80 | 85 ሐዋርያ ውያት ቀኖናት ቀኖና 85 |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን |
| 11 | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ |
| 12 | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ |
| 13 | 1ኛተሰሎንቄ | 1ኛተሰሎንቄ | 1ኛተሰሎንቄ | 1ኛተሰሎንቄ | 1ኛተሰሎንቄ |
| 14 | 2ኛተሰሎንቄ | 2ኛተሰሎንቄ | 2ኛተሰሎንቄ | 2ኛተሰሎንቄ | 2ኛተሰሎንቄ |
| 15 | 1ኛ ጢሞ | 1ኛ ጢሞ | 1ኛ ጢሞ | 1ኛ ጢሞ | 1ኛ ጢሞ |
| | ቴዎስ | ቴዎስ | ቴዎስ | ቴዎስ | ቴዎስ |
| 16 | 2ኛ ጢሞ | 2ኛ ጢሞ | 2ኛ ጢሞ | 2ኛ ጢሞ | 2ኛ ጢሞ |
| | ቴዎስ | ቴዎስ | ቴዎስ | ቴዎስ | ቴዎስ |
| 17 | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ | ቲቶ |
| 18 | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና |
| 19 | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን |
| 20 | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ |
| 21 | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ |
| 22 | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ | 1ኛ ዮሐንስ |
| 23 | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ | 2ኛ ዮሐንስ |
| 24 | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ | 3ኛ ዮሐንስ |





www.ethiopianorthodox.org

| ተራ ቁ | ትእዛዝ 57 ቀኖና 56 | አብጥሊሳት 82 ቀኖና 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት 80 ቀኖና 80 | አብጥሊስ 81 ቀኖና 80 | 85 ሐዋርያ ውያት ቀኖናት ቀኖና 85 |
|---|---|---|---|---|---|
| 25 | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ |
| 26 | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ |
| 27 | አቡቀለም ሲስ | አቡቀለም ሲስ | - - | አቡቀለም ሲስ | - - |
| 28 | - - | መ/ቀለሚን ጦስ 1ኛ | - - | - - | መ/ቀለሚን ጦስ 1ኛ |
| 29 | - - | - - | - - | - - | መ/ቀለሚን ጦስ 2ኛ |
| 30 | ቀለሚንጦስ 1ኛ | ቀለሚንጦስ 1ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 1ኛ | ቀለሚንጦስ 1ኛ |
| 31 | ቀለሚንጦስ 2ኛ | ቀለሚንጦስ 2ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 2ኛ | ቀለሚንጦስ 2ኛ |
| 32 | ቀለሚንጦስ 3ኛ | ቀለሚንጦስ 3ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 3ኛ | ቀለሚንጦስ 3ኛ |
| 33 | ቀለሚንጦስ 4ኛ | ቀለሚንጦስ 4ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 4ኛ | ቀለሚንጦስ 4ኛ |
| 34 | ቀለሚንጦስ 5ኛ | ቀለሚንጦስ 5ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 5ኛ | ቀለሚንጦስ 5ኛ |
| 35 | ቀለሚንጦስ 6ኛ | ቀለሚንጦስ 6ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 6ኛ | ቀለሚንጦስ 6ኛ |
| 36 | ቀለሚንጦስ 7ኛ | ቀለሚንጦስ 7ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 7ኛ | ቀለሚንጦስ 7ኛ |
| 37 | ቀለሚንጦስ 8ኛ | ቀለሚንጦስ 8ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 8ኛ | ቀለሚንጦስ 8ኛ |
| | 81 | 81 | 63 | 81 | 78 |



## 1.2 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሳት - መጻሕፍተ ቀኖናት ሥነ ትርጓሜና ትንተና

በተደጋጋሚ የተዘረዘሩት አራት ግእዝ ትርጉሞ ቀኖናት አንድም በሥነ ትርጓሜ /ዝርዝር ማብራርያዊ ትርጓሜ/ ወይም በሥነ ሰነድ ትርጉም /የቃል በቃል ትርጉም/ ሥርዐት የተመለሱባቸው 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና አቅሮአቸው የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር = 41/+1/ እና 36 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት /አቡቀለምሲስ አልተመለከተም/16 ግን ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስና 8 ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ 10+26 =36/ ሲደመሩ 41+36 = 77 ወይም 41+1 = 42+36 = 78 መጻሕፍትን ይዞ ይገኛል:: በሌላ በኩል ግን በዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ያልተመዘገቡ ግን በሌሎች ቀኖናተ መጻሕፍት የተመዘገቡ ቀኖናት በእነዚህ 3ቱ ግእዝ ትርጉም ቀኖናት ተይዘው ይገኛሉ::

1. ዮዲት
2. ጦቢት-ጦቢያስ
3. ቶግሣጽ
4. ጥበበ ሰሎሞን
5. አቡቀለምሲስ

በርግጥ እነዚህን መጻሕፎት ይዘው የሚገኙት ቀኖናተ መጻሕፍት: መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ በፋሲካ መልእክት/መነበብ የሚችሉ ተብለው በመጨረሻ ከተያዙት መካከል/፣ ቀኖና አምፊሎኪዮስ /አስቴር በአንድ አንዶች ዘንድ/፣ 24/32 ቀኖና ካርታጌነስ /ቅርጣግና/ ሲሆኑ እነዚህም ወደ ግእዝ

16. ከዚሁ ገጽ 33 - 41



www.ethiopianorthodox.org

ተተርጉመው ስመገኘታቸው ርግጥኛ ለመሆን አልቻለም[17]::

በሌላ በኩል ግን ይህ ሐሳብ እንዳይደገም እነዚህ በተወሰኑ ቀኖናት በአንድ ቢበዛ በሁለት ቀኖናት ከተመለከቱት ሌሎች ከ6ቱ ቀኖናተ መጻሕፍት ቢያንስ በ5ቱ ቀኖናት ማለት ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና በስተቀር በሌሎቹ ሁለት(2) ቀኖናት የተያዙ መጻሕፍት: ባሮክ፣ ሰቆቃው ኤርምያስ፣ መልእክተ ኤርምያስ ለምን አልተያዙም? የሚለው ጥያቄ ይነሳል:: ምን አልባት ብዙ ጊዜ በትርጓሚያተ ቀኖናት ተደጋግሞም እንደሚደገፈው «በኤርምያስ ይሸፈናሉ» የሚለው ሐሳብ ተቀባይነትን ከአላገኘ በስተቀር:: ስለዚህ ከ6ቱ ቀኖናት በአንዱ ወይም በሌላው ቀኖና እየተያዙ የተገኙት ቅዳሳት መጻሕፍት ብዛት 88 መሆኑን ደጋግመን ገልጸናል::

ታዲያ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከ88ቱ መጻሕፍት መካከል 10ሩ መጻሕፍት-ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ /ሁለት መልእክታተ ቀላሚንጦስና 8 ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ/ ከቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር የሚቃረኑ ባዕዳን ትምህርቶችን ይዘው ይገኛሉ በሚል ምክንያት በ692 የትሩሎ 3ኛ-6ኛ ሲኖዶስ ሳይጸድቁ እንደ ቀሩ ይታወቃል::

የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ አብነ አል አሳል እነዚህን ቀኖናት ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስን በምንጭነት አልተጠቀመባቸውም:: እንዲያውም የሚገርመው ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት አመላካውያት መጽሐፍት ቁጥር 81 ነው ብሎና ምንጮችንም /ረስጠአ 81 እና ረስጠብ 56 - ግን ማለት የነበረበት ረስጠጅ 56 እንጂ ረስጠብ 56 አልነበረም/[18] ተመርኩዞ ተነስቶ እነዚህን «አምላካውያት» መጻሕፍት ሲዘረዝር 8ቱ ትእዛዛትን ምስለ ቀለሚንጦስ[19] ባለማካተቱና ግን ሦስት መቃብያንን በመያዙ 73 መጻሕፍትን ብቻ ቆጥሮ ያቆማል[20]:: ያውም ሁለቱ ጥያቄ ያለባቸው::

በሌላ በኩል ለ81 መጻሕፍት በምንጭነት የተጠቀሱት የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት /ትርጉም/ ግእዝ ቀኖናት በእነዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ያልተያዙ መጻሕፍትን: ዮዲትን፣ ጦቢትን፣ ጥበበ ሰሎሞንን፣ ተግሣጽ ዘሰሎሞንና ኩፋሌን ይዘው ይገኛሉ:: ሆኖም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስምንቱ ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ /8 ብሔር ዘቀለሚንጦስ/ እንደ ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተቆጥረው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ቁጥር ወደ 35 እንደ አደረሱ የሚነገር ቢሆንም እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማንና ሊቃውንት ጉባኤ አይደሉም::

እንግዲህ እነዚህ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉሞች እንደሆኑ የሚታመኑት አራት ግእዝ ሐዋርያውያት ቀኖናት ይዘዋቸው የሚገኙት መጻሕፍት በ85 ሐዋርያውት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና የተዘረዘሩትን መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን ዮዲት፣ ጦቢት፣ ጥበበ ሰሎሞን፣ አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስ እንዲያውም በየትኛውም ቀኖና ያልተመለከተ መጽሐፈ ኩፋሌ ተመዝግበው ይገኛሉ::

ሁለት መጻሕፍተ ዕዝራን በሚመለከት አንድ ችግር አለ::

---

17 ከዚሁ ገጽ 132 - 135::

18. ዲበኩሉ ዘውዴ: ፍትሐ ነገሥት: ብሔረ ሕግ ወቀኖና= ረስጠአ ገጽ 135-166፤ ረስጠጅ ገጽ 197 - 200፤ ረስጠብ ገጽ 167 - 196::

19. 85 ሐዋርያውያት ቀኖ 85ኛ ቀኖና ከቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ከ8ቱ ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በፊት ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስ መገኘታቸው ሲታወቅ በእነዚህ ቀኖናት ረስጠአ እና ረስጠጅ ከአለመመ ልከታቸው በላይ እነዚህ መልእክታት ብዙም የሚታወቁ ሆነው አይገኙም::

20. በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ሦስት መቃብያን መገኘታቸው ሲታይ በፍትሐ ነገሥት ሁለቱ መቃብያን የማያጠያይቁ ሲሆኑ 3ኛው መቃብያን = እሱም መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደኮርዮን መሆኑን ለመቀበል የታመነበት ከሆነ ይሆናል:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2::


www.ethiopianorthodox.org

1ኛ ዕዝራ እና 2ኛ ዕዝራ ተብለው ተቀንነው ሲገኙ ቆይቶ አንድ ጊዜ 1ኛ ዕዝራ እና 2ኛ ዕዝራ በመባል ቀርቶ አንድ ዕዝራ እና 2ኛ ዕዝራ በነህምያ ተተክቶ ሲገኝ ሌላ ጊዜ ደግሞ 1ኛ ዕዝራ እና 2ኛ ዕዝራም ኑረው ነህምያም ሊገኝ ችሏል:: ነገር ግን በሊቃውንት የሚታመነው 1ኛ ዕዝራ እንደተጠበቀ ሆኖ 2ኛ ዕዝራ ከሁለት ተከፍሎ ከ1-10 ምዕራፎች ያለው ክፍል ራሱ 2ኛ ዕዝራ ሆኖ 11-13 መጨረሻ ሌሎች ምዕራፎች ሁነው ተለይተው ለነህምያ ተሰጥተው ይህ ክፍል ነህምያ ሊባል እንደቻለ ነው:: ስለዚህም ነው ነህምያ የዕዝራ ክፍል ይባላል በግእዝ ትርጉሙ[21]:: እንዲያውም 1ኛ ዕዝራ መጽሐፍ ዘዳግም ቀኖና ሆኖ 2ኛ ዕዝራ እና ነህምያ መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ሁነው ይገኛሉ:: በሌላ በኩል እንዲያውም በመቀነስም-አንድ ወይም ሁለት መቃብያንን በመዝለል 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስንና ሁለቱን መልእክታተ ቀለሚንጦስ ግን ጨርሶ በመተው ቢገኙም ቅሉ በሌሎች ቀኖናተ መጻሕፍትም ሰፍረው የሚገኙ መጻሕፍትን ይዘው እንደ መገኘታቸው መጠን በእነዚህ 6 ቀኖናተ መጻሕፍት ተዘርዝረው የሚገኙት መጻሐፍት ብዛት 88 ሲሆን እንዴት ወደ 81 መጻሕፍት ወረዱ - ተሰበሰቡ? እነዚህስ የትኞቹ ናቸው?

ከ88ቱ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን 81 መጻሕፍት ውስጥ ያልተያዙት መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው:: አንድ መቃብያን /1ኛው፣ 2ኛው ወይም 3ኛው መሆኑ አልተመለከተም[22]:: ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስ[23]፣ ትምህርተ ሐዋርያት እና ኖላዊ፣ መልእክተ ኤርምያስ፣ ባሮክ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ[24] ሰባት/7/ መጻሕፍት ይሆናሉ::

---

21. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 387::
22. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2::
23. የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና::
24. 39ኛ መልእክተ አትናቴዎስ፣ 60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ(ሎዶቅያ)::



ስለዚህ 88-7=81 መጻሕፍት ይቀራሉ ማለት ነው:: ነገር ግን ወደ ብሉይ ኪዳን-ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስንመለከት ይህ በ6 ቀኖናተ መጻሕፍት ተዘርዝረው የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር ሊታለፍ ይችላል::

በዚህ 88 መጻሕፍት ቁጥር 49 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሲሆኑ 39 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው::

ከዚህ ስንነሳ እንደሰብዓ ሊቃናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 49 ናቸው::

እነዚህንም በሁለት ክፍለን ልንመለከታቸው እንችላለን: መጻሐፍት በቀዳሚ ቀኖ እና መጻሕፍት ዘዳግም - ካልዕ ቀኖና ናቸው::

1. መጻሐፍት ዘቀዳሚ ቀኖና: አምስቱ ወይም ስምንቱ ብሔረ ኦሪት፣ አራት ነገሥት፣ ሁለት ዜና መዋዕል-ትሩፋተ ነገሥት፣ ዕዝራ /2ኛ ዕዝራ/ እና ነህምያ፣ አስቴር ቀጥለን እንደምንመለከተው በሙሉም ባይሆን፣ ምሳሌ ሰሎሞን፣ መክብብ፣ ማሕልየ መሓልይ፣ 12 ደቂቀ ነቢያትና 4 ዐበይት ነቢያት፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ ድምር 37፤ መጻሕፍት ዘዳግም/ካልዕ/ ቀኖና: 1ኛ ዕዝራ፣ ጦቢት፣ ዮዲት ከፊል አስቴር ምዕራፍ 1. 1ሀ-1ወ፣ 3.3ሀ-3ረ፣ 4. 17ሀ-17በ፣ 5.1ሀ-1ረ፣ 5.2ሀ-2ለ፣ 8. 12ሀ-12ደ፣ 10.3ሀ-3ተ፣ 3መቃብያን /ቡሏጋታን 2 መቃብያን/፣ 4ኛው መቃብያን መስመ መቃብያን በመባል ይታወቃል:: (ከእነዚህ 4 መቃብያን የመጀመሪያው መቃብያን በ103 ቅድመ ክርስቶስ /ልደተ ክርስቶስ/ በአንድ ፍልስጥኤማዊ አይሁዳዊ በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው የተጻፈው፡፡ይህም ዕብራይስጥ ጠፍቶ አሁን የሚገኘው በግሪክ ትርጉሙ ተገኝቶ ነው:: 2ኛው መቃብያን በ2ኛው መጨረሻና በ3ኛው መጀመሪያ ክፍለ ዘመን ቅድመ ክርስቶስ በአንድ የታላቁ እስክንድር ተከታይ አይሁዳዊ ሰው በግሪክ ቋንቋ እንደጻፈው ይተረካል::

www.ethiopianorthodox.org

3ኛው መቃብያን በ1ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ቅድመ ክርስቶስ በእስክንድርያ በአንድ ባልታወቀ ጸሐፊ በግሪክ ቋንቋ እንደተጻፈ ይታመናል):: ባሮክ፣ መልእክተ ኤርምያስ፣ ከዳንኤል ሶስና ቁጥር 1-64[25]፣ ጸሎተ አዛርያስና ሠለስቱ ደቂቅ ምዕ.3 24-90፣ ቤልና ደራጎን - ተረፈ ዳንኤል ቁጥር 1-42[26] ሲሆኑ ብዙ ጊዜ መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና የሚባሉት በሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን እንጂ በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የማይገኙት ናቸው:: ግን ለምን? የሚለው ጥያቄ የሚያረካ መልስ የሚያስገኝ አይደለም:: ምክንያቱም ለምሳሌ ሰቆቃወ ኤርምያስ መጽሐፍ ዘቀዳሚ ቀኖና ሆኖ ሲገኝ ባሮክ ለምን መጽሐፍ ዘዳግም ቀኖና ሆኖ ተመደበ? ቢባል መልሱ አስቸጋሪ ነው:: ቢሆንም ጠለቅ ተብሎ የሚታይበት ምርምር አያስፈልገውም ማለት አይደለም::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በ1980 የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይዘቶች በሁለት ክፍሎና /መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና እና መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና/ መድቦ ከመገኘቱ ሁኔታ ሲታይ የራሱን ጥያቄ ይዞ ይመጣል:: ይህም አብዛኛውን ጊዜ ከይዘት ሳይሆን ከቅርጽ አንጻርም ነው:: እስኪ እንመልከተው በመጠኑም እንኳን ቢሆን 1) መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖናን በሚመለከት የዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘት ከሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን ይዘት አይለይም:: ቢሆንም ተግሣጽ ዘሰሎሞን ከምሳሌ ሰሎሞን ተለይቶ መያዙ ይታያል:: በሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳን «ተግሣጽ» የሚባል መጸሐፍ ተለይቶ አይታይም:: ሆኖም ይህን ጨምሮ በሁለቱም ሰነዶች 21 መጻሕፍት ተዘርረው 2) መጻሕፍት ዘዳግም ካልዕ ቀኖናን በሚመለከት መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤልን፣ ጸሎተ ምናሴን፣ ተረፈ ኤርምያስን /ተረፈ ኤርምያስ ከመልእክተ ኤርምያስ ጋር ሲመስል ...ችልም ፈጽሞ የተለየ መጽሐፍ መሆኑንም/ ተመልክተናል::

25. ምዕራፍ አልተሰጠውም::
26. ምዕራፍ አልተሰጠውም



በቅዱሳት መጽሐፍት ዝርዝር ውስጥ መልእክተ ኤርምያስ አልተመለከተም /ከዚህ በስተቀር በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ የሚገኙት ክፍሎች/ እንደ መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና የሚቆጠሩት ክፍሎች/ በአንድ መጽሐፈ አስቴር ውስጥ ከየምዕራፉ ጋር ተጣምረው ተይዘው ይገኛሉ:: ስለዚህም እነዚህን ክፍሎች ለይቶ ከማስቀመጥ ይልቅ ራሱ መጽሐፈ አስቴርን በሁለት መልኮች ለመለየት ተሞክረዋል::

ስለዚህም በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ምዕራፍ 1.1ሀ-1ወ፣ 3.3ሀ-3ረ፣ 4.17ሀ-17 በ፣ 5.1ሀ-1ረ፣ 5.2ሀ-2ለ፣ 8.12ሀ-12ደ፣ 10-3ሀ-3ተ ይዘቶች የመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ሁነው ስለሚቆጠሩ ራሱ መጽሐፈ አስቴር እነዚህን ክፍሎች ይዞ መጽሐፍ ዘዳግም ቀኖና ሆኖ እንዲታተም ሲደረግ[27] እነዚህን ክፍሎች ሳይዝ ደግሞ መጽሐፍ ዘቀዳሚ ቀኖና ሆኖ ታትሟል[28]:: እንደዚሁም ሶስና፣ ተረፈ ዳንኤልና ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ እንደ መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ቢቆጠሩም ከዳንኤል ተለይተው አይገኙም:: ከእነዚህ በስተቀር ራሳቸውን ችለው የሚገኙት መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና የሚከተሉት ናቸው: ዕዝራ ካልዕ፣ ጦቢት፣ ዮዲት፣ 3 መቃብያን /ስለ 3ኛው መቃብያን በቀኖናቱ እንደ አልተያዘ ተመልክተናል/፣ ጥበበ ሰሎሞን፣ ጥበበ ሲራክ፣ ባሮክ፣

27. መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 400-406፣ በ1947 (1953) ኅትመት መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ ኦፍ ሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ግን እንደ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ሳይለዩ ነው የሚገኙት::
28. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት(1980) ገጽ 785-795::



www.ethiopianorthodox.org

ኩፋሌ በግእዝ ቀኖናት ብቻ ነው የሚገኘው/29 እና ሄኖክ /በማንኛውም ቀኖና ተመልክቶ የማይታወቅ መጽሐፍ ነው/::

እንግዲህ በሌላ በኩል ይህን አዲሱ የ1980 እትም መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት በውስጡ ተይዘው የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 85 ነው:: ታዲያ ይህ ቁጥር ከ81 ጋር እንዴት ይሄዳል? ይህ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲታተም ሲፈቀድ መታየት የነበረበት ጥያቄ ነበር:: ሆኖም የታየ አልመሰለኝም::

ቢሆንም አሁን መደምደሚያውን የምንሻበት ጥበብ መፈለግ ሚያስፈልግ ምንጩ ይህ ከዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘት አይደለም::

በመሠረቱ ከጥናት ላይ የተመሠረተ መረጃ ባይኖርም ከፍትሐ ነገሥቱም ላይ በመመሥረትም ሆነ በ85 የሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ላይ በመመርኮዝ 81ዱ መጻሕፍት የሚባለው አነጋገር ሲያያዝ የመጣ ልምድ ነው ማለትም 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተደምረው 81 ቅዱስ መጻሕፍት ተብለው ይታወቃሉ:: ስለዚህ እነዚህን መጻሕፍት ለማግኘት ከፍትሐ ነገሥት ላይ ስንነሳ ቅዱሳት መጻሕፍት 81 መሆናቸውን ከነምንጮቻቸው ሐዋርያውያት ቀኖናት /ረስጠአ 81 እና ረስጠጅ 56/ ጋር ለመመልከት ሲቻል መጻሕፍቱ ሲዘረዘሩ ግን 71 (ወይም 73) ሁነው ይገኛሉ:: ነገር ግን መተርጉማነ ፍትሐ ነገሥት ጸሐፊው እብነ አል አሳል በዚህ ፍትሐ ነገሥት 81 መጻሕፍት ብሎ ተነስቶ ከ71 ወይም 73 መጻሕፍት ላይ በመቆሙ የተከሰተውን ልዩነት ለመሸፈን ሲሉ ከእነዚህ በፍትሐ ነገሥቱ ከተዘረዘሩት 73 መጻሕፍት ላይ 8 መጻሕፍትን: ሁለት መጻሕፍተ ኪዳንን፤ አራት መጻሕፍተ ሲኖዶስን፤ አንድ መጽሐፈ ቀላሚንጦስንና አንድ ዲድስቅልያን በመጨመር 81 ቁጥር እንዲሞላላቸው ያደርጋሉ:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ግብኤ ይህን መስመር ነው ሲከተል የሚታየው::

ነገር ግን እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት «ክቡራትና ቅዱሳት»፣ «ንባባውያትና ምንባባውያት»፣ «ቀኖናውያትና ምቅናናውያት» «እሙሪት»፣ «አምላካውያት»ና «ጽሑፋት በመንፈስ እግዚአብሔር» መጻሕፍት ዝርዝርን ለማመልከት የተቀረጹ ሦስት ሲኖዶሰውያት ቀኖናትንና ሦስት ቀኖናተ አበውን /ከእነዚህ አንዱ መልእክት/ በድምሩ 6 ቀኖናተ መጻሐፍት መኖራቸውን አይተናል:: ነገር ግን ከእነዚህ 6 ቀኖናተ መጻሐፍት ከአንዱ 85 ሐዋርያውያት 85ኛ ቀኖና በስተቀር ሌሎች አምስቱ ቀኖናት የላአዶቅያ/ሉዶቅያ/ 60ኛውን ቀኖና ጨምሮ ወደ ግእዝ ቋንቋ ተመልሰው አለማግኘታችንን ተምልክተናል::

ስለዚህ አሁን እነዚህን 81 መጻሕፍትን ለማግኘት ምንጮቻችን 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት አራት ግእዝ ትርጉሞች ቀኖናት ናቸው:: ከእነዚህም ረስጠአ እና ረስጠጅ /ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ዘጸሐፈ ቀለሚንጦስ በእንተ ጴጥሮስ መምህሩ[30] እና ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን ዘወሀብዎ ሐዋርያት በእደ ቀለሚንጦስ ዘለአክዎ ቀዲሙ[31] ናቸው::

በመሠረቱ አራቱ ግእዝ ሲኖዶሳት-ቀኖናት የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉሞች መሆናቸውን ለመቀበል

29. ኩፋሌ፤ መጽሐፈ ኩፋሌ በመሠረቱ ከአምስቱ ብሔረ ኦሪት የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ: ዘፍጥረትና ዘጸአት የተከፈለና ይዘቱም የዘመንን አከፋፈል-ክፍለ ዘመናትን የሚናገር [illegible] መጽሐፍ [illegible] አለቃ ወልደ ክፍሌ [illegible] ገጽ 543::

30. ከዚሁ ገጽ 95 - 97::
31. ከዚሁ ገጽ 99 - 105::



www.ethiopianorthodox.org

የሚያስቸግር አለመሆኑ ሲታይ ግን የአንድ ቋንቋ ሰነድ ወደ ሌላ ቋንቋ ሰነድነት ለመተርጐም-ለመመለስ የሚደረገውን ሥነ ሰዋስው ተከትለው ተመልሰው ከሆነ ርግጥም እነዚህ አራት ሲኖዶሳት-ቀኖናት የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉሞች ናቸው:: ነገር ገን የልሳነ ጽርእ (ግሪክ) 85 ሐዋርያውያት ቀኖናትንና እነዚህን ሲኖዶሳት-ቀኖናት ለማስተያየት ሲሞከር የተከሰተው ሁኔታ እነዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ወደ ግእዝ የተመለሱት በአብዛኞቹ ቀኖናት በሥነ ሰዋስዋዊ ትርጉም/ቃል በቃል ትርጉም/ ሳይሆን በሥነ አንድምታ ዓይነት ትርጉም ሆኖ ነው የምንመለከተው ምክንያቱም አንድ አንዶች ቀኖናት በመጠኑም ቢሆን ሰዋስዋዊ ቅጅን ሲከተሉ ለምሳሌ ረስጠጅ /ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን/ እንዲህ ሲል ይጀምራል «በቤተ /ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን/ ውስጥ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን/ ዘትካት ወዘሐዲስ ክርስቲያን ውስጥ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን/ ዘትካት ወዘሐዲስ /መጻሕፍት በሁሉም ካህናትም ሕዝብ /ሕዝባውያን/ ክቡራን ቅዱሳን/ ክቡራትና ቅዳሳት/ ይሁኑ[32]፣ አንድ ኤጲስቆጶስ በሦስት ይህም ካልሆነ በሁለት ኤጲስ ቆጳሳት ይሾም፣ ቄስና፣ ዲያቆን በአንድ ኤጲስቆጶስ ይሾም[33] የሚለው ድንጋጌ በተቃረበ መልኩ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉም ሆኖ ይገኛል:: ሌላው ቀኖና /ሥርዐተ ሐዋርያት/ ኤጲስቆጶስ በሁለት ወይም በሦስት ኤጲስቆጳሳት በዕለት ሰንበት ይሾም[34]፣ ሌሎችም እንደዚሁ ይላል[35]:: ይህ ቀኖና አሁንም የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ትርጉም መሆኑ ቢታይም በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ዕለተ ሰንበት የሚል ሐረግ የለም[36]፣ ቢሆንም ይህ ሥርዓተ

32. ቀኖና 56=85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀኖና 85::
33. ቀኖና 1=85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀኖና 1::
34. ቀኖና 1=85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀኖና 1::
35. ቀኖና 2=85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ቀኖና 2::
36. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 1ኛ ቀኖና::



ሐዋርያት ምንም እንኳን ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት አስቴርን፣ መቃብያንን፣ ሲራክን፣ ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስን፣ 8 ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስን ይዞ ባይገኝም ቅሉ በአጭር በቀኖናዊ ቅርጽ ሥርዐተ ሕጋዊ ቅርጽን ይዞ የተመለሰ ሆኖ ይታያል:: ሌሎች ሁለት ቀኖናት በጣም ለየት ባለ ዝርዝር ተቀርጸው ይገኛሉ::

ስለዚህ እነዚህ ሲኖዶሳት - ቀኖናት፡ ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን[37]፣ ሲኖዶስ ዘቅዱስ ሐዋርያት-አብጠሊሳት[38]፣ ሥርዐተ ሐዋርያት[39] እና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጠሊስ[40] አንድም አንዱ ሌላውን ወይም ሌላውን አንዱ ሲኖዶስ/ቀኖናትን/ ሳያገኝ እየአንዳንዳቸው ቀኖናት በሥነ ሰዋስው ትርጉም ሆነ ወይም በሥነ አንድምታ ትርጓሜ ይሁን ተመልክተዋል ወይም አንዱ የመጀመርያ ትርጉም ሰዎች (ሊቃውንት) እንደመሰላቸው እያስፋፉ ቀርጸዋቸዋል::

ስለዚህ እስኪ በአጭሩ የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና እንዴት ቢተረጎም ነው? ከ78 መጻሕፍት /78+1=79/ ወደ 81 ከፍ ብለው እንደተገኙ እንይ:: ቀደም ብለን በስንጠረዥ አስደግፈን እንደተመለከትነው[41] እነዚህ አራት ቀኖናት በመግቢያቸው ላይ የአምላካውያት መጻሕፍት ቁጥር 81 መሆኑን ገልጠው እናገኛለን:: ከነዚህም:

### 1.2.1 ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቤተክርስቲያን . . ትእዛዝ 57/56/ - ረስጠጅ

ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን . . . ትእዛዝ 57/56/[42] በፍትሐ

37. ሲኖዶስ ገጽ 41-48 ከዚሁ ገጽ 95፣ 96 - 99::
38. ሲኖዶስ ገጽ 49-70 ከዚሁ ገጽ 93: 99 - 105::
39. ሲኖዶስ ገጽ 81-86 ከዚሁ ገጽ 105 - 108፣ 95፣ 108 - 111::
40. ሲኖዶስ ገጽ 87-98 ከዚሁ ገጽ 108 - 111፣ 229 - 231::
41. ሰንጠረዥ 5 ከዚሁ 232 - 236::
42. ሲኖዶስ ገጽ 41-48::



www.ethiopianorthodox.org

ነገሥት ረስጠጅ (ቀለሚንጦስ ሣልስ) ተብሎ የሚታወቀው[43] መጽሐፈ ቀኖናት በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ተመዝግበው ከተላለፉት «ክቡራትና ቅዱሳት» መጻሕፍት መካከል ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 3ኛ መቃብያንና ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁለቱም መልእክታተ ቀለሚንጦስን ትቶና በሌሎች ቀኖናት መጻሕፍት ተመዝግበው የሚገኙትን መጻሕፍት: ዮዲትን፣ ጦቢትን፣ ተግሣጽ ዘሰሎሞንን[44]፣ ጥበበ ሰሎሞንን፣ ግን ደግሞ በየትኛውም ቀኖና ተይዞ የማይገኝ ኩፋሌን በድምሩ 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን = /46+35=81/81 መጻሕፍትን ይዞ ይገኛል::

## 1.2.2. ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 82 /ረስጠአ/

ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 82[45] እንደ ፍትሐ ነገሥት ረስጠአ /ቀለሚንጦስ ቀዳማዊ/[46] እንደ ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን .../ረስጠጅ/ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 2 መቃብያንን ሳይሆን አንድ መቃብያን ብቻ ይዞ ሲገኝ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ግን ከሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስ አንዷን መልእክተ ቀለሚንጦስ የያዘ ይመስላል - ሁሉንም መጻሕፍት ይዞ ይታያል::

ይህንን ለመመልከት የሚከተለውን 81ኛ ቀኖና የመጨረሻ አረፍተ ነገሮችን እንመለከታለን::

«... ምቅዋም ዘቀለሚንጦስ 8 እምሐዋርያት መጻሕፍት ወባቲ መደልወ ወአሐዱ ኢይወጽእ ዘነደጉ አበው አእምሩ

---

43. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::
44. ተግሣጽ ሰሎሞን የምሳሌ ሰሎሞን ክፍል ( ም. 25-31) መሆኑን ደጋግመን መግለጻችን ይታወሳል::
45. ሲኖዶስ ገጽ 49-70::
46. ፍትሐ ነገሥት መቅድም ክፍል 2::



መልእክተ ቀለሚንጦስ ወኩሉ ዘአዘዘናሁ ሙ ባቲ ኦ አበው ኤጲስ ቆጶሳት፣ ወጳጳሳት ወሊቃነ ጳጳሳት ወሊቃነ ካህናት በእደ ቀለሚንጦስ ረድኡ ለጴጥሮስ ሐዋርያ ወእንቲ 8 መጻሕፍት ወኢይደሉ ያርእይዎ ለኩሎሙ ምእመናን በእንተ ዘሀሎ ባቲ ሕግ ወሥርዐት ዘኢይደሉ ከመ ያንብብዎ ዘእንበለ ሊቃውንት ሥዩማን ...»[47]

እነዚህን አረፍተ ነገሮች ስንመለከት ጳጳሳት ... መልእክተ ቀለሚንጦስንና በእሷም ያዘዝነውን ሁሉ ዕወቁ የሚለው ሐረግ ከ8ቱ መጻሐፍት - ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ጋር መልእክተ ቀለሚንጦስም ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው ከታዘዙት «ክቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት» መካከል አንዷ መሆንዋን ለመረዳት ይቻላል::

ሆኖም ዐረፍተ ነገሩ ግልጥ ባለመሆኑ ትርጉሙ ሊያሻማ ይችላል:: ምክንያቱም በሌላ በኩል መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ «መልእክታተ ቀለሚንጦስ»ም ስለሚባሉም የመለየቱ ችግር በግልጥ ይታያል::

ስለዚህ መልእክተ ቀለሚንጦስ በሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት - አብጠሊሳት በክቡራትና ቅዱሳት መጻሐፍት መካከል ተይዛለች የሚለው ትርጉም ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነ ይህ ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 82/ረስጠአ/ 45 (46-1=45) የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 45 እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት 36(35+1=36) ሲደመሩ (45+36=81) 81 መጻሕፍትን ይዞ ይገኛል::

በሌላ በኩል ደግሞ ይህችን መልእክተ ቀለሚንጦስ መቀበል የማይቻል ከሆነ 80/45+35=80/ መጻሕፍት ይዞ ሊገኝ ይችላል:: ራሱ ሲነሳ 81 መጻሕፍት /ጉልቆ መጻሕፍት 81/ ብሎ ስለሚጀምር ይህን 81 ቁጥር ለማሟላት የሚቻልበት

---

47. ሲኖዶስ ገጽ 70::



www.ethiopianorthodox.org

ምክንያት ሁለት መቃብያን ይዞ እንደሚገኝ ማሰቡ ነው:: ምናልባት በአንድ መቃብያን ብቻ ተወስኖ ሊገኝ የቻለው ተደጋግሞ እንደተገለጠው ሰንዱ ከአንድ ቅጅ ወደ ሌላ ቅጅ በእጅ ጽሑፍ እየተገለበጠ በሚተላለፍበት ጊዜ አንዱ መቃብያን ተዘሎ /ተገድፎ/ ሊሆን ይችላል:: ወደ ዚህ መደምደሚያ ለመድረስ የሚያስገድደው መልእክተ ቀለሚንጦስን ለመቀበል ያዳገተ ሆኖ ሲገኝ ነው::

## 1.2.3 ሥርዐተ - ቀኖናተ ሐዋርያት ትእዛዝ 80

ሲኖዶስ - ሥርዐተ ሐዋርያት ተብሎ የሚለየው መጽሐፈ ቀኖናት[48] የቅዱሳት መጽሐፍት ቁጥር ስንት እንደሆነ በመግቢያው አያመለክትም:: ግን አሁንም መጽሐፈ ቀኖናት በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ከተመዘገቡት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሦስቱንም መቃብያን፣ አስቴርንና ጥበበ ሲራክን ሆኖም በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ሳይመዘገቡ ግን በሌሎች ቀኖናት የተመዘገቡ ሆኖም በአለፉት ሁለት ሲኖዶሳት መጻሕፍተ-ቀኖናት /ረስጠጅ እና ረስጠአ/ ተመዝግበው የሚገኙትንም መጻሕፍት: ዮዲትን[49]፣ ጦቢትን[50]፣ ተግሣጽ ዘሰሎሞንን[51]፣ ጥበበ ሰሎሞንን[52]፣ ኩፋሌን[53] ባለመጨመር 37 መጻሕፍትን ይዞ ሲገኝ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ያልተመዘገበው ግን በአለፉት ሁለት መጻሕፍተ ቀኖናት ተመዝግቦ ከሚገኘው አቡቀለምሲስ

48. ሲኖዶስ ገጽ 81 - 86::
49. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 771-784::
50. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 762-771::
51. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 513-519::
52. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪደን መጽሐፍት(1980) ገጽ 905-922::
53. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 929-986::



ዘዮሐንስ ጋር ሁለቱን መልእክታተ ቀለሚንጦስንና በምንት ትእዛዛትን ምስለ ቀለሚንጦስ በመተው 26 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ብቻ ይዞ ስለሚገኝ በድምሩ 37 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እና 26 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን /37+26=63/ 63 መጽሐፍትን ይዞ ይገኛል:: ይህ ሰነድ ነው ቀደም ብለን እንደገለጥነውም በቁጥርም በቅርጽም የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በሥነ ሰዋሰው ትርጉም ትርጉም ሆኖ የሚታየው፣ ልዩነት ቢኖር በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ተይዘው የሚገኙ አስቴርንና 3ቱንም መቃብያን መዝለሉ ነው:: አንድነት ደግሞ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ያልተመዘገቡ ሆኖም በሌሎች ቀኖናተ መጻሕፍት ተይዘው የሚገኙትና በአለፉት ሁለት ሲኖዶሳት-መጻሕፍተ ቀኖናት ተመዝግበው የሚገኙት መጻሕፍትም አለመጨመራቸው ነው::

ስለዚህም በቁጥር ከ81 በጣም ርቆ - በ18 ቁጥር /18 መጻሕፍት/ ርቆ ይገኛል::

## 1.2.4 ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን ... አብጦሊስ 81 -

ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን ዘጸሐፈ-ዘቤነወ ቀለሚንጦስ ... አብጠሊስ 80[54] ከሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 81/ረስጠአ/ ጋር አንድ መቃብያንን ብቻ ሳይሆን ሁለት መቃብያንን ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምናልባት ከላይ እንደተገለፀው መልእክተ ቀለሚንጦስን ይዞ መገኘቱ የሚታመንበት ከሆነ ይህችን መልእክተ ቀለሚንጦስ ባለመያዙ ሊለይ ሲችል ከሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን ... ትእዛዝ 57/56 -ረስጠጅ/ ጋር አንድ ዓይነት ይዘትንና ቁጥርን ይዞ ይገኛል::

54. ሲኖዶስ ገጽ 87-98::



www.ethiopianorthodox.org

በበዚህም ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 82/ረስጠአ/ 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በድምሩ 81 /46+35=81/ መጻሕፍትን ወይም 45 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና 36 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር (45+36=81) 81 መጻሕፍት ይዞ ይገኛል::

እንግዲህ በሥርዐተ ሐዋርያት እና በሌሎች 3 ሲኖዶሳት: ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን... ትእዛዝ 57/56/ - ረስጠጅ/፣ ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት .. አብጠሊሳት 82 /ረስጠአ/ እና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን ... አብጠሊስ 81 መካከል የሚታየው ልዩነት ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 82 /ረስጠአ/ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደሌሎች ሁለት ሲኖዶሳት ሁለት መቃብያን ሳይሆን አንድ መቃብያንና ከሐዲስ መጻሕፍት ምናልባት ጥያቄው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ መልእክተ ቀለሚንጦስን ይዞ በመገኘቱ ብቻ ነው:: በዚህ መልክ 3 ሲኖዶሳት 81 መጻሕፍትን ይዘው ይገኛሉ::

እንግዲህ በእነዚህ አራት ሲኖዶሳት: መጻሕፍተ ቀኖናት: ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን... ትእዛዝ 57/56-ረስጠጅ/፣ ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 82 /ረስጠአ/፣ ሲኖዶስ - ሥርዐተ ሐዋርያት ... ትእዛዝ 80፣ ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን ... አብጠሊስ 81 እና በፍትሐ ነገሥት ላይ በመመሥረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን 81 መጻሕፍት ሲባሉ የትኞቹ መጻሕፍት እንደሆኑ እንመለከታለን::

## 1.3 ፍትሐ ነገሥት

ፍትሐ ነገሥት «81 አምላካውያት መጻሕፍት» ብሎ ቢነሳም ቅሉ መጻሕፍቱን ቆጥሮ የሚያቆመው ከ81 ላይ አይደለም:: ከ71 አምላካውያት መጻሕፍት ወይም የሚከተለው ትርጉም ልዩነት ተጠብቆ ከ73 ላይ ነው ማለትም የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ ቤተክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙና



ቁጥራቸው 81 የሆነ « አምላካውያት መጻሕፍት» በሚል ርእስ ተነስቶ በአንድ በኩል የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን -አምላካውያት መጻሕፍትን ዘርዝሮ ከቆጠረ በኋላ[55] በመጨረሻም ከእነዚህ ውጭ የሆነ ወይም የሆኑ ጥበበ ኢያሱ ወልደሲራክ እና መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ከርዮን /ውፁእ እምእሉ ጥበበ ኢያሱ ወልደሲራክ ... ወካዕበ መጻሕፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን/ በሚል ቅጽላዊ (ውስጠዘ ቅጽል) ሐረግ ሁለት መጻሕፍትን ... ጥበበ ኢያሱንና መጻሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን አስፍሮ ይገኛል[56]:: በሌላ በኩል ደግሞ ወውፁእ እምእሉ = ከእነዚህ የተውጣ/የተውጣጡ/ ተብሎ ተተርጉሞ ይገኛል::

ይህ ትርጉም በተለይ ለጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክ /ጥበበ ሲራክ/ አያስኬድም፣ ከታሪክ ጋር አይሄድም-ይጋጫል ምክንያቱም የ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖናን ስንመለከት ይህን ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክ /ጥበበ ሲራክን/ ከ«ክቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት» ውጭ የሚል ቅጽልን ሰጥቶና ይዞ ነው የሚገኘው::

ስለዚህ 1ኛ. ከእነዚህ ሁለት መጻሕፍት አንድ ጥበበ ኢያሱ ወልደሲራክ /ጥበበ ሲራክ/ በመሆኑ ሁለተኛው መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደኮርዮን 2ኛውም /ወካዕበ/ ብሎ አጫፍሮት ስለሚገኝ ይህ ከእነዚህ ውጭ ውፁእ እምእሉ /ሁለቱንም ሊመለከት የሚችል በመሆኑም ሁለቱም መጻሕፍት ከአምላካውያት መጻሕፍት ውጭ ናቸው ብሎ መተርጐሙ ነው የሚያስኬደው:: በሌላ በኩል ከይዘት አንጻር እነዚህ ሁለቱ መጻሕፍት ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር መዛመዳቸው - መጣቀሳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተውጣጡ ግን አይደሉም:: የትኞቹ ከየትኞቹ?

---

55. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ [illegible]
56. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ [illegible]



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ይህ ከእነዚህ ውጭ የሚለው ትርጉም ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነ ስለዚህም ከታሪካዊ ምንጩ አንጻር «ከእነዚህ መጻሕፍት ውጭ» የሚለው ትርጉም ተቀሳባይነት ስለሚኖረው እንደ ፍትሐ ነገሥት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 44 ይሆናሉ:: ነገር ግን የግድ 81 ቁጥርን ለማሟላት ሲባል ከእነዚህ «አምላካውያት መጻፍት» ውጭ የሚለውን ቅጽልዊ ሐረግ የተውጣጣ /የተውጣጡ / ብሎ በመተርጐም እነዚህን ሁለት መጻሕፍት ከ44 ጋር በመደመር ወደ 46 /44+2=46/ ማድረስ ይቻላል::

በሌላ በኩል አሁንም የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ የሐዲስ ኪዳን አመላካውያት መጻሕፍትን ሲዘረዝር ከ27ኛ መጽሐፍ ላይ ያቆማል:: ስለዚህ 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት = 73 /46+27=73/ መጻሕፍት ይሆናሉ:: አሁንም ይህ 81 ቁጥር አይሟላም:: ከ81 - 73 =8 መጻሕፍት ይቀራሉ:: በዚህ ጊዜ የፍትሐ ነገሥት ጸሐፊ እብነ አል አሳል 81 ብሎ ተነስቶ 71 ቀርቶ ከ73 ላይ ሲያቆም ስለ 8ቱ መጻሕፍት በአእምሮ የታሰቡት የትኞቹ መጻሕፍት መሆናቸውን ማሰላሰል ያስፈልጋል:: ስለዚህ የፍትሐ ነገሥት መተርጉማን እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሁለት መጻሕፍተ ኪዳንን፣ አራት መጻሕፍተ ሲኖዶስን፣ አንድ መጽሐፈ ቀለሚንጦስን እና አንድ ዲድስቅልያን ከ73 ላይ በመጨመር 81 ቁጥርን ያገኛሉ[57]:: በሌላ በኩል ግን የታወቁት 8 መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ /8 ብሔር ዘቀለሚንጦስ/ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንደሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

---

57. ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው አፍሴት ኀትመት ገጽ 43፣ የ7/06/1987 የሊቃውንት ጉባኤ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ::



እንደሚቆጠሩ ሲያያዝ ስለመጣም ይህን 81 ቁጥር የሚያሟሉት ከ73 የብሉይ እና ከ27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ሁነው ነው::

## 1.4 ሲኖዶሳት

ሶስተኛው ሲኖዶስ - ሥርዐተ-ቀኖና ሐዋርያት ቅዱሳን ይዘቱ በ63 መጻሕፍት ብቻ በመወሰኑ ሲዘለል አንደኛው ሲኖዶስ - ሲኖዶስ ቀኖናት - ዘቤተክርስቲያን ... ትእዛዝ 57 /56 - ረስጠጅ/ እና 4ኛ ሲኖዶስ - ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳት ... አብጠሊስ 81 ተመሳሳይ አንድ ዓይነት መጻሕፍትንና ቁጥርን ይዘው ተገኝተው 81 ቁጥርን ሲያሟሉ 2ኛው ሲኖዶስ - ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት ... አብጠሊሳት 82 /ረስጠአ/ ሁለቱ ሲኖዶሳት ሁለት ሁለት መቃብያንን ይዘው ሲገኙ ይህ ሲኖዶስ ግን አንድ መቃብያንን ብቻ ይዞ ቢገኝም በአንድ በኩል በሌላ በኩል አንድዋን መልእክተ ቀለሚንጦስ ይዞ እንደሚገኝ ስለሚታሰብ የያዛቸው መጻሕፍት ቁጥርም እንደአለፉት ሁለት ሲኖዶሳት ቀኖናት 81 ይሆናል:: ምናልባት ግን የአንድ መቃብያን መዘለል ደጋግመን እንደገለጽነው ሰነዱ ከአንድ ቅጅ ወደ ሌላ ቅጅ በእጅ ጽሑፍ በሚገለበጥበት ጊዜ ተዘሎ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም ራሱ 81 መጻሕፍትን እንደያዘ ነው የሚናገረው ወይም የግድ መልእክተ ቀለሚንጦስ ከአምላካውያት መጻሕፍት አንድዋ መሆኗን መቀበል ነው::



www.ethiopianorthodox.org

# በአራቱ ሲኖዶሳት - ግእዝ ትርጉሞች ሐዋርያውያት ቀኖናት መሠረት የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 81 ማሳያ

## ሰንጠረዥ 7

| ተ.ቁ | ብሉይ ኪዳን | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን- ትእዛዝ 56 | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት- አብጠሊሳት 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት- ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን- አብጠሊስ 80 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት | ዘፍጥረት |
| 2 | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት | ዘጸአት |
| 3 | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን | ዘሌዋውያን |
| 4 | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ | ዘኍልቁ |
| 5 | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም | ዘዳግም |
| 6 | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ | ኢያሱ |
| 7 | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት | መሳፍንት |
| 8 | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት | ሩት |
| 9 | ነገሥት 1ኛ | ነገሥት 1ኛ | ነገሥት 1ኛ | ነገሥት 1ኛ | ነገሥት 1ኛ |
| 10 | ነገሥት 2ኛ | ነገሥት 2ኛ | ነገሥት 2ኛ | ነገሥት 2ኛ | ነገሥት 2ኛ |
| 11 | ነገሥት 3ኛ | ነገሥት 3ኛ | ነገሥት 3ኛ | ነገሥት 3ኛ | ነገሥት 3ኛ |
| 12 | ነገሥት 4ኛ | ነገሥት 4ኛ | ነገሥት 4ኛ | ነገሥት 4ኛ | ነገሥት 4ኛ |
| 13 | ትሩፋት 1ኛ | ትሩፋት 1ኛ | ትሩፋት 1ኛ | ትሩፋት 1ኛ | ትሩፋት 1ኛ |
| 14 | ትሩፋት 2ኛ | ትሩፋት 2ኛ | ትሩፋት 2ኛ | ትሩፋት 2ኛ | ትሩፋት 2ኛ |
| 15 | ዕዝራ 1ኛ | ዕዝራ 1ኛ | ዕዝራ 1ኛ | ዕዝራ 1ኛ | ዕዝራ 1ኛ |
| 16 | ዕዝራ 2ኛ | ዕዝራ 2ኛ | ዕዝራ 2ኛ | ዕዝራ 2ኛ | ዕዝራ 2ኛ |
| 17 | አስቴር | አስቴር | አስቴር | - - | አስቴር |
| 18 | ዮዲት | ዮዲት | ዮዲት | - - | ዮዲት |
| 19 | ጦቢት | ጦቢት | ጦቢት | - - | ጦቢት |
| 20 | መቃብያን 1ኛ | መቃብያን 1ኛ | መቃብያን 1ኛ | - - | መቃብያን 1ኛ |
| 21 | መቃብያን 2ኛ | መቃብያን 2ኛ | መቃብያን 2ኛ | - - | መቃብያን 2ኛ |
| 22 | መቃብያን 3ኛ | መቃብያን 3ኛ | መቃብያን 3ኛ | - - | መቃብያን 3ኛ |
| 23 | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር | መዝሙር |
| 24 | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ | ኢዮብ |
| 25 | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ | ምሳሌ |
| 26 | ተግሣጽ | ተግሣጽ | ተግሣጽ | - - | ተግሣጽ |
| 27 | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ | መክብብ |
| 28 | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ | ማ/መሓልይ |
| 29 | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን | ጥ/ሰሎሞን | - - | ጥ/ሰሎሞን |
| 30 | ጥ/ሲራክ | ጥ/ሲራክ | ጥ/ሲራክ | - - | ጥ/ሲራክ |
| 31 | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| 32 | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ | አሞጽ |
| 33 | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| 34 | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ | አብድዩ |


www.ethiopianorthodox.org

| ተ.ቁ | ብሉይ ኪዳን | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን-ትእዛዝ 56 | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት-አብጠሊሳት 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት-ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን-አብጠሊስ 80 |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ | ዮናስ |
| 36 | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ | ሚክያስ |
| 37 | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም | ናሆም |
| 38 | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም | ዕንባቆም |
| 39 | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ | ሶፎንያስ |
| 40 | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ | ሐጌ |
| 41 | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ | ዘካርያስ |
| 42 | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ | ሚልክያስ |
| 43 | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ | ኢሳይያስ |
| 44 | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ | ኤርምያስ |
| 45 | ባሮክ | - - | - - | - - | ባሮክ |
| 46 | ሰቆቃው | ሰቆቃው | ሰቆቃው | ሰቆቃው | ሰቆቃው |
| 47 | መ/ኤርም ምያስ | መ/ኤርም ምያስ | - - | - - | - - ምያስ |
| 48 | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል |
| 49 | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል | ዳንኤል |
| 50 | - - | ኩፋሌ | ኩፋሌ | - - | ኩፋሌ |
| ድምር | | 46 | 45 | 37 | 46 |

| ተ.ቁ | ሐዲስ ኪዳን | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን-ትእዛዝ 56 | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት-አብጠሊሳት 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት-ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን-አብጠሊስ 80 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ | ማቴዎስ |
| 2 | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ | ማርቆስ |
| 3 | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ | ሉቃስ |
| 4 | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ | ዮሐንስ |
| 5 | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት | ግ/ሐዋርያት |
| | ጳውሎስ ወደ | ጳውሎስ ወደ | ጳውሎስ ወደ | ጳውሎስ ወደ | ጳውሎስ ወደ |
| 6 | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ | ሮሜ |
| 7 | ቆሮንቶስ1ኛ | ቆሮንቶስ1ኛ | ቆሮንቶስ1ኛ | ቆሮንቶስ1ኛ | ቆሮንቶስ1ኛ |
| 8 | ቆሮንቶስ2ኛ | ቆሮንቶስ2ኛ | ቆሮንቶስ2ኛ | ቆሮንቶስ2ኛ | ቆሮንቶስ2ኛ |
| 9 | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ | ገላትያ |
| 10 | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን | ኤፌሶን |
| 11 | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ | ፊልጵስዩስ |
| 12 | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ | ቆላስይስ |
| 13 | ተሰሎንቄ1ኛ | ተሰሎንቄ1ኛ | ተሰሎንቄ1ኛ | ተሰሎንቄ1ኛ | ተሰሎንቄ1ኛ |
| 14 | ተሰሎንቄ2ኛ | ተሰሎንቄ2ኛ | ተሰሎንቄ2ኛ | ተሰሎንቄ2ኛ | ተሰሎንቄ2ኛ |
| 15 | ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጢሞቴዎስ 1ኛ | ጢሞቴዎስ 1ኛ |
| 16 | ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጢሞቴዎስ 2ኛ | ጢሞቴዎስ 2ኛ |


www.ethiopianorthodox.org

| ተ.ቁ | ሐዲስ ኪዳን | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን-ትእዛዝ 56 | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት-አብጠሊሳት 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት-ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን-አብጠሊስ 80 |
|---|---|---|---|---|---|
| 17 | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና | ፊልሞና |
| 18 | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን | ዕብራውያን |
| 19 | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ | ጴጥሮስ 1ኛ |
| 20 | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ | ጴጥሮስ 2ኛ |
| 21 | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ | ዮሐንስ 1ኛ |
| 22 | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ | ዮሐንስ 2ኛ |
| 23 | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ | ዮሐንስ 3ኛ |
| 24 | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ | ያዕቆብ |
| 25 | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ | ይሁዳ |
| 26 | አቡቀለሚሲስ | አቡቀለሚሲስ | አቡቀለሚሲስ | - - | አቡቀለሚሲስ |
| 27 | ቀለሚንጦስ 1ኛ | ቀለሚንጦስ 1ኛ | ቀለሚንጦስ 1ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 1ኛ |
| 28 | ቀለሚንጦስ 2ኛ | ቀለሚንጦስ 2ኛ | ቀለሚንጦስ 2ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 2ኛ |
| 29 | ቀለሚንጦስ 3ኛ | ቀለሚንጦስ 3ኛ | ቀለሚንጦስ 3ኛ | - - | ቀለሚንጦስ 3ኛ |



| ተ.ቁ | ሐዲስ ኪዳን | ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን-ትእዛዝ 56 | ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት-አብጠሊሳት 81 | ሥርዐተ ሐዋርያት-ትእዛዝ 80 | ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን-አብጠሊስ 80 |
|---|---|---|---|---|---|
| 30 | ቀለሚን ጦስ 4ኛ | ቀለሚን ጦስ 4ኛ | ቀለሚን ጦስ 4ኛ | - - | ቀለሚን ጦስ 4ኛ |
| 31 | ቀለሚን ጦስ 5ኛ | ቀለሚን ጦስ 5ኛ | ቀለሚን ጦስ 5ኛ | - - | ቀለሚን ጦስ 5ኛ |
| 32 | ቀለሚን ጦስ 6ኛ | ቀለሚን ጦስ 6ኛ | ቀለሚን ጦስ 6ኛ | - - | ቀለሚን ጦስ 6ኛ |
| 33 | ቀለሚን ጦስ 7ኛ | ቀለሚን ጦስ 7ኛ | ቀለሚን ጦስ 7ኛ | - - | ቀለሚን ጦስ 7ኛ |
| 34 | ቀለሚን ጦስ 8ኛ | ቀለሚን ጦስ 8ኛ | ቀለሚን ጦስ 8ኛ | - - | ቀለሚን ጦስ 8ኛ |
| 35 | መ/ቀለሚን ጦስ 1ኛ | መ/ቀለሚን ጦስ 1ኛ | መ/ቀለሚን ጦስ 1ኛ | - - | - - |
| 36 | መ/ቀለሚን ጦስ 2ኛ | መ/ቀለሚን ጦስ 2ኛ | መ/ቀለሚን ጦስ 2ኛ | - - | - - |
| ድምር | 85 | 81 | 81 | 63 | 81 |



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ በዚህ መልክ እንደ ፍትሐ ነገሥትም ሆነ እንደ ሲኖዶስቱ-መጻሕፍተ ቀኖናት ከዚህ ጋር በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 81 ተሟልቶ መገኘቱ ቢታይም ቅሉ ወይም ከዚህ ቁጥር 81 አልፎ አልፎ 80 እየሆነ መገኘቱ ብዙ ባያሳስብም ነገር ግን ይህ የ81 ቁጥር መሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ ችግሩ እነዚህ 81 ወይም 80 መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙትና በጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናት የተያዙት መጻሕፍት መሆናቸውን ማረጋገጡ ላይ ነው::

ስለዚህ ለችግሩ መነሻ የሚሆኑት ነጥቦች በአንድ በኩል በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ከተመለከቱት /ከተቀነሱት 3 መቃብያን/ 3 መጻሕፍተ መቃብያን ሁለቱ መቃብያን በሁለቱ ሲኖዶሳት-ቀኖኖት (1ኛውና 4ኛው = ሲኖዶሳት ዘቤተ ክርስቲያንና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን)፣ አንድ መቃብያን በአንድ ሲኖዶስ (2ኛው - ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት) ተይዘውና በአንዱ ሲኖዶስ (3ኛው ሲኖዶስ - ሥርዐተ ሐዋርያት) ሳይያዙ መገኘታቸው ሲሆን በሌላ በኩል ከአራቱ በሦስቱ ሲኖዶሳት (1ኛው፣ 2ኛውና 4ኛው ሲኖዶሳት - ሲኖዶስ ዘቤተ ክርስቲያን፣ ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያት እና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን) በተጠቀሱት የጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናተ መጻሕፍት በአንድም ያልተመለከተ ኩፋሌ የሚባል መጽሐፍ[58] ተይዞ መገኘቱ ነው:: እንግዲህ ቀኖ ሆኖ የሚታየው እንደ አጋጣሚም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሦስት መቃብያን ተይዘዋል:: ይህም ሊረዳ ስለሚችል ኩፋሌን ከቁጥር በማስወጣትና መቃብያንን በማስገባት በጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናተ

58. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገጽ 926 - 986::



መጻሕፍት መሠረት ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጻሕፍት ቁጥር 81 ሆኖ መገኘቱን ማረጋገጥ ይቻላል:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ በታተመ መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተይዘው የሚገኙትን መቃብያን በጽርእ - ግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት ከተያዙት 3 መቃብያን ጋር አንድ አለመሆናቸው ማለት የፊተኞቹ መቃብያን የኋላኞቹ መቃብያን (ግእዝ መቃብያን የጽርእ-ግሪክ መቃብያን) ትርጉሞች መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ሁለቱን መጻሕፍት ጎን ለጎን አስቀምጦ ማነጻጸሩ ግዴታ ይሆናል::

ከዕብራይስጥ ተተርጎመ እንዳይባል 1ኛው መቃብያን በዕብራይ ስጥም ቋንቋ ቢጻፍ ቅሉ ጠፍቶ በግሪክ ትርጉም እንደ ተገኘ ሲታወቅ ሁለቱ መቃብያን ግን በግሪክ-ጽርእ ቋንቋ ነው የተጻፉት:: በዚህም መሠረት 3ቱም መቃብያን በዕብራይስጥ ቋንቋ አይገኙም:: ተተርጉመው ካልሆነ መስተቀር:: ስለዚህ እነዚህ የግእዙ - አማርኛው 3 መቃብያን[59] እና የግሪኩ 3 መቃብያን[60] መመሳከር ይኖርባቸዋል[61]:: ይህ እስከሚሆን

59. መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 795-853::
60. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατὰ τοὺς ἑβδομήκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 465-519::
61. ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መቅድም የሰነዶችም እንኳን ባይሆን ከቃላትና ዐረፍተ ነገሮች አንጻር ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥና ከግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት፣ ሐዲስ ኪዳንን ከግሪክ ሐዲስ ኪዳን ጋር ማስተያየት እንደተደረገ ተገልጧል::
ታዲያ ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን ከማስተያየት ጋር እነዚህ 3 መቃብያን በግሪክ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ጋር ተያይተው ይሆን? ተያይተው ከሆነ ምን አልባት ይህ ልዩነት ሳይታይ ቀርቶ እንዴት እንዲታተሙ ተደረገ? ነገር ግን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተቻለ መጠን ይበልጥ ከዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር የተመሳከሩት በ1947(1953) በተደረገ ኅትመት በመሆኑ በግሪኩ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር የተተረጎሙት ከእነዚሁ እንኳን ቢሆን በጊዜ ርዝመት አንጻር ልዩነታቸው በቀላሉ ሊታይ የሚችል አይደለም::

www.ethiopianorthodox.org

ድረስ ተመሳሳይ ሐሳቦች መነሳታቸው አይቀርም:: በአጋጣሚ በግሪክ ቋንቋ ከ6ቱ ቀኖናት በአንዱም ባይገኝም ቅሉ በብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት 4ኛ መቃብያን ይገኛል[62]:: ግን ከ3ቱ መቃብያን ተለይቶ መስመ መቃብያን(Apocryphal -'Αηόκρυφη) ይባላል:: ወደ ግእዝም ያልተመለሰ መቃብያን ነው:: ሌላው ከዚህ ጋር የሚታየው ጉዳይ አንድ አንድ መጻሕፍት: ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ መልእክተ ኤርምያስ፣ ባሮክ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ባይያዙም በሌሎች ከ6ቱ በ2ቱ በሌሎችም በትርጓሜ ቀኖናት ተይዘው መገኘታቸው ነው[63]:: ነገር ግን በእነዚህ አራት ግእዝ ትርጉሞች ቀኖናት አልተያዙም:: በሌላ በኩል ደግሞ በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት ሳይሆን በሌሎች ቀኖናት ያውም በተወሰኑት ቀኖናት ተይዘው የሚገኙትን መጻሕፍት: ዮዲትን[64]፣ ጦቢትን[65]፣ ጥበበ ሰሎሞን[66] በቀኖናት ከምሳሌ ሰሎሞን ተለይቶ ያልተመለከተም ተግሣጽ ዘሰሎሞንን ይዘው ይገኛሉ::

ስለዚህ ለዚህ የሚሰጠው ትርጉም ሦስቱም /ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ መልእክተ ኤርምያስና ባሮክ/ በኤርምያስ ስም ከትንቢቱ ጋር ተሸፍኗል ነው:: ይህም ብዙ ድጋፍን ያገኘ አስተሳሰብ - ትርጉም ስለሆነ ፍትሐ ነገሥትም ሆነ ሲኖዶሳቱም የተቀበሉት ይመስላል:: በዚህም መሠረት እነዚህ መጻሕፍት ከ81 ውጪ ናቸው ወደ ማለት አያደርስም:: በሌላም በኩል

62. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατα τοὺς ἑβδομήκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 852 - 864::
63. ቀኖናት ዘላኦዶቅያ (ሎዶቅያ) ቀኖና 60፤ (ቀኖናት ዘክርታጌኒስ(ቅርጣግና) ቀኖና 24/32፤) መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ፤ (ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት፣ ቀኖና አምፊሎኪዮስ)::
64. ቀኖናት ዘካርታጌኒስ(ቅርጣግና) ቀኖና 24/32፤ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ::
65. ቀኖናት ዘካርታጌኒስ (ቅርጣግና) ቀኖና 24/32፤ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ::
66. ቀኖናት ዘካርታጌኒስ (ቅርጣግና) ቀኖና 24/32፤ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ::



በዚሁ መልክም እንኳን ባይሆን አንድ አንድ ጊዜ ተለይተው ራሳቸውን ችለው የሚገኙ መጻሕፍት: ሶስና[67]፣ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ[68]፣ ቤል እና ደራጎን /ተረፈ ዳንኤል/[69] ምንም እንኳን መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና እየተባሉ ቢገኙም በዳንኤል ስም ተሸፍነው ከትንቢተ ዳንኤል ጋር አንድ ሆነው ይቆጠራሉ:: በዚህ መልክ መጽሐፈ አስቴርንም መመልከት ይቻላል:: ቀጥሎም ከሁለቱ መልእክታተ ቀላሚንጦስ አንድዋ መልእክት ተደጋግሞ እንደተገለጠው ርግጠኛ ለመሆን ካለመቻል ጥርጣሬ ጋር ትምህርተ ሐዋርያት - በአንድ አንዶች መጻሐፍት ስመንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ትምህርተ ሐዋርያት ናቸው የሚባለውን ባንቀበለውም እንደ ተጠበቀ ሆኖ እና ኖላዊ ዘሄርማ በፍትሐ ነገሥትም ሆነ በሲኖዶሳቱ - መጻሐፍተ ቀኖናት ሊታዩ አልቻሉም:: ስለዚህ ሳይታወቁ የቀሩ መጻሕፍት ናቸው::

ነገር ግን በመጨረሻ መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል፣ ኩፋሌ፣ ሄኖክ፣ ተረፈ ኤርምያስና ጸሎተ ምናሴ ታሪክና ቀኖናዊነት በጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናተ መጻሕፍት ያልታወቁ መጽሕፍት ናቸው:: ግን በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንደ ቀኖናውያት ቅዱሳት መጻሕፍት ተቆጥረው ተይዘው ይገኛሉ::

67. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τοὺς ἑβδομήκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ገጽ 834 - 835፤ መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 900 - 902::
68. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τοὺς ἑβδομήκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 839 - 840:: መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 922 - 924::
69. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατά τοὺς ἑβδομήκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 850 - 851:: መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት(1980) ገጽ 924 - 926::

www.ethiopianorthodox.org

አሁን ከላይ እንደታየው በርግጥ ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጦስ በፍትሐ ነገሥት ኀልቆ መጻሕፍት አምላካውያት - በአምላካውያት መጻሕፍት ቁጥር ውስጥ አልተመዘገቡም:: በሲኖዶሳትም ቢሆን እንደተመለከተው ሆኖ የሰምንቱ ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቁጥር ወደ 81 ያደረሱ መሆናቸው ሲረጋገጥ ውዝፍ ጥያቄ የትኞቹ ስምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ናቸው? እነዚህ ስምንቱ ትእዛዛት? የሚለው ነው[70]:: በእውነቱ በቀለሚንጦስ ስም ስምንቱ ሱርሰጥ ብሔረ ቀኖናት፣ ሰምንቱ ዐረብኛ ብሔረ ቀኖናት፣ ሰብዓቱ ቅብጥ ብሔረ ቀኖናት እና ሰምንቱ ግእዝ ብሔረ ቀኖናት፣ ከዚያም ሰምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ እንደ አሉ ተመልክተዋል[71]:: በመጨረሻም በሲኖዶስ የተያዙ ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን /8 ብሔር ዘቀለሚንጦስ/ አግኝተን ምን ዓልባት በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና ከተያዙት ስምንት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ የተመሰሉ ሁነው ይገኙ እንደሆነ ለማመሳከር ቢፈለግ ሁለቱን ሰነዶች በዝርዝር ማነጻጸሩ አስፈላጊ ነው::

---

70. ከዚሁ ገጽ 216::
71. ከዚሁ ገጽ 210 - 220::



## 2. መደምደሚያ

«በቅድስት ቤተክርስቲያን ተቀባይነታቸው ስለታዘዘና ቀጥራቸው 81 ስለሆነ አምላካውያት መጻሕፍት»[1] .. ወይም «ምእመናን በቤተ ክርስቲያን የተቀበሏቸው መጻሕፍት»[2] ቀኖናዊነት ምርምር ተግባራዊነት ትርጉም ችግር ከስፋት መጠን አንጻር በተወሰኑ ምዕራፎችና በታዘሉባቸው ገጾች ግዴታ ሊሆን ቢችልም ቅሉ በምልዓት - ዓይነት አንጻር ግን በቤተ ክርስቲያን ተቀባይነታቸው ወይም ምእመናን ሊቀበሏቸው /የተቀበሏቸው/ የታዘዙ «ክቡራትና ቅዱሳት» «አምላካውያትና ጽሑፋት መንፈሰ እግዜአብሔር» መጻሕፍት በዚህ መልክ ተቀባይነታቸው በታዘዙባቸው ቀኖናት ዝርዝር መሠረት ሊገናዘቡና ሊመሰክሩ እንዲችሉ ተደርጓል::

በጥንት ቤተክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናዊነት የታዘዙባቸው ቀኖናት /ሲኖዶሳውያት ቀኖናትና ቀኖናተ አበው/ ብዙችም ባይሆኑ ጥቂቶች አልነበሩም:: በድምሩ 6 ቀኖናት እንደሆኑ ተመልክቷል::

በእነዚህ ቀኖናት የተቀነኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ማለትም ሁሉም መጻሕፍት በሁሉም ቀኖናተ መጻሕፍት ተይዘው አይገኙም:: ግን አንድ አንዶች መጻሕፍት በተወሰኑት ቀኖናት ሌሎችም አንድአንዶች መጻሕፍት በሌሎች አንድአንዶች ቀኖናት ተይዘው ሲገኙ ሆኖም ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ አንዶች በተወሰኑት ቀኖናት ወይም ሌሎች በሌሎች ቀኖናት እየተያዙ መገኘታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት በ6ቱ ቀኖናት ተይዘው የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር ብዛት 88 ነው::

ቢሆንም ሁሉም መጻሕፍት እስከ መጨረሻ ቅዱሳት መጻሕፍት ሆነው የደረሱ አይደሉም ለምሳሌ ትምህርተ

---

1. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2/ርዕስ/::
2. ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ቁ15::



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያትና ኖላዊ/ዘሄርማ/[4] ነገር ግን እነዚህ 6 የጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናት መጻሕፍት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉመው ወይም አልተተረጎሙ እንደሆነ ለመመልከት በተደረገው ሙከራ ሲታይ ለመተርጎማቸው ምንጭን ባናገኝም ቅሉ አልተተረጎሙም ብሎ ወደ መጨረሻ መደምደሚያ ለማድረስ ግን ዕቀባ ተደርጓል።

ቢሆንም በ6ቱ ቀኖናት መጻሕፍት አንዱ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት በተለያየ ስፋት እና ጥበት ሰፍነው እንደመታየታቸው መጠን በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ ተርጓሚያን ሊሆን ይችላል ወደግእዝ ተመልሰውና በአራት ሰነዶች-ሲኖዶሳት ተይዘው ይገኛሉ።

ነገር ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝር በሚመለከት በእነዚህ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና የተዘረዘሩት ብቻ ሳይሆኑ በሌሎችም ቀኖናተ መጻሕፍት የተዘረዘሩ መጻሕፍት ጨምር ተይዘው ይገኛሉና[5]። ሆኖም በሌላ በኩል በእነዚህ

---

4. መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ።
5. -ዮዲት: 24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ ቅርጣግና/፣ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ
   - <u>ጦቢት/ጦቢያስ/</u>: 24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ/ ቅርጣግና/፣ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ፣
   - <u>ባሮክ</u>፣ 60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ /ሉዶቅያ/፣ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ፣ /24ኛ/ 32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ/ ቅርጣግና/፣ ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት፣ ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢንቆዩን ?/
   - <u>ሰቆቃው</u>: 59ኛ + 60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ /ሉዶቅያ/፣ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ/24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ/ቅርጣግና ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት፣ ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቶንዩን ?/
   - <u>መልእክተ ኤርምያስ</u>: ቀኖና 60ኛ ዘላኦዶቅያ /ሉዶቅያ/፣ መልእክተ አትናቴዎስ
   - 39ኛ /24ኛ/32ኛ ቀኖሃ ዘካርያጌኒስ/ ቅርጣግና/፣ ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት፣ ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንዩን/
   - <u>አቡቀለምሲስ-ራእየ ዮሐንስ</u>: 24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና/፣ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ/ (ቀኖና አምፊሎኪዮስ ዘኢቆንማዩን)።



ሲኖዶሳት የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር የመሰባሰብ ሁኔታ ይታይበታል። ስለዚህም ከ88 መጻሕፍት ወደ 81 መጻሕፍት ተሰባስበው መገኘታቸው ሲታይ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን(ባሮክ፣ ሰቆቃውና መልእክተ ኤርምያስ ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር እንደ አንድ ሆነው) የተዘለሉ ደግሞ ይገኛሉ (ትምህርተ ሐዋርያትና ኖላዊ ዘሄርማ)፣ 3ኛ መቃብያን አልተያዘም ግን በማንኛውም ቀኖና መጻሕፍት የማይገኝ መጽሐፍ ኩፋሌ ተይዞ ይገኛል።

እንግዲህ ትልቁ ጥያቄ የዚህ ጽሑፍ (መጽሐፍ) መነሻ ዓላማ ይህ 81 ቁጥር ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤት ክርስቲያን ክልል ቅዱሳት መጻሕፍት በእነዚህ ቀኖናት መሠረት ሆኖ ሊሆንም ይችላል ወይም በትውፊት በዚህም ምርኩዝነት ፍትሐ ነገሥት ሲተረጎም ቅዱሳት መጻሕፍት 81 መሆናቸው ሲያያዝ መጥቷል።

ነገር ግን በትክክል በእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት 81 ናቸው? ይበዛሉ? ወይስ ያንሳሉ? የሚለው ጥያቄ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም።

ስለዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት 81 መሆኑ ሲያያዝ ከመጣው ትውፊት በስተቀር በግልጽ የተወሰነ ነገር አያጋጥምም። ሆኖም ግን የግድ ከአባቶች ሲያያዝ የመጣውን 81 ቁጥር ለማመሳከር ምንጮችን በማሰባሰብ በሚከተለው ዓይነት ይታያል።

## 2.1 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ:

### 2.1.1 81 ቅዱሳት መጻሕፍት በሥርጭት ላይ እንደሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት

በአለፉት ወደ 100 ዓመታት በተጠጉ ጊዜያት - 8 ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር በሥርጭት ላይ የሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት እንድ ወጥ



www.ethiopianorthodox.org

ቁጥርን ወይም አንድ ወጥ መጻሕፍትን ይዘው አለመገኘታቸው ይታያል:: ሆኖም ግን በመካከላቸው የሚታየው ቁጥር ልዩነት ይበልጥ ጎልቶ የሚታየው አንድ አንድ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት መጻሕፍት ከመዋሐድ ሌላ ጊዜ እነዚህን መጻሕፍት ከመከፋፈል ወይም አንድ አንድ መጻሕፍትን ከመጨመር ሌላ ጊዜ ከመቀነስ የተነሳ አንድ ወጥ ቁጥርን ስመከተል ካለመቻሉ በመመንጨት ነው::

ስለዚህ አሁን በጠቀስናቸው ዘመናት /1918 - 1987 = 80 ዓመታት/መካከል ቅዱሳት መጻሕፍት አራት /4/ ጊዜ በ1918 በእጅ ጽሐፈት ተቀድተው፣ የ1929 እነዚህ በ1918 የእጅ ጽሑፎች ራሳቸውም በፎቶ አፍሴት ተባዝተው፣ በ1947/1953/ እና በ1980 ታትመው ተሠራጭተዋል::

እንግዲህ እነዚህ በተከታታይ በእጅ ጽሕፈትም ሆነ በኅትመት ዘዴ ተሠራጭተው ከሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛትን በሚመለከት የ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም 1929 ፎቶ አፍሴት ኅትመትና የ1947 /1953/ ኅትመት ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 52 ወይም 54 ሆኖ ሲገኝ የ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት ግን 58 ሆኖ ይታያል::

ይህም ልዩነት ሊከሰት የቻለው በአንዱ ሥርጭት ተይዘው በሌላው ሥርጭት የተዘለሉ መጻሕፍት ወይም በአንዱ ሥርጭት ተጠቃለው በሌላው ሥርጭት ተለያይተው የሚገኙ በመሆኑ የ1918 ወይም የ1929 ሥርጭት ቅዱሳት መጻሕፍት እና የ1947/1953/ ሥርጭት ቅዱሳት መጻሕፍት 1/ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ብዛት 52 ወይም 54 ሆነው በመገኘታቸው የቁጥር እኩልነት ሲኖር በመካከላቸው ግን ሌላ አንድ ልዩነት ይታያል:: በ1918 ወይም በ1929 ሥርጭት 52 ወይም 54 መጻሕፍት መካከል መጽሐፈ ኤርምያስ ሲገኝ በ1947/1953/ ኅትመት



ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ይህ መጽሐፈ ኤርምያስ ተዘሎ ተግሣጽ ዘሰሎሞን ተይዞ ይገኛል:: እንግዲህ በአንድ በኩል የይዘት ልዩነት ሲኖር የቁጥር አንድነት 52 ወይም 54 ቁጥር ይታያል::

በሌላም በኩል የ1918 ወይም 1929 ሥርጭት ቅዱሳት መጻሕፍት በአራት ክፍሎች ተከፍለው ሲታዩ ከእነዚህም ሦስቱን ክፍሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እና አራተኛውን ክፍል የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይዘው ይገኛሉ:: ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 3ኛውን ክፍል ይዘው የሚገኙት በሰብዓ ሊቃናት እንጂ በማሶራዊ - ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል የማይገኙትና ከዚህም የተነሳ መጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና /Deuterocanonical/ ተብለው የሚታወቁት ናቸው::

ከዚህ ላይ ግን እንደሚስማሙ ቅዱሳት መጻሕፍት መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና እና መጻሕፍተ ዘዳግም ቀኖና /Protocanonical-Πρωτοκανονικά βιβλία/ እና Deuterocanonical-Δευτεροκανονικά βιβλία/ ተብለው በቀኖናተ መጻሕፍት ጥናት መታወቃቸው ግልጥ ነው:: ይህ ዓይነቱ አከፋፈል ወይም አጣራር-አሰያየም ሊፈጠር የቻለው ከብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት መጻሕፍት መካከል አብዛኞቹ ከተመለሰበት ዕብራይስጥ ቋንቋ ሲገኙ የተወሰኑት ደግሞ አንድም በዚህ ቋንቋ አልተጻፉም:: በርግጥም ያልተጻፉ/አለ/ 2ኛና 3ኛ መቃያን/ ወይም ተጽፈው ጠፍተው ቅጂቸው በጽርእ-ግሪክ ቋንቋ ብቻ ከመገኘታቸው የተነሳ ይህን ሁኔታ ለማሳየት ሲባል ነው:: በመካከላቸው ልዩነት አለ? ወይም አንዱ ክፍል ከሌላው ክፍል ይበልጣል? መጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ከመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ይበልጣሉ? ወይም በመካከላቸው አንድ ዓይነት ተዋረድ አለ? ከዚህም የተነሳ ሁለቱም ክፍሎች በቤተክርስቲያን ዘንድ «ክቡራትና ቅዱሳት- አምላካውያት መጻሕፍት» ናቸው? ወይስ አይደሉም? ወደፊት በመጠኑም ቢሆን ይታያሉ:: እንግዲህ



www.ethiopianorthodox.org

ይህ እንደተከበረና እንደተጠበቀ ሆኖ ከመጻሕፍት ዘደግም ቀኖና መካከል ራሳቸውን ችለው ከሚገኙት ለምሳሌ ጦቢትና ዮዲት መጻሕፍት ሌላ በዕበራይስጥ ቋንቋ ከሚገኙት መጻሕፍት መካከል ትንቢተ ዳንኤልና መጽሐፈ አስቴር በዕብራይስጥ ባለመገኘታቸው እንደ መጻሐፍት ዘዳግም ቀኖና ሁነው የሚቆጠሩ ክፍሎችን ይዘው ይገኛሉ::

ስለዚህ በትንቢተ ዳንኤል እንደ ሰብዓ ሊቃናት ተይዘው የሚገኙ ግን በዕብራይስጥ ቋንቋ ብሉይ ኪዳን የማይገኙ ሶስና፣ ተረፈ ዳንኤል እና ጸሎተ-መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ፣ ከመጽሐፈ አስቴር ከተወሰኑ ምዕራፎች (1፣3፣5፣8፣10) የተወሰኑ ክፍሎች ይገኙባቸዋል:: ስለዚህ በ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት ሶስናና ተረፈ ዳንኤል ከትንቢተ ዳንኤል ተለይተውና ተገልብጠው ወይም ተቀርጸው ሲገኙ በ1947/1953/ ኅትመት ግን እነዚህ ሁለት ክፍሎች ከትንቢተ ዳንኤል ሳይለዩ ይገኛሉ:: ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ ግን በሁለቱም ሥርጭቶች ተለይቶ አልተወሳም:: ቀጥሎም በ1928 የእጅ ጽሑፎች ወይም በ1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት 3 መቃብያን አንድ መጽሐፈ መቃብያን ተብለው ሲታዩ በ1947/1953/ ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ሦስት መቃብያን ተብለው ተዘርዝረው ተይዘዋል:: ይህ ቀምር ነው የቁጥር ልዩነትን ያላስከተለው::

የ1947/1953/ ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍተን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብሎ ከመከፋፈል አልፎ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እንደ 1929 ኦፍሴት ኅትመት በአራት ወይም በሦስት ክፍሎ አያሳይም:: በሌላ በኩል ግን የ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚመለከት እንደ 1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በሦስት ሳይሆን በሁለት ክፍሎች ተከፍለው ክፍል አንድና ክፍል ሁለት ክፍል አንድ ሁነው ሲገኙ ሁለተኛው ክፍል «የ2ኛ ቀኖና መጻሕፍት»



በሚል ርእስ ተይዞ የሚገኘው የ1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት 3ኛው ክፍል /ጥራዝን/ ነው:: ሆኖም ግን በይዘትም በቁጥርም ልዩነት ይታይበታል::

እንደ 1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም እንደ 1929 ፎቶ ኦፍሴት ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት: ሶስናና ተረፈ ዳንኤለ ብቻ ሳይሆኑ ጸሎተ-መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ (ጸሎተ አዛርያስ ቁ. 1 - 51 እና መዝሙረ ሠለስተ ደቂቅ ቁ. 51 - 90) ተለይቶ ታትሞ ይገኛል:: ቀጥሎም መጽሐፈ አስቴር በማሶራዊ-ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የማይገኙ ክፍሎችንም ይዞ መገኘቱ ይታወቃል:: በዚህም መሠረት በአንድ በኩል በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የሚገኙ ክፍሎችን ብቻ ለይቶ ይዞ በመጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና/አንደኛ ክፍል/ ታትሞና በሌላ በኩል በዕበራይስጥ ብሉይ ኪዳን የማይገኙ ክፍሎችን በብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ይዞ ስለሚገኝ በዚህ ቅርጹ በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ክፍልም ተይዞ ይገኛል::

ይህም ክፍል የሚከተሉትን ቅርጾች ይዞ ይታያል:

1. - በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት:
   - በምዕራፍ ከቁ. 1-22 በፊት ምዕራፍ ሳይሰጥ ግን 1-16 ቁጥርሮችን
   - በብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት: ምዕራፍ 1 ከቁ. 1- 22 በፊት 1 አልፋ - 1ሮ /1-17/ ቁጥሮችን፣
2. - በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት:
   - ምዕራፍ 3 ከቁ. 13 ቀጥሎ በቅንፍ 1-6 ቁጥሮችን
   - በብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት:
     አሁንም ምዕራፍ 3 ከቁ. 13 ቀጥሎ 13 አልፋ - 13 ኢታ /6/ ቁጥሮችን፣
3 - በ1980 ኅትመት ቅዱሳት መጻሕፍት
   - ምዕራፍ 5 ከቁ. 1 በኋላ ቁጥር ሳይሰጥ ከዚያም ከቁ.2

www.ethiopianorthodox.org

የግል ቤተ መጻሕፍት

አሁንም ቁጥር ሳይሰጥ ዓረፍተ ነገሮችን
በብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት:
ምዕራፍ 5 ከቁ. 1. በኋላ 1 አልፋ - 1 ዚታ /6/ ከቁ.2
ቀጥሎ 2 አልፋ 2 ቪታ /2/ ቁጥሮችን፣

4. - በ1980 ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት:
- ምዕራፍ 8 ከቁ. 12 ቀጥሎ በቅንፍ 1-24 ቁጥሮችን
በብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓሊቃናት፣
ም. 8 ከቁ. 12 በኋላ 12 አልፋ - 12ፊ(21) ቁጥሮችን

5. - በ1980 ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት:
ምዕራፍ 10 ያልተቀነሩ ቁ. 1-13 ማለትም ከ3-13
ቁጥሮችንና 11ኛ ምዕራፍ፤
- በብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት ምዕራፍ 10 ከቁ.3 አልፋ -
3 ላምዳ/11/ ቁጥርቶችን[6] ::

ስለዚህ በዕብራይስጥ ቋንቋ የማይገኙትን ክፍሎች ብቻ ይዞ በመጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ሲገኝ በዕብራይስጥ ቋንቋ የማይገኙትን ክፍሎች ይዞ ዳግሞ በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ይገኛል::

ከዚህም በስተቀር በሌሎች ኀትመቶች ቅዱሳት መጻሕፍት ያልተያዘ ከዚህም በላይ በማንኛውም ቀኖና መጻሕፍት ያልተመለከተ ጸሎተ ምናሴ ተይዞ ይገኛል:: በርግጥ በ2ኛ ነገሥትና 2ኛ ዜና መዋዕል ንጉሥ ምናሴ ስለ ጥፋቱ ወደ አምላክ እንደጸለየና ይህም ጸሎት በነገሥታት መጻሐፍ ተጽፎ

6. በመጻሕፍት ዘቀዳሚ ቀኖና ክፍል የሚገኘው መጽሐፈ አስቴር በምዕራፍ 10 ቁጥር 1-3 ሲጨርስ በመጻሕፍት ዘዳግም ቀኖና ክፍል የሚገኘው መጽሐፈ አስቴር በምዕራፍ 10 ከቁ.3 በኋላ ከ1-13 ያሉ ቁጥሮችን እንደ አለፉት በቅንፍ እንኳን ሳያመለክት ከመገኘታቸው ጋር የሚጨርስበት 11ኛ ምዕራፍ ሲሆን ይህ 11ኛ ምዕራፍ ሆኖ የሚነበበው በብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት 3 ላምዳ ሆኖ ይገኛል::



እንደሚገኝ ይነበባል[7]:: የጸሎተ ምናሴ ሙሉ ቃል በ8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ተቀድቶ ይገኛል[8]:: ግን በዚህ በ1980 ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ሰፍሮ የሚገኘው ጸሎተ ምናሴ አይታይም:: ሆኖም እነዚህ ብዙም የማያስጨንቁ ልዩነቶች አብዛኛውን የቅርጽ ልዩነቶች እንደተጠበቁና የሚደቱ አንዱ ገጽታው ሆነው ሲታዩ ሌላው ገጽታው ደግሞ መጽሐፈ-ተረፈ ኤርምያስ በጥንት ቀኖናተ መጻሕፍት ተይዞ ከሚገኘው መልእክቱ ኤርምያስ ልዩ መሆኑ እየታወቀ፣ ሌሎችም በጥንት ቀኖናተ መጻሕፍት በግእዝ ሲኖዶሳት ቀኖናትና በፍትሐ ነገሥት ያልታወቁ መጻሕፍት: ዕዝራ ሱቱኤልን፣ ሄኖክን፣ ጸሎተ ምናሴን፣ ኩፋሌን ምንም እንኳን ከሲኖዶሳቱ በ3ቱ ሲኖዶሳት ተይዞ ቢገኝም ቅሉ በጥንት የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናት ያልታወቁ መሆኑ እየታወቀ ይህንም ይዘው መገኘታቸው ነው::

እንግዲህ በአጭሩ የ1918 የእጅ ጽሑፎች ወይም የ1929 ፎቶ አፍሴት ኀትመት እና የ1947(1953) ኀትመት ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር: 52 የብሉይ ኪዳንና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት = /52+27=79/79 ሆኖ ይገኛል::

ከዚህ በመነሳት የ1918 ወይም የ1929፣ የ1947/1953/ እና የ1980 ሥርጭት ቅዱሳት መጻሕፍት ከጥንት ቀኖናተ መጻሕፍት፣ ሲኖዶሳትና ፍትሐ ነገሥት ጋር እንዲጣጣሙ አልተደረጉም:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤም በእነዚህ በተሠራጩም የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር እንደማይስማማ በ7/06/1987 በአደረገው ስብሰባ ቃለ ባኤ መረዳት ይቻላል::

7. 4ኛ ነገሥት (2ኛ ነገሥት) 21. 1-17፣ 2ኛ ዜና መዋዕል 33.1-13::
8. ትእዛዛት ዘቅዱሳት ሐዋርያት ምስለ ቀለሚንጦስ 2ኛ መጽሐፍ አንቀጽ 22.ቁ. 12-14 F. Funk; Didascalia et Constitutiones Apostolorum, Paderborn 1906, βιβλιοθήκη Ἑλλήνων πατέρων καὶ Ἐκκλησιαστικῶν συγγραφέων T.B. ገጽ 30 - 31::



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቀኖናተ መጻሕፍት፣ ሲኖዶሳትና ፍትሐ ነገሥት መሠረት በማጠቃለልም ቢሆን ወይም በመዘርዘር ሊሆን ይችላል ግን በትክክል የምትቀበላቸው የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንድ ወጥ ዝርዝርንና ቁጥርን ይዘው መገኘት ይኖርባቸወል:: እንደ አጋጣሚ እየታተሙና እየተሠራጩ መገኘታቸው ግን ግራ ያጋባል::

በሌላ በኩል በጥንት ቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍተ ከዚያም በሲኖዶሳትና በፍትሐ ነገሥት ያልተወሱ መጻሕፍት፡ ዕዝራ ሱቱኤል፣ ኩፋሌ፣ ሄኖክ ጸሎተ መናሴ፣ መጽሐፈ- ተረፈ ኤርምያስ በተከታታይ በእጅ ጽሐፈትም ሆነ በኅትመት ዘዴ ከተሠራጩት ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል መገኘታቸው ጥያቄን ማስነሳቱ ታይቷል:: ግን ጥያቄው እነዚህ የተዘረዘሩት መጻሕፍት «ቅዱሳት መጻሕፍት» ናቸው? ወይስ አይደሉም? አይደለም:: በቀኖናተ መጻሕፍት ቀጥሎም በሲኖዶሳትም ሆነ በፍትሐ ነገሥት አልተያዙም ነው::

ከዚህ ላይ አንድ የሚታወስ ነገር አለ:: አንድ አንድ ጊዜ አንድን መጽሐፍ በቤተክርስቲያን እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ቆጥሮ - አድርጎ ለመቀበል እንደ ማረጋገጫ ምስክርነትና ድጋፍ ሆኖ የሚቀርበው በተለይ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጠቅሶ መገኘቱ ነው::

በርግጥ ይህ ሊባል ይችላል ምክንያቱም አንድ መጽሐፍ በሌላ ገጽታውም ለምሳሌ ከታሪክነት አንጻር ሊጠቀስ ይችላል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በቀኖናተ መጻሕፍት ተመልክተው የማይታዩ ሆኖም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጠቅሰው የሚገኙ ሆኖም እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ተቆጥረው በቤተ ክርስቲያን ተቀባይነትን ያላገኙ መጻሕፍት ይገኛሉ::



ስለዚህም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደሰብዓ ሊቃናት ዝርዝር ውስጥ ሳይሆን በመጨረሻ በአባሪነት ተይዞ የሚገኘው 4ኛ መቃብያን[9] ም.2 ቁ. 5 በሮሜ 7.7 እና 7.19፣ ማቴ. 23.32 ተጠቅሶ ይገኛል:: ቀጥሎም በቀኖናተ መጻሕፍት ቀርቶ በጥንት የሃይማኖት ሥነ ጽሑፎችና ምርምሮች በሥርዐት ታውቀው ያልደረሱን በተለይ በኢትዮጵያ የሚገኙባቸውን ቦታዎች አግኝቶ ለማመሳከርና ለማረጋገጥ ያልቻልኩባቸው የሚከተሉት መጻሕፍት፡ ዕርገተ ኢሳይያስ (Ascention of Isaiah) ም.5 ቁ.11-14=ዕብራውያን 11.37፣ ገድለ ሙሴ (Assumption of Moses) = መልእክተ ይሁዳ 9.፣ - Aratus, Phaenomena 5 = ግብረ ሐዋርያት 17.28፣ የኤጲሜኒዲስ ለእይ (Epimenides, de oraculis) = ቲቶ 1.12፣ መዝሙራተ ኤጲሜኒዲስ(Psalms of Epimenides)= ግብረሐዋርያት 17.28፣ Menander thais (218) = 1ኛ ቆሮ. 15.33 ስለሄኖክ ቀደም ብለን አውስተናል[10] ተጠቅሰው እንደሚገኙ በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት በታተመ ሐዲስ ኪዳን በጥቅስ ማመልከቻ ክፍሉ መመልከት ይቻላል[11]::

ስለዚህ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ መጻሕፍት እየዋለና እያደረ ከሚሄድ ጊዜ ጋር ሊያጋጥሙ ይችሉ ይሆናል:: ግን እነዚህን መሰል መጻሕፍት «ቅዱሳት መጻሕፍት» ብሎ መቀበሉ የማይጠበቅ ነው:: ሆኖም ግን የጥንት ቀኖናተ መጻሕፍትም ቢሆኑ ከያዟቸው መጻሕፍት ውጪ ክቡራትና ቅዱሳት መጻሕፍት ሊከሰቱ ይችሉ እንደሆነ ተከስተውም

---

9. Η ΠΑΛΑΙΑ ΔΙΑΘΗΚΗ κατα τουζ εβδομηκοντα (ብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት) ገጽ 852 - 864::
10. ከዚሁ ገጽ 199 - 201::
11. The Greek New Testament. London, New York, Stuttgart, Edinburgh, Amesterdam 1966, ገጽ 918 - 920::



www.ethiopianorthodox.org

የሚያጋጥም ከሆነ ከአሉት - ከታወቁት ቅዱሳት -አምላካውያት መጻሕፍት ጋር ተጨምረው ሊቆጠሩ ይችሉ ወይስ አይችሉም እንደሆነ ቀኖናተ መጻሕፍት ምን እንደሚሉ መመልከቱ ይታያል።

እንግዲህ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝርና ቀኖናዊነት ሁኔታ የሚመለከቱ ቀኖናትን ስንመለከት ከየስሟቸው የባሕርይ - ገላጭ ቅጽሎች ላይ ሁለት አቋሞች ሊተረጎሙ ሲችሉ የመጻሕፍቱ ዝርዝርና ቁጥር ሲታይ ደግሞ ልዩነት አለ። አንዱ ቀኖና የያዘውን መጽሐፍ ሌላው ቀኖና ዘሎት፣ አንዱ ቀኖና የዘለለውን መጽሐፍ ሌላው ቀኖና ይዞት የሚገኝበት ሁታ ግልጥ ነው። ከዚህም በመነጨ በትክክል ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጻሕፍት በቀኖናት (በአንዱ ቀኖና ተዘለውም ሆነ በሌላው ቀኖና ተጨምረው) የተመለከቱት መጻሕፍት ናቸው? ወይስ ሌሎችም ሊያጋጥሙ ቢችሉ እንድትቀበላቸው እንደሚታዘዙ ይጠበቃሉ? የሚለው ጥያቄ ቀኖናቱ በዝርዝር እንደሚተረጎሙ ሆነው መገኘታቸውን አነሳስቷል።

ስለዚህ ይህን ጥያቄ በሁለት ከፍሎ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።

1. ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት መጻሕፍት እነዚህ ናቸው ብለው የማይደነግጉ ግን ያሉትን - የታወቁትን መጻሕፍት ከተለያዩ ቅጽሎች ጋር ቀኖናዊ ኃይልን የሚሰጡ ቀኖናት በአንድ በኩል ሲኖሩ[12] እነዚህም ቀኖናት ስለ ሌሎች መጻሕፍት መጨመር ጉዳይ በርን የማይዘጉ «ባለ ክፍት በር ቀኖናት» ተብለው ይታወቃሉ።
2. ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት ቅዱሳት መጻሕፍት እነዚህ ናቸው በማለት በመወሰን ቀኖናዊ ኃይልን

12. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና፤ 60ኛ ቀኖና ዘላኦዶቅያ እና ቀኖና አምፊሉኪዮስ ዘኢቆንዮን።



www.ethiopianorthodox.org

መጻሕፍት ውጪ ሌሎች መጻሕፍት ወደፊት መጨመር እንደማይኖርባቸው በርን የሚዘጉ - «ባለ ዝግ በር ቀኖናት» በመባል የሚታወቁ ቀኖናት ናቸው[13]። ሆኖም ግን ያለው የቀኖናት መተርጉማን አመለካከት ራሳቸውን ቀኖናቱን እንደ ማስረጃ በመውሰድ በቀኖናቱ ከተመለከቱት መጻሕፍት ውጭ ጽሑፋት በመንፈስ እግዚአብሔር መሆናቸው የታመነባቸው መጻሕፍት ከአጋጠሙ ቤተ ክርስቲያን ልትቀበላቸው እንደምትችል ነው።

በሌላ በኩል ያሉትን - የተዘረዘሩትን መጻሕፍትም ቢሆን ቀኖናቱ በሁለት መልኩ ነው አስቀምጠዋቸው የሚገኙት:

1. «ቀኖናውያት መጻሕፍት» - ቀኖናዊ ኃይልን ያገኙት መጻሕፍት - ቤተክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት-መቀበል ግዴታ ያለባቸው መጻሕፍት ሲሆኑ[14]፣
2. ሌሎች «ምቅናውያት መጻሕፍት» ቀኖና ኃይልን ወደፊት ማግኘት የሚኖርባቸው-የሚጠበቅባቸው ለጊዜው መቀበል ግዴታ ያልጣለባቸው መጻሕፍት ሁነው ይገኛሉ[15]፣

ስለዚህ እስከ አሁን ቀኖናዊ ኃይልን ያላገኘ መጻሕፍ ገና ይገኘል ወደ ማለት መደምደሚያ የመድረስ ሁኔታ ይታያል ማለት ነው።

ከዚህ አንጻር ከፍ ብለን በጥያቄ መልክ ችግሩን እንደአስቀምጥነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን «ቤተ ክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙት አምላካውያት መጻሕፍት» የትኞቹ

13. 24ኛ/32ኛ ቀኖና ዘካርታጌኒስ(ቅርጣግና)፤ መልእክተ አትናቴዎስ 39ኛ እና ቀኖና ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት።
14. 24ኛ/32ኛ ቀኖና ካርታጌኒስ (ቅርጣግና)።
15. መልእክተ አትናቴዎስ።

እንድትቀበላቸው የታዘዙት አምላካውያት መጻሕፍት» የትኞቹ እንደሆኑ የምትቀበላው በሲኖዶሳትና ፍትሐ ነገሥት ተዘርዝረው ከሚገኙት በተጨማሪ ሌሎችንም መጻሕፍት ተቀብላ እንደምትገኝ ሲታይ ግን ደጋግመን እንደአወሳነው ቢቻል በመሰል አብያተ ክርሰቲያናት (የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት) ጋር በመሆን ይህም ባይሆን ራሷ በግልጥ ቤተክርስቲያን እንድትቀበላቸው የታዘዙትን መጻሕፍት ደጋግመን እንደአወሳነው ዘርዝራ ማስቀመጥ ይኖርባታል::

በግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የ692 የትሩሎ ሲኖዶስ ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅዱሳት መጻሕፍትን የመጨረሻ ቀኖናዊ ዝርዝራቸውን ለማስያዝ አንድ ዐቢይ ሲኖዶስን ለመጥራት ብዙ ሙከራና ዝግጅት እየተደረገ ቢሆንም እስከአሁን አልተጠራም::

ስለዚህ አሁንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተጠቀሱት መጻሕፍት አስፈላጊዎች ሆነው መገኘታቸውን ከአመነችበትና ማመን ብቻ ሳይሆን ማሳመንም ከቻለች ቅዱሳት መጻሕፍት ብላ (አድርጋ) ልታውጃቸው ትችላለች:: ይህም የቅዱስ ሲኖዶስ ኃላፊነት ነው::

እንግዲህ ወደፊት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደገና ታትመው የሚሠራጩ ከሆነ አስፈላጊ የሚሆኑበት ጊዜ መምጣትም ስለማይቀር ከጥንት ቀኖናተ መጻሕፍት፣ ከሲኖዶሳትና ፍትሐ ነገሥት ጋር እንዲመሳከሩ ከዚያም ሌሎች መጻሕፍትን ዕዝራ ሱቱኤልን፣ ሄኖክን፣ ኩፋሌን፣ ጸሎተ ምናሴን፣ መጽሐፈ ኤርምያስን ጨምሮ ለማሳተም ከተፈለገ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናዊ ስያሜ ተሰጥቶ መታተም ይኖርባቸወል:: ይህ እስከ አልሆነ ድረስ ተለይተው ለብቻቸው ቢታተሙ ይመረጣል::

ከእኛ በኩል አቅም በፈቀደ መጠን የሚቻለውን ትብበር ለማድረግ ወደኋላ አይባልም::



በዚህ መንገድ ግልጎም እንደ በመሆን ባይቻል 81 ቅዱሳትን መጻሕፍት በአጭሩ ከአሐዝ አንጻር ለማሳየት ሲሞከር ግን በ85 ሐዋርያውያት ቀኖናትም ሆነ በሲኖዶሳት የተመለከቱት 8ቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ (ስመንቱ ብሔር ዘቀለሚንጦስ) ሳይወሰኑ ነው:: ይህን ወደፊት እንመለከታለን::

### 2.1.2 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት

በአንቀጽ 2 ርእስ ላይ «በቤተክርሰቲያን ተቀባይነታቸው የታዘዘ ቁጥራቸውም 81 የሆነ አምላካውያት መጻሕፍት» ብሎ ተነስቶ ነገር ግን ሲዘረዝር 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ቆጥሮ በድምሩ 46+27 = 73 መጻሕፍት ላይ ይቆማል:: ግን ከተነሳባቸው 81 መጻሕፍት ላይ 73 መጻሕፍት ሲቀነሱ /81-73 = 8/ 8 መጻሕፍት ይቀራሉ:: እነዚህም 8 መጻሕፍት በቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ የሚታወቁት 8ቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ መሆናቸው ነበር:: ሆኖም ፍትሐ ነገሥቱ ሲተረጎም እነዚህ 8ቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ራሳቸው ሳይሆኑ ግን በሌሎች መጻሕፍት ተተክተው 81 መጻሕፍት እንዲሟሉ ተደርጓል::

ፍትሐ ነገሥት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በ46 መጻሕፍት ላይ መወሰኑ ከሲኖዶሳት ቀኖናት ጋር አንድ ይሆናል:: ሦስቱን መጻሕፍት፡ ባሮክን፣ ሰቆቃውንና መልእክተ ኤርምያስን ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር በማዋሐድ /አንድ አድርጎ በመቁጠር/ እና ሁለተኛ ነህምያን ከዕዝራ ካልዕ ባለመለየት በ46 መጻሕፍት ሊወሰን ችሏል:: ቢሆንም በትርጓሜ እንጂ በሰነድነቱ 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስን (8ቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን) ይዞ ባለመገኘቱ ይለያል::

ስለዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ወደ 35 መጻሕፍት የሚያደርሷቸውን 8 መጻሕፍት ይዘው ባለመገኘታቸው 27ቱ መጻሕፍትን ብቻ ዘርዝረው በመገኘታቸው 73 እንጂ 81 መጻሕፍት አይደሉም



www.ethiopianorthodox.org

ወይም ባሮክ፣ ሰቆቃውና መልእክተ ኤርምያስ ከትንቢተ ኤርምያስ ባይለዩም = (46+3 = 49)49 የብሉይ ኪዳንና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት = /49+27 = /76 መጻሕፍት ይሆናሉ:: ይህም ነህምያ ከዕዝራ ካልዕ አለመለየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው ግን ቢለይ = /76+1=77/77 መጻሕፍት ነው የሚሆኑት:: ስለዚህ ወደ 81 ለመድረስ ብዙ ይቀራል = /81-77=4)4 መጻሕፍት ይቀራሉ::

በዚህ መልኩ በተለይ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በሚመለከት ነህምያን በጥበበ ባጎር በመተካትና ባሮክን፣ ሰቆቃውንና መልእክተ ኤርምያስን ከትንቢተ ኤርምያስ በመለየትና ወደ 49 መጻሕፍት በመድረስ ከብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት ጋር ማስማማት ይቻላል::

በሌላ በኩል ጥበበ ባጎር ወልደ በኩ/ጥበበ አጉር ወልደ ያኪ-ያቄ ዘሀገረ ማሳ/16 በሌላ ግን በተለመደ አነጋገር ተግሣጽ ዘሰሎሞንንን ተክቶ የሚገኝ መሆኑን መቀበል የሚቻል ሆኖ ቢታይም ቅን ግን መጽሐፉ-ጥበበ ባጎር ተገኝቶ ከዚህ ከሚታወቀው ተግሣጽ-ምሳሌ ሰሎሞን ምዕራፎች 25-31/1-7/ ጋር መመሳከር ነበረበት:: ግን አልተቻለም:: ቢሆንም ለጊዜው ያለው አማራጭ አንድም የተግሣጽ ምትክ ምሳሌ ሰሎሞን ም.25-31/1-7/ መሆኑን ወይም ምዕራፍ 30ን ብቻውን ለይቶ በማውጣትና ይህን ስም በመስጠት መቀበል ይሆናል::

ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት ከሰነድነቱ አንጻር 81 መጻሕፍት አይደሉም 73 እንጂ. ያውም ሁለቱ መጻሕፍትም (ጥበበ ኢያሱ ወልደ ሲራክና መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደኮርዮን) በጥያቄ ውስጥ መሆናቸው እንደተጠበቀ መሆኑ ሳይዘነጋ ነው::

16. ምሳሌ ሰሎሞን ምዕራፍ 30.1(እንደ ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን)::



### 2.1.3 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማንና እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ

የፍትሐ ነገሥት መተርጉማን በፍትሐ ነገሥት የተዘረዘሩትን 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ተቀብለው ነገር ግን 81 ቁጥርን ለማሟላት 8 መጻሕፍትን ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ጨምረው ይገኛሉ::

ይህንም ትርጉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ተስማምቶበት ይታያል:: ግን ከምን ላይ ተመርኩዘው እንደሆነ ሁለቱም ክፍሎች አላመለከቱም:: የሚመለከትም አይመስልም:: ሆኖም ግን ወደፊት ሊሰማ ይችል ይሆናል:: ለጊዜው ግን ከቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖናት ታሪክ ጋር አይሄድም:: በመሠረቱ በቀኖናተ ቅዱሳት መጻሕፍት የተመለከቱት መጻሕፍት ዝርዝር 88 ቢሆን 37ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ነበሩ:: ከእነዚህም 37 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አሥሩ(10ሩ): ሁለት መልክታተ ቀሌሚንጦስና 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀሌንጦስ ነበሩ:: እነዚህም ሁለት መልእክታተ ቀለሚንጠስ ተደጋግመው ሳይወሰዱ ሲቀሩ ግን 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ግን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ከ27 ወደ 35 አድርሰው እንደሚገኙና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ከ49 ወደ 46 በመሰባሰብ 81 ቁጥርን /46+35=81/ ሊሰጡ እንደቻሉ ለመስማማት የሚቻል ቢሆንም ቅሉ ትልቁ ችግር እነዚህ በጥንት ቀኖናተ መጻሕፍት በግእዝ ትርጉሞቻቸው/ትርጉማቸው/: ሲኖዶሳትም-ቀኖናትም የሚገኙት 8ቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ -8ቱ ሐዋርያውያት ቀኖናት ምስለ ቀለሚንጦስ በሌሎች በሁለቱ መጻሕፍተ ኪዳንና ዲድስቅልያ

www.ethiopianorthodox.org

ከእነዚህም በስተቀር ግልጥ ባልሆነ ሁኔታ አራት መጻሕፍተ ሲኖዶስና መጽሐፈ ቀለሚንጦስ ተተክተው መገኘታቸው ነው::

ችግሩ የተኩትን መጻሕፍት በሚመለከት ሳይሆን በምኖች ተኳቸው? ነው::

ሌላው ቀርቶ ሁሉም እንኳን ባይሆን የተወሰኑት ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን ወደሚገኙባቸው በታሪክ ወደሚታወቁት ሰመንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ - ሰመንቱ ሱርስጥ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስ ተጠግተው ቢገኙ ኑሮ ከዚህም አልፈው በግእዝ ሰመንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ -ግእዝ ሰመንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሚንጦስን ቢይዙም ኑሮ አንድ ነገር ነበር::

ስለዚህ እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማን እነዚህ ስምንት/8/ መጽሐፍት 81 መጽሐፍትን ያሟሉ ወይም አያሟሉ እንደ ግል አስተያት - ትርጉም ነው የሚወስደው ግን:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ትርጉም የግል-የግለሰቦች/የጉባኤው አባላት/ የግል አመለካከት ወይም ትርጉም ሆኖ አይወሰድም:: የቤተ ክርስቲያኗ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የቤተ ክርስቲያኗ ትርጓሜ ወይም የተሻለ አቋምና ውሳኔ ሆኖ ነው ሚታሰበው::

እንግዲህ ይህን የመሳሰለውን ጉዳይ ከጥንቃቄ ውስጥ የማስገባቱ ግዴታ የሚያጠያይቅ አይሆንም:

ስለዚህም ለጊዜውም ቢሆን በፍትሐ ነገሥት መተርጉማንም ሆነ በሊቃውንት ጉባኤ ትርጉም እነዚህ ናቸው 81 ቅዱሳት መጻሕፍት ብሎ መቀበሉ ያስቸግራል::

## 2.1.4 81 ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ሲኖዶሳት-ቀኖናት

ከ85 ሐዋርያውያት ቀኖናትና ከሌሎችም የጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናተ መጻሕፍት ላይ ተመርኩዘው የተመለሱ አራት/4/ ግእዝ ሲኖዶሳት-ቀኖናተ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዘረዝራሉ:: ከሚዘረዘሩት ቀኖናትም ከአንዱ ሲኖዶስ-ሥርዐተ ሐዋርያት ቀኖና 80 63 መጻሕፍተን ይዞ



ከሚገኘው በስተቀር ሦስቱ ሲኖዶሳት/ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቤተክርስቲያን ትእዛዝ 57 /ረስጠጅ/ ቀኖና 56፣ ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቅዱሳን ሐዋርያት-አብጠሊሳት 82/ረስጠአ/ ቀኖና 81 እና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን - አብጠሊስ 80 ቀኖና 80 81 81 (ወይም 80) ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዘው ይገኛሉ:: ስለዚህ ከጥንት ቤተ ክርስቲያን ቀኖናተ መጻሕፍት ብዙም ሳይርቁ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በሚመለከት ተግሣጽን ዘሰሎሞን ከምሳሌ ሰሎሞን/ም.25=31/ ለይተው ከመያዛቸው ጋር ባሮክን፣ ሰቆቃውንና መልእክተ ኤርምያስን ከትንቢተ ኤርምያስ፣ ነህምያን ከዕዝራ ካልዕ /ሁለተኛ ዕዝራ/ ሳይለዩና ከ3 መቃብያን መካከል ሁለቱን/ 1ኛ እና 2ኛ መቃብያንን ብቻ ከዚያም በብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናትም ሆነ በማሶራዊ ዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የማይታወቅና በማንኛውም ቀኖና መጻሕፍት ያልተመለከተ ኩፋሌን ይዘው ይገኛሉ:: ቆይቶ የተጨመረ መሆን ሲኖርበት 3ኛው መቃብያን ከሌሎች ሁለቱ መቃብያን /1ኛ እና 2ኛ/ ለየት ያለ ይዘት ከሃይማኖት ይዘት ይልቅ ወደ ፍልስፍና አቅጣጫ ያዘነበለ በመሆኑ ምን አልባት ሆነ ተብሎ ተዘሎ ሊሆን ይችላል[17]:: ከዚህም ጋር በተመሳሳይነት በቀኖናት ዘካርታጌኒስ /ቅርጣግና ላቲን ሰነድ ሁለቱ/ 1ኛ እና 2ኛ መቃብያን ብቻ ናቸው ተይዘው የሚገኙት፣ ቢሆንም እስከ አሁን በብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናት ተጠብቆ እንደ መገኘቱ መጠን ምን አልባት በገልባጭ ስህተት ተዘሎ /ተገድፎ/ ይሆናል:: ስለዚህ በዚህ ዓይነት ዝርዝር እንደ ሲኖዶሳት - ቀኖናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ሰብዓ ሊቃናት ከ49 ወደ 46 ማለት በሦስት መጻሕፍት ተሰባስበው ይገኛሉ::

---

17. ፍትሐ ነገሥት ከሁለቱ መቃብያን ለይቶ በመጨረሻ ከዚህ ውጪ = «ውፁእ እምእሉ . . . ወከዕበ. . .» ብሎ የያዘው ስለዚህም ይሆናል::



www.ethiopianorthodox.org

ከአራት ሲኖዶሳት - ቀኖናት አንዱ ሲኖዶስ - ሲኖዶስ ዘቅዱሳን ሐዋርያ - አብጥሊሳት 82/ረስጠአ/ ከሁለቱ መልእክታተ ቀለሚንጦስ መካከል አንድዋን መልእክት የያዘ ሆኖ እንደሚታይ አጠራጥሯል:: ይህም ጥርጣሬ የሚመነጨው ጽሑፉ ግልጥ ካለመሆኑ የተነሳ መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጽዋል::::

ስለዚህ ሌለቹ ሁለት ሲኖዶሳት: ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን /ረስጠጅ/ እና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን/ አብጠሊስ 86/ ሲታዩ እነዚህን ሁለት መልእክታት ሁለቱንም ወይም አንድዋን መልእክት ይዘው እንደ አለመገኘቻው ሁሉ ይህም ሲኖዶሳ ከ8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ በስተቀር በተጨማሪ አንድዋን መልእክት እንደ አልያዘ ወደ መደምደሚያ መድረሱ አማርጧል::

## 2.2 የሚታሰብባቸው አማራጮች

### 2.2.1 አማራጭ አንድ

ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን - አብጠሊሳት 82/ረስጠአ/ እንደ ሌሎች ሁለት ሲኖዶሳት /ሲኖዶስ ዘቤተክርስቲያን/ ረስጠጅ/ እና ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳን - አብጠሊስ 80 ከ3ቱ መቃብያን ሁለቱን መቀብያን ሳይሆን አንድ መቃብያንን ብቻ ይዞ ይገኛል:: ይህም ቢሆን ከ8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ጋር አንድ መልእክተ ቀለሚንጦስን ይዞ እንደሚታይ በመታሰቡ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 45 እና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት 36/8+1=9+27=36/ ሆነው ሲታዩ ቻሉ ስለነበር ያው 81 ቁጥር ይሞላ ነበር:: ሆኖም ግን ከአጠራጣሪነቱ በመነጨ መልእክተ ቀለሚንጦስ አለመያዙ እንደ መደምደሙ መጠን ሲኖዶስ ዘሐዋርያት ቅዱሳት እንደ ሌሎቹ ሲኖዶሳት ሁለት መቃብያንን እንደ ያዘ በማሰብ - በመቁጥር 46 የብሉይ ኪዳንና 35 የሐዲስ ኪዳን /46+35/=81/81 መጻሕፍትን እንደያዘ ይቆጠራል::

ስለዚህ ሁለቱ መልእክታተ ቀለሚንጦስ በሲኖዶሳት እንደማይታወቁ መረዳት ይቻላል:: በሌላ በኩል ከአራቱ ሳይሆን 37 መጻሕትንና ከሐዲስ ኪዳን አሁንም እንደ እነዚህ ሶስቱ ሲኖዶሶት 35 መጻሕፍትን ሳይሆን 26 መጻሕፍት በድምሩ 37 የብሉይ ኪዳንና 26 የሐዲስ ኪዳን 37+26=63 መጻሕፍትን ይዞ ሲገኝ 8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስን ብቻ ሳይሆን አቡቀለምሲስ ዘዮሐንስንም ይዞ አይገኝም::

ሌሎች 3ቱ ኖዶሳት: ኖዶሳት - ቀኖናት ዘቤተ ክርስቲያን /ረስጠጅ/፣ ሲኖዶስ-ቀኖናት ዘቅዱሳን ዘሐዋርያት - አብጠሊሳት 82/ረስጠአ/ እና ሲኖዶስ - ቀኖናት ዘሐዋርያት ቅዱሳን አብጠሊስ 80=81 81 ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዘው ይገኛሉ::

እንግዲህ በአጭሩ ተደጋግመው በሥርጭት ላይ የሚገኙትን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ፍትሐ ነገሥትን፣ የፍትሐ ነገሥት መተርጉማንንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤን በመጨረሻም ሲኖዶሳትን ቀኖናተ ቤተክርስቲያንን ስንመለከት ስለቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ወደ አንድ መደምደሚያ መድረስ ቀላልም አይደለም::

በሥርጭት ላይ ከሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል በቀኖናተ መጻሕፍት፣ ሲኖዶሳት - ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያንና ፍትሐ ነገሥት የማይታወቁ በፍትሐ ነገሥት መተርጉማንና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ ያልተደገፉ መጻሕፍት: ዕዝራ ሱቱኤል፣ ሄኖክ፣ ኩፋሌ፣/ኩፋሌ ከአራቱ ሰኖዶሳት በ3ቱ ተይዞ ቢገኝም ቅሉ ቆይቶ የተጨመረ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይመስልም) መጽሐፈ-ተረፈ ኤርምያስ/ ከመልእክተ ኤርምያስ የተለየ እንደ መሆኑ መጠን/ እና ጸሎተ ምናሴ ተይዘው ቢገኙም ከ81 ቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ገብተው ሊቆጠሩ አይችሉም::

እነዚህ መጻሕፍት ከላይ እንደተመለከተው ቅዱስ ሲኖዶስ አምኖበትና ሊቃውንትንም አሳምኖ በግልጥ በቀኖና መጻሕፍት ሥርዐት እስከ አልተወሰነ ድረስ ወደፊት ከቅዱሳት መጽሐፍት


www.ethiopianorthodox.org

ጋር ተዳብለው መሁራጨት እንደሌለባቸው ሳይዘነጋ በሲኖዶሳትና ፍትሐ ነገሥት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት 46 ሲሆኑ በሁለቱ መልኮች ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ሰብዓ ሊቃናት ይለያሉ:: ባሮክ፣ ሰቆቃውና መለእክተ ኤርምያስ ከትንቢተ ኤርምያስ እንደዚሁ ነህምያ ከዕዝራ ካልዕ /2ኛ ዕዝራ/ ሳይለዩና ከሦስት መቃብያን ሁለት መቃብያንን ብቻ ይዘው ስለሚገኙ ግን አንዱ 3ኛ መቃብያን እንጂ የተዘለለው ሌሎቹ አራቱ መጻሕፍት በመዋሐድ በስተቀር ተይዘው ስለሚገኙ በመካከል የሚታየው ልዩነት በቁጥር የአምስትና በይዘት ግን የአንድ መጽሐፍ ልዩነት ነው::

ስለዚህ ከቁጥር አንጻር ከ49 ሲቀንስ 5 /49-5=44/44 መጻሕፍት ነገር ግን እንደ ብሉይ ኪዳን እንደ ሰብዓ ሊቃናት ከምሳሌ ሰሎሞን ተለይቶ የማይታይና በየትኛውም ቀኖና መጻሕፍት ተይዞ የማይገኝ ተግሣጽ ዘሰሎሞንና አሁንም በማንኛውም ቀኖና መጻሕፍት ተመልክቶ የሚታወቅ ኩፋሌን ይዘው ስለሚገኙና እነዚህ ሁለት መጻሕፍተ ከ44 ጋር ሲደመሩ:: /44+2=46/46 መጻሕፍት ይሆናሉ ወይም 46 ቁጥር ይሟላል::

ነገር ግን ወደ 81 ቁጥር ለማድረስ ይህ 46 ቁጥር በአለበት መልኩ አያዋጣም::

ስለዚህ በመሠረቱ ኩፋሌ መውጣት ይኖርበታል:: ዕዝራ ነህምያ ከዕዝራ ካልዕ/2ኛ ዕዝራ/ ተለይቶ መቆጠር አለበት:: በዚህ ሁኔታ ተግሣጽን ከምሳሌ ሰሎሞንን ባለመለየትና 3ኛ መቃብያንን በመያዝ አሁንም ከአሐዝ አንጻር ተግሣጽ በ3ኛ መቃብያን ይተካል ማለት ነው: በሁለቱም መንገዶች 46 መጻሕፍት ይመጣሉ/46 ቁጥር ይመጣል/:: ቢሆንም የ3ኛው መቃብያን ጉዳይ በፍትሐ ነገሥት እንደ አለም ስለሚቆጠር[18]

---

18. መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን እሱም መጽሐፈ መቃብያን፣ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2 ቁ. 17::



ከዚህ አንጻር ይታያል:: ይህ የግል አስተሳሰብ ወይም ትርጉም ነው ውሳኔ አይደለም::

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በሚመለከት ከቁጥር አንጻር ከ27 ላይ ስምንት መጻሕፍት እስከ ተጨመሩ ድረስ 35 ቁጥር ይመጣል:: ግን ጥያቄው በሲኖዶሳት፣ በፍትሐ ነገሥት መተርጉማንና ሊቃውንት ጉባኤ መካከል ልዩነት አለ:: የእኔም አቋም ወደ ሲኖዶሳት-ቀኖናተ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ግን የተጠቀሱት ስምንት መጻሕፍተ ቀለሚንጦስ ከ8ቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ጋር መመሳከር አስፈላጊነት ግድም መሆኑ ተጠብቆ ነው::

ስለዚህ በሲኖዶሳቱ መሠረት 46 የብሉይ ኪዳንና 35 የሐዲስ ኪዳን = 81 መጻሕፍትን መቀበሉ አንድ አማራጭ ይሆናል::

## 2.2.2 አማራጭ ሁለት

እንደ ሁለተኛ አማራጭ ሊታይ የሚችለው አሁንም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደሰብዓ ሊቃናት: 49 መጻሕፍትን በመውሰድ ማለት በቀኖናተ መጻሕፍት መሠረት ባሮክን፣ ሰቆቃውንና መልእክተ ኤርምያስን ከትንቢተ ኤርምያስ ለይቶና ቦጥንት ቀኖናተ መጻሕፍት ነህምያን ከዕዝራ ካልዕ/ 2ኛ ዕዝራ/ ለይቶ ባይታወቅም ቅሉ ግን ቆይቶ መለየቱ ተቀባይነትን በማግኘቱ አሁንም ተለይቶ፣ ተግሣጽ ዘሰሎሞንን ከምሳሌ ሰሎሞን ባለመለየትና 3ኛ መቃብያንን በመጨመር ይሆናል ማለትም 49 መጻሕፍት ይገኛሉ::

ቀጥሎም ከ27ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ችግሩ /ስምንቱ መጻሕፍተ ቀለሚንጦስን ከስምንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ጋር ማመሳከሩ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ያው ስምንት መጻሕፍትን በመጨመር= /49+35=84/84 መጻሕፍት ይመጣሉ::

ይህም አማራጭ በቀኖናተ መጻሕፍት የተደገፈው አማራጭ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

### 2.2.3 አማራጭ ሦስት

ከብሉይ ኪዳን እንደሰብዓ ሊቃናትም ሆነ ሲኖዶሳት /ኩፋሌ እንደማይገዝ ሆኖ/ እና ፍትሐ ነገሥት 46 ወይም 49 መጻሕፍትን እና የ8ቱ ተጨማሪ መጻሕፍት በቁጥራቸው ሳይሆን በዓይነታቸው፣ ይዘታቸውና መጠናቸው የአብዛኞቹ አጠያያቂ ስለሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አመሳክሮ እስኪያጣራቸው ቆይተው 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ብቻ በመውሰድ ይሆናል።

ስለዚህ እንደሲኖዶሳት-ቀኖናትና ፍትሐ ነገሥት 46 የብሉይ ኪዳንና 27 የሐዲስ ኪዳን = /46+27=73/73 መጻሕፍት ወይም እንደ ሰብዓ ሊቃናት 49 የብሉይ ኪዳንና 27 የሐዲስ ኪዳን = /49+27=76/76 መጻሕፍት ይሆናሉ።

ምናአልባት በታሪክ በኩል ትክክለኛው የቱ እንደሆነ ደጋግመን መግለጻችን እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከላይ እንደተመለከተውና የ8ቱ ተጨማሪ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንድም እንደ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና እና እንደ ሲኖዶሳት - ቀኖናት ስምንቱ ሐዋርያውያት ትእዛዛት ምስለ ቀለሚንጦስ ወይም እንደ ፍትሐ ነገሥት መተርጉማንና እንደ ሊቃውንት ጉባኤ ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን፣ አራት መጻሕፍት ሲኖዶስ፣ ዲድስቅልያና መጽሐፈ ቀለሚንጦስ መሆንና አለመሆናቸው በበቂ ማስመኛ ታሪካዊ ሐቅ ተረጋግጠው እስኪለዩ ድረስ ለጊዜው ይህ የተሻለው አማራጭ ነው።



## APPENDIX

# THE 81 HOLY BIBLES AND THE SOURCES - CANONS SHORT OUTLINES OF THE MAIN TOPICS EXAMINED IN THE BOOK


1. INTRODUCTION
   The aiming point - purpose and the attainment of its end.

CHAPTER ONE
THE DIVINE BOOKS ACCEPTED BY THE HOLY CHURCH AND ARE 81 IN NUMBER

1. The Divine Books and the Sources-Canons
   1.1 The holy synodes
   1.2 Church's Fathers

CHAPTER TWO
THE CANONS OF THE HOLY BOOKS

1. Synodical Canons
   1.1 The 85 Apostolical Canons
   1.2 The Canons of the Synode of Loadicea
   1.3 The Canons of the Synode of Carthage
2. The Canons of the Fathers of the Church
   2.1 The paschal epistle of Athanasius, the Great
   2.2 The Canon of Gregory, the Theologian
   2.3 The Canon of Amphelocius of Iconion
3. Comparative Table 1
4. Enumeration, Canonical form and Force of the Holy Books




www.ethiopianorthodox.org

## CHAPTER THREE
## GEEZ THE VERSIONS OF THE CANONS OF THE HOLY BOOKS

1. Synodical Canons
   1.1 The 85 Apostolical Canons
   1.2 Synodos - Collection of the Canons
      1.2.1 Synodos - Canons of the Church 57(56)(Restege)
      1.2.2 Synodos-Canons of the Holy Apostles 82 (Resta)
      1.2.3 Synodos-constitutions of the Apostles 80
      1.2.4 Synodos-Canons of Apostles, the Holy 81
2. Fetha Nagast - the Nomocanon
3. The hermeneutes of the Fetha Nagast-Nomocanon
4. The Council of Scholars of the Ethiopia Orthodox Church
5. Comparative Table Between 85th Canon of the 85 Apostolical Canons and each Canon of The Four Geez Versions of it including the 2nd Aticle of the Fetha Nagast Table 2.

## CHAPTER FOUR
## SIMILARITIES AND DIFFERENCES BETWEEN THE SYNODICAL CANONS, THE CANONS OF THE FATHERS OF THE CHURCH AND THE FOUR GEEZ VERSIONS OF THE CANONS

1. Between the 85th Canon of the 85 Apostolical Canons and of each last Canon of the four Geez Versions of it.
   1.1 Between the 85th Canon of the 85 Apostolical Canons and the 56th Canon of the Synodos - Canons of the Church 57(RESTEGE) 1.2 Between the 85th Canon of The Apostolical Canons and the 81st Conon of the Synodos-Canons of the Holy Apostles 82 (RESTA)



   1.3 Between the 85th Canon of the 85 Appostolical Canons and the 80th Canon of the Synodos-Constitutions of the Apostles 80.
   1.4 Between the 85th Canon of the 85 Apostolical Canons and the 80th Canon of the Synodos-Canons of Apostles the holy 81.
   1.5 Between the 60th Canon of the Canons of the Synodos of Loadicea and The Four Geez Versions of the Canon (Canons)
   1.6 Between 24th/32th Canon of the Canons of the Synodos of Carthage and the four Geez Versions of the Canon (Canons)

2. Between The Canons of the Fathers of the Church and the four Geez Versions of the Canons.
   2.1 The Paschal Epistle of Athanasius, The Great
   2.2 The Canon of Gregory, the Theologian
   2.3 The Canon of Amphelocius of Iconion Comparative Table on the 6 Canons.

## CHAPTER FIVE
## THE HOLY BOOKS AND THEIR CANONICAL DESCRIPTIVE ADJECTIVES AND DISTRIBUTIONS

1. The Kinds of the Canonical Descriptive Adjectives
2. The Editions and Distributions of the Holy Books
   2.1 Hebrew - Masoretic Old Testament
   2.2 Greek Holy Bibles
      2.2.1 Greek-Septuagint old Testament
      2.2.2 Greek New Testament



www.ethiopianorthodox.org

2.3 Geez - Amharic Holy Bibles
- 2.3.1 The 1918(1925 - 1926) Manuscripts-(written by hand) Holy Bibles
- 2.3.2 The 1929(1936 - 1937) photo offset edition Holy Bibles
- 2.2.3 The 1947(1953(1954 - 1955) (1960 - 1961) edition Holy Bibles
- 2.3.4 The 1980 (1987 -1988) edition Holy Bibles

## CHAPTER SIX
## SIMILARITIES AND DEFERENCE'S BETWEEN GEEZ-AMHARIC HOLY BIBLES OLD TESTAMENT AND GREEK-SEPTUAGINT OLD TESTAMENT

3. Differences shown in 1925, 1936, 1954 and 1987 editions and distributions Geez-Amharic Holy Books
4. Comparative table among the Holy Books
5. Geez-Amharic Holy Books in comparison with their original sources

## CHAPTER SEVEN
## 85th CANON OF THE 85 APOSTOLICAL CANONS, 8 APO-STOLICAL CONSTITUTIONS OF CLEMENT AND ORIENTAL OCTATEUCHUS - CLEMENT

1 Clement's Octateuchus
- 1.1 Syriac Clement's Octateuchus
- 1.2 Arabic Clement's Octateuchus



- 1.3 Coptic Clement's eptateuchus
- 1.4 Geez-Ethiopic Clement's Octateuchus

2. Apostolical constitutions in Eight books

## CHAPTER EIGHT
## COMPREHENSIVE COMPARISION BETWEEN THE HOLY BOOKS AND THEIR SOURCES-CANONS AND CONCLUSIONS

1. Comprehensive Comparison with:
   - 1.1 Summarization and Historical Canonization of the Holy Books
   - 1.2 Examination and hermeneutical Methodology of the synodosat-Canons in the Ethiopian Orthodox Church
2. Conclusion
   - 2.1 81 Holy Books how:
     - 2.1.1 As for the Holy Books: manuscripts, published and distributed (1925 - 1988)
     - 2.1.2 As for the Synodosat-ecclesiastical Canons
     - 2.1.3 As for the Fetha Nagast - Nomocanon
     - 2.1.4 As for the hermeneuts of the Fetha Nagast
     - 2.1.5 As for the Council of Scholars of the Ethiopian Orthodox Church
3. Alternative Suggestions

   For the Problems which realy require Uniformity of the Numbers of the Holy Books.

www.ethiopianorthodox.org

## ሰውም በአምሳሉና በአርአያው የሰውን አካል እንኳን ባይሆን ሰብእናን ይቀርጻል

አንድ ጽሑፍ ተጠናቆና ለኃራ-ለማኅበረሰብ ንባብ ሲታደል ሲገመገምና ሲተች (ለምስጋና ሲቀርብና ለነቀፌም ሲደረግ) እንደሚኖርበት መጠበቁ አይዘለልም:: የሚደረገው ግምገማና ትችት ከዚህም የመነጨ አስተያየት ወይም አመለካከት «ለሰሚ አውሪ ይንገረው» ሳይሆን በሥነ ጽሑፍ ሂስ ሥርዐትና ደንብ፣ ምንጭና መረጃ ሐቅነት ላይ ተመሥርቶ ከሆነ ቅዱስ ነገር ነው:: ይህም ወደፊት ለሚቀጥል ጥረት ገንቢ ትምህርትን ስለሚሰጥ በተስፋ የሚጠበቅ ነው::

ሆኖም የአንድ ጽሑፍ ዝግጅት መጠናቀቅ ረጅም ጊዜንና ከፍተኛ ድካምን ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሌሎችንም ሰዎች (በተናጠል ወይም በማኅበር) ትብብር፣ ድጋፍና በተለየ የቤተሰብ አባላትን ስፊ ትእግሥት የሚጠይቅና ከዚህም በመነጨ ለብዞች ባለወረታነትን እንደሚያስጠብቅ ነው::

ስለዚህ ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት መሳካት ከሁሉም የበለጠ በተለየ የቤተሰቦቼን (የውድ ባለቤትንና ልጆቼን) የመንፈስና የጉልበትም ሳይቀር ድጋፍ፣ ትብብርና ትእግሥት (ያለመሰልቸት የጊዜና የሌሊት ዕንቅልፍ መሠዋዕትነትን) ጠይቋል::

ከዚህም የተነሳ ከልብ ከማማስገን ጋር የልጆችን ሰብአና ለታላቅ ዓላማና ግብ አርአያነት ለመቅረጽ አንዱ ዘዴ መሆኑን በሌላው መጽሐፌ «የመንግሥት ገጻተ ባሕርያት» እንደአረጋገጥኩት አሁንም ወረታ ሳይሆን ይህን መሰል ጥረት አርአያ በማድረግ ለአገራቸውና ቤተ ክርስቲያናቸው የየበኩላቸውን የኃላፊነት ድርሻ ለማበርከት ይበረታታሉ በሚል ተስፋ ሥዕሎቻቸው በመጽሐፉ ሽፋን ጀርባ እንዲሰፍሩ ተደርገዋል::



Other new books of the Author

EQUALITY OF MEN AND CITIZENS BEFORE THE LAW: legal & political human equality — 1994?
- . . . .

CHARACTERSTICS OF STATE — 199.
- Form of State
- Sovereignty of State
- Polity and Power of State
- Peoples' State Power
- . . . . . . .

FETHA NAGAST : NOMOCANON — 199.
- The title - onomatopoeia
- The concept
- The Sources
- . . . . .

-THE RELATIONS OF CHURCH AND STATE in Ethiopia According to the 1995 Constitution, Athens — 1975

Soon expected

-The Constitutions and Public Constitutional Psychology in Ethiopia — 199. . .

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org